# የአማኞች ጋሻ

## በአላህ ስሞችና ባህሪያት ዙሪያ የሚነሱ ውዝግቦች የሚፈቱባቸው መርሆዎችን ያዘለ ትምህርታዊ ጥንቅር

- የተሳሳቱት የሚታረሙበት
- የተጠራጠሩት የሚረጉበት
- ያረጋገጡት የሚፀኑበት

ዝግጅት

ኢሊያስ አሕመድ

የመጀመሪያ እትም
1434 ዓ.ሂ / 2013 እ.ኤ.አ

ሁለተኛ እትም
1437 ዓ.ሂ / 2016 እ.ኤ.አ

© የመፅሃፉን አዘጋጅ ካስፈቀዱ በኋላ
አሳትሞ በነፃ ለማሰራጨት ካልሆነ በቀር
የማሳተምና የማባዛት መብቱ የተጠበቀ ነው።

حقوق الطبع والنشر محفوظة
إلا لمن أراد طبْعَه وتتوزيعَه مجّانا بعد مراجعة المؤلف.

بسم الله الرحمن الرحيم

...በደፈናው የፈጣሪን ስሞችና ባህሪያት በተገቢው መልኩ መገንዘብ ወደ ሐሰት የአምልኮ መስኮች የሚያመሩ መንገዶችን ሙሉ በሙሉ የሚዘጋ ከመሆኑ ባሻገር በዚህች ምድር የመገኘታችን ምክንያት የሆነውን ክቡር አምልኳዊ ግዴታ በአግባቡ እንድንወጣ ይረዳናል!

መቼም የማንኛውም ሰው ልቦና ስለሚገዛው አምላክ ማንነት በጥቅሉም ቢሆን ለማወቅ ይጓጓል፤ ጭራሽ የማያውቁትን ማምለክና መውደድ የሚያዳግት ነውና!

ታዲያ አላህን እርሱ ራሱና መልዕክተኞቹ በገለፁት መልኩ ማወቅ ከጥራዝ-ነጠቅ ንትርኮችና ከህሊናዊ ውጥንቅጦች በማሳረፍ የእምነት እርካታን ያወርሰናል። የኢማናችንን አድማስም በየአቅጣጫው ያሰፋልናል፤ ለርሱ ያለንን ውዴታና ፍራቻም በውስጠ-ልቦናችን በማሳደግ በአምልኮ መስክ ላይ ብርታትን ያላብሰናል! ምክንያቱም እያንዳንዱን የአላህ ስም እና ባህሪ በአግባቡ ማወቅ በዚያው ልክ ራሱን የቻለ የአምልኮ ፍሬ ያፈራልና!..

(ከመፅሀፉ የተወሰደ)

## ማውጫ

| ርዕስ | ገፅ |
| --- | --- |
| የሁለተኛው እትም መቅድም | 9 |
| የመጀመሪያው እትም መቅድም | 14 |
| መሸጋገሪያ | 20 |
| ክፍል 1 | |
| የጉዳዩ አንገብጋቢነት | 20 |
| ክፍል 2 | |
| የውዝግቡ አነሳስ | 25 |
| የአንጃዎች መፈልፈል | 26 |
| ክፍል 3 | |
| ማን ይፍረደን? | 33 |
| የአእምሮ ድርሻ | 39 |
| ምን ይጠበቅብናል? | 41 |
| ምዕራፍ አንድ | 44 |
| ሶስቱ መርሆዎች | 45 |
| ክፍል 1 | |
| የመጀመሪያው መርሆ ማብራሪያ | 46 |
| መነሻ | 46 |
| መድረሻ | 50 |
| መቋጫ | 52 |
| አራቱ ጠንቆች | 57 |
| አንደኛው ጠንቅ (ተክዪፍ) | 58 |

ታሪካዊ ምሳሌ ........................................ 60
ሁለተኛው ጠንቅ (ተምሢል) .......................... 62
ሶስተኛው ጠንቅ (ተዕጢል) .......................... 65
ብዥታ ................................................ 71
እርማት ............................................... 73
አራተኛው ጠንቅ (ተሕሪፍ) .......................... 77
የእውነት ሚዛናዊነት .................................. 81
የሰለፎች ጎዳና ........................................ 84
ጥቂት ጥቅል ጥቅሶች ................................ 85
ጥቆማ ................................................ 106
ክፍል 2
የሁለተኛው መርሆ ማብራሪያ ......................... 109
አንደኛው ነጥብ ...................................... 109
ሁለተኛው ነጥብ ..................................... 116
ሶስተኛው ነጥብ ...................................... 118
ክፍል 3
የሶስተኛው መርሆ ማብራሪያ ......................... 120
የቃላት ምድብ ........................................ 120
የ“ጂስም” ምሳሌ...................................... 125
ሽብር ................................................ 128

ምዕራፍ ሁለት ........................................ 133
መግቢያ
ጠርዘኞች ............................................ 134
ክፍል 1
ምድብ አንድ (ሙሸብ-ቢሃህ) ......................... 135

ጥፋታቸው .................................... 136
ብዥታቸው .................................... 137
መልሶች .................................... 137
ክፍል 2
ምድብ ሁለት (ሙዐጥ-ጢላህ) ..................... 142
አንደኞቹ ........................................143
ሁለተኞቹ .................................... 144
ሶስተኞቹ .................................... 145
አራተኞቹ .................................... 146
ምርመራ .................................... 147
የበሽታው መዘዝ .............................. 150
ክፍል 3
መድሃኒት .................................... 153
አንደኛው መሠረት (የስያሜ መመሳሰል..) ........... 153
ምሳሌዎች .................................... 154
የጀነት ምሳሌ .................................. 156
መቋጫ .................................... 160
ቁርአናዊ ማረጋገጫ .............................. 161
ቀላሉ መፍትሄ .................................. 177
ሁለተኛው መሠረት (ስለ ከፊል ባህሪያት..) ......... 178
ምሳሌ .................................... 178
ሶስተኛው መሠረት (ስለ ባህሪያት መናገር..) ........ 185
“ዛት”ና ባህሪ አይነጣጠሉም........................ 187
ክፍል 4
ሸሪዓዊ ልባስ .................................. 194
(لَيْسَ كَمِثْلِهِ شَيْءٌ) ስለሚለው አምስት ጥቆማዎች ....... 194

ክፍል 5
የበሽታው እውነተኛ መነሻ ......................... 197
“ዒልሙ’ል-ከላም”................................ 198
ጉዱ እንዲህ ነው! ................................ 200
ጥቆማ ............................................. 203
ተውሒድን በንፅፅራዊ አመክንዮ .................... 211
ወሳኝ ማብራሪያ ................................... 213
የሩሕ ምሳሌ ....................................... 214
መቋጫ ............................................. 217
ክፍል 6
ተእዊል ............................................ 223
ጉልህ መልዕክት .................................... 226
የተእዊል መስፈርቶች ............................... 229
ማጣሪያዎች ......................................... 231
ምሳሌ («በሁለት እጆቼ ..»)........................ 235
“እናንተም እንደኛው..!” ........................... 253
ምሳሌ ............................................. 253
መልስ ............................................. 254
ክፍል 7
የማንቂያ ደወል .................................... 264
ፅኑ ጥያቄዎች ..................................... 265
ታሪካዊ ውይይት.................................... 270
ክፍል 8
እውነታውን ለተፃረሩት ያለን ምልከታ.............. 274
ማስጠንቀቂያ......................................... 277

መዝጊያ ........................................................ 281

ሶስት ምክሮች

1ኛ ................................................ 283

2ኛ ................................................ 284

3ኛ ................................................ 284

ዋና ዋና ዋቢዎች ........................................ 287

የዐረብኛ መግቢያ ........................................ 289

ooo

# የሁለተኛው እትም መቅድም

ይህ የ"አማኞች ጋሻ" ሁለተኛ እትም ነው። ይህ እትም በይዘቱና በአወቃቀሩ የመጀመሪያውን ቅርፁን ባይለቅም አንዳንድ ቦታዎች ላይ ተጨማሪ ጥቅሶችንና ማብራሪያዎችን እንዲሁም ጥቂት የገለፃ ማሻሻያዎችን አካትቷል።

መፅሐፉ በተለያዩ የእውቀት ደረጃ ላይ ያሉ ሙስሊሞችን እንዲያስጠቅም የተናጠቀረ ቢሆንም እንደማንኛውም ትምህርታዊ ፅሑፍ ሁሉ ይህም ሁሉም ዘንድ በእኩል ግንዛቤ የሚስተናገድ አይሆንም፤ አቀራረቡም ለአንዳንዶች ቀላል፣ ለሌሎች ደግሞ በከፊልም ቢሆን ጠጣር መሆኑ አይቀርም። ይህን አስመልክቶ ሶስት ጥቆማዎችን ለማሳለፍ እወዳለሁ:-

**አንደኛው:-**

በመሠረቱ ማንኛውንም መፅሃፍ በድጋሚ ማንበብ ቅድሚያ ያልተገነዘቡትን የሀሳብ ትስስር ለመገንዘብ፣ ወይም ያላስተዋሉትን ቁልፍ ሃሳብ ለማስተዋል ያስችላል። የዚህ ፅሑፍ ከፊል አካል ደግሞ ውይይትን መሰረት ያደረጉ የመረጃ አቀራረቦችን የሚዳስስ ከመሆኑ አንፃር ንባብ ብቻ ሳይሆን ጥናትም የሚያሻቸው ቁምነገሮችን አዝሏል። ሆኖም ጥቅል መልእክቱ ከአንባቢያን እንደማይሰወር አያጠራጥርም።

**ሁለተኛው:-**

የመጀመሪያዎቹ ትውልዶች የነበሩበት ትክክለኛው ኢስላማዊ እምነት በቁርኣንና በሐዲሥ ለተነገሩት እውነታዎች እጅ በመስጠት ላይ የተመሰረተ በመሆኑ **በመርሆ ደረጃ** ግልጥ ያለና ከመወሳሰብ የራቀ እንደሆነ ይታወቃል። ሆኖም አንዳንድ አንባቢዎች ርእሱን የተመለከቱ አንዳንድ ትምህርቶች ላይ የሚያጋጥማቸው አቀራረብና ማብራሪያ ለግንዛቤያቸው የማይመጥን ሆኖ ይሰማቸው ይሆናል። የዚህ ዋነኛ ምክንያት በመሰል ትምህርቶች ላይ ከሚነሱት ነጥቦች መካከል ጥቂት የማይባሉት የስህተተኞችን ብዥታ በመግለጥና ምላሾቻቸውን በማብራራት ላይ ስለሚመሰረቱ ነው። ስለዚህ በዋነኛነት የሚጠናው እውነታውን የተቃረኑ ወገኖች የሚያነሱት ፍልስፍናዊ ውዥንብርና ለእሱም ዝርዝር ምላሽ የመስጠቱ ሂደት ይሆናል እንጂ እውነታው ራሱ አይደለም።

ሁለቱን አቀራረቦች ለያይቶ ለማጣጣም እንዲያግዝ የመፅሐፉ የመጀመሪያ ምዕራፍ በአመዛኙ ትክክለኛውን እምነት በማብራራት ላይ ያተኮረ እንዲሆን፣ ሁለተኛው ደግሞ መንገድ የሳቱ ቡድኖች የሚታረሙባቸው መሠረቶችን ያማከለ እንዲሆን ጥሬያለሁ።

በመሰረቱ ከትክክለኛው እምነት ጋር የሚጣረሱ ባዕድ ፈሊጦችን የሚያስሩጩ ባይኖሩ ኖሮ የሐቅ ተከታዮች አንፃራዊ ማብራሪያዎችንና ምላሾችን ለመስጠት መድከም ባላስፈለጋቸው ነበር! ሌሎች ያለአግባብ ሲዘባርቁ ግን ህዝበ ሙስሊሙን ከጥመት ለመታደግ እውነቱን ከሀሰት፣ ምራቻንም ከጥመት ለይቶ መተንተን የግድ ይላቸዋል።

➢ **አል-ኢማም አሕመድ** (241 ዓ.ሂ)[1] እንዲህ ብለዋል፡-

«كُنَّا نَأْمُرُ بِالسُّكُوتِ، وَنَتْرُكُ الْخَوْضَ فِي الْكَلَامِ وَفِي الْقُرْآنِ، فَلَمَّا دُعِينَا إِلَى أَمْرٍ مَا كَانَ بُدٌّ لَنَا مِنْ أَنْ نَدْفَعَ ذَاكَ وَنُبَيِّنَ مِنْ أَمْرِهِ مَا يَنْبَغِي»

*«ዝም እንዲባል እናዝ ነበር፤ ስለ "ከላም"-ነክ ጉዳዮችና ስለ ቁርኣን ምንነት ሀተታ ውስጥ ጠልቆ መግባትንም እንተው ነበር። ወደ ባዕድ ነገር በተጠራን ጊዜ ግን ያንን ከመጋፈጥና ስለምንነቱ ተገቢውን ገለፃ ከማድረግ ውጪ ምርጫ አልነበረንም!»*[2]

➢ እንዲሁም **አል-ኢማም ዑሥማን ኢብኑ ሰዒድ አድ-ዳሪሚይ** (280 ዓ.ሂ) እንዲህ ብለዋል፡-

«وَقَدْ كَانَ مَنْ مَضَى مِنَ السَّلَفِ يَكْرَهُونَ الْخَوْضَ فِي هَذَا وَمَا أَشْبَهَهُ، وَقَدْ كَانُوا رُزِقُوا الْعَافِيَةَ مِنْهُمْ، وَابْتُلِينَا بِهِمْ عِنْدَ دُرُوسِ الْإِسْلَامِ، وَذَهَابِ الْعُلَمَاءِ؛ فَلَمْ نَجِدْ بُدًّا مِنْ أَنْ نَرُدَّ مَا أَتَوْا بِهِ مِنَ الْبَاطِلِ بِالْحَقِّ..»

---

(1) በዚህ መፅሐፍ ከግለሰብ ስሞች ጎን እንዲህ አስከትዬ በቅንፍ የማሰፍራቸው አሃዞች የሚያመለክቱት ግለሰቡ እንደ ሂጅራ አቆጣጠር የሞተበትን አመት መሆኑ ይታወቅልኝ።

(2) "አስ-ሱን-ናህ" ሊኻል-ኸል-ላል (5/134) ቁጥር 1797

*«ያለፉት አበው ትውልዶች በዚህና መሰል ጉዳዮች ላይ ሀተታ ውስጥ ጠልቆ መግባትን ይጠሉ ነበር። እነርሱ (ከጥመት አሰራጮች) ሰላምን ተለግሰው ነበር፤ እኛ የኢስላም ፋና በደበዘዘበትና ዑለማዎች በተመናመኑበት ጊዜ በነርሱ ተፈትነናልና ያመጡትን ሐሰት በእውነት ከመመለስ ውጭ አማራጭ አላገኘንም!..»*[1]

**ሶስተኛው ጥቆማ፡-**

በዚህ ፅሑፍ ላይ ከኢስላም ሊቃውንት የተወሰዱ አንዳንድ አእምሯዊ ማስረጃዎችና ትንታኔዎች እንዳሉ ግልፅ ነው። እነኚህን ትንታኔዎች ከአንዳንድ አንጃዎች ፍልስፍናዊ ሙግት ጋር ደባልቀው በአንድ አይን የሚያዩ እጅግ የተሳሳተ ፍርድ ፈፅመዋል።

የሁለቱ ልዩነት በብዙ ነጥቦች መብራራት የሚችል ከመሆኑ ጋር ሁለቱን ብቻ ላውሳ፡-

1- ትክክለኛ አእምሯዊ አስረጆች የሚጠቀሱት ቁርአናዊ እውነታዎችን አስከትለው ሳይሆን ተከትለው፤ እነርሱንም ተፃርረው ሳይሆን አፅንተው መሆኑ ሊስተዋል ይገባል።

(1) "አር-ረድ-ዱ ዐለ'ል-ጀህሚይ-ያህ" ሊ'ድ-ዳሪሚይ ገፅ 33፤ በተጨማሪም "ነቅዱ ዑሥማን ኢብኒ ሰዒድ ዐላ ቢሽር አል-መሪሲ አል-ዐኒድ" ሊ'ድ-ዳሪሚይ (1/536 – 541) ይመልከቱ።

በአንፃሩ እነዚያ ሙግቶች ቅድሚያ ለተወጠነ መደምደሚያ እማኝ እንዲሆኑ ሲመዘዙና ቁርኣናዊ እውነታዎችን ለመፃረር ሲውሉ ይስተዋላል።

2- ትክክለኛ አእምሯዊ ማስረጃ ማንኛውም ንፁህ አእምሮ ሊያብላላቸው የሚችሉ ቀላልና ግልፅ መመዘኛዎችን የሚያማክል ነው።
ፍልስፍናዊ ሙግቶች ግን አንዳንዴ አእምሯዊ መመዘኛዎችን ሊመርኮዙ ቢችሉም በዋነኛነት የሚመሰረቱት ጥቂት "አዋቂዎች" በሚቀይሱት መስመርና ዘርፍ ላይ ነው። ስለሆነም ይህንን ዘርፍ ያላጠና ሰው ሊገነዘባቸው የሚያዳግቱ የሀሳብ ቀመሮችና ገለፃዎች ይስተዋሉባቸዋል።

አላህ ይበልጥ አዋቂ ነው።

በተረፈ የትኛውንም አይነት አስተያየት በሚከተለው የኢሜይል አድራሻ ቢልኩልኝ ምስጋናዬ የላቀ ነው።

**ilypia@gmail.com**

*ሸዕባን 1437*

# የመጀመሪያው እትም መቅድም

ክንባቢ ሆይ! ይህ ፅሁፍ ከበርካታ ጥናቶች ተጨምቆ የወጣ ትምህርታዊ ጥንቅር ነው፤ በቁርኣንና በትክክለኛ የሐዲሥ ዘገባዎች በተወሱት የአላህ መገለጫዎች ዙሪያ የሚራገቡ "ውዝግቦች"ን አስመልክቶ ሁሉም ሙስሊሞች ሊጓዙበት የሚገባውን የመፍትሄ ጎዳና በግላጭ ያመላክታል።

ፅሁፉ በሁሉም የአላህ ባህሪያት ዙሪያ ዝርዝር አስተምህሮቶች እንዲሰጥ ታቅዶ የተዘጋጀ አይደለም። ሆኖም በአላህ ፈቃድ መሠረታዊና መርኋዊ በሆነ ዳሰሳ ትክክለኛውን የኢማን አድማስ አጉልቶ ለማሳየትና በርዕሱ ላይ የሚነሱ ውዥንብሮችን ከስር-መሠረታቸው ለመፈንቀል የሚያበቃውን ብቃት እንደተጎናፀፈ አስባለሁ።

በተቻለኝ አቅም በተለያዩ የእውቀት ደረጃዎች ላይ ያሉ ወንድሞችንና እህቶችን ግንዛቤ የሚመጥንና ከግልፅነት ጋር ጥልቀትን፣ ከአስተማሪነት ጋር አራሚነትን፣ ከመርሆዎች ጋር ምሳሌዎችን ያቀራኘ እንዲሆን ለማድረግ ሞክሬያለሁ። የቁርኣንና የሐዲሥ ጥቅሶችን ከቀደምት ሊቃውንት የአንድነት አቋም ("ኢጅማዕ") ጋር በማዛመድና ከትክክለኛ አእምሯዊ አስረጆች ጋር በሚዛናዊነት በማስተሳሰር ለግንዛቤና ለጥናት በሚያመች ቅደም-ተከተል በአጭሩ ከትቤዋለሁ።

የትምህርቱ አበይት አጀንዳዎች የተጠናቀሩት በሁለት ምዕራፎች ሲሆን እያንዳንዳቸው በተያያዥ ርዕሰ-ጉዳዮች የተከፋፈሉ ናቸው። የመጀመሪያው ምዕራፍ ትክክለኛው እምነት በሚብራራባቸው መርሆዎች ዙሪያ በዋነኝነት የሚያጠነጥን ሲሆን ሁለተኛው ደግሞ መንገድ የሳቱ ቡድኖች የሚታረሙባቸው መሠረቶችን ያማከለ ነው።

አላማዬ ትክክለኛውን እምነት በእውቀትና በእውነት ሚዛን አጣርቶ ለሙስሊም ወንድሞቼና እህቶቼ ማቅረብ ነው! ከአንባቢያን የሚጠበቀው ደግሞ **ቅንነትና አስተውሎት** ብቻ ነው፤ ሁለቱ ካሉ በአላህ ፈቃድ እውነቱ = ቀድሞውኑ የነበረ፣ ግልፅ፣ ለአእምሮ የማይከብድና ያልተወሳሰበ መሆኑን፣ በአንፃሩ ደግሞ ስህተቱ = መጤ፣ ግራ የሚያጋባ፣ የተምታታና ውስብስብ መሆኑን በቀላሉ መረዳት ይቻላል!

---

አዎን! ጥቂት የማይባሉ ግለሰቦች በአላህ ባህሪያት ዙሪያ የሚስተጋቡ አለመግባባቶችን በኢስላም ሊቃውንት መካከል የተከሰቱ ተራ የውዝግብ ርዕሶች አድርገው ስለሚገምቱ የትምህርቱ አንገብጋቢነት ላይታያቸው እንደሚችል አልጠፋኝም! ብዙዎቹ ይህን መሰል አደገኛ ድምዳሜ የሚያንፀባርቁት ከግንዛቤ እጥረት በመጣ የዋህነት ሲሆን ሌሎች ደግሞ በጉዳዩ ላይ ከሚነሳ እሰጥ አገባ ጭራሹኑ ለመሸሽ ነው።

ይህንን ብዥታ ለማስወገድ ባጭሩ አንድ ቁም ነገርን ማስታወስ እወዳለሁ:-

በሸሪዓዊ ጉዳዮች ላይ ስለሚነሱ ውዝግቦች ሊኖረን የሚገባውን ምልከታ በሁለት ከፍለን ልናይ እንችላለን፡-

**1- በጉዳዩ ላይ የሚሰጠው ሸሪዓዊ ፍርድ በግልጽ ቁርአናዊና ነቢያዊ አስተምህሮቶች የተቋጨና በቀደምት ዑለማዎች ሙሉ ስምምነት የፀደቀ እንደሆነ የትኛውም ዓይነት ውዝግብ የሚስተናገድበት መድረክ አይኖርም፤ ብይኑንም ያለምንም ማንገራገር ተቀብሎ ማስተናገድ የግድ ይሆናል። ይህንን እውነታ ከተረዱ በኋላ በአጀንዳው ላይ ከተመለከተው ሸሪዓዊ አስተምህሮት ጋር የሚጣረስ አቋም ማንፀባረቅ አላህ ከዘረጋልን ቀጥተኛ ጎዳና ማፈንገጥ በመሆኑ ለውግዘት ይዳርጋል!**

📖 قَالَ تَعَالَىٰ: ﴿وَمَن يُشَاقِقِ ٱلرَّسُولَ مِنۢ بَعۡدِ مَا تَبَيَّنَ لَهُ ٱلۡهُدَىٰ وَيَتَّبِعۡ غَيۡرَ سَبِيلِ ٱلۡمُؤۡمِنِينَ نُوَلِّهِۦ مَا تَوَلَّىٰ وَنُصۡلِهِۦ جَهَنَّمَۖ وَسَآءَتۡ مَصِيرًا﴾ [النساء: ١١٥]

➡ «(የ)ምሪቱ (መንገድ) ከተገለጠለት በኋላ መልዕክተኛውን የሚፃረርና ከሙእሚኖች መንገድ ሌላ የሚከተል የመረጠውን (ጥመት) እናሸክመዋለን፤ ጀሀነምም እናስገባዋለን፤ ከመመለሻነቷ (ስፍራ)ም የከፋች ሆነች!» [አን-ኒሳእ 115]

**ለዚህ ክፍል ምሳሌ ሊሆኑ የሚችሉ በርካታ ድንጋጌዎች አሉ፤ ከአላህ በቀር ማንንም (የአምልኮ ጥሪ) አለመጣራት፣ የአላህ ስሞችንና ባህሪያቱን መልዕክታቸውን ሳያዛቡ በተገቢው መልኩ ተቀብሎ ማስተናገድ፣ ኢማን መልካም ንግግርንና ተግባርን እንደሚያካትት ማረጋገጥ፣ በቀደር በአግባቡ ማመን ...ወዘተ።**

እነኚህ ከእምነት ህልውና ጋራ ቀጥተኛ ዝምድና ያላቸው ጉዳዮች ላይ ምንም አይነት ቦታ የሚሰጠው "ኺላፍ" (ውዝግብ) የለም!

በርግጥ ከመጀመሪያዎቹ ምርጥ ትውልዶች በኋላ ከመጡት የኋለኞቹ ሊቃውንት መካከል አንዳንዶቹ እንደሌሎች ርዕሶች ሁሉ በዚህኛውም ላይ በተለያዩ ምክንያቶችና ተፅዕኖዎች የተነሳ ስህተት ላይ መውደቃቸው ይታወቃል። ይህ አቋማቸው ግን እንደ ስህተት ታይቶ በአግባቡ ይታረማል እንጂ የቀድሞዎቹን ትውልዶች (ሰለፎች) ስምምነት የሚንድ "ኺላፍ" በፍፁም አይሆንም!

አዎን! እውነትን ፍለጋ ለተሳሳቱ ዓሊሞች የሚሰጠው ማስተካከያ ክብራቸውን በሚጠብቅ ስርዓትና ሂደት እንጂ በቢድዓ አራማጅ ጎጠኞች ላይ እንደሚደርሰው ውግዘት አይደለም! ሆኖም ስህተት ማንም ይስራው ማን ሁሌም ስህተት ነው! ስህተት ሁሉ ደግሞ የመደበኛ «ኺላፍ» ሚዛን ላይ አይሰቀልም፤ አጀንዳው በግልጽ ቁርአናዊና ነብያዊ አስተምህሮቶች የተቋጨና በቀደምት ዑለማዎች ሙሉ ስምምነት የተዘጋ **የአንድነት ርዕስ** እንጂ የኺላፍ ርዕስ አይደለምና! አለበዚያ ማንም በዲን ስም ያሻውን አቋም ያለተቃውሞ እንዲያራምድ ሰፊ በር መክፈት ይሆንብናል!

**ይህ ፅሑፍ** የሚያጠነጥንበት ርዕሰ-ጉዳይ ላይ የሚነሱ አንዳንድ "ውዝግቦች"ም ከዚህኛው ጎራ እንደሚመደቡ እማኝ የሚሆኑ ማስረጃዎችንና ሰለፎችም ዘንድ በዚሁ እይታ እንደተስተናገዱ የሚያረጋግጡ አስተማማኝ ዘገባዎችን በንባብዎ ውስጥ ያገኛሉ።

እናም ይህንን መሰል መሠረታዊ ጉዳይ ከአንዳንዶች እንደምንሰማው "ተራ የኺላፍ ርዕስ" ወይም "ፍሬ-አልባ

ውዝግብ" ብሎ መሰየም የቀደምት የኢስላም ምርጥ ትውልዶችንና ተተኪ መሪዎችን የክፍለ-ዘመናት ልፋት፣ ገድልና መስዋትነትን ከንቱና እርባና-ቢስ አድርጎ መቁጠርና አደራቸውንም መብላት መሆኑን ማወቅ ያሻል!

2- በርዕሶቹ ላይ የሚጠቀሱት ማስረጃዎች የሚጠቁሙትን መልዕክት በተመለከተ ቀደምት የኢስላም ሊቃውንት በግንዛቤ ልዩነት የተለያየ አቋም ያንጸባረቁ ከሆነና ጉዳዮቹ በዑለማዎች ዘንድ ሸሪዓዊ ምልከታን ("ኢጅቲሃድ"ን) የሚያስተናግዱ መሆናቸው የታወቀ እንደሆነ አንድ ዓሊም ከዚህ በፊት ከነበሩት የዑለማዎች አቋሞች አንዱን ቢመርጥ፣ ብሎም ቢሳሳት ፍርዱ እንደሙሉ ጥፋት ተወስዶ አይኮነንም፤ መልዕክተኛው (ﷺ) እንደዚህ ብለዋል፦

☜ «إِذَا حَكَمَ الْحَاكِمُ فَاجْتَهَدَ ثُمَّ أَصَابَ فَلَهُ أَجْرَانِ، وَإِذَا حَكَمَ فَاجْتَهَدَ ثُمَّ أَخْطَأَ فَلَهُ أَجْرٌ»

➥ «አንድ ፈራጅ ሲፈርድ (እውነታን ለመረዳት) ተጣጥሮ ትክክል ከሆነ ሁለት ምንዳ (አጅር) አለው፤ ሲፈርድ (እውነታን ለመረዳት) ተጣጥሮ ከተሳሳተ ደግሞ አንድ አጅር አለው!»(1)

ሆኖም የላይኛው ሐዲሥ እንደሚያስረዳው በዚህኛውም ርዕስ ላይ ቢሆን እውነትን ለማወቅ ሁሉም እንደየአቅሙ መጣር ይጠበቅበታል።

---

(1) አል-ቡኻሪይ (7352) ፣ ሙስሊም (1716)

---

በመጨረሻም ይህ ፅሁፍ ለስህተተኞች ምራቻን፣ ለተጠራጣሪዎች እርግጠኝነትን፣ ለእርግጠኞች ደግሞ ፅናትን የሚያወርስ እንዲሆን አላህን እማፀናለሁ! በመፅሃፉ ላይ የተብራሩትን ቁም ነገሮች በአግባቡ መረዳት በአላህ ፈቃድ ከጥመት ውዥንብሮች መጠበቂያ እንዲሆን ተስፋ በማድረግ "የአማኞች ጋሻ" ብዬ ሰይሜዋለሁ።

*ኢልያስ አሕመድ*

# መሸጋገሪያ

## ክፍል አንድ

### የጉዳዩ አንገብጋቢነት

የዕውቀት አይነቶች ብዙ ናቸው፤ የአስፈላጊነታቸውም ደረጃ እንዲሁ ይለያያል። ታዲያ የአንድ ዘርፈ-ዕውቀት ክብርና ቦታ በዋነኝነት የሚለካው በውስጡ ባካተተው ርዕስ ታላቅነት መሆኑ ይታወቃል። በዚህም መሠረት በዕውቀት ሊዳሰሱ ከሚችሉ አጀንዳዎች ሁሉ ይበልጥ ክቡርና አሳሳቢ የሆነው የጌታችን ማንነት የሚገለፅባቸውን አምላካዊ ስሞቹንና ባህሪዎቹን የተመለከተው ርዕሰ-ጉዳይ ነው።

✷ የርዕሱን ታላቅነት ከሚያጎሉት ምክንያቶች አንዱ ከፍጥረተ-ዓለሙ መገኘትና በውስጡ ከሚስተናበሩት ሂደቶች በስተኋላ ካሉት ጥበቦች ጋር ያለው ቁርኘት ነው:-

📖 قَالَ تَعَالَى: ﴿ٱللَّهُ ٱلَّذِى خَلَقَ سَبۡعَ سَمَٰوَٰتٍ وَمِنَ ٱلۡأَرۡضِ مِثۡلَهُنَّ يَتَنَزَّلُ ٱلۡأَمۡرُ بَيۡنَهُنَّ لِتَعۡلَمُوٓاْ أَنَّ ٱللَّهَ عَلَىٰ كُلِّ شَىۡءٍ قَدِيرٌ وَأَنَّ ٱللَّهَ قَدۡ أَحَاطَ بِكُلِّ شَىۡءٍ عِلۡمَا﴾ [الطلاق: ١٢]

➡ «አላህ ያ ሰባት ሰማያትን ከምድርም መሰላቸውን የፈጠረ ነው፤ በመካከላቸው ትዕዛዙ ይወርዳል:- <u>አላህ በሁሉ ነገር ላይ ቻይ መሆኑንና ሁሉን ነገር በዕውቀቱ እንዳካበበ ታውቁ ዘንድ</u>» [አጥ-ጦላቅ 12]

አዎን! የዚህን ግዙፍ ዓለም ረቂቅ ሂደትና ክንውን የሚቆጣጠረውና የሚያስተናብረው ፈጣሪያችን ችሎታው ያለ ልኬት የመጠቀ፣ ጥበቡ ያለ አምሳያ የረቀቀ፣ ዕውቀቱ ያለ ገደብ የጠለቀ ስለመሆኑ የፍጥረተ-ዓለሙ ትዕይንት ራሱ መስካሪ ነው። ይህን ማወቃችንም ፍጥረታት ከተገኙበት ክቡር ዓላማዎች አንዱ መሆኑን የላይኛው አንቀፅ በግልፅ ያስረዳል።

✸ እንደሚታወቀው ከኢማን መሰረቶች የመጀመሪያውና ዋነኛው ምሰሶ በአላህ ማመን ነው፤ ይህ ደግሞ ብቸኛ ጌትነቱንና አምላክነቱን ከማረጋገጥ ጋር በመልካም ስሞቹና ባህሪያቱ ማመንን ያጠቃልላል። እንዲያውም አላህ በእነዚህ ስሞቹና መገለጫዎቹ ተጋሪ የሌለው ብቸኛ መሆኑን ማፅደቅ ሌሎቹን የተውሒድ ዘርፎች በአግባቡ ለማረጋገጥ የሚደለደል መሠረት ነው! ምክንያቱም፦

✸ በቁርኣንና በነብዩ (ﷺ) አስተምህሮቶች የተዘረዘሩት መልካም ስሞቹና እንከን - የለሽ ባህሪያቱ ፍፁምነቱንና ምሉዕነቱን በተለያዩ መንገዶች የሚገልፁ ናቸው። እነዚህ የጌትነት መገለጫዎቹ ደግሞ የአምልኮ ብቸኛ ባለቤትና ባለመብት እንደሆነ ስለሚያረጋግጡ ባሮች ጌታቸውን በነዚህ ያማሩ ስሞች እንዲጠሩትና እንዲለምኑት ታዘዋል።

📖 قَالَ تَعَالَى: ﴿وَلِلَّهِ ٱلۡأَسۡمَآءُ ٱلۡحُسۡنَىٰ فَٱدۡعُوهُ بِهَاۖ وَذَرُواْ ٱلَّذِينَ يُلۡحِدُونَ فِيٓ أَسۡمَٰٓئِهِۦۚ سَيُجۡزَوۡنَ مَا كَانُواْ يَعۡمَلُونَ﴾ [الأعراف: ١٨٠]

➥ «ለአላህም ከሁሉ የተሻሉ መልካም ስሞች አሉት፤ በነሱም ጥሩት፤ እነዚያ ስሞቹን የሚያጣምሙትንም ተዉዋቸው፤ ይሰሩት የነበረውን (ዋጋ) ይመነዳሉ፡፡» [አል-አዕራፍ 180]

✸ እንዲሁም ነብያት አላህ ያለ አንድም ተጋሪ ሊመለክ የሚገባው መሆኑን ለህዝቦቻቸው ሲያስተምሩ የዚህ ታላቅ መብት ብቸኛ ባለቤት የሚያደርጉትን ባህሪያቱንና መገለጫዎቹን እያወሱ ነበር! በአንፃሩ ደግሞ ቢያንስ እንደ ማየት፣ መስማትና መናገር ያሉ የምሉዕነት ባህሪያት የሌሉት ማንኛውም አካል ይህ ጉድለቱ ለርሱ የሚውለውን የትኛውንም የአምልኮ ዘርፍ ከመሠረቱ ፉርሽ ከሚያደርጉ አስረጆች እንደሚመደብ በማስረዳት ጥሪያቸውን ያካሂዱ ነበር! ለምሳሌ፡- አላህ በቁርኣኑ ታላቁ ነብይ ኢብራሂም ﷺ ለጣዖት አምላኪ አባታቸው የተናገሩትን ሲያስተላልፍልን እንዲህ ይላል፡-

📖 ﴿ إِذْ قَالَ لِأَبِيهِ يَـٰٓأَبَتِ لِمَ تَعْبُدُ مَا لَا يَسْمَعُ وَلَا يُبْصِرُ وَلَا يُغْنِى عَنكَ شَيْـًٔا ﴾ [مريم: ٤٢]

➥ «ለአባቱ፡- "አባቴ ሆይ! ለምን የማይሰማ፣ የማያይና ምንም የማይጠቅምህን ታመልካለህ?!" ባለ ጊዜ..» [መርየም 42]

እንደዚሁም አላህ የሙሳ (ﷺ) ህዝቦችን ሲነቅፋቸው እንዲህ ይላል፡-

📖 ﴿ وَٱتَّخَذَ قَوْمُ مُوسَىٰ مِنۢ بَعْدِهِۦ مِنْ حُلِيِّهِمْ عِجْلًا جَسَدًا لَّهُۥ خُوَارٌ ۚ أَلَمْ يَرَوْا۟ أَنَّهُۥ لَا يُكَلِّمُهُمْ وَلَا يَهْدِيهِمْ سَبِيلًا ﴾ [الأعراف: ١٤٨]

➥ «የሙሳ ህዝቦችም ከርሱ (መሄድ) በኋላ ጩኸት ያለው በድን ጥጃ ከጌጦቻቸው (በመስራት) (አምላክ አድርገው) ያዙ፤ እርሱ እንደማያናግራቸውና መንገድ እንደማይመራቸው አላዩምን?!..»[አል-አዕራፍ 148]

✸ በደፈናው የፈጣሪን ስሞችና ባህሪያት በተገቢው መልኩ መገንዘብ ወደ ሐሰት የአምልኮ መስኮች የሚያመሩ መንገዶችን ሙሉ በሙሉ የሚዘጋ ከመሆኑ ባሻገር በዚህች ምድር የመገኘታችን ምክንያት የሆነውን ክቡር አምልኳዊ ግዴታ በአግባቡ እንድንወጣ ይረዳናል!

✸ መቼም የማንኛውም ሰው ልቦና ስለሚገዛው አምላክ ማንነት በጥቅሉም ቢሆን ለማወቅ ይጓጓል፤ ጭራሽ የማያውቁትን ማምለክና መውደድ የሚያዳግት ነውና!
ታዲያ አላህን እርሱ ራሱና መልዕክተኞቹ በገለፁት መልኩ ማወቅ ከጥራዝ-ነጠቅ ንትርኮችና ከህሊናዊ ውጥንቅጦች በማሳረፍ የእምነት እርካታን ያወርሰናል። የኢማናችንን አድማስም በየአቅጣጫው ያሰፉልናል፤ ለርሱ ያለንን ውዴታና ፍራቻም በውስጠ-ልቦናችን በማሳደግ በአምልኮ መስክ ላይ ብርታትን ያላብሰናል! ምክንያቱም እያንዳንዱን የአላህ ስም እና ባህሪ በአግባቡ ማወቅ በዚያው ልክ ራሱን የቻለ የአምልኮ ፍሬ ያፈራልና!

ለምሳሌ፡- አላህ ሰሚ፣ ተመልካች እና ሁሉን አዋቂ መሆኑን በፅኑ ያመነ ሰው አንደበቱን እና አካሉን አላህ ከማይወደው ንግግርና ተግባር ለመጠበቅ ሳይታክት ይጥራል! አላህ መልካም ሰሪ አማኞችን እንደሚወድ ያረጋገጠም የርሱን ውዴታ ለመጎናፀፍ ለመትጋት ይነሳሳል፤ በሩህሩህነቱ የሚያምንም እዝነቱን ይለምናል፤

ከቁጣውም ይጠነቀቃል!.. ለዚህ ነው “ከሰዎች አላህን ይበልጥ የሚፈሩት ይበልጥ የሚያውቁት ናቸው” የሚባለው!

ስለሆነም ሀይማኖቱን በትክክለኛ መሠረት ላይ መገንባት የሚሻ ማንኛውም ሙስሊም ይህንን የእምነት መሠረት ከሚበክሉ ወረርሽኞች ራሱን ሊያድን ይገደዳል!

ooo

## ክፍል ሁለት

### የ"ውዝግቡ" አነሳስ

የመጨረሻው መልዕክተኛ ﷺ የቀድሞዎቹን ነብያት ተልዕኮ የሚያረጋግጡና የሚያሟሉ ግልፅ መለኮታዊ መመሪያዎችን ይዘው ብቅ እንዳሉ በዐረቢያ ምድር አጥልቶ የነበረው የመሃይምነት ፅልመት ተገርስሶ የቅናቻ ወጋገን በየአድማሱ ተሰራጨ። የመልዕክተኛው ታታሪ ሰሓቦችም ከጌታቸው ዘንድ ለተላከው ፍፁም መመሪያ በቅን ልቦና ተገዢ መሆናቸውን በንፁህ ተግባራቸው አስመሰከሩ። አዎን! በጥራዝ ነጠቅ ፍልስፍና አእምሯቸው አልተበረዘም፤ በአጉል ፈሊጥም እይታቸው አልተሟሸም፤ የመልዕክተኛው አስተምህሮት ስብእናቸውን በቁርአናዊ ስርዓት አንፆታልና!

ከእሳቸው (ﷺ) ሕልፈተ-ሕይወት በኋላ በነበሩት ዘመናትም በተለያዩ የዓለም ማዕዘናት የኢስላም ስርጭት ሲቀጥል ሰሓቦችና ቅን ተከታዮቻቸው በጫንቃቸው ላይ የተጣለውን የእምነት ሀላፊነት በመወጣት ረገድ ለተተኪው ትውልድ መልካም አርዓያ ሆኑ። በተለያዩ የእምነት መስኮችም የቀድሞውን ነብያዊ ፋና በመከተል በወንድማማችነት መንፈስ ተዋህደው አንድነታቸውን ጠብቀው ሰነበቱ። ይህንን ድንቅ የኢማን ትስስር ሊያላሉ የሚችሉ አንዳንድ አለመግባባቶች ከተከሰቱ ወደ ቁርአንና ወደ መልዕክተኛው (ﷺ) ፈለግ በመመለስ መፍትሄን ይሹ ነበር።

ሆኖም ወደሚቀጥሉት ትውልዶች በጥራት እየተላለፈ የነበረውን የእምነት አደራ የሚያደፈርሱ አዳዲስ ፈሊጦች በሙስሊሙ ማህበረሰብ መሐል ማጎጥጎጥ የጀመሩት ገና ከረፋዱ ነበር።

**ነገሩ እንዲህ ነው፡-**

አንዳንዶች በጠባብ "አእምሯዊ" እይታዎች ላይ ተመርኩዘው በመለኮታዊው መመሪያ በተገለፁት እምነታዊ ጉዳዮች ላይ አዳዲስ አመለካከቶችን መሰንዘር ጀመሩ! ይህ አጋጣሚ የደላቸው ከጥንቱ የኩፍር አሻራ ያልተፈወሱ አንዳንድ አሜኬላዎች በማህበረሰቡ መሀል ተሰግስገው መርዛቸውን በማር እያላወሱ በመርጨት እገዛ አደረጉላቸው።

ይህ ሁሉ ሲሆን በዕውቀት የተካኑት የኢስላም ባለአደራ ጀግኖች እጃቸውን አጣምረው አላዩም። የሰሓባዎች ትውልድ ሳይገባደድ በፊት አንዳንድ የፈጠራ ተግባራትና አመለካከቶች ቢስተዋሉም በአብዛኛው በውስን ግለሰቦች ላይ የተገደቡ ስለነበሩ እነርሱ የሚጭሩትን የቢድዓ እሳት የመልዕክተኛው (ﷺ) ምርጥ ወራሾች በዕውቀት ባህራቸው ከመቅፅበት አዳፍነው ያከስሙት ነበር።

**የአንጃዎች መፈልፈል**

ለመጀመሪያ ጊዜ በአዲስ ፈሊጣዊ እምነት ላይ የተገነባ አንጃ መስርተው በቡድናዊነት ራሳቸውን ከብዙሀኑ ሕዝበ-ሙስሊም ያገለሉት *«አል-ኸዋሪጅ»* የተባሉት ጭፍራዎች ነበሩ። እነርሱም *በዐሊይ ኢብኑ አቢ ጧሊብ* (رضي الله عنه) ዘመነ-መንግስት ነበር ብቅ ያሉት። *«ከባባድ ኃጢያቶችን የፈፀመ ሁሉ ካፊር ነው!!»* የሚል

**አዲስ መፈክር አነሱ። ይሄኛው አቀበት ደግሞ ወደሌሎች የቢድዓ አዘቅቶች ተንሸራተው እንዲገቡ አደረጋቸው።**

**ከዚያም *ዐሊይ ኢብኑ አቢጣሊብን* እና የረሱልን (ﷺ) ቤተሰቦች በመውደድ ሽፋን የተከለሉ ቅቤ አንጓቾች የ«ሺዓህ» እምነትን መሰረት ዘረጉ።**

**ቀጥሎም ከዋነኛ የኢማን መሰረቶች አንዱ የሆነውን «ቀደር»ን ያስተባበሉ ግለሰቦች ተገኙ።**

**ተግባርን ከእምነት በመነጠል የታወቁት የ*«ሙርጂአህ»* ቡድኖችም *«ኢማን አይጨምርም፤ አይቀንስም!»* ብለው አረፉት።**

**የ*«ሙዕተዚላህ»* ጭፍራዎችም ከተለያዩ የቢድዓ አቋሞች ጋር ራሳቸውን ለሙስሊሙ ማህበረሰብ አስተዋወቁ። ያኔ ቢድዓቸው በብዛት ያጠነጥን የነበረው ኃጢያት ለሰራ ሙስሊም በሚሰጠው ብይንና በ“ቀደር” ዙሪያ ነበር።**[1]

## የባሰ ጣጣ..

**የከፋው ዱብዳ የተከሰተው ግን በሁለተኛው ምዕተ-አመት የመጀመሪያ አጋማሽ ላይ ነበር። በተለያዩ የግሪክና የሮማን ሚዛን-የለሽ ፍልስፍናዎች የታነፁ ግለሰቦች አላህ በቁርኣኑ፣ መልዕክተኛው**

(1) *መጀመሪያ ብቅ እንዳሉ ለተወሰኑ ጊዜያት ስለ አላህ ስሞችና ባህሪያት መናገር አልጀመሩም ነበር።* [“ሸርሑ’ል-ዐቂደቲ’ል-አስበሃኒይ-ያህ” ሊሸይኺ’ል-ኢስላም ገፅ 111 ]

ደግሞ በአስተምህሮቶቻቸው ያፀደቋቸውን የጌታችንን ስሞችና ባህሪያት በተምታታ ፈሊጣቸው ማስተባበልና ትርጉማቸውን ማዛባት ጀመሩ። በዚህም ሂደት የፈጣሪን ህልውና ትርጉም በሚያሳጡ ንግግሮች መዘላበድ ቀጠሉ።

በኢስላም ታሪክ ውስጥ የዚህን እንግዳ ፈሊጥ የመሰረት ድንጋይ በማኖሩ የሚታወቀው ግለሰብ *አል-ጀዕድ ኢብኑ ዲርሀም* ተብሎ ይጠራል።[1] ይህንን ጥመት ከርሱ ወርሶ ከሌሎች ፈሊጦች ጋር በመቀየጥ በተባው ልሳኑ ወደ ሕዝበ-ሙስሊሙ መርዙን የረጨው ጋሻ ጃግሬው *አል-ጀህም ኢብኑ ሰፍዋን (128 ዓ.ሂ)* ነበር።

በዚህም የተነሳ **በሙሉም ይሁን በከፊል** የአላህን ስሞችና ባህሪያት ቀጥተኛ መልዕክት ላለመቀበል ትርጉማቸውን የሚያዛቡ ሁሉ ሰለፎች ዘንድ **"ጀህሚይ-ያህ"** (جهميَّة) በሚል መጠሪያ ስር ይካተቱ ነበር።

(1) አንዳንድ ሊቃውንትና የታሪክ ዘጋቢዎች እንደሚያስገነዝቡት ግለሰቡ የጥመቱን ፅንሰ-ሀሳብ የወሰደው ከ*አባን ኢብኑ ሰምዓን* ሲሆን እርሱ ደግሞ *'ጧሉት'* ከተባለ *የለቢድ ኢብኑ'ል-አዕሰም* እህት ልጅ ነው የተማረው፤ *ጧሉት* ደግሞ ከአጎቱ *ለቢድ! ለቢድ ኢብኑ'ል-አዕሰም* እንደሚታወቀው በመልዕክተኛው ላይ ድግምት የተበተበው አይሁዳዊ ግለሰብ ነው! ["ታሪኹ ዲመሽቅ" ሊ'ብኒ ዐሳኪር (72/99-100)፣ "አል-ካሚል ፊ'ት-ታሪኽ" ሊብኒ'ል-አሢር (6/149)፣ "አል-ቢዳያህ ወ'ን-ኒሃያህ" ሊ'ብኒ ከሢር (13/147) ..እና ሌሎች መዛግብትን ይመልከቱ።]

ይኸኛውን የቢድዓ ጎዳና ከሌሎቹ የከፋ ከሚያደርጉት ምክንያቶች መካከል ሁለት ነገሮች አሉ፡-

**አንደኛው፡-** ጉዳዩ በቀጥታ ከጌታ ማንነትና ህልውና ጋር የተያያዘ መሆኑ ሲሆን፤

**ሁለተኛው፡-** የዚህኛው ቢድዓ አራማጆች የቁርኣንና የሐዲሥ አስተምህሮትን በተለያዩ ተፃራሪ «ፍልስፍናዊ» ፈሊጦች በድፍረት መጋፈጣቸው ነው![1]

ይኸኛውም አባዜ እያደር ወደተለያዩ ቡድኖች መሸጋገር ያዘ።

ሁኔታውን በጣም ያባባሰው ደግሞ በመእሙን የኸሊፋነት ዘመን (198 - 218 ዓ.ሂ) የተከፈተው ሰፊ የጥመት በር ነበር! ይህ ኸሊፋ ባልተለመደ መልኩ ታላላቅ የቢድዓ አቀንቃኞችን በመወዳጀት የቅርብ አማካሪው ሲያደርጋቸው ነበር ነገር የተበላሸው!

የተለያዩ የግሪክና የህንድ ቀደምት ፈላስፋዎች መለኮታዊ የእምነት ጉዳዮችን ጨምሮ በተለያዩ ርእሶች ዙሪያ የፃፏቸውን ድርሳናት ከቤዛንታይን ግዛቶች (በተለይ ከቆጵሮስ) በማስላክ ወደ ዐረብኛ ቋንቋ እንዲተረጎሙ አደረገ! ይህ ደግሞ ለግድፈቶቹ ዋነኛ መንስኤ

(1) ከነሱ በፊት የነበሩት የቢድዓ አራማጆች የቁርኣንና የሐዲሥን ትክክለኛ መልዕክት በማዛባት፣ በመጨመርና በመቀነስ አዳዲስ የጥመት ጎዳናዎችን ቢደለድሉም እንደነኚህ መለኮታዊ መመሪያዎችን ከመሰረቱ ገሸሽ በማድረግ ለቁንፅል አእምሯዊ ፈሊጦቻቸው ቅድሚያ ለመስጠት አልዳዱም ነበር!

የሆነው “ዒልሙ’ል-ከላም” እንዲስፋፉ ትልቅ እገዛ አደረገ![1] በዚህ ላይ ኸሊፋው የህዝበ-ሙስሊሙን የጠራ እምነት በስልጣኑ ሀይል ለመበከል ትዕዛዙን በሁሉም ግዛቶች በተዋረድ አስተላለፈ! ከርሱ በኋላ የተተኩት ሁለት ኸሊፋዎችም በደመነፍስ ዱካውን ተከተሉ! ወይ ፈተና..!

በዚህ መልኩ የጥንቱን የጧቱን ቀጥተኛ መንገድ የለቀቁ አንጃዎች በተለያዩ ርዕሰ-ጉዳዮች ላይ ባይተዋር የእምነት ፈሊጦችን አንግበው በየአቅጣጫው ተፈለፈሉ። የመልዕክተኛውም (ﷺ) ነብያዊ ትንቢት በገሀዱ ዓለም ተፈፃሚ ሆነ፦

☜ عن مُعَاوِيَةَ بْنِ أَبِي سُفْيَانَ، قال: إِنَّ رَسُولَ اللهِ –صَلَّى اللهُ عَلَيْهِ وَسَلَّمَ– قَالَ: « إِنَّ أَهْلَ الْكِتَابَيْنِ افْتَرَقُوا فِي دِينِهِمْ عَلَى ثِنْتَيْنِ وَسَبْعِينَ مِلَّةً، وَإِنَّ هَذِهِ الْأُمَّةَ سَتَفْتَرِقُ عَلَى ثَلَاثٍ وَسَبْعِينَ مِلَّةً - يَعْنِي: الْأَهْوَاءَ-، كُلُّهَا فِي النَّارِ إِلَّا وَاحِدَةً، وَهِيَ الْجَمَاعَةُ، وَإِنَّهُ سَيَخْرُجُ فِي أُمَّتِي أَقْوَامٌ تَجَارَى بِهِمْ تِلْكَ الْأَهْوَاءُ كَمَا يَتَجَارَى الْكَلَبُ بِصَاحِبِهِ، لَا يَبْقَى مِنْهُ عِرْقٌ وَلَا مَفْصِلٌ إِلَّا دَخَلَهُ »

(1) “ዒልሙ’ል-ከላም” ስለፈጣሪ መኖርና መሰል እምነታዊ ጉዳዮች ሀይማኖታዊ ባልሆነ መንገድ የሚያጠና የተምታታ ፍልስፍናዊ አካሄድ ነው፤ ይህ መንገድ የተለያዩ አንጃዎች በአላህ ባህሪያት ዙሪያ እንዴት ትክክለኛውን እምነት እንዲቀይሩ እንዳደረጋቸው በምዕራፍ ሁለት ላይ ተብራርቷል።

➥ ከሙዓዊየህ ኢብኑ አቢ-ሱፍያን እንደተዘገበው የአላህ መልዕክተኛ (ﷺ) እንዲህ አሉ፡-

«የሁለቱ መፃህፍት ባለቤቶች በሀይማኖታቸው ወደ ሰባ ሁለት መንገዶች ተከፋፈሉ፤ ይሄኛውም ህዝበ-ሙስሊም ወደ ሰባ ሶስት መንገዶች ይከፋፈላል፤ ከአንዷ በስተቀር ሁሉም ለእሳት የተገቡ ናቸው፤ እሷም "አል-ጀማዓ" ናት። ከኔ ኡመትም ውስጥ ልክ የዕብድ ውሻ በሽታ በታማሚው እንደሚሰርፀው ግሳዊ ዝንባሌያቸው በውስጣቸው የሚሰርፅ ሰዎች ይመጣሉ፤ (በሽታው) ሳይዘልቀው የሚተወው ስር ወይም መገጣጠሚያ የለም!»[1]

እነዚህ መጤ የቢድዓ ጭፍራዎችና ግለሰቦች ያኔ.. በቀድሞዎቹ የኢስላም ትውልዶች መካከል የሚገፉት ኑሮ ውግዘትና ባይተዋርነት የተሞላበት ነበር፤ ህዝበ-ሙስሊሙ ሰርጎ-ገብነታቸውን አውቆ በአብዛኞዎቹ ከተሞችና ግዛቶች ያገልላቸውና ይጠነቀቃቸው ነበር። ሆኖም ቀስ በቀስ የተለያዩ የቢድዓ ፈሊጦቻቸው በተለያዩ ተፅዕኖዎች አጋዥነነት እየተሰራጩ ሄዱ፤ ትውልድ በትውልድ በተተካ ቁጥር ውዥንብሮች አየሉ፤ ተባዙ፤ ብዙ ሰዎችም ተሸነገሉ..! አላህ ከፈተና ያውጣን!

---

(1) ሙስነዱ'ል-ኢማሚ አህመድ (16937)፣ ሱነኑ አቢ ዳዉድ (4597)፤ ይህ ሐዲሥ በጥቅሉ ከተለያዩ ሰሓቦች የተዘገበ ሲሆን በርካታ የሐዲሥ ሊቃውንት ትክክለኝነትቱን አፅድቀዋል፤ በመሠረቱ የሐዲሡ መልዕክት ከሌሎች ሐዲሦች የተለየበት እውነታ ቢኖር የአንጃዎቹ ብዛት በቁጥር መጠቀሱ እንጂ በጥቅሉ ህዝበ-ሙስሊሙ መከፋፈሉ በሌሎች መረጃዎች የተመላከተ ከመሆኑ ባሻገር በገሀዱ ዓለም የሚስተዋለው ነባራዊው ሁኔታም የሚያረጋገጠው ነው።

በርግጥ ህዝበ-ሙስሊሙ ከላይ ለተገለፀው ክፍፍል ቢበቃም የጥንቱን ቀና ጎዳና አጥብቀው በመከተል በእውነት ላይ የፀኑና የሚፀኑ ጭፍራዎች ሁሌም አልጠፉም፤ አይጠፉምም! ከቀድሞው ፋና ያፈነገጡት ወደ ቀጥተኛው መስመር እንዲመለሱ ዘወትር ይታገላሉ፤ የሀሰት አራማጆች ለሚያነሷቸው ውዥንብሮችና ማምታቻዎች ትክክለኛ ምላሾችን ይሰጣሉ፤ እውነተኛው ዲን እንዳይበረዝ አላህ የሰየማቸው የኢስላም ዘቦች ናቸው!

☜ عن معاوية قال: سَمِعْتُ رَسُولَ اللَّهِ —صلى الله عليه وسلم– يَقُولُ: « لاَ تَزَالُ طَائِفَةٌ مِنْ أُمَّتِي قَائِمَةً بِأَمْرِ اللَّهِ لاَ يَضُرُّهُمْ مَنْ خَذَلَهُمْ أَوْ خَالَفَهُمْ حَتَّى يَأْتِيَ أَمْرُ اللَّهِ وَهُمْ ظَاهِرُونَ عَلَى النَّاسِ ».

➥ ከሙዓዊያ በተላለፈው ዘገባ የአላህ መልዕክተኛ እንዲህ ሲሉ ሰማሁ ይላል፡-

«ከእኔ ኡመት የተወሰኑ ጭፍራዎች በአላህ ትዕዛዝ ላይ የፀኑ ከመሆን አይወገዱም፤ የከዳቸው ወይም የተፃረራቸው አይጎዳቸውም - ከሰዎች (ሁሉ) የበላይ ሆነው እንዳሉ የአላህ ውሳኔ እስኪመጣ ድረስ!»[1]

አላህ ከነርሱ ይበለን!

ooo

(1) አል-ቡኻሪ (7312)፤ ሙስሊም (1037)… ሀዲሡ ከተለያዩ ሰሓቢዮች በተለያዩ ገለፃዎች የተዘገበ ነው።

## ክፍል ሶስት

### ማን ይፍረደን?!

ማንኛውንም የእምነት ጉዳይ አስመልክቶ እያንዳንዱ ሙስሊም መነሻውን፣ መድረሻውንና መመለሻውን የቁርኣንና የሐዲሥ መረጃዎች ላይ ማድረግ እንዳለበት ሳይታለም የተፈታ ነው። ሊነሱ የሚችሉ ውዝግቦች ሁሉ በአላህና በመልዕክተኛው ቃል ዳኝነት ሊቋጩ ይገባል። በእንዲህ አይነት ጉዳዮች ላይ የሚነሱ ውዝግቦችን ሊፈታ የሚችለው ብቸኛው ፍርድ ከበላይ የሚመጣ አምላካዊ ብይን ብቻ ነውና! ሁሉም የራሱን አእምሯዊ ሚዛን ዳኛ አድርጎ ከሰየመ ግን የሰዎች አእምሮ እንደ መልካቸው ዥንጉርጉር ስለሆነ መስማማት ላይ አይደረስም!

አላህ በታላቁ ቁርኣን እንዲህ ይላል፡-

﴿فَإِن تَنَٰزَعۡتُمۡ فِي شَيۡءٖ فَرُدُّوهُ إِلَى ٱللَّهِ وَٱلرَّسُولِ إِن كُنتُمۡ تُؤۡمِنُونَ بِٱللَّهِ وَٱلۡيَوۡمِ ٱلۡأٓخِرِۚ ذَٰلِكَ خَيۡرٞ وَأَحۡسَنُ تَأۡوِيلًا﴾ [النساء: ٥٩]

➥ «በምንም ነገር ብትወዛገቡ በአላህና በመጨረሻው ቀን የምታምኑ ከሆናችሁ ወደ አላህና ወደ መልዕክተኛው መልሱት፤ ይህ የተሻለና መመለሻው (ውጤቱ) ይበልጥ መልካም የሆነ ነው።» [አን-ኒሳእ 59]

﴿فَلَا وَرَبِّكَ لَا يُؤۡمِنُونَ حَتَّىٰ يُحَكِّمُوكَ فِيمَا شَجَرَ بَيۡنَهُمۡ ثُمَّ لَا يَجِدُواْ فِيٓ أَنفُسِهِمۡ حَرَجٗا مِّمَّا قَضَيۡتَ وَيُسَلِّمُواْ تَسۡلِيمٗا﴾ [النساء: ٦٥]

➥«በጌታህም እምላለሁ! በመካከላቸው በተከራከሩበት ጉዳይ እስከሚያስፈርዱህ ከዚያም በፈረድከው (ብይን) በነፍሶቻቸው ውስጥ ጥበትን (ቅሬታን) እስከማያገኙና ፍፁም እጅ እስኪሰጡም ድረስ አያምኑም ::» [አን-ኒሳእ 65]

አዎን! የአላህና የመልዕክተኛውን መመሪያ በምንም አይነት ፈሊጥና ፍልስፍና መጋፈጥ የኢማን ፀር ነው።

እንደዚሁም እነዚህን ቁርአናዊና ነብያዊ መልዕክቶችን አላህና መልዕክተኛው (ﷺ) በፈለጉት መልኩ ለመገንዘብ ስለቀናነታቸው በዘልዓለማዊ ቃል የተመሰከረላቸው ሰሓቦችን ፋና መከተል የግድ ነው፤ የነርሱ ስብዕና የታነፀው ከታላቁ መልዕክተኛ ያለአማካይ በቀሰሙት መለኮታዊ ትምህርት ነውና።

📖 قَالَ تَعَالَى: ﴿وَٱلسَّٰبِقُونَ ٱلْأَوَّلُونَ مِنَ ٱلْمُهَٰجِرِينَ وَٱلْأَنصَارِ وَٱلَّذِينَ ٱتَّبَعُوهُم بِإِحْسَٰنٍ رَّضِىَ ٱللَّهُ عَنْهُمْ وَرَضُوا۟ عَنْهُ وَأَعَدَّ لَهُمْ جَنَّٰتٍ تَجْرِى تَحْتَهَا ٱلْأَنْهَٰرُ خَٰلِدِينَ فِيهَآ أَبَدًا ذَٰلِكَ ٱلْفَوْزُ ٱلْعَظِيمُ﴾ [التوبة: ١٠٠]

➥ «ከሙሐጂሮችና ከአንሳሮች የመጀመሪያዎቹ ቀዳሚዎች እነዚያም በበጎ ሥራ የተከተሏቸው አላህ ከነርሱ ወዷል ፤ ከርሱም ወደዋል፤ ከስሮቿ ወንዞች የሚፈሱ የሆኑትን ጀነትም ለነርሱ በውስጧ ዘልዓለም የሚዘወትሩ ሆነው አዘጋጅላቸው፤ ይህም ታላቁ እድል ነው::»[አት-ተውባህ 100]

እንዲሁም ዐብዱላህ ኢብኑ መስዑድና ሌሎች ሰሓቦች በሚያስተላልፉት ዘገባ የአላህ መልዕክተኛ (ﷺ) እንዲህ ብለዋል፡-

☜ «خَيْرُ النَّاسِ قَرْنِي، ثُمَّ الَّذِينَ يَلُونَهُمْ، ثُمَّ الَّذِينَ يَلُونَهُمْ،..»

➥ «ከሰዎች (ሁሉ) በላጩ የእኔ ትውልድ ነው፤ ከዚያም የነርሱ ቀጣዮች፤ ከዚያም የነርሱ ቀጣዮች፤..»[1]

---

✸ ታዲያ ስለጌታችን ማንነት ለመረዳት መለኮታዊ ምንጮቻችን (ቁርኣንና ሀዲሥ) ይበቁናል? ወይስ ሰው-ሰራሽ ጥናቶችና ፈሊጦች ያስፈልጉናል?!

↳ አላህ የዘረጋልን የአምልኮ ጎዳና ሁለንተናዊ በመሆኑ በሁሉም መስኮች ላይ ስለሚያስፈልጉን ጉዳዮች በቀጥታም ይሁን በተዘዋዋሪ በቂ ገለፃዎችን እንዳደረገልን ይታወቃል።

📖 قَالَ تَعَالَى: ﴿وَنَزَّلْنَا عَلَيْكَ ٱلْكِتَـٰبَ تِبْيَـٰنًا لِّكُلِّ شَىْءٍ وَهُدًى وَرَحْمَةً وَبُشْرَىٰ لِلْمُسْلِمِينَ﴾ [النحل: ٨٩]

(1) አል-ቡኻሪ (3651)፣ ሙስሊም (2533) እና በሌሎችም ቦታዎች ተዘግቧል።

➥ «መፅሀፉንም ለሁሉ ነገር ማብራሪያ፣ እንዲሁም ለሙስሊሞች መመሪያ፣ እዝነትና ብስራት እንዲሆን በአንተ ላይ አወረድን፡፡» [አን-ነሕል 89]

📖 قَالَتَعَالَى: ﴿ٱلۡيَوۡمَ أَكۡمَلۡتُ لَكُمۡ دِينَكُمۡ وَأَتۡمَمۡتُ عَلَيۡكُمۡ نِعۡمَتِي وَرَضِيتُ لَكُمُ ٱلۡإِسۡلَٰمَ دِينٗا﴾ [المائدة: ٣]

➥ «ዛሬ ሀይማኖታችሁን ሞላሁላችሁ፤ ፀጋዬንም በናንተ ላይ ፈፀምኩ፤ ከሀይማኖትም ኢስላምን ወደድኩላችሁ» [አል-ማኢዳህ 3]

☜ عن عَبْدِ اللَّهِ بْنُ عَمْرِو بْنِ الْعَاصِ، عن النَّبِي –صلى الله عليه وسلم– أنه قال: «إِنَّهُ لَمْ يَكُنْ نَبِيٌّ قَبْلِي إِلاَّ كَانَ حَقًّا عَلَيْهِ أَنْ يَدُلَّ أُمَّتَهُ عَلَى خَيْرِ مَا يَعْلَمُهُ لَهُمْ، وَيُنْذِرَهُمْ شَرَّ مَا يَعْلَمُهُ لَهُمْ...»

➥ *ዐብዱላህ ኢብኑ ዐምር (رضي الله عنه) እንዳስተላለፉት የአላህ ነብይ (ﷺ) እንዲህ አሉ፡-*

«እነሆ! ከኔ በፊት ነብይ ኖሮ ለህዝቦቹ የሚያውቅላቸውን መልካም ነገር እንዲያመላክታቸውና የሚያውቅላቸውንም መጥፎ ነገር እንዲያስጠነቅቃቸው ግዴታ ያልሆነበት የለም፡፡»(1)

- እንዲሁም እንደሚከተለው አሉ፡-

(1) ሙስሊም (1844)

☜ «قَدْ تَرَكْتُكُمْ عَلَى الْبَيْضَاءِ، لَيْلُهَا كَنَهَارِهَا، لَا يَزِيغُ عَنْهَا بَعْدِي إِلَّا هَالِكٌ..»

**➥ «ሌሊቱ እንደ ቀን በሆነ ፍንትው ባለ (ግልፅ ጎዳና) ላይ በርግጥ ትቻችኋለሁ፣ ከጠፊ በስተቀር ከእኔ በኋላ ከርሱ የሚያፈነግጥ የለም!...»**[1]

☜ عن عبْدِ الرَّحْمَنِ بْنِ يَزِيدَ عَنْ **سَلْمَانَ [الفارسي]** قَالَ: قِيلَ لَهُ: قَدْ عَلَّمَكُمْ نَبِيُّكُمْ –صلى الله عليه وسلم– كُلَّ شَيْءٍ حَتَّى الْخِرَاءَةَ؟ قَالَ: فَقَالَ: أَجَلْ! لَقَدْ نَهَانَا أَنْ نَسْتَقْبِلَ الْقِبْلَةَ لِغَائِطٍ أَوْ بَوْلٍ، أَوْ أَنْ نَسْتَنْجِىَ بِالْيَمِينِ، أَوْ أَنْ نَسْتَنْجِىَ بِأَقَلَّ مِنْ ثَلاَثَةِ أَحْجَارٍ، أَوْ أَنْ نَسْتَنْجِىَ بِرَجِيعٍ أَوْ بِعَظْمٍ.

**➥ *ዐብዱ'ር-ረሕማን ኢብኑ የዚድ እንዳስተላለፉት ታላቁ ሰሓቢ ሰልማን አል-ፋሪሲ እንዲህ ተብለው ተጠየቁ፡- «ነብያችሁ ሁሉንም ነገር አስተማራችሁ፣ መፀዳዳትንም ጭምር?!»***

**እሳቸውም፡- *«እንዴታ! በሰገራና በሽንት ጊዜ ወደ ቂብላ እንዳንቀጣጭ፣ ወይም በቀኝ እጃችን እንዳንፀዳዳ፣ ወይም ከሶስት ባነሰ ድንጋይ እንዳንፀዳዳ፣ አሊያም በፋንድያ ወይም በአጥንት እንዳንፀዳዳ በርግጥ ከልክለውናል።»* ብሉ::**[2]

---

(1) አሕመድ (17142) እና ሌሎች የዘገቡት ትክክለኛ ሐዲሥ ነው።
(2) ሙስሊም (262)

➢ *አል-ሙዘኒይ (264 ዓ.ሂ)* ከአል-ኢማም አሽ-ሻፊዒ (204 ዓ.ሂ) አጣቅሰው እንዳስተላለፉት *አል-ኢማም ማሊክ (179 ዓ.ሂ)* በተውሂድ ላይ ስለሚነሳ «ከላም» ተጠይቀው እንዲህ አሉ፡-

«محال أن يُظَنَّ بالنَّبي –صلى الله عليه وسلم– أنه علَّم أمَّته الاستنجاءَ، ولم يُعَلِّمْهُم التوحيد..! »

*«መልዕክተኛው ሕዝባቸውን ስለ መፀዳዳት ስርዓት አስተምረው ስለ 'ተውሒድ' አላስተማሩም ብሎ መገመት ዘበት ነው!..»*[1]

**ታዲያ..**

- እነዚህንና ከነዚህም የጠለቁ ዝርዝር ርዕሰ-ጉዳዮችን በተብራሩ መመሪያዎች ያካለለው የጌታችን ቁርኣንና የመልዕክተኛው (ﷺ) አስተምህሮት ይህን ከሁሉ በላይ ክቡርና አንገብጋቢ የእምነት መሠረትና የሁሉም ነብያት ተልዕኮ መዞሪያ ዛቢያ ያልገለፀ ሊሆን ይችላልን?!

- *«ዲናችሁን ምላሁላችሁ..!»* እያለ "ባሮቹ ሊያመልኩት ስለሚገባው እውነተኛ አምላክ ማንነት ተገቢ አስተምህሮት አላስተላለፈም!" ተብሎ ይታመናልን ?!

(1)"ዘም-ሙ'ል-ከላም ወአህሊሂ" ሊ'ል-ሀረዊ (4/282-283) ቁጥር 1128፣ "አሓዲሥ ፊ ዘም-ሚ'ል-ከላሚ ወአህሊህ" ሊአቢ'ል-ፈድል አል-ሙቅሪእ ገፅ 92

- ሰዎች ስለፈጣሪያቸው ማንነትና መገለጫ በራሳቸው ቁንጽል ግንዛቤ ላይ ተመርኩዘው እንዲዘላብዱ ሊፈቅድስ ይችላል?! ልብ ያለው ልብ ይበል!

ooo

## የአእምሮ ድርሻ

አእምሮ ታላቅ ፀጋ ሲሆን በእምነት አጀንዳዎች ላይ ያለው ድርሻ እውነታን ማገናዘብና ለይቶ መምረጥ ነው! ስለሆነም በቁርኣንና በነብዩ (ﷺ) አስተምህሮት አእምሮን የሚቀሰቅሱ ብዙ ጥሪዎችንና የመረጃ አቀራረቦችን እናገኛለን።

ሆኖም ከሰዎች "አእምሮ" አድማስ ውጭ ስላለ የእምነት ጉዳይ በ"አእምሮ" ላይ ብቻ ተመስርቶ መዘላበድ "አእምሮ" ራሱ የሚፈቅደው እርምጃ አይደለም! ምክንያቱም አላህ ለፈጠረው ነገር ሁሉ ወሰን አበጅቷልና! አይን የሚያየው የተወሰነ ርቀት ድረስ ብቻ ነው፤ ቅርብ ነገሮችንም ለመመልከት የግድ ብርሃን ያስፈልገዋል! እንደዚሁ አእምሮ በግንዛቤው የሚያካልለው ርቀትም የተገደበ ነው፤ ለግንዛቤውም "ብርሃን" ያስፈልገዋል፤ አዎን! የ"ወሕይ" ብርሃን!

አላህ እንዲህ ይላል፡-

﴿وَكَذَٰلِكَ أَوۡحَيۡنَآ إِلَيۡكَ رُوحٗا مِّنۡ أَمۡرِنَاۚ مَا كُنتَ تَدۡرِي مَا ٱلۡكِتَٰبُ وَلَا ٱلۡإِيمَٰنُ وَلَٰكِن جَعَلۡنَٰهُ نُورٗا نَّهۡدِي بِهِۦ مَن نَّشَآءُ مِنۡ عِبَادِنَا﴾ [الشورى: ٥٢]

➥ «እንደዚሁም ወደ አንተ ከትዕዛዛችን (ህይወት የሚዘራ) "ሩሕ"ን (ቁርኣንን)ገልፀናል፤ መፅሃፉም እምነቱም ምን እንደሆነ (ቀድሚያ) የምታውቅ አልነበርክም! ግን ከባሮቻችን የምንሻውን የምንመራበት ብርሃን አደረግነው..»[አሽ-ሹራ 52]

➢ በአንዳንድ መዛግብት ላይ እንደተጠቀሰው በአንድ አጋጣሚ አንድ ሰው ልጁን ታላቁ ሰሓቢይ ***ዐብዱ'ላህ ኢብኑ ዐብ-ባስ*** (رَضِيَ اللهُ عَنْهُ) ዘንድ ይዞ ቀረበና እንዲህ አላቸው፦

*"ይህ ልጄ አእምሮውን ክርክር አናውጦታል፤ ልቡናውን ንትርክ ሰልቦታል፤ ያለ አቅም መፍጨርጨር ከጌታው ጋርዶታል!"*

- እርሳቸውም ለልጁ እንዲህ አሉት፦ *"የወንድሜ ልጅ ሆይ! እስቲ በአይንህ አርቀህ አማትር፤ ከማዶ የምታየው አካል ምንድነው?"*

- ልጁም፦ *"እገሌ ነው!"* አላቸው።

- እርሳቸውም ቀጥለው፦ *"ከርሱ ኋላ እንደ ሰመመን የሚታየው ብዥታ ምንድነው?"* አሉት።

- ልጁም፦ *"እኔ እንጃ!"* አለ።

- ያኔ ***ዐብዱ'ላህ ኢብኑ ዐብ-ባስ*** (رَضِيَ اللهُ عَنْهُ) እንዲህ አሉት፦

« يَا ابْنَ أَخِي! فَكَمَا جَعَلَ اللَّهُ لِإِبْصَارِ الْعُيُونِ حَدًّا مَحْدُودًا مِنْ دُونِهَا حِجَابًا مَسْتُورًا؛ فَكَذَلِكَ جَعَلَ لِإِبْصَارِ الْقُلُوبِ غَايَةً لَا يُجَاوِزُهَا، وَحُدُودًا لَا يَتَعَدَّاهَا!»

*“የወንድሜ ልጅ ሆይ! አላህ ለአይኖች እይታ የተገደበ ወሰንና ከበስተፊቱ የተሸፈነ ግርዶሽን እንዳደረገው ሁሉ ለልቦች እይታም የማይሻገሩትን ወሰንና የማይተላለፉትን ድንበሮች አድርጓል!”*

ልጁም በዚህ ጊዜ የተሰለበው ህሊናውን አላህ መለሰለት፤ ስለማይመለከተው ነገር መጠየቅና ስለማይጠቅመው ጉዳይ መመራመርን ተወ..![1]

●●●

## ምን ይጠበቅብናል?

ስለ አላህ መጠሪያዎችና መገለጫዎች ማወቅ ከላይ እንደተገለፀው ከሁሉ ይልቅ ክቡርና አስፈላጊ ዘርፍ ቢሆንም ከፈጣሪ ህልውና ጋር በቀጥታ የተዛመደ መለኮታዊ ጉዳይ መሆኑ እጅግ ከፍተኛ ጥንቃቄ የሚሻ ያደርገዋል። ስለሆነም በዚህ ላይ የሚሰጡ ትንታኔዎች ሙሉ በሙሉ በቁርኣንና በሐዲሥ ማስረጃዎች ላይ የተመረኮዙ መሆናቸው የሚሰጠው አፅዕኖት በሌሎች ርዕሶች ላይ ከሚሰጠው የበዛ ነው፤ የአላህ ስሞችና መገለጫዎች በሰዎች አስተያየትና አዕምሯዊ ምርምር የሚፀድቁና የሚሻሩ አይደሉምና!

(1) “አል-ኢባናህ” ሊብኒ በጥ-ጣህ (1/422) ላይ የተዘገበ ሲሆን የተላለፈበት ሰነድ ድክመት ቢኖርበትም ከሌሎች መረጃዎች ጋር የሚገጥም የጥበብ ንግግር በመሆኑ እንዳለ አስፍሬዋለሁ።

➢ ***አል-ኢማም አሕመድ*** (241 ዓ.ሂ) **እንዲህ ብለዋል፡-**

«..ولا يُوصف اللهُ – تعالى- بأكثرَ مما وَصف به نفسَه أو وصفه به رسولُه...ولا نتعدّى القرآنَ والحديث؛ فنقول كما قال، ونصفه كما وصف نفسه، ولا نتعدى ذلك..»

***«አላህ ራሱን ከገለፀበት ወይም መልዕክተኛው እርሱን ከገለፁበት ባለፈ አይገለፅም፤ ...ቁርኣንና ሀዲሥን አንተላለፍም፤ እርሱ እንዳለው እንላለን፤ እራሱን እንደገለፀው እንገልፀዋለን፤ ይህንንም አንተላለፍም..»***[1]

➢ ***አል-ኢማም አቡ ነስር አስ-ሲጅዚ*** (444 ዓ.ሂ) **እንዲህ ብለዋል፡-**

«قد **اتفقت الأئمة** على أن الصفات لا تؤخذ إلا توقيفا، وكذلك شرحها لا يجوز إلا بتوقيف.. »

***«የአላህ ባህሪያት ከ"ተውቂፍ" (ቀጥተኛ የቁርኣንና የሐዲሥ ማስረጃ) በስተቀር እንደማይወሰዱ የኢስላም መሪዎች***

(1) "አል-ኢባናህ" ሊ'ብኒ በጥ-ጠህ (3/326)፣ "ዘምሙ'ት-ተእዊል" ሊ'ብኒ ቁዳማህ፤ ገፅ 22

*ተስማምተዋል፤ እንዲሁም በ“ተውቂፍ” ካልሆነ እነሱን ማብራራትም አይፈቀድም..!»*[1]

(1) “ሪሳላህ ኢላ አህሊ ዘቢድ” ሊ’ስ-ሲጅዚ፤ ገፅ 139

# ምዕራፍ አንድ

- ሶስቱ መርሆዎችና ማብራሪያዎቻቸው
- አራቱ ጠንቆች
- የቀድሞት አበው መንገድ

## ሶስቱ መርሆዎች

ይህን እጅግ አሳሳቢ ጉዳይ አስመልክቶ አላህ በመለኮታዊ መፃህፍቱ ያወረደው፣ ነብያት ለተከታዮቻቸው ያወረሱት፣ ሰሓቦችና ተተኪ ትውልዶች በአደራ ያቆዩት ትክክለኛ የእምነት አቋም ምን ይመስላል? ይህ በማንኛውም ሐቅ ፈላጊ ሙስሊም አእምሮ ውስጥ ሊፀነስ የሚችል ጥያቄ ነው።

መልሱ ጠቅለል ባለ መልኩ በሚከተሉት ሶስት ዋና ዋና ነጥቦች ውስጥ ሊካተት ይችላል፡-

1- አላህ በቁርኣኑ ራሱን የገለፀባቸውን ወይም መልዕክተኛው (ﷺ) በተረጋገጡ ዘገባዎች ላይ ያፀደቋቸውን የጌታችንን ስሞችና ባህሪያት በሙሉ እንዳሉ ተቀብሎ ማፅደቅ፤

2- በቁርኣንና በሐዲሥ በቀጥታ ወይም በተዘዋዋሪ ውድቅ የተደረጉ ጉድለቶችን ሁሉ ውድቅ ማድረግ፤

3- በርዕሱ ላይ በቁርኣንና በሐዲሥ ያልተወሱ ቃላትንና ገለፃዎችን መልዕክታቸውን ሳያጣሩ አለመቀበል።

ooo

# ክፍል አንድ

## የመጀመሪያው መርሆ ማብራሪያ

አላህ በቁርኣኑ ራሱን የገለፀባቸውን ወይም መልዕክተኛው (ﷺ) በተረጋገጡ ዘገባዎች ላይ ያፀደቋቸውን የጌታችንን ስሞችና ባህሪያት በሙሉ እንዳሉ ተቀብሎ ማፅደቅ፤

### መነሻ

**ይህንን መርሆ በጥልቀት ለመረዳት በቅድሚያ የሚከተሉትን ሶስት መሠረታዊ ነጥቦች አብረን እናጢን፡-**

**1ኛ፡-** አላህ ስለራሱም ይሁን ስለሌሎች ከማንም ይበልጥ አዋቂና እውነተኛ በመሆኑ በቁርኣንም ይሁን በመልዕክተኛው አንደበት ለራሱ ያፀደቀውን ማንኛውንም እውነታ በክፍት ልቦና ተቀብሎ ማረጋገጥ የሁሉም ሙስሊም ግዴታ ነው። ለእርሱ ልቅና ተገቢ የሚሆኑትንና የማይሆኑትን መለኮታዊ ባህሪያት ከርሱ ከራሱና ከመልዕክተኞቹ ይበልጥ ለይቼ አውቃለሁ ብሎ ማን ይሞግታል?

📖 قَالَ تَعَالَىٰ: ﴿قُلْ ءَأَنتُمْ أَعْلَمُ أَمِ ٱللَّهُ﴾ [البقرة: ١٤٠]

➥ «"እናንተ ይበልጥ ታውቃላችሁ ወይስ አላህ?!" በል።» [አል-በቀራህ 140]

📖 قَالَ تَعَالَىٰ: ﴿وَمَنْ أَصْدَقُ مِنَ ٱللَّهِ حَدِيثًا﴾ [النساء: ٨٧]

➥ «በንግግር ከአላህ የበለጠ እውነተኛ ማን ነው?!» [አን-ኒሳእ 87]

📖 قَالَ تَعَالَى:﴿ وَمَنْ أَصْدَقُ مِنَ ٱللَّهِ قِيلًا ﴾[النساء: ١٢٢]

➥ «በንግግር ከአላህ የበለጠ እውነተኛ ማን ነው?!»[አን-ኒሳእ 122]

**2ኛ፡-** ጌታችን አላህ ቁርኣንን ያወረደው ለሰዎች መመሪያ እንዲሆን ነውና ግልፅና የማያሻማ ንግግር አድርጎታል፤ እንዲህም ብሏል፡-

📖 ﴿ إِنَّآ أَنزَلْنَٰهُ قُرْءَٰنًا عَرَبِيًّا لَّعَلَّكُمْ تَعْقِلُونَ ﴾[يوسف: ٢]

➥«እኛ እናንተ እንድታገናዝቡ ዐረብኛ ቁርኣን አድርገን አወረድነው»[ዩሱፍ 2]

📖 ﴿ كِتَٰبٌ فُصِّلَتْ ءَايَٰتُهُۥ قُرْءَانًا عَرَبِيًّا لِّقَوْمٍ يَعْلَمُونَ ﴾[فصلت: ٣]

➥ «ለሚያውቁ ሕዝቦች ዐረብኛ ቁርኣን ሆኖ አንቀጾቹ የተብራሩ መጽሐፍ ነው፡፡»[ፉስ-ሲለት 3]

📖 ﴿ وَإِنَّهُۥ لَتَنزِيلُ رَبِّ ٱلْعَٰلَمِينَ ﴿١٩٢﴾ نَزَلَ بِهِ ٱلرُّوحُ ٱلْأَمِينُ ﴿١٩٣﴾ عَلَىٰ قَلْبِكَ لِتَكُونَ مِنَ ٱلْمُنذِرِينَ ﴿١٩٤﴾ بِلِسَانٍ عَرَبِيٍّ مُّبِينٍ ﴿١٩٥﴾ ﴾[الشعراء: ١٩٢ – ١٩٥]

➥ «እሱም (ቁርኣን) ከአለማቱ ጌታ የተወረደ ነው፤ ታማኙ መንፈስ (ጂብሪል) አወረደው፤ ከአስጠንቃቂዎቹ እንድትሆን በልብህ ላይ (አወረደው)፤ በግልፅ የዐረብኛ ቋንቋ»[አሽ-ሹዐራእ 192-195]

📖 ﴿شَهۡرُ رَمَضَانَ ٱلَّذِيٓ أُنزِلَ فِيهِ ٱلۡقُرۡءَانُ هُدٗى لِّلنَّاسِ وَبَيِّنَٰتٖ مِّنَ ٱلۡهُدَىٰ وَٱلۡفُرۡقَانِۚ﴾[البقرة: ١٨٥]

➡ «ያ ለሰዎች ቅን መመሪያ፣ እንዲሁም በመመሪያነታቸውና (እውነትን ከውሸት) የሚለዩ በመሆናቸው ግልፅ የሆኑ ማስረጃዎችን ያዘለ ይሆን ዘንድ ቁርኣን የተወረደበት የረመዷን ወር ነው።»[አል-በቀራህ 185]

ከዚህም በተጨማሪ የቁርኣን መልዕክት ቁርኣን በወረደባቸው ነብይ (ﷺ) አስተምህሮት አማካይነት ተብራርቷል።

📖 قَالَ تَعَالَىٰ: ﴿وَمَآ أَنزَلۡنَا عَلَيۡكَ ٱلۡكِتَٰبَ إِلَّا لِتُبَيِّنَ لَهُمُ ٱلَّذِي ٱخۡتَلَفُواْ فِيهِ وَهُدٗى وَرَحۡمَةٗ لِّقَوۡمٖ يُؤۡمِنُونَ﴾[النحل: ٦٤]

➡ «መፅሀፉንም እነርሱ የተለያዩበትን (ጉዳይ) እንድትገልጽላቸውና፣ ለሚያምኑ ህዝቦች ምሩቻና እዝነት እንዲሆን እንጂ (ለሌላ) ባንተ ላይ አላወረድነውም።»[አን-ነሕል 64]

↪ እንዲሁም ፈጣሪ የሚልካቸው ነብያት በሙሉ ግልፅ መልዕክትን ያስተላልፉ ዘንድ በህዝቦቻቸው ቋንቋ እንዲናገሩ አድርጓቸዋል። አላህ እንዲህ ብሏል፡-

📖 ﴿وَمَآ أَرۡسَلۡنَا مِن رَّسُولٍ إِلَّا بِلِسَانِ قَوۡمِهِۦ لِيُبَيِّنَ لَهُمۡۖ﴾[إبراهيم: ٤]

➥ «ማንንም መልዕክተኛ በህዝቦቹ ቋንቋ (የሚናገር አድርገን) እንጂ አልላክንም = ለነርሱ እንዲገልፅላቸው!»[ኢብራሂም 4]

«በህዝቦቹ ቋንቋ» የሚለው ሀረግ የነብያት ትምህርት ህዝቦቻቸው ከተላመዱት የቋንቋ ስርዓትና የገለፃ ሂደት ያፈነገጠ እንግዳ ዘይቤና እንቆቅልሽ እንደማይሆን በተጨማሪ ይጠቁማል።

ታዲያ ከዚህ የገለፃ ችሎታ ታላቁን ድርሻ የተጎናፀፉት የመልዕክተኞች መደምደሚያ የኛው ነብይ (ﷺ) መሆናቸው የታወቀ ነው።

**3ኛ፡-** ሩህሩሁና አዛኙ አላህ እኛን ወደ ቀጥተኛው መንገድ ሊመራን እንጂ ሊያጠመን አይወድም፤ እውነትን ሊገልፅልን እንጂ ሊያዳፍንብን አይሻም፤

📖 قَالَ تَعَالَى: ﴿ يُرِيدُ ٱللَّهُ لِيُبَيِّنَ لَكُمْ وَيَهْدِيَكُمْ سُنَنَ ٱلَّذِينَ مِن قَبْلِكُمْ وَيَتُوبَ عَلَيْكُمْ ۗ وَٱللَّهُ عَلِيمٌ حَكِيمٌ ﴾ [النساء: ٢٦]

➥ «አላህ ለናንተ ሊገልፅላችሁ፣ ከበፊታችሁ የነበሩትንም (ቀና ህዝቦች) ፋና ሊመሩችሁና ይቅር ሊላችሁ ይፈልጋል፤ አላህም አዋቂውና ጥበበኛው ነው፡፡»[አን-ኒሳእ 26]

⮎ እንዲሁም ነብያችን ለህዝባቸው መድህንና ቅናቻ እጅግ የሚጓጉና የሚቆረቆሩ መሆናቸው ይታወቃል፡-

📖 ﴿لَقَدۡ جَآءَكُمۡ رَسُولٞ مِّنۡ أَنفُسِكُمۡ عَزِيزٌ عَلَيۡهِ مَا عَنِتُّمۡ حَرِيصٌ عَلَيۡكُم بِٱلۡمُؤۡمِنِينَ رَءُوفٞ رَّحِيمٞ﴾ [التوبة: ١٢٨]

➡ «ከራሳችሁ የሆነ፣ ችግራችሁ ፅኑ የሚሆንበት፣ በእናንተ (መድህን) ላይ የሚጓጓ፣ ለአማኞችም በጣም ሩህሩህና አዛኝ የሆነ መልዕክተኛ በርግጥ መጥቶላችኋል!»[አት-ተውባህ 128]

**መድረሻ**

⤷ የሶስቱ ነጥቦች ማጠቃለያ = አላህ ስለራሱና ስለሌሎች ከሁሉ በላይ የሚያውቅ ከመሆኑ ባሻገር ንግግሩ ባሮቹ ተገንዝበውት እንዲመሩበት የወረደ በመሆኑ በዚህም ይሁን በሌሎች ጉዳዮች ላይ ከሁሉ በላይ እውነትን ገልፆ በማብራራት ወደ ቅን ጎዳና የሚመራ ቃል ነው።

📖 قَالَ تَعَالَىٰ: ﴿وَٱللَّهُ يَقُولُ ٱلۡحَقَّ وَهُوَ يَهۡدِي ٱلسَّبِيلَ﴾ [الأحزاب: ٤]

➡ «አላህም እውነታውን ይናገራል፤ እርሱም (ትክክለኛውን) መንገድ ይመራል፡፡»[አል-አሕዛብ 4]

📖 ﴿إِنَّ هَٰذَا ٱلۡقُرۡءَانَ يَهۡدِي لِلَّتِي هِيَ أَقۡوَمُ﴾ [الإسراء: ٩]

➡ «ይህ ቁርኣን ይበልጥ ወደ ተቃናችዋ (መንገድ) ይመራል»[አል-ኢስራእ 9]

እንዲሁም የአላህ መልዕተኛ (ﷺ) **ከማንኛውም ሰው የበለጠ** ስለጌታቸው ማንነት የሚያውቁና ቁርኣንን በንግግራቸውና በተግባራቸው አብራርተው የሚገልፁ፣ እንዲሁም ለህዝበ-ሙስሊሙ የሚቆረቆሩ ቅን ነበሩ።

**↳ ይህ ከመሆኑ ጋር** ኢስላምን ለመማር አዋቂውም አላዋቂውም፣ ከተሜውም አገሬውም፣ ትልቁም ትንሹም ሁሉም ከተለያየ የግንዛቤ ደረጃቸው ጋር ወደርሳቸው ሲመጡ አንዱን ከሌላው ሳይለዩ የአላህን ባህሪያት ያዘሉትን ቁርኣናዊ አንቀፆችና ነብያዊ አስተምህሮቶች ያለ "ማስጠንቀቂያ" በገሀድ ያስተላልፉ ነበር። ግልፅ መልዕክቶቻቸው የተፈለጉ ባይሆን ኖሮ የግድ የ"ተእዊል"[1] ማብራሪያዎችን በማከል ተከታዮቻቸውን ከውዥንብር ያድኑ ነበር!
→ እናስ? እናማ እነዚህ ቁርኣናዊ አንቀፆችና ነብያዊ አስተምህሮቶች በንፁህ ልቦና ለተገነዘባቸው አማኝ ግልፅ ያለና የማያሻማ መልዕክት ያዘሉ ናቸዋ!

ይህንን ድምዳሜ መፃረር ከላይ ያየናቸውን መንደርደሪያ ነጥቦች መፃረርና የአላህንና የመልዕክተኛውን አስተምህሮት በተዘዋዋሪ ማጣጣል ይሆናል! ምክንያቱም፡-

✷ እንደሚታውቀው የአንድ ተናጋሪ ንግግር በተወሰኑ ርዕሶች ላይ ሁል ጊዜ አሻሚና የተድበሰበሰ የሚሆነው፡-

(1) ወይ ስለ ጉዳዩ ካለው እውቀት ማነስ ነው፤

(1) የ"ተእዊል" ትክክለኛ ምንነት ወደፊት ተብራርቷል።

(2) ወይ ደግሞ ካለው የአገላለፅ ችሎታ ማነስ ነው፤

(3) አሊያም እውነታውን የመግለፅ ፍላጎት (ቅንነት) ካለመኖር ነው!

ከእነኚህ ሶስት እንከኖች አንዱም በአላህና በመልዕክተኛው ንግግር ወስጥ ፍፁም ሊኖር እንደማይችል ደግሞ የማይታበል እውነታ ነው። ከላይ ያየናቸው ሶስት ነጥቦችም ይህንኑ የሚያረጋግጡ ናቸው።

**መቋጫ**

⮎ ከነዚህ መሠረቶች ተነስተን የምንደርስበት መቋጫ = የሩህሩሁ ፈጣሪያችን ንግግር፡ እንኳን በእንዲህ ያለ መሠረታዊና ከባድ አጀንዳ ላይ ቀርቶ በሌሎችም ርዕሰ-ጉዳዮች ላይ ከተድበሰበሰ ትዕዛዝም ሆነ ዜና የጠራና የላቀ መሆኑን ነው። በግልፅ ከሚስተዋለው መልዕክት ጋራ የሚፃረሩ ድብቅ ጥቆማዎችንም አያስተላልፍም። ለሰው ዘር መመሪያነት ያወረደው ቃሉም በእንቆቅልሽ የተሞላ የትንግርት መፅሀፍ አይደለም፤ ሰምና ወርቁ የሚያደናግር የቅኔ ፈተናም የለበትም፤ አል-ሐምዱ ሊላህ!

⮎ **ስለዚህም** የተለያዩ የአላህ ስሞችና ባህሪያት የተወሱባቸው የቁርኣንና የሱን-ናህ ማስረጃዎች በዐረብኛው ቋንቋዊ ስልትና አገባብ መሠረት ግልፅ መልዕክቶችን ያዘሉ ስለሆኑ ቃላቱንም መልዕክታቸውንም ምንም ሳይጨምሩና ሳይቀንሱ በቀጥታ ተቀብሎ በእምነት ማስተናገድ የግድ ነው።

➢ *አል-ኢማም ኢብኑ ቁተይባህ (276 ዓ.ሂ) እንዲህ ብለዋል፡-*

«الواجب علينا أن ننتهي في صفات الله حيث انتهى في صفته أو حيث انتهى رسوله -صلى الله عليه وسلم-، **ولا نزيل اللفظ عما تعرفه العرب وتضعه عليه،** ونمسك عما سوى ذلك.»

***«ግዴታችን በአላህ ባህሪያት ላይ እርሱ በገለፀው ወይም መልዕክተኛው በገለፁት ልክ መገደባችን ነው፤ ቃሉን ዐረቦች ከሚያውቁትና ከሚጠቀሙበት መልዕክት አናስወግደውም፤ ከዚያ ውጭ ስላለው ደግሞ እንቆጠባለን»***[1]

➤ ***አል-ኢማም አቡ ነስር አስ-ሲጅዚ (444 ዓ.ሂ)*** **እንዲህ ይላሉ:-**

«الواجب أن يُعلم أن الله تعالى إذا وصف نفسه بصفةٍ هي معقولةٌ عند العرب، والخطابُ ورد بها عليهم بما يتعارفون بينهم، ولم يبيّن سبحانه أنها بخلاف ما يعقلونه، ولا فسّرها النبيُّ- صلى الله عليه وسلم- بتفسيرٍ يخالف الظاهر= فهي على ما يعقلونه ويتعارفونه!»

***«አላህ ዐረቦች ዘንድ በሚታወቅ መገለጫ ራሱን ገልፆ፣ ንግግሩም እነሱ በተላመዱት ስልት መጥቶ፣ እነርሱ ከሚገነዘቡት በተለየ መልኩ መሆኑን ካልገለፀ፣ መልዕክተኛውም ከጉልህ መልዕክቱ***

(1) "አሊ'ኽቲላፍ ፊ'ል-ለፍዝ.." ሊ'ብኒ ቁተይባህ ገፅ 44

*በሚለይ መልኩ ካላብራሩት = እነርሱ (ዐረቦች) በሚገነዘቡትና በሚግባቡበት (ትርጓሜ) ላይ መሆኑን ማወቅ የግድ ነው።»*[1]

*አዎን! ነገሩ ግልፅ ነው!*

**ስለሆነም** በቁርአንና በነብዩ (ﷺ) አንደበት በፀደቁት በሁሉም የአላህ ስሞችና ባህሪያት ያለምንም ማመንታት ማመን የግድ ነው። በአገላለፅ ደረጃም በተቻለ አቅም በማስረጃዎቹ ላይ የተጠቀሱበትን ሂደትና አገባብ መከተል ያስፈልጋል።

*በዚህም መሠረት የአላህ መጠሪያ ሆነው የተወሱት ስሞቹን በስምነታቸው እናፀድቃለን! እርሱም እንዳዘዘን በነርሱ እንጠራዋለን፤ እንለምነዋለን! በውስጣቸው ያዘሉትንም መገለጫ ባህሪያት ተቀብለን እናረጋግጣለን!*

قَالَ تَعَالَى: ﴿وَلِلَّهِ ٱلْأَسْمَآءُ ٱلْحُسْنَىٰ فَٱدْعُوهُ بِهَا ۖ وَذَرُوا۟ ٱلَّذِينَ يُلْحِدُونَ فِىٓ أَسْمَـٰٓئِهِۦ ۚ سَيُجْزَوْنَ مَا كَانُوا۟ يَعْمَلُونَ﴾ [الأعراف: ١٨٠]

«ለአላህም ከሁሉ የተሻሉ መልካም ስሞች አሉት፤ በነሱም ጥሩት፤ እነዚያ ስሞቹን የሚያጣምሙትንም ተዉዋቸው፤ ይሰሩት የነበሩትን (ዋጋ) ይመነዳሉ::» [አል-አዕራፍ 180]

(1) "ሪሳላህ ኢላ አህሊ ዘቢድ" ሊ'ስ-ሲጅዚ ገፅ 183

**ለምሳሌ፡-** ٱلرَّحْمَٰنُ (አር-ረሕማን) (በጣም ሩህሩሁ/ አዛኙ) የሚለውን ስሙን በተመለከተ፡-

- ከአላህ መጠሪያ ስሞች አንዱ መሆኑን እናምናለን፤

- በውስጡ ያዘለውን መልዕክትም ለልቅናው በሚገባ መልኩ በማፅደቅ አላህ የእዝነት (رحمة) ባለቤት መሆኑን አያይዘን እናፀናለን!

- በዚህ ባህሪውም የተነሳ ለባሮቹ እንደሚያዝን ከወዲሁ አረጋግጠን፡- *"አር-ረሕማን ሆይ! እዘንልን.."* እያልን እንማፀነዋለን።

- ይህን ስሙን ወይም ስሙ ያዘለውን ባህሪውን መልዕክት ከማዛባት እንቆጠባለን፤ አንዳንድ የፍልስፍና ሰለባዎች እንደሚሉት፡- *«መራራት ለጌታነቱ ስለማይገባ ትርጓሜውን፡- "ፀጋውን ለመስጠት መፈለግ.." እንለዋለን..!»* በማለት የምሉዕነት *መገለጫውን* አናጓድልም!

**እንደዚሁም** ሌሎች ባህሪያቱንም በተጠቀሱበት መልኩ አረጋግጠን እናልፋለን። ሆኖም ባህሪያቱ ለአላህ መጠሪያ ስም ሆነው የተወሱበትን አገባብ ካላገኘን በስተቀር ቃላቱን ወደ ስያሜ በመቀየር አዳዲስ ስሞች አናበጅም!

**ለምሳሌ፡-** አላህ በፈለገው ሁኔታ እንደሚናገርና የፈለገውንም እንደሚያናግር ለመቁጠር በሚያዳግቱ ማስረጃዎች የተረጋገጠ ነው። ቁርኣንም የርሱ ቃል መሆኑ እሙን ነው! ታዲያ ይህንን ባህሪ

ለአላህ ያለ አምሳያ እናፀድቃለን እንጂ እንደ አንዳንድ ጭፍራዎች *“የአላህ ንግግር ቃልና ፊደል አይደለም፤ ..ወዘተርፈ..”* እያልን በእጅ አዙር ባህሪውን አናስተባብልም!

በሌላም በኩል ይህንን ባህሪ ወደ መጠሪያ ስም በማሳደግ *“አል-ሙተከል-ሊም” (ተናጋሪው)፣* ወይም *“አል-ሙከል-ሊም” (አናጋሪው)* የሚል ስም አናወጣለትም።

ooo

## አራቱ ጠንቆች!

የነብያት ተከታዮች እነዚህን ባህሪያት ለፈጣሪ ታላቅነትና ልቅና በሚገባ መልኩ የሚያረጋግጡ ሲሆኑ በዚህ እምነታቸው ላይ አጥብቀው የሚጠነቀቋቸው **አራት አፍራሽ ጠንቆች** አሉ፤ እነርሱም፡-

1- የባህሪያቱን ሁኔታ ወይም ውስጣዊ ይዘት መገመት (تَكْيِيف)

2- ከፍጡራኑ ጋር ማመሳሰል (تَمْثِيل)

3- ባህሪያቱ የተጠቀሱባቸውን መረጃዎች ጉልህ መልዕክት ባለመቀበል ትርጉም ማሳጣት (تَعْطِيل)

4- ባህሪያቱ የተጠቀሱባቸውን መረጃዎች ቃላት ወይም ትክክለኛ ትርጉም አዛብቶ መቀየር (تَحْرِيف)

✷ ከነዚህ ጠንቆች አንዱንም መፈፀም በቀጥታም ይሁን በተዘዋዋሪ ለሚከተለው አምላካዊ ዛቻ የሚዳርግ ነው፡-

📖 قَالَ تَعَالَى: ﴿وَذَرُوا۟ ٱلَّذِينَ يُلْحِدُونَ فِىٓ أَسْمَـٰٓئِهِۦ ۚ سَيُجْزَوْنَ مَا كَانُوا۟ يَعْمَلُونَ﴾ [الأعراف: ١٨٠]

➥ «እነዚያ ስሞቹን የሚያጣምሙትንም ተዉዋቸው፤ ይሰሩት የነበረውን (ዋጋ) ይመነዳሉ፡፡»[አል-አዕራፍ 180]

**ማብራሪያ**

**እነዚህ አራት ጠንቆችን መጠንቀቅ የግድ የሚሆንበት ምክንያት በአጭሩ እንደሚከተለው ይብራራል፡-**

**1ኛው ጠንቅ** ***የባህሪያቱን ሁኔታ ወይም ውስጣዊ ይዘት መገመት***

**የአንድን ነገር ሁኔታና ይዘት ማወቅ የሚቻልባቸው አማራጮች ሶስት ብቻ ናቸው፡-**

**- እርሱን ማየት፣**

**- አምሳያውን ማየት፣**

**- ምንነቱን በተመለከተ እውነተኛ የሆነ ገለጻ ማግኘት።**

**↳ አላህ ግን በዚህኛው ህይወት ለማንም አይታይም፣ በወዲያኛው ዓለም አማኞች ሲያዩትም በእይታ አያካልሉትም፤ አምሳያም ፍፁም የለውም፤ ስለዚህ ስለርሱ ማወቅ የምንችልበት ብቸኛ መንገድ ሶስተኛው ነው፤ እውነተኛ ገለፃ! ይህ ገለፃ ደግሞ ከአላህ ከራሱና ከመልዕክተኛው (ﷺ) ንግግር ውጭ ሊሆን እንደማይችል አውቀናል፤**

**↳ ታዲያ ስለባህሪያቱ ሁኔታና ዝርዝር ይዘት በቁርኣንም ይሁን በሐዲሥ አልተነገረንም፤ የባህሪያቱ ምጥቀትም በሰዎች ግምት የሚለካ ስላልሆነ ዝርዝር ይዘታቸውን አስመልክቶ የሚነገር ወሬ ሁሉ ያለ እውቀት የሚሰነዘር መላምት ነው! ይህ ደግሞ በጣም የተወገዘ የእምነት ፀር ነው! ስለዚህ የእኛ ድርሻ የተነገረንን**

ተቀብለን ቃሉንም ጥቅል መልዕክቱንም ማፅደቅ እንጂ ስላልተነገረን የ«ገይብ»(1) ጉዳይ በውስን እእምሮዓችን መገመት አይደለም፤ አላህ እንዲህ ይላል፦

📖﴿وَلَا يُحِيطُونَ بِهِۦ عِلۡمٗا﴾[طه: ١١٠]

➥ «በእውቀት እርሱን አያካብቡትም»[ጧሃ 110]

አዎን! ፍጡራን ስለፈጣሪ የሚያውቁት ነገር ቢኖርም ሙሉ ማንነቱን በእውቀታቸው ሊያዳርሱ አይቻላቸውም።

✸ ታዲያ ስለ ፈጣሪ ባህሪያት ሁኔታና ዝርዝር ይዘት መናገርና ማሰብ የተከለከለው አላህ በባህሪያቱ የራሱ ሁኔታ የሌለው ሆኖ አይደለም፤ ማንኛውም ነገር የራሱ ሁኔታ እንዳለው ግልፅ ነው፤ የፈጣሪ ሁኔታ ግን በሰው አእምሮ የሚደረስበት አይደለም። አላህ እንዴት እንዳልለ ከእርሱ በቀር የሚያውቅ የለም!

ሆኖም አላህ ለራሱ ያፀደቃቸውን ባህሪያት የተላበሰው ለታላቅነቱ በሚገባ ልዩ መልኩ መሆኑን ማመንና ሁሌም ማስታወስ ተገቢ ነው። ከዚህ አኳያ የባህሪያቱን ጥቅል መልዕክት ማረጋገጥ ሁኔታቸውን ከመግለፅ አይመደብም፤ ያ ሌላ ይሄ ሌላ! ያስተውሉ!

---

(1) «ገይብ» (غَيْب) የሚባለው ከህዋስ የራቀና በአእምሮ ምርምር ሊደረስበት የማይችል ጉዳይ ነው።

**ታሪካዊ ምሳሌ**

***አንድ ግለሰብ በአንድ አጋጣሚ ወደ አል-ኢማም ማሊክ (179 ዓ.ሂ) መጣና የሚከተለውን ቁርአናዊ አንቀፅ አንብቦ አንድ ጥያቄ አቀረበላቸው:-***

📖قَالَ تَعَالَىٰ:﴿ٱلرَّحۡمَٰنُ عَلَى ٱلۡعَرۡشِ ٱسۡتَوَىٰ ۝﴾[طه: ٥]

➥ «አር-ረሕማን በዐርሹ ላይ ሆነ።»[ጧሃ 5]

***"አላህ በዐርሹ ላይ የሆነው እንዴት ነው?" አላቸው!***

**ይህንን ሲሰሙ ፊታቸውን ደፉ፤ ላብም አጠመቃቸው፤ ከዚያም እንዲህ ብለው መለሱ:-**

«الِاسْتِوَاءُ غَيْرُ مَجْهُولٍ، وَالْكَيْفُ غَيْرُ مَعْقُولٍ، وَالْإِيمَانُ بِهِ وَاجِبٌ، وَالسُّؤَالُ عَنْهُ بِدْعَةٌ.»

➤ *«የአላህ ከዐርሽ በላይ መሆን ("ኢስቲዋእ") **የማይታወቅ አይደለም** (መልዕክቱ ግልጽ ነው)። 'እንዴት?' (የሚለው ጥያቄ መልስ) በአዕምሮ የሚደረስበት አይደለም፤ በዚህ (በተጠቀሰው ባህሪ) ማመንም ግዴታ ነው፤ ስለዚህ መጠየቅም (በዲን ዉስጥ የመጣ) ፈጠራ "ቢድዓ" ነው!» ከዚያም (ጠያቂውን):-*

*«የቢድዓህ ሰው (ሙብተዲዕ) ትመስለኛለህ!» ካሉት በኋላ*

*ከመስጂዱ እንዲወጣ ትዕዛዝ አስተላለፉ!*[1]

**☞ ይህን መሰል ጥያቄ ለርሳቸው መምህር *አል-ኢማም ረቢዓህ ኢብን አቢ ዐብዲ'ር-ረህማን* (136 ዓ.ሂ) ቀርቦላቸውም በተመሳሳይ መልኩ እንዲህ ብለው ነበር፦**

« الاِسْتِوَاءُ غَيْرُ مَجْهُولٍ، وَالْكَيْفُ غَيْرُ مَعْقُولٍ، وَمِنَ اللهِ الرِّسَالَةُ، وَعَلَى الرَّسُولِ الْبَلاَغُ، وَعَلَيْنَا التَّسْلِيمُ.»

➢ ***«የአላህ ከዐርሽ በላይ መሆን ("ኢስቲዋእ") የማይታወቅ አይደለም (መልዕክቱ ግልጽ ነው)። 'እንዴት?' (የሚለው ጥያቄ መልስ) በአዕምሮ የሚደረስበት አይደለም፤ መልዕክቱ ከአላህ ዘንድ***

---

(1) "አል-አስማኡ ወስ-ሲፋት" ሊ'ል-በይሀቂይ (2/150-151)፣ "አሊ'ዕቲቃድ" ሊ'ል-በይሀቂይ ገፅ 56፣ "አር-ረድ-ዱ ዐለ'ል-ጀህሚያህ" ሊ'ድ-ዳሪሚይ ገፅ 33፣ "አት-ተምሂድ" ሊ'ብኒ ዐብዲ'ል-በር (7/151)፣ "ሒልየቱ'ል-አውሊያእ" ሊአቢ ኑዐይም (6/325-326)፣ "ሸርሑ ኡሱሊ'ዕቲቃዲ አህሊ'ስ-ሱን-ነቲ ወል-ጀማዐህ" ሊ'ል-ላለካኢይ (2/398)፣..በሌሎችም በርካታ መዛግብት ሰፍሯል። ይህ በተለያዩ ሰነዶች የተረጋገጠ ዘገባ ሲሆን የተለያዩ ሊቃውንት ትክክለኛ ስለመሆኑ መስክረዋል፤ አንድም ታዋቂ ዓሊም በዚህ እውነታ ላይ የሚያጠራጥር ቃል አልተናገረም!

*ነው፤ በመልዕክተኛው ላይ ያለው (ሀላፊነት) ማድረስ ነው፤ በእኛ ላይ ያለው (ግዴታ) መቀበል ነው።»*[1]

**ይህ ከሁለቱ ድንቅ ኢማሞች የተሰጠው ድንቅ ምላሽ በየትኛቸውም የአላህ ባህሪያት ላይ ለሚነሳ የ"እንዴት?" ጥያቄ አጥጋቢ መልስ ያዘለ መርሆ ነው።**

---

**2ኛው ጠንቅ** <u>ከፍጡራኑ ጋር ማመሳሰል</u>

**መቼም በፈጣሪና በፍጡር መካከል መመሳሰልና አንድነት ሊኖር እንደማይችል ማንኛውም ንፁህ አዕምሮ ያረጋግጣል።**

**ለዚህ ማስረጃነት ከሚጠቀሱት አንቀፆች መካከል:-**

﴿لَيۡسَ كَمِثۡلِهِۦ شَيۡءٞۖ وَهُوَ ٱلسَّمِيعُ ٱلۡبَصِيرُ﴾ [الشورى: ١١]

➥ «እንደርሱ ያለ (አምሳያ) ምንም የለም፤ እርሱም ሰሚውና ተመልካቹ ነው::»[አሽ-ሹራ 11]

﴿وَلَمۡ يَكُن لَّهُۥ كُفُوًا أَحَدُۢ﴾ [الإخلاص: ٤]

---

(1) "አል-አስማኡ ወስ-ሲፋት" ሊ'ል-በይሀቂይ (2/151)፤ "ሸርሑ ኡሱሊ'ዕቲቃዲ አህሊ'ስ-ሱን-ነቲ ወል-ጀማዐህ" ሊ'ል-ላለካኢይ (2/398)፤ "ታሪኹ'ሥ-ሢቃት" ሊል-ዒጅሊ ገፅ 158 ቁጥር 431፤ "አል-ዑሉዉ ሊል-ዐሊይ-ዩ'ል-ገፍ-ፋር" ሊ'ዝ-ዘሀቢይ ገፅ 98

➥ «ለእርሱም አንድም ብጤ የለውም፡፡»[አል-ኢኽላስ 4]

📖﴿هَلۡ تَعۡلَمُ لَهُۥ سَمِيّٗا﴾[مريم: ٦٥]

➥ «ለእርሱ በስሙ ወደር ታውቃለህን?»[መርየም 65]

➢ ታላቁ ሰሓቢይ *ኢብኑ ዓብ-ባስ* (رضي الله عنه) ይህን አንቀፅ ሲያብራሩ እንዲህ ይላሉ:

« هل تعلم للربّ مِثلًا أو شبيهًا ؟!»

*“ለጌታ አምሳያ ወይም ቢጤን ታውቃለህን?”*(1)

**ስለዚህ** የጌታ መጠሪያዎችና መገለጫዎች አንዳንዴ ከፍጡራን ስያሜዎችና ባህሪያት ጋር በቃላት ደረጃ ቢገጥሙ እንኳ በይዘት ግን ፍፁም አይመሳሰሉም፤ ጌታ በጌታነቱ ከፍጡራን መለያዎች የጠራና በስሞቹም ይሁን በባህሪያቱ ተጋሪ የሌለው ብቸኛ ነውና!

**ታዲያ** “ማመሳሰል” የሚባለው ባህሪያቱን ከፍጡራን ጋር በሁኔታ ማዛመድ እንጂ አላህና መልዕክተኛው ያፀደቁትን መቀበል እንዳልሆነ ሊታወቅ ይገባል(2)፤

(1) “ተፍሲሩ’ጥ-ጦበሪ” (18/226)
(2) ማብራሪያውን ክፍል ሁለት ላይ ይደርሱበታል፤ ኢን-ሻአ’ላህ!

➢ *አል-ኢማም **አት-ቲርሚዚይ** (279 ዓ.ሂ)* እንደሚያስተላልፉት **ታዋቂው** *አል-ኢማም* ***ኢስሓሃቅ ኢብኑ ራሀወይህ***[1] እንዲህ ብለዋል፦

«إِنَّمَا يَكُونُ التَّشْبِيهُ إِذَا قَالَ: يَدٌ كَيَدٍ أَوْ مِثْلُ يَدٍ، أَوْ سَمْعٌ كَسَمْعٍ أَوْ مِثْلُ سَمْعٍ. فَإِذَا قَالَ: سَمْعٌ كَسَمْعٍ أَوْ مِثْلُ سَمْعٍ فَهَذَا التَّشْبِيهُ، وَأَمَّا إِذَا قَالَ- كَمَا قَالَ اللَّهُ تَعَالَى-: يَدٌ، وَسَمْعٌ، وَبَصَرٌ، وَلاَ يَقُولُ: كَيْفَ، وَلاَ يَقُولُ: مِثْلُ سَمْعٍ وَلاَ كَسَمْعٍ، فَهَذَا لاَ يَكُونُ تَشْبِيهًا. »

*«ማመሳሰል የሚሆነው "እንዲህ ያልለ ወይም ይሄ አይነት እጅ"፣ "እንዲህ ያልለ ወይም ይሄ አይነት መስማት" ሲባል ነው፤...ነገር ግን አላህ እንደተናገረው "እጅ፣ መስማት፣ ማየት" ብሎ "እንዴት" ካላለ፣ "እንዲህ አይነት፣ እንዲያ ያለ መስማት.." ካላለ ማመሳሰል አይሆንም!»*[2]

**አዎን! የቁርኣን ገለፃን የተከተለን ሰው ማውገዝ በተዘዋዋሪ ቁርኣንን ራሱን ማውገዝ እንደሆነ ማስታወስ ያሻል!**

---

(1) *ኢስሓቅ ኢብኑ ኢብራሂም (ኢብኑ ራሀወይህ)* (161 – 238 ዓ.ሂ)፤ ታላቁ የሙስሊሞች ኢማም፤ በዘመናቸው የነበሩት *አል-ኢማም አህመድ* "በዱንያ ላይ ለኢስሓቅ ወደር አላውቅለትም!" ብለዋል።

(2) "ሱነኑ'ት-ቲርሚዚይ"፤ ኪታቡ'ዝ-ዘካህ፤ ከሐዲሥ ቁጥር (662) ቀጥሎ

**3ኛው ጠንቅ** <u>ባህሪያቱ የተጠቀሱባቸውን መረጃዎች ጉልህ መልዕክት ባለመቀበል ትርጉም ማሳጣት</u>

ከላይ እንደተመለከተው የአላህ ስሞችና ባህሪያት የተወሱባቸው የቁርአንና የሱን-ናህ ማስረጃዎች በዐረብኛው ቋንቋዊ ስልትና አገባብ መሠረት ግልፅ መልዕክቶችን ያዘሉ ስለሆኑ **ቃላቱንም መልዕክታቸውንም** በቀጥታ ተቀብሎ በእምነት ማስተናገድ የግድ ነው።

ከዚህ አንፃር አንዳንዶች እንደሚሉት *"የነዚህ አንቀጾችና ነብያዊ ንግግሮች መልዕክት አይታወቅም፣ ወይም አሻሚ ነው! ሰሓቦችና ተከታይ ትውልዶችም የእነኚህን አንቀፆች መልዕክት አያውቁም ነበር!"* ብሎ መሞገት ስህተት ብቻ ሳይሆን ትንግርትም ነው! **እንዲያው ለመሆኑ፡-**

- ከጌታችን ማንነት ጋር የተያያዘውን ይህን ታላቅና አንገብጋቢ ርዕስ ለሁሉም መስከ መመሪያ የሆነው ቁርአን ያለ በቂ ማብራሪያ አለባብሶ ያልፈዋልን?!

- ሩህሩሁ ፈጣሪያችን በእንዲህ ያለ መሠረታዊና ከባድ አጀንዳ ላይ መልዕክታቸው የማይታወቅ አሻሚ ቃላትን አውርዶ ባሮቹን ያምታታል ተብሎ ይታሰባልን?!

- ወይስ እነዚህ ግልፅ ቋንቋዊ ይዘትና አገባብ ያላቸው አንቀፆች በአንዳንድ ምዕራፎች መግቢያ ላይ እንዳሉት (እንደ ﴿الٓمٓ﴾፣ ﴿الٓر﴾፣ ﴿حمٓ﴾ እና የመሳሰሉት) ያልተለመዱ ተዓምራዊ የፊደል ክሽኖች ናቸው?!

- አላህ የቁርአንን መልዕክት የማይረዱ ሰዎችን በተለያዩ አንቀፆች ኮንኖ ሳለና ይህንንም ከከሃዲያን መገለጫዎች መካከል እየቆጠረው በዚህ ወሳኝ ጉዳይ ላይ ያሉ አንቀፆችን ትርጓሜ ማወቅ አይቻልም ማለት ግራ አያጋባምን?![1]

- የአላህ ባህሪያት የተወሱባቸው አንቀፆች እጅግ ብዙ ከመሆናቸው ጋር አላህ ቁርአንን ከፊሉን ከከፊሉ ሳይለይ ሁሉንም ለመገንዘብ መጣጣርና ማስተንተን እንዳለብን ከመንገሩ ባሻገር ቃሉን የማያስተውሉትን አላወገዘምን?![2]

---

(1) አላህ እንዲህ ብሏል፡-

﴿وَإِذَا قَرَأْتَ ٱلْقُرْءَانَ جَعَلْنَا بَيْنَكَ وَبَيْنَ ٱلَّذِينَ لَا يُؤْمِنُونَ بِٱلْأَخِرَةِ حِجَابًا مَّسْتُورًا ۝٤٥ وَجَعَلْنَا عَلَىٰ قُلُوبِهِمْ أَكِنَّةً أَن يَفْقَهُوهُ وَفِىٓ ءَاذَانِهِمْ وَقْرًا﴾ [الإسراء: ٤٥ – ٤٦]

➥ «ቁርኣንን ባነበብክም ጊዜ ባንተና በመጨረሻው ዓለም በማያምኑት መካከል የሚሸሽግ ግርዶሽ አድርገናል፤ እንዳይገነዘቡትም በልቦቻቸው ላይ ሽፋንን፣ በጆሮዎቻቸውም ላይ ድንቁርናን አደረግን»[አል-ኢስራእ 45-46]

እንዲሁም፡-

﴿فَمَالِ هَٰٓؤُلَآءِ ٱلْقَوْمِ لَا يَكَادُونَ يَفْقَهُونَ حَدِيثًا﴾ [النساء: ٧٨]

➥ «እነዚህ ህዝቦች ምን ሆነው ነው ንግግርን ሳስመረዳት የደረሱት?!»[አን-ኒሳእ 78]

(2) አላህ እንዲህ ብሏል፡-

﴿أَفَلَا يَتَدَبَّرُونَ ٱلْقُرْءَانَ أَمْ عَلَىٰ قُلُوبٍ أَقْفَالُهَآ﴾ [محمد: ٢٤]

➥ «ቁርኣንንም አያስተነትኑምን? በልቦቻቸው ላይ ቁልፎቿ አሉባትን?»[ሙሐመድ 24]

- ታላቁ መልዕክተኛና ባልደረቦቻቸው በዚህ ታላቅ ርእስ ላይ እንደ መሀይማን መልዕክታቸውን የማያውቋቸውን አንቀጾችን ያነበንቡ ነበር ተብሎስ ይገመታልን?!

- ነብያችን ካለባቸው እውነትን የማድረስ ሀላፊነትና ካላቸው ቅንነት አንፃር እንዴት አንድም ቀን *"የነዚህ አናቅፅ ትክክለኛ ትርጓሜ ስለማይታወቅ ግልፅ መልዕክታቸውን አትቀበሉ!"* ሳይሉ ቀሩ?!

- ሰሓቦችስ ከታላቁ መልዕክተኛ በተማሩት መሠረት ለተከታዩ ትውልድ ቁርኣንን በሙሉ ሲያብራሩ "የነዚህን አንቅፆች ትርጉም አናውቅም!" ለምን አላሉም?![1]

---

(1) ለአብነት ያህል፦

- عن ابن مسعود، قال: كانَ الرجل مِنَّا إذا تعلَّم عَشْر آياتٍ لم يجاوزهُنّ حتى يعرف معانيهُنَّ، والعملَ بهنَّ.

➢ ***ዐብዱላህ ኢብኑ መስዑድ*** እንዲህ አሉ፦ *«ከኛ መካከል አንዳችን አስር አንቅፆችን ሲማር መልዕክታቸውንና አተገባበራቸውን እስኪያውቅ ወደ ሌላ አያልፍም ነበር!»* [*"ተፍሲር ኢብኒ ጀሪር"* (1/80)]

- عَنْ أَبِي عَبْدِ الرَّحْمَنِ قَالَ: «حَدَّثَنَا مَنْ كَانَ يُقْرِئُنَا مِنْ أَصْحَابِ النَّبِيِّ - صَلَّى اللهُ عَلَيْهِ وَسَلَّمَ - أَنَّهُمْ كَانُوا يَقْتَرِئُونَ مِنْ رَسُولِ اللهِ- صَلَّى اللهُ عَلَيْهِ وَسَلَّمَ- عَشْرَ آيَاتٍ، فَلَا يَأْخُذُونَ فِي الْعَشْرِ الْأُخْرَى حَتَّى يَعْلَمُوا مَا فِي هَذِهِ مِنَ الْعِلْمِ وَالْعَمَلِ، قَالُوا: فَعَلِمْنَا الْعِلْمَ وَالْعَمَلَ.»

➢ ***አቡ ዐብዲ'ር-ረሕማን [አስ-ሱለሚይ]*** እንዲህ አሉ፦ *«ከነብዩ ሰሃቦች መካከል ቁርኣን ያስተምሩን የነበሩት ከመልዕክተኛው አስር አንቀፆችን ማንበብ እንደተማሩ በእነኚህ ውስጥ ያለውን እውቀትና ተግባር* =>

- በየትኛውም ጊዜና ቦታ፣ በየትኛውም ተራ የህይወት መስክ ላይ የሚያተኩር የፅሁፍ መመሪያ የደረሰው ትውልድ የመመሪያውን መልዕክት ያልተረዳ ሆኖና ለመረዳትም ምንም አይነት ፍላጎትና ጉጉት ሳይኖረው፣ ስለ ጉዳዩም ጭራሽ ጥያቄ ሳያነሳ ያከትማል ተብሎ ይጠረጠራልን?! ታዲያ እንዴት ያ ከሁሉም የተሻለው ብርቅዬው የሰሓቦችና የታቢዒዮች ትውልድ ከጌታቸው ዘንድ የመጣላቸው ታላቅ መለኮታዊ መመሪያ፣ በተለይ ደግሞ ስለተወዳጁ ፈጣሪያቸው ማንነት የተመለከተው ወሳኝ ርዕስ በበቂ ሁኔታ ያልተገለፀ ቢሆን ኖሮ ስለጉዳዩ ለማወቅ ሳይጓጉና ጥያቄን ሳያነሱ ያልፉሉ?!

---

=> *እስኪማሩ ድረስ ሌሎች አስሮችን የማይቀበሉ እንደነበሩ ነግረውናል፤ "እውቀትንና ተግባርን (በአንድ ላይ) ተማርን" አሉ!»* [አሕመድ (23482)፣ ኢብኑ አቢ ሸይበህ (10/460-461)፣ አል-ሓኪም (1/557)፣ አል-በይሀቂይ (3/119-120) እና ሌሎችም ዘግበውታል።]

– عن مجاهد، قال: «عرضتُ المصحفَ على ابن عباس ثلاث عَرْضات، من فاتحته إلى خاتمته، أُوقِفه عند كلِّ آية منه وأسألُه عنها».

➢ *ሙጃሂድ እንዲህ ይላሉ፡- «ቁርኣንን ሶስት ጊዜ ከመጀመሪያው እስከ መጨረሻው ወደ ኢብኑ ዐብ-ባስ (ለትምህርት) አቀረብኩኝ፤ እያንዳንዱ አንቀፅ ላይ እያስቆምኩ ስለ እርሱ እየጠየቅኩት!»* ["ተፍሲር ኢብኒ ጀሪር" (1/90)]

- ከላይ እንደተጠቀሰው ሁለቱ ታላላቅ ኢማሞች *«"ኢስቲዋእ" የማይታወቅ አይደለም»* ብለው ግልፅነቱን ጠቀሱ እንጂ *"የሚታወቅ አይደለም!"* ለምን አላሉም?![1]

---

(1) *አል-ኢማም ማሊክ* እና *አል-ኢማም ረቢዐህ* "ኢስቲዋእ" የታወቀ መሆኑን ሲናገሩ የፈለጉት መልዕክት = ቃሉ በዚህ መሰል አገባብ የሚያስተላልፈው ቋንቋዊ መልዕክት ግልፅ በመሆኑ ማብራሪያ እንደማይሻ መሆኑን ለመረዳት ብዙ ማስተዋል አይጠበቅም! የማሊኪያው ዓሊም *አቡ በክር ኢብኑ'ል-ዐረቢ* «የማሊክ አካሄድ (መዝሀብ) **የሁሉም መሰል ሀዲሦች መልዕክት የታወቀ መሆኑ ነው፤** ስለዚህም ነው ለጠየቃቸው ሰው "ኢስቲዋእ የታወቀ ነው፤ አኳኋኑ የማይታወቅ ነው..." ያሉት..» ብለዋል![“ዓሪዶቱ'ል-አሕወዚይ” (3/166)] ሌላኛው የማሊኪያ ሊቅ *አል-ቁርጡቢ* ይህን ሲገልፁ፦ «"የታወቀ ነው" ሲሉ በቋንቋ ደረጃ ማለታቸው ነው» ብለዋል። [“ተፍሲሩ'ል-ቁርጡቢ” (7/219)] በተጨማሪም *የአል-ኢማም አዝ-ዘሀቢን* [“አል-ዑሉው” ገጽ 251]፣ *የኢብኑ'ል-ቀይ-ዪምን* [“መዳሪጁ'ስ-ሳሊኪን” (2/84)]፣ እና *የአል-አሉሲን* [“ገራኢቡ'ሊ'ግቲራብ” ገፅ 387] ንግግር በዋቢነት ይመልከቱ!

**ሆኖም** አንዳንዶች *«ኢማሙ (ኢስቲዋእ) የታወቀ እንደሆነ ሲናገሩ ማለት የፈለጉት "በቁርኣን ውስጥ በቃል ደረጃ መጠቀሱ የታወቀ ነው" ለማለት ነው!»* ብለው በከንቱ ለመሞገት ይጥራሉ!

↳ ይህን የሚሉ ሰዎች *"ኢማሙ እንዲህ ያለ መልስ የሰጡት ጠያቂው ያነሳው ጥያቄ ይህንን የተመለከተ ስለሆነ ነው!"* ማለታቸው ከሆነ እንዲያው ለመሆኑ፦

- ጠያቂው ራሱ የቁርኣን አንቀፁን አንብቦላቸው ሳለ ይህ ቃል ቁርኣን ውስጥ ስለመኖሩ ይጠይቃል ተብሎ ይጠረጠራልን?!

=>

=> - በሁሉም ዘገባዎች ላይ እንደሚስተዋለው “ኢስቲዋእ”ን አስመልክቶ *“እንዴት ነው?”* ብሎ ጠየቃቸው እንጂ “ቁርኣን ላይ ተጠቅሷል ወይ?” አላቸውን?!

- ጥያቄው እንዲያ ቢሆን ኖሮ ለምን ላብ አጠመቃቸው?! *“ሙብተዲዕ”* ሳትሆን አትቀርም ብለውስ ለምን ገሰጹት?! ለምንስ ከመስጂድ እንዲወጣ አደረጉት?!

- ለምንስ ስለ አኳኋኑ (كيفية) መልስ መስጠት አስፈለጋቸው?!

↳ *“እይ! እሳቸው በራሳቸው አነሳኝነት የተናገሩት ማብራሪያ ነው!”* ከተባለ ደግሞ፦

- ሁለቱም ኢማሞች በግልፅ ቋንቋ “(ኢስቲዋእ) ተጠቅሷል (مَذْكُور)!” ወይም መሰል ግልፅና የማያሻማ ገለፃ መጠቀም ይሳናቸዋል?! [በዚህ አጋጣሚ “አድ-ደሊሉ’ል-ቀዊም” በተሰኘው *የዐብዱላህ አል-ሀረሪ* መፅሐፍ ገፅ 36 (የቀድሞው ህትመት) ላይ «(ኢስቲዋእ) ተጠቅሷል (مَذْكُور)!» በሚል ቃል *አል-ላለካኢይ* ዘንድ የተወራ ዘገባ እንዳለ ለማስመሰል የተደረገው ሙከራ **ግልፅ ቅጥፈት** መሆኑ ሊታወቅ ይገባል!]

- *“የታወቀ ነው!”* ያሉት ቃሉን (ኢስቲዋእ) እንጂ የአንቀፁን ሙሉ አረፍተ-ነገር አለመሆኑ የቃሉ መልዕክት ግልፅ እንደሆነ ማመላከታቸውን አያሳይምን?!

- በየትኛውስ አተረጓጎም ነው ስለአንድ ነገር አኳኋን ተጠይቆ “ቃሉ የታወቀ ነው” ሲባል “መጠቀሱ የታወቀ ነው” ማለት የሚሆነው?!

- ሌላው ቢቀር አኳኋኑን (كيفية) ማወቅ እንደማይቻል መናገራቸው በአንፃሩ መሠረታዊ መልዕክቱን መረዳት እንደሚቻል አያሳይምን?! መሠረታዊ መልዕክቱን ጭራሽ የማያውቅ ሰው ከዚያ በላይ ስላለው ዝርዝር ምን አስወራው?!

ልብ ይበሉ!

ስለሆነም አንዳንዶች እንደሚሞግቱት የአላህ ባህሪያት የተወሱባቸው አንቀፆችን መልዕክት የሚያውቀው አላህ ብቻ እንደሆነና ትርጓሜያቸው ጭራሽ የማይታወቅ ወይም አሻሚ መሆኑን መናገር ፍፁም የስህተት ጎዳና እና በመረጃ ላይ ያልተገነባ ፈሊጥ መሆኑን ማወቅ ያስፈልጋል![1] አዎን! አላህ እነዚህን ባህሪያት የተላበሰበትን ሁኔታ ከርሱ በቀር ማንም አያውቅም፤ የአንቀፆቹ መሠረታዊ መልዕክት ግን ግልፅ መሆኑን ከላይ ተረድተናል።

ብዥታ

ሆኖም በርዕሱ ላይ እንደ መረጃ የሚጠቅሱት አንድ የቁርኣን አንቀፅ አለ። እርሱም፦

﴿ هُوَ ٱلَّذِىٓ أَنزَلَ عَلَيۡكَ ٱلۡكِتَٰبَ مِنۡهُ ءَايَٰتٌ مُّحۡكَمَٰتٌ هُنَّ أُمُّ ٱلۡكِتَٰبِ وَأُخَرُ
مُتَشَٰبِهَٰتٌۖ فَأَمَّا ٱلَّذِينَ فِى قُلُوبِهِمۡ زَيۡغٌ فَيَتَّبِعُونَ مَا تَشَٰبَهَ مِنۡهُ ٱبۡتِغَآءَ ٱلۡفِتۡنَةِ وَٱبۡتِغَآءَ

(1) ይህ አካሄድ «ተፍዊድ» (تفويض) በመባል የሚታወቅ ሲሆን የዚህኛው ጠንቅ (ተፅጢል) አንድ ገፅታ ነው። የሚደንቀው የዚህ አቋም ባለቤቶች "የማያውቁት" "ውስጣዊ" ትርጓሜውን እንጂ - እንደነሱ አባባል ማስረጃዎቹ የሚያስተላልፉትን ቀጥተኛ መልዕክት ማፅደቅ "ማመሳሰል" በመሆኑ ጉልህ መልዕክቱ ተፈላጊ አለመሆኑን በእርግጠኝነት "ያውቃሉ"! ይህ አካሄዳቸውም የሰለፎች መንገድ እንደሆነ ይሞግታሉ፤ ይህ ቅጥፈት መሆኑን የሚያረጋግጥ ጥቆማ ወደ ፊት ይመጣል፤ ኢን-ሻአ'ላህ።

تَأۡوِيلِهِۦۖ وَمَا يَعۡلَمُ تَأۡوِيلَهُۥٓ إِلَّا ٱللَّهُۗ وَٱلرَّٰسِخُونَ فِي ٱلۡعِلۡمِ يَقُولُونَ ءَامَنَّا بِهِۦ كُلّٞ مِّنۡ عِندِ رَبِّنَاۗ ﴾ [آل عمران: ٧]

➥ «እርሱ ባንተ ላይ መፅሐፉን ያወረደው ነው፤ ከርሱ ፍፁም የሆኑ (ግልፅ) አንቀፃች አሉ፤ እነሱም የመፅሐፉ 'እናት' (መሠረትና ዋነኛ መገለጫ) ናቸው፤ ሌሎች (ደግሞ) "ሙተሻቢህ" (በአንፃሩ አሻሚ ገፅታ ያላቸው) ናቸው፤ እነዚያ በልባቸው ጥመት ያለ ፈተናን በመፈለግና "ተእዊሉን" በመፈለግ የተመሳሰለውን (አሻሚውን) ይከታተላሉ፤ "ተእዊሉን" ከአላህ በቀር ማንም አያውቅም፤ በእውቀት ውስጥ የሰፈፁትም "በርሱ አምነናል፤ ሁሉም ከጌታችን ዘንድ ነው" ይላሉ፤..» [አሊ ዒምራን 7]

ይህንን እንደመረጃ በማቅረብ ከላይ የተጠቀሰው ድምዳሜ ላይ የሚደርሱት ሁለት የተዛነፉ መንደርደሪያ ሀሳቦችን በማለፍ ነው፤

**አንደኛው፡-** *"ሙተሻቢሃት" የተባሉት አንቀፆች የአላህ ባህሪያት የተወሱባቸው መሆናቸው፤*

**ሁለተኛው፡-** *"ተእዊል" ማለት ከንግግሩ ግልፅ መልዕክት የሚለይ ውስጣዊ መልዕክት ወይም ትርጓሜ ማለት መሆኑ!*

ከዚያም እነዚህን ቅድመ-ሀሳቦች አንድ ላይ በመቀመር፡- *"የነዚህን አንቀፆች መልዕክት ወይም ትርጓሜ (ከላይ በተጠቀሰው አንቀፅ መሠረት) ከአላህ በቀር ማንም አያውቅም!"* የሚል አደገኛ መደምደሚያ ላይ ደረሱ!

፫ የሚደንቀው ሁለቱም የመንደርደሪያ ሀሳቦች ፍፁም ስህተት መሆናቸው ነው![1]

እርማት

**የመጀመሪያው መንደርደሪያ መሠረት የሌለው መሆኑን ለመረዳት ቀደምት የኢስላም ሊቃውንት ይህንን አንቀፅ ሲያብራሩ በጉዳዩ ላይ የተሰነዘሩትን ሁሉንም የዑለማዎች አስተያየቶች ከመጥቀሳቸው ጋራ አንዳቸውም የአላህ ባህሪያት በደፈናው "ሙተሻቢህ" እንደሆኑ አለመናገራቸውንና ከሰሓቦችም ይሁን ከተከታዮቻቸው መሰል አባባሎችን አለመዘገባቸውን ማወቁ ብቻ በቂ ነው!**[2]

➢ ታላቁ የኢስላም ጠቢብና ሊቅ ***ኢብኑ ተይሚይ-ያህ*** (728 ዓ.ሂ) ይህንን ሲያረጋግጡ እንዲህ ብለዋል፡-

«...فَإِنِّي مَا أَعْلَمُ عَنْ أَحَدٍ مِنْ سَلَفِ الْأُمَّةِ وَلَا مِنْ الْأَئِمَّةِ، لَا أَحْمَد بْنِ حَنْبَلٍ وَلَا غَيْرِهِ؛ أَنَّهُ جَعَلَ ذَلِكَ مِنْ الْمُتَشَابِهِ الدَّاخِلِ فِي هَذِهِ الْآيَةِ وَنَفَى أَنْ يَعْلَمَ أَحَدٌ مَعْنَاهُ..»

(1) ማንኛውም የሀሳብ ድምዳሜ ትክክል የሚሆነው የተገነባባቸው ሁሉም መንደርደሪያዎች በእውነት ሚዛን ተለክተው ሲያልፉ እንደሆን የታወቀ ነው፤ አንዱ እንኳ ከወደቀ ድምዳሜው ሙሉ በሙሉ ይፈረሳል!

(2) ለአብነት ያህል *የአል-ኢማም ኢብኑጀሪር* ተፍሲርን (3/172-175)፣ "መቃላቱ'ል-ኢስላሚይ-ዪን" የተባለውን *የአቡ'ል-ሐሰን አል-አሽዐሪይ* መፅሐፍን (1/293)፣ እንዲሁም "ዛዱ'ል-መሲር" የተባለውን *የኢብኑ'ል-ጀውዚ* ተፍሲር (1/351) እና ሌሎችንም ይመልከቱ!

*«እኔ ከዚህ ህዝበ-ሙስሊም ቀደምት ትውልዶችም፣ ከኢማሞችም - አሕመድ ኢብኑ ሐንበልም ይሁኑ ሌሎች - ይህንን (የአላህን ባህሪያት) በዚህ አንቀፅ ውስጥ የሚካተት "ሙተሻቢህ" ያደረገና ትርጓሜውንም ማንም እንደማያውቀው የምገተ አንድንም አላውቅም!»*[1]

**በተጨማሪም** አላህ ራሱን የገለፀባቸው ባህሪያት በግልፅ ቋንቋዊ ሂደትና አገባብ መጠቀሳቸውን ከላይ ባሳለፍናቸው ማብራሪያዎች ላይ አይተናል፤ ስለሆነም የአንቀፆቹ ጥቅል መልዕክት "ሙተሻቢህ" የሚለው ስያሜ ውስጥ ሊካተት አይችልም! አዎን! ስለ ሁኔታቸውና ዝርዝር ይዘታቸው ግን ከአላህ በቀር ማንም በትክክል ማወቅ እንደማይችል እንስማማለን።

**ሁለተኛውን መንደርደሪያ** በተመለከተ ደግሞ ብዙዎች እንደሚሳሳቱት በዚህም ይሁን በሌሎች የቁርኣን አንቀፆች ላይ "ተእዊል" የሚለው ቃል አንድም ጊዜ *"የአንድን ቃል ትርጓሜ ከጉልህ መልዕክቱ ወደ ሌላ ንፅፅራዊ መልዕክት ማዞር"* የሚል ትርጉም ይዞ አልመጣም። ምክንያቱም ይህ እንደ "ኡሱሉ'ል-ፊቅህ" ያሉ በስተኋላ የተዋቀሩ ዘርፎች እያደር ሲስፋፉ ጥቅም ላይ የዋለ "ቴክኒካዊ" ፍቺ እንጂ በመጀመሪያዎቹ ዘመናት የሚታወቅ አልነበረምና!

(1) *"መጅሙዑ'ል-ፈታዋ"* (13/294-295)

**ነገር ግን ቃሉ በቁርአናዊ አገባቡ መሠረት የሚያስተላልፈው፡- “የአንድ ንግግር ገሃዳዊ ይዘት ወይም ውጫዊ ፍፃሜ” የሚለውን መልዕክት ሲሆን ይህንን ገሀዳዊ ይዘት ወይም ፍፃሜ በቃል ደረጃ መግለፅም እንዲሁ “ተእዊል” ይባላል።**(1) **ለዚህም አገባቦቹን ማጤኑ ብቻ በቂ ነው።**

**ለምሳሌ ያህል፡-**

📖 ﴿هَلۡ يَنظُرُونَ إِلَّا تَأۡوِيلَهُۥۚ يَوۡمَ يَأۡتِي تَأۡوِيلُهُۥ يَقُولُ ٱلَّذِينَ نَسُوهُ مِن قَبۡلُ قَدۡ جَآءَتۡ رُسُلُ رَبِّنَا بِٱلۡحَقِّ﴾ [الأعراف: ٥٣]

**➥ «“ተእዊሉ”ን (ገሀዳዊ ፍፃሜውን) እንጂ (ሌላን) ይጠባበቃሉን? "ተእዊሉ" የሚመጣ ቀን እነዚያ ከዚያ በፊት የዘነጉት “በርግጥ የጌታችን መልዕክተኞች በእውነት መጡ” ይላሉ።።»**[አል-አዕራፍ 53]

📖 ﴿وَقَالَ يَٰٓأَبَتِ هَٰذَا تَأۡوِيلُ رُءۡيَٰيَ مِن قَبۡلُ قَدۡ جَعَلَهَا رَبِّي حَقًّا﴾ [يوسف: ١٠٠]

**➥ «እርሱም (ዩሱፍ) አለ፦ አባቴ ሆይ! ይህ የበፊት ህልሜ “ተእዊል” (ውጫዊ ፍጻሜ/ክስተት) ነው፤ ጌታዬ በርግጥ እውን አደረጋት!»**[ዩሱፍ 100]

---

(1) ስርወ-ቃሉ በግስም ይሁን በስም መልኩ የሚያስጨብጠው መልዕክት በዚህ ዙሪያ ያለ ነው። ስለሆነም አንዳንድ ጊዜ ከቁርኣን ውጭ ሰፋ ባለ አገባቡ በጥቅሉ “ተፍሲር” (መግለፅ፣ ማብራራት) የሚል መልዕክት ይኖረዋል። ሆኖም በ“ግልፅ”ም ይሁን በ“ድብቅ” ፣በ“ውጫዊ”ም ይሁን በ“ውስጣዊ” ትርጓሜ አይገደብም!

📖 ﴿فَإِن تَنَٰزَعۡتُمۡ فِي شَيۡءٖ فَرُدُّوهُ إِلَى ٱللَّهِ وَٱلرَّسُولِ إِن كُنتُمۡ تُؤۡمِنُونَ بِٱللَّهِ وَٱلۡيَوۡمِ ٱلۡأٓخِرِۚ ذَٰلِكَ خَيۡرٞ وَأَحۡسَنُ تَأۡوِيلًا﴾ [النساء: ٥٩]

➡ «**በምንም ነገር ብትወዛገቡ በአላህና በመጨረሻው ቀን የምታምኑ ከሆናችሁ ወደ አላህና ወደ መልዕክተኛው መልሱት፤ ይህ የተሻለና "ተእዊሉ" (ውጤቱ) ይበልጥ መልካም የሆነ ነው!**»[አን-ኒሳእ 59]

**በዚህ መሠረት ስለ ታላቁ የፍርድ እለት ወይም ከዚያ በኋላ ስለሚኖረው ክስተት የሚነገር ዜና ወይም ትንቢት እና ነገሩ በገሀድ ተከስቶ እውን መሆኑ ለየቅል ናቸው፤ ህልም እና የህልሙ ፍቺ በገሀድ መከሰቱ አንድ አይደሉም። የዚህ ውጫዊ ፍፃሜ ገሀዳዊ ይዘት ነው "ተእዊል" የሚባለው። ታዲያ ይህን "ተእዊል" በተሟላ መልኩ ለማወቅ ዝርዝር አኳኋኑንና አፈፃፀሙን ማወቅ የግድ ይላል። ይህንን ደግሞ ከክስተቱ በፊት የሚያውቀው የ"ገይብ" እውቀት ባለቤት የሆነው አላህ ብቻ ነው! ለዚህም ነው ከላይ በተመለከተው የቁርኣን አንቀፅ ከአላህ በቀር "ተእዊሉን" የሚያውቅ እንደሌለ የተነገረው።**

**በዚህ ማብራሪያ መሠረት አላህ ብቻ የሚያውቀው የባህሪያቱ "ተእዊል" የሚወክለው ባህሪያቱ ያሉበትን ሁኔታና ውስጣዊ ይዘት እንጂ በቋንቋዊ አገባባቸው የሚያስገነዝቡትን መሠረታዊ መልዕክት አይደለም! ስለ ትንሳኤና መሰል ርዕሶች የተነገሩንን ትንቢቶች ቋንቋዊ መልዕክት በጥቅሉ እንደምንረዳው ሁሉ ስለአምላካችን ባህሪያት የሚያወሱትን ገለፃዎችንም መልእክት በጥቅሉ እንረዳለንና! ያስተውሉ!**

---

**4ኛው ጠንቅ** **ባህሪያቱ የተጠቀሱባቸውን መረጃዎች ቃላት ወይም ትክክለኛ ትርጉም አዛብቶ መቀየር** (1)

**ቃላትንና ጉልህ መልዕክታቸውን ሆን ብሎ መቆልመም በብርቱ የተኮነነ የአይሁዳውያን መገለጫ ነው! አላህ እንዲህ ይላል፡-**

﴿أَفَتَطْمَعُونَ أَن يُؤْمِنُوا۟ لَكُمْ وَقَدْ كَانَ فَرِيقٌ مِّنْهُمْ يَسْمَعُونَ كَلَـٰمَ ٱللَّهِ ثُمَّ يُحَرِّفُونَهُۥ مِنۢ بَعْدِ مَا عَقَلُوهُ وَهُمْ يَعْلَمُونَ﴾ [البقرة: ٧٥]

➥ «(አይሁዶች) እንዲያምኑላቸሁ ትጓጓላቸሁን? - በርግጥ ከነሱ ከፊሎቹ የአላህን ቃል የሚሰሙና ከዚያም ከተረዱት በኋላ እያወቁ የሚቀይሩት የነበሩ ሆነው ሳሉ!»[አል-በቀራህ 75]

---

(1) ይኸኛው ጠንቅ (“ተሕሪፍ”) ከሶስተኛው (“ተዕጢል”) የሚለየው ይሄ ማስረጃዎች የሚያፀኑትን ትክክለኛ ትርጉም አብሮ በማይሄድ ሌላ ትርጉም መቀየር ሲሆን “ተዕጢል” ደግሞ ተለዋጭ ትርጉም ቢሰጡም ባይሰጡም በጥቅሉ ቀጥተኛውን መልዕክት ውድቅ ማድረግ ነው። ስለዚህ ማንኛውም “ተሕሪፍ” ከ“ተዕጢል” ሊነጠል አይችልም፤ “ተዕጢል” ግን የግድ “ተሕሪፍ” ላይከተለው ይችላል። “ተሕሪፍ” በሁሉም ቁርአናዊ አገባቡ በውግዘት የተወሳ ሲሆን የቢድዓህ አቀንቃኞች “ተእዊል” በሚል ስያሜ የሚያራምዱት የቃል ጥምዘዛ ይኸኛው ጠንቅ ውስጥ የሚካተት ነው፤ በዋነኝነት ትክክለኛ መልዕክቱን በመቀየር ላይ የሚያተኩሩ ቢሆንም በጥቂት አጋጣሚዎች (በተለይ የሐዲሥ ማስረጃዎች ላይ) ፊደላትን ወይም ቃላትን በመጨመር፣ በመቀነስ ወይም አነባበቡን በመለወጥ የማደናገር ስልት ይጠቀማሉ!

📖﴿مِّنَ ٱلَّذِينَ هَادُواْ يُحَرِّفُونَ ٱلۡكَلِمَ عَن مَّوَاضِعِهِۦ﴾ [النساء: ٤٦]

➥ «ከእነዚያ አይሁዳውያን ከሆኑት (መካከል) ቃላትን ከአቀማመጣቸው ያቀያይራሉ..!»[አን-ኒሳእ 46]

☇ ከላይ እንደተረጋገጠው ፈጣሪያችን ከማንም በላይ አዋቂ፣ እውነተኛና ለባሮቹ አዛኝ በመሆኑ፡ እንኳን በእንዲህ ያለ መሠረታዊና ከባድ አጀንዳ ላይ ቀርቶ በሌሎችም ርዕስ-ጉዳዮች ላይ በቁርኣኑ በግልፅ ከሚስተዋለው መልዕክት ጋራ የሚፃረሩ ጥቆማዎችን በማስተላለፍ ሀይማኖታችንን አያወሳስብብንም። መቼም ቁርኣን ግልፅ የዐረብኛ ንግግር መሆኑን ነግሮን ሲያበቃ እንደ ቅኔ "ሰምና ወርቁን ለዩ!" ብሎ አይፈትነንም!

እናም የዚህ ጠንቅ ተጠቂዎች እንደሚያስተጋቡት እነዚህ ቁርኣናዊ አንቀፆች በቀጥታ የሚያስተላልፉት መልዕክት "አላህን ከፍጡራኑ ጋር የሚያመሳስል" እንደሆነ በማሰብ የተለየ ዘይቤያዊ ትርጓሜ እንደሚያስፈልጋቸው መናገር ቋንቋዊ አግባቡን ራሱ ያልተከተለ ሙግት ከመሆኑ ባሻገር ለሌሎች በርካታ መዘዞች ያጋልጣል፤ ለምሳሌ ያህል፡-

- የአላህና የመልዕክተኛው (ﷺ) ንግግር የሚያንፀባርቀው መልዕክት ጉድለትን ያስገነዝባል ብሎ በክፉ መጠርጠር፣
- አላህ ለራሱ ያፀደቀውን ባህሪ አለመቀበል፣
- ትክክለኛውን ቁርኣናዊ መልዕክት ማስተባበል፣
- በቦታው ስህተተኛ ትርጓሜን መተካት፣

- የአላህና የመልዕክተኛው (ﷺ) ቃል በሙስሊሞች ዘንድ ያለውን ከበሬታ በመቀነስ ሁሉም ያሻውን ትርጓሜ እንዲሰጥ መንገድ መጥረግ፣
- የነቢያትን መንገድ መፃረር፣
- በጥብቅ የተኮነነውን የአይሁዳውያን መገለጫ መተግበር፣
- ስለአላህ የማያውቁትን በመናገር የሰይጣንን መንገድ መከተል[1]፣ እና የመሳሰሉት ይገኙሉ።

ለዚህ ምሳሌ ከሚሆኑ የተለመዱ የትርጉም ጥምዘዛዎች መካከል፦

× የአላህን መስማትና ማየት : *"ማወቅ"!*

× መውደዱን፣ መደሰቱንና እዝነቱን (ርህራሄውን) : *"በጥሩ መመንዳት መፈለግ"!*

× መቆጣቱን : *"ቅጣቱ"!*

× ሁለት እጆቹን : *"ችሎታው ወይም ፀጋው"!*

× ከዐርሹ በላይ መሆኑን : *"ስልጣኑን መቆጣጠሩ"!*

(1) አላህ የሰይጣንን ወጥመዶች ሲያመላክት እንዲህ ይላል፦

﴿ إِنَّمَا يَأۡمُرُكُم بِٱلسُّوٓءِ وَٱلۡفَحۡشَآءِ وَأَن تَقُولُواْ عَلَى ٱللَّهِ مَا لَا تَعۡلَمُونَ ﴾ [البقرة: ١٦٩]

➥ «እርሱም የሚያዛችሁ በመጥፎና በአፀያፊ ወንጀል፤ እንዲሁም በአላህ ላይ የማታውቁትን እንድትናገሩ ነው»[አል-በቀራህ 169]

× በፍርዱ ቀን መምጣቱን ፡ *“የትዕዛዙ መምጣት”!* ..ወዘተ እያሉ የታወቀውን ቀጥተኛ መልዕክት ማዛባት ይገኝበታል።[1]

ooo

(1) *ለዚህ ብዥታ ዋነኛ መነሻዎች በቂ ምላሾችን ያካተተውን ማብራሪያ ምዕራፍ ሁለት ላይ ይደርሱበታል.. ኢን-ሻአሏህ!*

## የእውነት ሚዛናዊነት

በጥቅሉ በቀጥተኛው መንገድ ላይ የፀኑት አማኞች በዚህ ረገድ ከቁርኣንና ከሀዲስ አስተምህሮት ፍንክች አይሉም፤ በአንድ በኩል አላህ ራሱን የገለፀባቸውን ስያሜዎችና ባህሪያትን በሙሉ **ለታላቅነቱና ለልእልናው በሚገባው መልኩ** ቢያፀድቁም በአንፃሩ በባህሪያቱ ይዘት ፍፁም አምሳያና ወደር የሌለው መሆኑን አስረግጠው ያምናሉ። ይህንን ቁርኣናዊ አቋማቸውን ሲያራምዱ መርሃቸው የሚከተለው የአላህ ቃል ነው:-

﴿لَيْسَ كَمِثْلِهِۦ شَىْءٌ ۖ وَهُوَ ٱلسَّمِيعُ ٱلْبَصِيرُ﴾ [الشورى: ١١]

➥ «እንደርሱ ያለ (አምሳያ) ምንም የለም፤ እርሱም ሰሚውና ተመልካቹ ነው።»[አሽ-ሹራ 11]

«እንደርሱ ያለ (አምሳያ) ምንም የለም» የሚለው የአንቀፁ የመጀመሪያ ክፍል ፈጣሪን ከፍጡር ጋር በምንም መልኩ ማመሳሰል ጭራሽ ውድቅና መሰረተ-ቢስ መሆኑን የሚያስገነዝብ ሲሆን፤ «እርሱም ሰሚውና ተመልካቹ ነው» የሚለው መቋጫ ደግሞ መስማትና ማየትን ጨምሮ ለአላህ በመረጃ የተረጋገጡትን ስሞችና ባህሪያት ተቀብሎ ማፅደቅ የግድ መሆኑን ይጠቁማል።

✸ በዚህም መሠረት የሐቅ ባለቤቶች የሚጓዙበት ጎዳና የአላህን ባህሪያት ከፍጡራን ባህሪያት ጋር ከሚያመሳስሉና ስለ ዝርዝር ሁኔታቸው ያለ እውቀት ከሚዘላብዱ ቡድኖች የጥመት ጎዳና የራቀ እንደሆነው ሁሉ በአንፃሩ ‘ከፍጡራን ጋር ላለማመሳሰል’ በሚል አባዜ ባህሪያቱ የተጠቀሱባቸውን ግልፅ ማስረጃዎች መልዕክት

ከሚቆለምሙና መገለጫዎቹንም ትርጉም ከሚያሳጡ ቡድኖች የጥመት መንገድ ፍፁም የራቀ ነው! ሐቁ ያለው ባፈነገጡት ሁለቱ ጠርዘኛ ጐራዎች መካከል ነውና።

**ስለሆነም ለአላህ የተረጋገጡትን መገለጫዎች ሲያፀድቁ ባህሪያቱን ከፍጡራን ባህሪያት ጋር በማመሳሰል አይደለም፤ ፈጣሪያቸው ፍጡራንን ከመምሰልና ከሌሎች የጉድለት መገለጫዎች የጠራና የላቀ መሆኑን ሲያምኑም የትክክለኛ ባህሪያቱን መልዕክት እያስተባበሉና እያዛቡ አይደለም፤ አላህ ራሱን የገለፀባቸው ስያሜዎችና ባህሪያት ምንጊዜም ምሉዕነትንና ፍፁምነትን እንጂ ጉድለትንና እንከንን የሚያስተላልፉ አይደሉምና።**

➢ **ታላቁ የኢስላም ምሁር *ኑዐይም ኢብኑ ሐም-ማድ*[1] ይህን ሚዛናዊ አቋም ሲጠቁሙ እንዲህ ብለዋል፡-**

«من شبّه اللهَ بخلقه فقد كفَر، ومن أنكر ما وَصف به نفسَه فقد كفر، وليس ما وصف اللهُ به نفسَه ولا رسولُه تشبيها»

(1) *ኑዐይም ኢብኑ ሐም-ማድ አል-ኹዛዒይ፤ ታላቁ ኢማም፤ ከዐብዱ'ላህ ኢብኑ'ል-ሙባረክና ከሌሎች እውቀትን የቀሰሙ ሲሆን እንደ አል-ኢማም አል-ቡኻሪ ያሉ ታላላቅ የሐዲሥ ሊቆች መምህር ነበሩ። "መጀመሪያ ላይ የጀህሚይ-ያህ ተከታይ ነበርኩ፤ ለዚህ ነው ንግግራቸውን በደንብ ያወቅኩት፤ ሐዲሥን ማጥናት ስጀምር አቋማቸው የፈጣሪን ህልውና ወደ መግፈፍ እንደሚመለስ ተረዳሁ!" ማለታቸው ተዘግቧል። አል-ኢማም አሕመድ "ኑዐይም ከታማኞች ነበር!" ብለዋል።* በ 229 ዓ.ሂ አረፉ።

*«አላህን ከፍጡራኑ ጋር ያመሳሰለ በእርግጥ ክህደትን ፈፅሟል፤ (አላህ) ራሱን የገለፀበትን ያስተባበለም በእርግጥ ክህደትን ፈፅሟል፤ አላህ ራሱን የገለፀበትም ሆነ መልዕክተኛው (እርሱን የገለፁበትን ማፅደቅ) ማመሳሰል አይደለም!»*[1]

አዎን! ፍጡራንን እንደማይመስል የነገረን ጌታ እራሱ እነኚህን ባህሪያት ለራሱ ማፅደቁ ግልፅ መልዕክታቸውን በጥቅሉ መቀበል ማመሳሰል እንዳልሆነ ያረጋግጣል።

ooo

(1) “ሸርሁኡሱሊ’ዕቲቃዲ አህሊ’ስ-ሱን-ነቲ ወል-ጀማዐህ” ሊ’ል-ላለካኢይ (3/532)፣ “ዘም-ሙ’ል-ከላሚ ወአህሊሂ” ሊ’ል-ሀረዊይ (4/263)፤ *አል-ኢማም አዝ-ዘሀቢይ* በጣም ትክክለኛ በሆነ ሰነድ እንደደረሳቸው መስክረዋል። [“ሲየሩ አዕላሚ’ን-ኑበላእ” (13/299)]
**ማስታወሻ፡-** አንድ ሙስሊም የክህደት ተግባርን ቢፈፅም እንኳ ከኢስላም መውጣቱ የሚፈረደው እንደ ማወቅ ያሉ መስፈርቶች ሲሟሉና ብይኑን የሚከለክሉ ምክንያቶች መወገዳቸው ሲረጋገጥ እንደሆነ ይታወቃል!

## የሰለፎች ጎዳና

የላይኛው ማብራሪያ የሕዝበ-ሙስሊሙ አበው ትውልዶች (ሰለፎች) እና የኢስላም ስመ-ጥር ሊቃውንት የተራመዱበትን መካከለኛ ጎዳና የሚገልፅ ነው! በተለያዩ የአላህ ባህሪያት ዙሪያ የተዘገቡትን ዝርዝር አስተምህሮቶቻቸውን ሳናነሳ በርዕሱ ላይ ከተዘገቡት **ጥቅል** ንግግሮቻቸው መካከል **ጥቂቱን ብቻ** ለአብነት ያህል በተጨማሪነት እናያለን።[1]

**በቅድሚያ** ግን ለዚህ እንደ መንደርደሪያ የሚሆነንን አንድ ታላቅ መርሆ እንጥቀስ፦ አንድ የእምነት ጉዳይ የሰለፎች አቋም መሆኑ የሚረጋገጠው **ከሁለት መንገዶች** በአንዱ ነው፦

1- ይህንን አቋም በቀጥታ የሚያሳዩ ያለአንድም ዓሊም ተቃውሞ የተሰራጩ ንግግሮቻቸውን በማጣቀስ፣

2- ይህ የነሱ የአንድነት አቋም መሆኑን የሚጠቅስ የታማኝና ጥናት-ሰፊ ዓሊም ምስክርነት በማጣቀስ!

ቀጥለን የምናያቸው ጥቅሶች **በሁለቱም መንገዶች** የቀደምት ሊቃውንትን የአንድነት አቋም የሚያረጋግጡ ናቸው![2]

---

(1) አስፈላጊ ሲሆን አጠር ያሉ ማብራሪያዎችን እያከልኩና አንዳንድ አንባቢያን ዘንድ ላይታወቁ የሚችሉትን ዑለማዎች ማንነት በግርጌ በአጭሩ እየጠቆምኩ አስፍሬያቸዋለሁ። አብዛኛዎቹ ከአራተኛው ክፍለ-ዘመን በፊት የኖሩ ናቸው። ከላይ ያለፉ ጥቅሶችን ደግሜ አልጠቅስም።

(2) ብዙ ስህተተኞች ግን እውነት ብለው የሚያራምዱትን አቋም ሁሉ ያለ ተጨባጭ ዘገባ በድፍረት ወደ ሰለፎች በማስጠጋት በባዶ ሙግት =>

## ጥቂት ጥቅል ጥቅሶች

በተለያዩ ጊዜያትና ከተሞች የኖሩትና ከተለያዩ የ"ፊቅህ" መዝሀቦች የተውጣጡት እነዚህ ብርቅ የኢስላም ዘቦች በአብዛኛው የራሳቸውን አቋም ብቻ ሳይሆን የሌሎች ሰለፎችን ስምምነትም እንዳሰፈሩ ልብ ይበሉ!

እነሆ...

1- ታዋቂዎቹ ታቢዒዮች ***መክሑል*** [1] እና ***አዝ-ዙህሪ*** [2] የአላህ ባህሪያት ስለተወሳባቸው ሐዲሦች ተጠይቀው:-

«أَمِرُّوها كما جاءت»

ብለው መለሱ። ትርጉሙም:- *«እንደመጡት (ተቀብላችሁ) አስኪዷቸው!»*[3]

---

=> ስህተታቸውን ሊያቃኑ መሞከራቸው የተለመደ "ብልሀት" ነው! "መጅሙዑ'ል-ፈታዋ" (4/151) ይመልከቱ።

(1) *መክሑል= አቡ ዐብዲ'ላህ አድ-ዲመሽቂይ፤* በእውቀታቸው ከመጠቁት ታዋቂ ታቢዒዮች አንዱ ናቸው። አንዳንዶች እንዲያውም ከ*አል-ኢማም አዝ-ዙህሪይ* ያስበልጧቸዋል! የሞቱት በ 116 ዓ.ሂ አካባቢ ነው።

(2) ታዋቂው ታቢዒይ *ሙሐመድ ኢብኑ ሙስሊም ኢብኑ ሺሃብ አዝ-ዙህሪይ* (50 – 124) ዓ.ሂ፤ በጊዜያቸው የነበሩ ዑለማዎች *አል-ኢማም አዝ-ዙህሪይ* ተወዳዳሪ እንደሌላቸው ይመሰክሩ ነበር።

(3) አል-አስማእ ወስ-ሲፋት ሊ'ል-በይህቂይ (2/377) እና ሌሎችም..

**2- እንደዚሁም *አል-ወሊድ ኢብኑ ሙስሊም*[1] እንዲህ አሉ፡-**

***«ማሊክ ኢብን አነስን፣ ሱፍያን አሥ-ሠውሪይን[2]፣ አል-ለይሥ ኢብን ሰዕድን[3]ና አል-አውዛዒይን በሲፋት (በአላህ ባህሪያት) ዙሪያ ስለተወሩት ዘገባዎች ጠየኳቸው፤ እነሱም፡-***

«أَمِرُّوها كما جاءت بلا كيف!»

***«ያለ "እንዴት" (ስለ አኳኋኑ ሳታወሱ) እንደመጡት (ተቀብላችሁ) አስኪዷቸው!» ብለው መለሱ።*** [4]

---

(1) *አል-ወሊድ ኢብኑ ሙስሊም*፤ የሻም ታላቅ ዓሊም፤ *አል-ኢማም አሕመድ* ስለርሳቸው ሲያወሱ "ከሻም ሰዎች እንደሱ ያለ ብልህ ሰው አላየሁም!" ብለዋል። በ 195 ዓ.ሂ ሞቱ።

(2) *ታዋቂው ሱፍያን ኢብኑ ሰዒድ አሥ-ሠውሪይ (97 – 161) ዓ.ሂ*፤ ከዱንያ ብርቅዬ ኢማሞች አንዱ ናቸው፤ በዒልማቸውና በዒባዳቸው ወደር አልነበራቸውም፤ በርካታ ታላላቅ ኢማሞች "የሐዲሥ አሚሩ'ል-ሙእሚኒን" ብለው ይሰይሟቸው ነበር።

(3) *አል-ለይሥ ኢብን ሰዕድ* (94 – 175) ዓ.ሂ፤ ታላቁ የግብፅ ኢማም፤ *አል-ኢማም አሽ-ሻፊዒይ* በፊቅህ ከ*አል-ኢማም ማሊክ* ያስበልጧቸው ነበር!

(4) "አስ-ሱን-ናህ" ሊ'ል-ኸል-ላል ገፅ 159፣ "አስ-ሲፋት" ሊ'ድ-ዳረቁጥኒይ ገፅ 57፤ "አት-ተውሒድ" ሊ'ብኒ መንዳህ (3/110)፣ "አሽ-ሸሪዓህ" ሊ'ል-አጁር-ሪይ ገፅ 310፣ "አል-ኢባናህ" ሊ'ብኒ በጥ-ጠህ (3/241)፣ "ሸርሑ ኡሱሊ'ዕቲቃዲ አህሊ'ስ-ሱን-ናህ" ሊ'ል-ላለካኢይ (3/527) ..እና ሌሎች መዛግብት ላይ በትክክለኛ ሰነድ ሰፍሯል።

**3-** ***አል-ኢማሙ አሕመድም*** **ለሚቀርበላቸው ተመሳሳይ ጥያቄ እንደዚሁ ዓይነት ምላሽ ይሰጡ ነበር።**[1]

**4-** ***ሱፍያን ኢብኑ ውየይናህ***[2] **በአላህ ባህሪያት ዙሪያ ስለተነገሩ የሀዲሥ ዘገባዎች ተጠይቀው እንዲህ ሲሉ መልሰዋል፡-**

«هِيَ كَمَا جَاءَتْ، نُقِرُّ بِهَا، وَنُحَدِّثُ بِهَا، بلا كَيْف!»

***«እነርሱ እንደመጡት ናቸው፤ ያለ "እንዴት" (ስለአኳኋኑ ሳናወሳ) እናፀድቃቸዋለን፤ (ዘገባዎቹንም) እናስተላልፋቸዋለን!»*** (3)

**5-** **ታዋቂው** ***አል-ኢማም አት-ቲርሚዚ*** **በታዋቂው የሃዲስ ጥራዛቸው ስለ መሰል ርዕሶች** **በርካታ የኢስላም ምሁራን** **የተናገሩትን እንዲህ ሲሉ ያስተላልፋሉ፡-**

---

(1) "አል-ኢባናህ" ሊ'ብኒ በጥ-ጠህ" (3/327፣331) ፣ "አሽ-ሸሪዓህ" ሊ'ል-ኣጁር-ሪይ ገፅ 329

(2) *ሱፍያን ኢብኑ ዑየይናህ* (107 – 198) ዓ.ሂ፤ ታላቁ ኢማም፤ *አል-ኢማም አሽ-ሻፊዒይ* "*እንደ ሱፍያን ኢብኑ ዑይይናህ* የዕውቀት ብቃት ያለው አላየሁም!" ብለዋል።

(3) "አስ-ሲፋት" ሊ'ድ-ዳረቁጥኒይ (ገፅ 72)፣ "አት-ተምሂድ" ሊ'ብኒ ዐብዲ'ል-በር (7/148)

«..قَالُوا: قَدْ ثبتت الرِّوَايَاتُ فِي هَذَا، وَيُؤْمَنُ بِهَا، وَلاَ يُتَوَهَّمُ، وَلاَ يُقَالُ: كَيْفَ. هَكَذَا رُوِيَ عَنْ مَالِكٍ وَسُفْيَانَ بْنِ عُيَيْنَةَ وَعَبْدِ اللَّهِ بْنِ الْمُبَارَكِ؛ أَنَّهُمْ قَالُوا فِي هَذِهِ الأَحَادِيثِ:أَمِرُّوهَا بِلاَ كَيْف. **وَهَكَذَا قَوْلُ أَهْلِ الْعِلْمِ مِنْ أَهْلِ السُّنَّةِ وَالْجَمَاعَةِ**، وَأَمَّا الجَهْمِيَّةُ فَأَنْكَرَتْ هَذِهِ الرِّوَايَاتِ وَقَالُوا: هَذَا تَشْبِيهٌ...»

*«"በዚህ ላይ ያሉ ዘገባዎች የተረጋገጡ ናቸው፤ ይታመንባቸዋል፤ በሀሳብ አይገመትም፤ እንዴትም አይባልም" ብለዋል፤ እንደዚሁ ከማሊክ፣ ከሱፍያን ኢብን ዑየይና እና ከዐብዱላህ ኢብኑ'ል-ሙባረክ እነኚህን ሐዲሦች አስመልክቶ "ያለ እንዴት (ስለ አኳኋኑ ሳታወሱ) (ተቀብላችሁ)* ***አስኪዷቸው!"*** *ማለታቸው ተዘግቧል።* ***(የተቀሩት) የአህሉ'ስሱና ወል-ጀማዓ ሊቃውንት አቋምም እንዲሁ ነው።*** *ጀህሚይ-ያዎች ግን እነዚህን ዘገባዎች አስተባበሉ፤ "ይህ ማመሳሰል ነው!" አሉም!..»*[1]

---

ከነዚህ አባባሎች ምን ተረዳን?

↳ እነዚህ ቀደምት ሊቃውንት በነዚህ ዘገባዎች ላይ ***«እንደመጡት*** *(ተቀብላችሁ)* ***አስኪዷቸው..!»*** ማለታቸው በእነዚህ አንቀፆችና ሐዲሦች የተወሱት የጌታ ባህሪያት በግልፅ ቋንቋዊ አገባብና የንግግር ሂደት በመጠቀሳቸው የተነሳ የተለየ ማብራሪያና ተጨማሪ

(1) "ሱነኑ'ት-ቲርሚዚይ" ኪታቡ'ዝ-ዘካህ፤ ከሐዲሥ ቁጥር (662) ቀጥሎ

ገለፃ እንደማይሹ ያስተምራል፤ ይህ ደግሞ ግልፅ መልዕክታቸውን ይቀበሉ እንደነበረና በ"ተእዊል" አባዜ ቀጥተኛ ትርጓሜያቸውን በፍፁም እንደማያዛቡ በቀላሉ ያስገነዝባል!

አንዳንድ ሰዎች ያለ እውቀት እንደሚገምቱት ሰለፎች ይህንን ያሉት እነዚህ አንቀፆችና ሐዲሦች መልዕታቸው ጭራሽ የማይታወቅ ወይም ትርጉም-አልባ እንደሆኑ አምነው አይደለም! እንዲያውም ነገሩ በተቃራኒው ነው! ምክንያቱም ***«እንደመጡት (ተቀብላችሁ) አስኪዷቸው..!»፣«..ይታመንባቸዋል..»፤*** ከሚለው ንግግራቸው በግልፅ የምንረዳው ባህሪያቱ የተጠቀሱበትን ቃልም ይሁን መልዕክት ሳይቀይሩ እንዳሉ መቀበልና ማፅደቅ የግድ መሆኑን ነው።

በተጨማሪም ነገሩ እንዲያ ቢሆን ኖሮ *«**ያለ እንዴት** (ስለ አኳኋኑ ሳታወሱ)»* ማለት ባላስፈለጋቸው ነበር፤ ምክንያቱም አንድ ሰው ቃላዊ ትርጓሜውን ጭራሽ ስለማያውቀው ወይም ስለማያፀድቀው መልዕክት አፍራሽ ንግግር ሲናገር *«**ያለ እንዴት** (ስለ አኳኋኑ ሳታወሱ)»* የሚል ጭማሪ ማከሉ ትርጉም አይኖረውም፤ **ስለ አኳኋኑ ማወቅ እንደማይቻል መናገር በተዘዋዋሪ መሠረታዊ መልዕክቱን መረዳትንና መቀበልን ያሳያልና!**

በሌላ አነጋገር የአንድን ገለፃ ቀጥተኛ መልዕክት ስለመቀበል ምንም አይነት ተቃውሞ ሳያንፀባርቁ ከዚያ ስላለፈው አኳኋንና ይዘት

የሚደረግ ግምታዊ ገለፃን ነጥሎ ማውገዝ መሠረታዊ መልዕክቱን መቀበልን ያስገነዝባል።[1]

ስለሆነም ***«እንደመጡት (ተቀብላችሁ) አስኪዷቸው..!»*** የሚለው ገለፃቸው ቀጥተኛ መልዕክታቸውን ላለመቀበል ትርጉማቸውን ማዛባትን የሚከለክል ሲሆን፤ *«ያለ እንዴት (ስለ አኳኋኑ ሳታወሱ)»* የሚለው ደግሞ አኳኋኑንና ይዘቱን መግለፅን ወይም ከፍጡር ጋር ማመሳሰልን ይከለክላል። ልብ ያለው ልብ ይበል!

---

ወደ ጥቅሶቹ እንመለስ፦

6- ታላቁ የኢስላም ሊቅ ***አል-ኢማም አል-አውዛዒይ***[2] እንዲህ ይላሉ፦

«كُنَّا وَالتَّابِعُونَ مُتَوَافِرُونَ نَقُولُ: إِنَّ اللَّهَ –تَعَالَى ذِكْرُهُ– فَوْقَ عَرْشِهِ، وَنُؤْمِنُ بِمَا وَرَدَتِ السُّنَّةُ بِهِ مِنْ صِفَاتِهِ»

***« ታቢዒዮች በብዛት (በህይወት) እያሉ፣ "አላህ ከዐርሹ በላይ ነው!" እንልና በሐዲሥ በተጠቀሱት ባህሪያቱም እናምን ነበር!»***[1]

(1) ለበለጠ ግንዛቤ "የ3ኛውን ጠንቅ" ማብራሪያ ደግመው ይመልከቱ።

(2) *አል-አውዛዒይ = ዐብዱ'ር-ረሕማን ኢብኑ ዐምር* (97 – 157) ዓ.ሂ ፤ በጊዜያቸው ከነበሩት ታላላቅ ኢማሞች አንዱ ናቸው፤ በዘመናቸው የነበሩት *አል-ኢማም ማሊክ* ስለርሳቸው ሲያወሱ "አል-አውዛዒይ በአርዓያነቱ የሚከተሉት ኢማም ነው!" ብለዋል።

---

**7- *አል-ኢማም አቡ ሐኒፋ*** (150 ዓ.ሂ) **እንዲህ ማለታቸው ተዘግቧል፡-**

«لا يُوصف الله –تعالى– بصفات المخلوقين، وغضبُه ورضاه صفتان من صفاته بلا كيف، **وهو قول أهل السنة والجماعة**، وهو يَغضب ويَرضى، ولا يقال: غضبه عقوبته! ورضاه ثوابه! ونصفه كما وصف نفسه... »

***«አላህ በፍጡራን ባህሪያት አይገለፅም፤ ቁጣውና ውዴታው ያለ "እንዴት" ከባህሪያቱ ሁለቱ ናቸው፤ ይህ የ"አህሉ'ስ-ሱን-ና ወ'ል-ጀማዓህ" አቋም ነው! እርሱም (አላህ) ይቆጣል፣ ይወዳል፤ "ቁጣው ቅጣቱ ነው! ውዴታው መልካም ምንዳው ነው!" አይባልም! እራሱን እንደገለፀው እንገልፀዋለን..»***[2]

**በሌላም ቦታ እንደሚከተለው ይላሉ፡-**

(1) **"አል-አስማኡ ወስ-ሲፋት" ሊ'ል-በይሀቂይ** (2/150)፣ ***አዝ-ዘሀቢይ*** **በትክክለኛ ሰነድ *መዘገቡን* መስክረዋል። ["ተዝኪረቱ'ል-ሑፍ-ፋዝ"** (1/181-182)]፤ ***ኢብኑ ሐጀርም*** **ጠንካራ ሰነድ ብለውታል። ["ፈትሑ'ል-ባሪ"** (13/406)]

(2) **"አል-ፊቅሁ'ል-አብሰጥ" ገፅ** 56፣ **"አል-ፊቅሁ'ል-አክበር" (ከዶ/ር አል-ኹመይስ ማብራሪያ ጋር የታተመው) ገፅ** 159

«..فَمَا ذكره الله تَعَالَى فِي الْقُرْآن من ذكر الْوَجْه وَالْيَد والنَّفس فَهُوَ لَهُ صِفَات بِلَا كَيفَ، وَلَا يُقَال إِن يَده قدرتُه اَوْ نعْمَته؛ لِأَن فِيهِ إبطَال الصّفة »

*«እንደ ፊት፣ እጅና ነፍስ ያልለ አላህ በቁርኣኑ ያወሳው ሁሉ ያለ "እንዴት" የርሱ ባህሪያት ናቸው! እጁ "ችሎታው ወይም ፀጋው ነው" አይባልም፤ ምክንያቱም ይህን ማለት ባህሪውን ማፍረስ ነውና!»*(1)

---

**8- *አል-ኢማም ዐብዱል-ዐዚዝ ኢብኑ'ል-ማጀሹን*(2) የአላህን ባህሪያት ስለሚያስተባብሉት ጀህሚይ-ያዎች ተጠይቀው በፃፉት ምላሽ ላይ እንደሚከተለው ብለዋል፡-**

«..فَمَا وَصَفَ اللَّهُ مِنْ نَفْسِهِ وَسَمَّاهُ عَلَى لِسَانِ رَسُولِهِ سَمَّيْنَاهُ كَمَا سَمَّاهُ، وَلَمْ نَتَكَلَّفْ منه علم ماسواه،- لَا هَذَا، وَلَا هَذَا-؛ لَا نَجْحَدُ مَا وَصَفَ، وَلَا نَتَكَلَّفُ مَعْرِفَةَ مَا لَمْ يَصِفْ.»

*«..አላህ ስለራሱ የገለፀበትንና በመልዕክተኛው አንደበት የተሰየመበትን (አስመልክቶ) እኛም እንደዚያው እንሰይመዋለን፤*

(1) "አል-ፊቅሁ'ል-አክበር" (ከዶ/ር አል-ኹመይስ ማብራሪያ ጋር የታተመው) ገፅ 27

(2) *አል-ኢማም ዐብዱል-ዐዚዝ ኢብኑ'ል-ማጀሹን፤* ታላቁ የመዲና ዓሊም፤ አንድ ጊዜ ከርሳቸውና *ከአል-ኢማም ማሊክ* ውጪ በመዲና ማንም ፈትዋ እንዳይሰጥ ጥሪ ተደርጎ ነበር፤ በ 164 ዓ.ሂ አረፉ።

*ከዚያ ወዲያ ያለውን ለማወቅ አንፍጨረጨርም፤ ይህንንም ያንንም (አናደርግም)፡- (ራሱን) የገለፀበትን አናስተባብልም፤ ራሱን ስላልገለፀበት ለማወቅም አንፍጨረጨርም!»*[1]

---

**9- *አል-ኢማም ሙሐመድ ኢብኑ'ል-ሐሰን አሽ-ሸይባኒ*[2] እንዲህ ብለዋል፡-**

«**اتّفق الفقهاءُ كلُّهم** مِن المشرق إلى المغرب على الإيمان بالقرآن والأحاديث التي جاء بها الثِّقاتُ عن رسول الله –صلى الله عليه وسلم– في صفة الرّب –عز وجل– من غير تفسير ولا وصف ولا تشبيه، فمَن فسّر اليوم شيئًا من ذلك، فقد خرج مما كان عليه النبي –صلى الله عليه وسلم–، وفارق الجماعة؛ فإنهم لم يَصِفوا ولم يفسِّروا، ولكن أفتَوا بما في الكتاب والسنة ثم سكتوا، فَمَنْ قَالَ بِقَوْلِ جَهْمٍ فَقَدْ فَارَقَ الْجَمَاعَةَ؛ لِأَنَّهُ قَدْ وَصَفَهُ بِصِفَةِ لَا شَيْءَ!»

***«ከምስራቅ እስከ ምእራብ ያሉት ሁሉም ሊቃውንት በጌታ ባህሪያት ዙሪያ በቁርአን የመጡትንና ታማኞች ያስተላለፏቸውን***

(1) "አል-ኢባነህ" ሊ'ብኒ በጥ-ጠህ (3/63)፤ "ሲየሩ አዕላሚ'ን-ኑበላእ" ሊ'ዝ-ዘሀቢይ (7/312)፤ "አል-ዑሉው" ሊ'ዝ-ዘሀቢይ ገፅ 141

(2) *ሙሐመድ ኢብኑ'ል-ሀሰን አሽ-ሸይባኒ* (189 ዓ.ሂ)፤ የዒራቁ ዓሊም፤ *የአቡ ሐኒፋ* ቅርብ ተማሪ፤ *አል-ኢማም አህመድ* "እነዚህን ረቂቅ የፊቅህ ዝርዝሮች ከየት አመጡ?" ሲባሉ "ከ*ሙሐመድ ኢብኑ'ል-ሐሰን* መፃህፍት!" አሉ።

*ሐዲሦች ያለ "ተፍሲር" ("ተእዊል")፣ ያለ (ተጨማሪ) ገለፃና፣ ያለ ማመሳሰል በማመን ላይ ተስማምተዋል፤ ዛሬ ከዚህ ውስጥ አንዱንም (በራሱ ገለፃ) ያብራራ መልዕክተኛው ከነበሩበት (መንገድ) ወጥቷል፤ ከ"ጀማዓህ"ም ተነጥሏል፤ እነርሱ (ስለይዘቱ) ገለፃ አላደረጉምና፣ አላብራሩምም፤ ነገር ግን ቁርአንና ሐዲሥ ውስጥ ባለው (ገለፃ) መልስ ሰጡና ከዚያም ዝም አሉ፤ የጀህምን ንግግር የተናገረ ከሙስሊሞች ስብስብ አፈንግጧል! ምክንያቱም ጭራሽ በሌለ ነገር መገለጫ ገልፆታልና!»*(1)

ማስታወሻ

እኚህ ታላቅ ኢማም በዚህ ንግግራቸው ሁሉም ቀደምት ዑለማዎች በርዕሱ ላይ አንድ አይነት አቋም እንዳላቸው ያስገነዘቡ ሲሆን እንደ "ጀህሚይ-ያህ" ያሉ የጥመት ጭፍራዎች በ"ተፍሲር" ስም የሚያዘወትሩትን የተዛባ ትርጓሜ አውግዘዋል(2)፤ ምክንያቱም

---

(1) "ሸርሑ ኡሱሊ'ዕቲቃዲ አህሊ'ስ-ሱን-ነቲ ወል-ጀማዐህ" ሊ'ል-ላለካኢይ (2/432)

(2) ጀህሚይ-ያዎች የሚተገብሩትን የትርጉም ማጣመም ስልት "ተፍሲር" ብለው ይሰይሙ እንደነበር ከሚያሳዩ ዘገባዎች መካከል፡-
*አል-ኢማም* **አሕመድ** አንድ ግለሰብ "..አላህ ጀሀነም ላይ እግሩን ያስቀምጥባታል" የሚለውን ሐዲሥ ሲሰማ ***"ይሄ 'ተፍሲር' አለው!"*** ብሎ እንደተናገረ ሲሰሙ እንዲህ አሉ፡-

"انْظُرْ إليه! كَمَا تَقُولُ الْجَهْمِيَّةُ سَوَاءً!"

➢ ***"ተመልከት! ልክ ጀህሚያዎች እንደሚሉት!"*** አሉ። =>

ብዙሃኑ ሙስሊሞች ከማመሳሰል በፀዳ ግንዛቤያቸው ከሚረዱት ቀጥተኛ መልዕክት ያፈነገጠ ትንታኔ በመሆኑ ነው! በእነዚህ አንቀፆችና ሐዲሦች የተወሱት የጌታ ባህሪያት በግልፅ ቋንቋዊ አገባብና የንግግር ሂደት በመጠቀሳቸው የተነሳ የተለየ ማብራሪያና ተጨማሪ ገለፃ አይሹምና! ለዚህ ነው በርካታ የአበው ሊቃውንት ከላይ እንደተጠቀሰው *"እንደመጡት አስኪዷቸው!"* ይሉ የነበረው ስለዚህም ነው:-

**10- *አል-ኢማም ሱፍያን ኢብኑ ዑየይነህ* እንዲህ ያሉት:-**

«كُلُّ شَيْءٍ وَصَفَ اللهُ بِهِ نَفْسَهُ فِي الْقُرْآنِ فَقِرَاءَتُهُ تَفْسِيرُهُ، لَا كَيْفَ وَلَا مِثْلَ!»

***«ማንኛውም አላህ በቁርኣን ራሱን የገለፀበት ነገር ንባቡ (ራሱ) ማብራሪያው ነው፤ "እንዴት"ም ሆነ ማመሳሰል የለም!»***[1]

---

=> ["አል-ኢባናህ" ሊ'ብኒ በጥ-ጠህ (3/330) ቁጥር 259]
አንዳንድ ቀደምት ሊቃውንት በጉዳዩ ላይ "ተፍሲር" (ማብራሪያ) ማከል በዋነኝነት የሚከለክሉት ከዚህ አኳያ ሲሆን አንዳንዴም ወደ ዝርዝር ይዘት ("ከይፊይ-ያህ") የሚያመራን የትንታኔ በር ከነአካቴው ለመዝጋት ነው!

(1) "አል-ኢባነህ ሊ'ብኒ በጥ-ጠህ" (3/166)፣ "አስ-ሲፋት" ሊ'ድ-ዳረቁጥኒይ (ገፅ 70)፣ "ሸርሑ ኡሱሊ'ዕቲቃዲ አህሊ'ስ-ሱን-ነህ" ሊ'ል-ላለካኢይ (3/431)፣ "አል-አስማኡ ወስ-ሲፋት" ሊ'ል-በይሀቂይ (397)፣ "አሊ'ዕቲቃድ" ሊ'ል-በይሀቂይ ገፅ 123 እና ሌሎችም ዘግበውታል።

☛ ***አል-ኢማም አዝ-ዘሀቢይ (748 ዓ.ሂ) ይህንንና መሰል ዘገባዎችን ሲያብራሩ እንዲህ ይላሉ:-***

«..وكما قال سفيانُ وغيره: قراءتها تفسيرها، **يعني**: أنها بيّنةٌ واضحة في اللغة، لا يُبتغى بها مضائقُ التأويل والتحريف، وهذا **هو مذهبُ السلف**..»

***«ሱፍያንና ሌሎችም እንዳሉት:- ንባባቸው ማብራሪያቸው ነው! ማለትም:- (መልዕክታቸው) በቋንቋ ደረጃ ፍንትው ያለ ግልፅ ነው፤ በእነሱም ላይ የ"ተእዊል" እና ትርጉም የማዛባት (ተሕሪፍ) ጠባብ መንገዶች ሊፈለግባቸው አይገባም፤ ይህ ነው የቀደምት (ደጋግ) ትውልዶች (ሰለፎች) መንገድ..!»***[1]

---

አሁንም ወደ ጥቅሶቹ እንመለስ:-

11- ***አል-ኢማም ዐብዱ'ር-ረህማን ኢብኑ'ል-ቃሲም***[2] ***እንዲህ ብለዋል:-***

(1) "አል-ዑሉው" ገፅ 251

(2) *ዐብዱ'ር-ረህማን ኢብኑ'ል-ቃሲም* (132 – 191 ዓ.ሂ)፤ ታላቁ የግብፅ ኢማም፣ አል-ኢማም ማሊክ ካወደሷቸው የቅርብ ተማሪዎቻቸውና የእውቀታቸው አስተላላፊዎች አንዱ ነበሩ።

«لَا يَنْبَغِي لِأَحَدٍ أَنْ يَصِفَ اَللَّهَ إِلَّا بِمَا وَصَفَ بِهِ نَفْسَهُ فِي اَلْقُرْآنِ، وَلَا يُشَبِّهَ يَدَيْهِ بِشَيْءٍ، وَلَا وَجْهَهُ بِشَيْءٍ، وَلَكِنْ يَقُولُ: لَهُ يَدَانِ كَمَا وَصَفَ نَفْسَهُ فِي اَلْقُرْآنِ، وَلَهُ وَجْهٌ كَمَا وَصَفَ نَفْسَهُ، يَقِفُ عِنْدَمَا وَصَفَ بِهِ نَفْسَهُ فِي اَلْكِتَابِ..»

***« አንድም ሰው አላህ ራሱን በቁርኣን በገለፀበት ባህሪ ካልሆነ በቀር እርሱን መግለፅ አይገባውም፣ ሁለት እጆቹንም ከምንም ጋር ማመሳሰል፣ ፊቱንም ከምንም ጋር ማመሳሰል የለበትም! ነገር ግን ራሱን በቁርኣን እንደገለፀው: "ሁለት እጆች አሉት፣ ፊትም አለው.." ብሎ አላህ በመፅሀፉ ራሱን የገለፀበት ላይ ሊቆም ይገባዋል..»***[1]

---

**12- *አል-ኢማም አሽ-ሻፊዒይ (204 ዓ.ሂ)* እንዲህ ብለዋል:-**

«لِلهِ –تبارك وتعالى– أسماءٌ وصفاتٌ، جاء بها كتابُه وخبَّر بها نبيُّه –صلى الله عليه وسلم– أمّتَه، لا يَسَعُ أحدًا مِن خلْقِ الله –عزَّ وجلَّ– قامت لديه الحُجّةُ أنّ القرآنَ نزل به، وصحَّ عنده قولُ النبيّ–صلى الله عليه وسلم– فيما رَوى عنه العدلُ؛ خلافُه، فإنْ خالف ذلك بعد ثبوت الحجّة عليه؛ فهو كافر بالله –عزَّ وجلَّ–. فأما قبل ثبوت الحجّةِ عليه من جهة الخبر؛ فمعذور بالجهل؛ لأن عِلم ذلك لا يُدرك بالعقل، ولا بالرَّوِيّة والفِكر، نحو إخبار الله سبحانه وَتَعَالَى إيّانا أنه سميع وأن له يدين بقوله: "بَلْ

(1) "ኡሱሉ'ስ-ሱን-ናህ" ሊ'ብኒ አቢ ዘመኒን፤ ገፅ 75

يَدَاهُ مَبْسُوطَتَانِ" وأن له يمينا بقوله: "وَٱلسَّمَٰوَٰتُ مَطْوِيَّٰتُۢ بِيَمِينِهِۦۚ" وأن له وجها...»

*«ለአላህ በመፅሐፉ ውስጥ የመጡና ነብዩም (ﷺ) ለህዝባቸው የተናገሯቸው ስሞችና ባህሪዎች አሉት፤ ከአላህ ፍጡራን ማንም ቢሆን በቁርአን እንደተወሱ ግልፅ መረጃ ከደረሰውና የነብዩም ንግግር ታማኝ አስተላላፊ ባወራው ትክክለኛ ዘገባ እርሱ ዘንድ ከተረጋገጠ በኋላ የተለየ አቋም የመያዝ ምርጫ አይኖረውም፤ መረጃው (በግልፅ ሁኔታ ፀንቶ) ከደረሰው በኋላ ከተፃረረው በአላህ የካደ ይሆናል፤ መረጃው በዘገባ በኩል (ግልፅ ሆኖ) ሳይደርሰው በፊት ከሆነ ግን ባለማወቁ ምክንያት ይታለፋል (ከሀዲ አይሆንም)፤ ምክንያቱም ይህ በአዕምሮ (ምርምር)፣ ወይም በእርጋታ በማሰብና በማሰላሰል የሚደረስበት አይደለምና! አላህ ሰሚ እንደሆነ፣ እንዲሁም “ሁለቱ እጆቹ የተዘረጉ ናቸው”* [አል-ማኢዳህ 64] *በሚለው ቃሉ ሁለት እጆች እንዳሉት፣ “ሰማያት በቀኙ የሚጠቀለሉ ሲሆኑ”* [አዝ-ዙመር 67] *በሚለው ቃሉ ቀኝ እጅ እንዳለው፣ ፊት እንዳለው.... እንደነገረን ማለት ነው።»*

**አሽ-ሻፊዒይ ሌሎች ምሳሌዎችን ካጣቀሱ በኋላ ንግግራቸውን እንዲህ ብለው ቋጩ፡-**

«لكن نُثْبِتُ هَذِهِ الصِّفَاتِ، وَنَنْفِي التَّشْبِيهَ كَمَا نَفَى عَنْ نَفْسِهِ –تعالى ذِكْرُه– فَقَالَ:

﴿لَيۡسَ كَمِثۡلِهِۦ شَيۡءٞۖ﴾»

*«..ግን እነኚህን ባህሪያት እናፀድቃለን፤ ማመሳሰልንም (አላህ) እራሱ «እንደርሱ ያለ (ለምሳያ) ምንም የለም»*[አሽ-ሹራ 11] *ብሎ ውድቅ እንዳደረገው ውድቅ እናደርጋለን።»*(1)

---

**13- የኢማሞች ኢማም በመባል የሚታወቁት *ኢብኑ ኹዘይማህ*(2) አላህ ለራሱ ስላፀደቀው ፊት (وَجْه) ሲናገሩ እንዲህ ብለዋል፡-**

«فنَحْنُ **وجميعُ عُلمائِنا** مِن أهلِ الحِجازِ وتِهامةَ واليَمَنِ والعِراقِ والشَّامِ ومِصْرَ مذْهبُنا: أنَّا نُثبتُ لله ما أثبته اللهُ لنفسه، نُقِرّ بذلك بألسنتنا، ونُصَدِّق ذلك بقلوبنا، مِن غَير أن نشبِّهَ وَجْهَ خالقِنا بِوَجْهِ أحدٍ مِن المخلوقين، عزّ ربُّنا عَن أنْ يُشْبِهَ المخلوقين، وجلَّ ربُّنا عن مقالة المعطِّلين..»

*<u>«እኛና ሁሉም ዑለማዎቻችን- ሒጃዝ፣ ቲሃማ፣ የመን፣ ዒራቅ፣ ሻም፣ ሚስር (ግብፅ) ያሉት-</u> መንገዳችን ለአላህ ራሱ ያፀደቀውን ማፅደቃችን ነው፤ ይህንን በአንደበታችን ስናረጋግጥና በልቦናችን*

(1) “ጁዝኡን ፊ’ዕቲቃዲ’ል-ኢማም አሽ-ሻፊዒይ” (የአቡ ጣሊብ አል-ዑሻሪ ዘገባ የእጅ ፅሁፍ መዝገብ) ገፅ 3፣ “ኢዕቲቃዱ’ል-ኢማም አቢ ዐብዲ’ል-ላህ ሙሐመድ ኢብኒ ኢድሪስ አሽ-ሻፊዒይ” ሊ’ል-ሀካሪይ ገጽ 20፣ “መናቂቡ’ሽ-ሻፌኢይ” ሊ’ብኒ አቢ ሃቲም [ኢብኑ ሐጀር በ“ፈትሁ’ል-ባሪ” (13/407) እንዳመላከቱት]፣ “ጠበቃቱ’ል-ሀናቢላ” ሊ’ብኒ አቢ የዕላ (1/283)፣ “ዘምሙ’ት-ተእዊል” ሊ’ብኒ ቁዳማ ገፅ 23

(2) *ሙሐመድ ኢብኑ ኢስሓቅ ኢብኒ ኹዘይማህ* (223 – 311 ዓ.ሂ)፤ *አድ-ዳረቁጥኒይ* “አቻ የሌለው ፅኑ ኢማም!” ብለው አወድሰዋቸዋል።

*ስናምን የፈጣሪያችንን ፊት ከፍጡራን መካከል ከአንዱም ፊት ጋር ሳናመሳስል ነው፤ ጌታችን ፍጡራንን ከመምሰል የላቀ ነው፤ ባህሪያቱን ከሚያስተባብሉት ንግግርም የከበረ ነው..!»*[1]

---

**14- አል-ኢማም አል-አጁር-ሪይ**[2] **እንዲህ ብለዋል:-**

«اعْلَمُوا -وَفَّقَنَا اللَّهُ وَإِيَّاكُمْ لِلرَّشَادِ مِنَ الْقَوْلِ وَالْعَمَلِ- أَنَّ أَهْلَ الْحَقِّ يَصِفُونَ اللَّهَ عَزَّ وَجَلَّ بِمَا وَصَفَ بِهِ نَفْسَهُ عَزَّ وَجَلَّ، وَبِمَا وَصَفَهُ بِهِ رَسُولُهُ ﷺ، وَبِمَا وَصَفَهُ بِهِ الصَّحَابَةُ رَضِيَ اللَّهُ عَنْهُمْ، **وَهَذَا مَذْهَبُ الْعُلَمَاءِ مِمَّنِ اتَّبَعَ وَلَمْ يَبْتَدِعْ**، وَلَا يُقَالُ فِيهِ: كَيْفَ؟»

*«አላህ እኛንና እናንተን ለቀናው ንግግርና ተግባር ያጋጥመንና የሐቅ ባለቤቶች አላህን ራሱን በገለፀበት እንዲሁም መልዕክተኛውና ሰሓቦች እርሱን በገለፁበት ባህሪይ እንደሚገልፁት እወቁ! ይህም (የቀድሞውን ፋና) የተከተሉትና (አዲስ ፈሊጥ) ያልፈጠሩት ዑለማዎች መንገድ ነው! "እንዴት" አይባልም!..»*[3]

---

(1) "አት-ተውሂድ" ሊ'ብኒ ኹዘይማህ (1/26)

(2) አል-ኢማም ሙሐመድ ኢብኑ'ል-ሑሰይን አል-አጁር-ሪይ፤ ታላቁ የመካህ ዓሊም፤ በርካታ ዑለማዎች አወድሰዋቸዋል፤ በ 360 ዓ.ሂ አረፉ።

(3)"አሽ-ሸሪዓህ" ሊ'ል-አጁር-ሪይ ገፅ 277

**15- አል-ኢማም ኢብኑ መንዳህ**[1] እንዲህ ብለዋል:-

«إن الأخبار في صفات الله عزّ وجلّ جاءت متواترةً عن نبيّ الله ﷺ موافقةً لكتاب الله عزّ وجلّ، نقلها الخلف عن السلف، قرنا بعد قرن؛ من لدن الصحابة والتابعين إلى عصرنا هذا، على سبيل إثبات الصفات لله عزّ وجلّ والمعرفة والإيمان به، والتسليم لما أخبر اللهُ عزّ وجلّ به في تنزيله، وبيّنه الرسول –صلى الله عليه وسلم– عن كتابه، مع اجتناب التأويل والجحود، وترك التمثيل والتكييف..»

***«በአላህ ባህሪያት ዙሪያ የተወሩ ዘገባዎች ከአላህ ነብይ (ﷺ) በብዙ ሰነዶች የተዘገቡና የአላህንም መፅሐፍ (ቁርኣንን) የሚገጥሙ ሆነው መጥተዋል፤ የኋለኞቹ ከቀድሞዎቹ ተቀብለው ከሰሓቦችና ተከታዮቻቸው (ታቢዒዮች) ጀምሮ እስከ ዘመናችን ድረስ ከትውልድ ትውልድ ባህሪያቱን ለአላህ በማፅደቅ፣ በማወቅና በማመን፣ አላህ ላወረደው (ቁርኣን)ና መልዕክተኛውም ከርሱ መፅሀፍ ለገለፁት እጅ በመስጠት፣ እንዲሁም ግልፅ መልዕክቱን በሌላ መተርጎምን (ተእዊል) እና ማስተባበልን ከመራቅና ማመሳሰልንም፣ ዝርዝር ይዘቱን መገመትንም ከመተው ጋራ አስተላልፈዋቸዋል።»***[2]

---

(1) አል-ኢማም ሙሐመድ ኢብኑ ኢስሓቅ ኢብኒ መንደህ (310 – 395 ዓ.ሂ)፤ ታላቁ የሐዲሥ ሊቅ፤ አቡ-ኢስማዒል አል-አንሷሪ "የዘመናቸው አለቃ" ብለዋቸዋል።

(2) "አት-ተውሒድ" ሊኢብኒ መንዳህ (3/7)

**16- ታዋቂው *አቡ'ል-ሐሰን አል-አሽዐሪይ*[1] የአህሉ'ስ-ሱን-ናህ የአንድነት አቋምን እንዲህ ሲሉ ይጠቅሳሉ፡-**

«**وأجمعوا** على وصْفِ اللهِ تعالى بجميع ما وصَف به نفسَه، ووصَفَه به نبيّه، من غير اعتراضٍ فيه ولا تكييفٍ له، وأَنّ الإيمانَ به واجبٌ، وترْكَ التكييفِ له لازم.»

***«አላህን ራሱን በገለፀበትና ነብዩም እርሱን በገለፁበት (ባህሪይ) በሙሉ ያለ ቅራኔና ስለአኳኋኑ ሳይመራመሩ በመግለፅ ላይ፣ እንዲሁም በዚህ ማመን ግዴታ በመሆኑና ስለ ሁኔታው ይዘት መመራመርን መተው የግድ በመሆኑ ላይ ተስማምተዋል።»***[2]

---

**17- ታዋቂው የኢስላም ሊቅ *አል-ኢማም ኢብኑ ዐብዲ'ል-በር*[3] እንዲህ ይላሉ፡-**

(1) *አቡ'ል-ሐሰን ዐሊይ ኢብኑ ኢስማዒል አል-አሽዐሪይ*፤ ለ 40 አመታት በሙዕተዚላዎች እምነት ውስጥ ከቆዩ በኋላ ያንን በግልፅ በመተው የሰለፎች መንገድ ወደመሰላቸው አካሄድ ፊታቸውን አዞሩ፤ ከዚያም የተለያዩ የቢድዓ መንገዶችን የሚያጋልጡባቸውን መፃህፍት አዘጋጁ፤ ነገር ግን ራሳቸውን ከአህሉ'ስ-ሱን-ናህ የሚቆጥሩት የ"ኢብኑ ኩል-ላብ" ተከታዮች አካሄድ ተፅዕኖ ስር ወድቀው ነበር፤ በጥቅሉ በተለይ በስተመጭረሻ ወደ ሰለፎች አቋም ተመልሰዋል!

(2) "ሪሳላህ ኢላ አህሊ'ሥ-ሠግር" ሊአቢ'ል-ሐሰን አል-አሽዐሪይ፤ ገፅ 133

(3) *አል-ኢማም ዩሱፍ ኢብኑ ዐብዲላህ ኢብኒ ዐብዲ'ል-በር* (368 – 463 ዓ.ሂ)፤ የዘመናቸው ግንባር-ቀደም ሊቅ!፤ *አል-ኢማሙ አዝ-ዘሃቢይ* "ሸይኹ'ል-ኢስላም" ብለው ሰይመዋቸዋል!

«أهل السّنة مُجْمِعُون على الإقرار بالصّفات الواردة كلِّها في القرآن والسنة، والإيمان بها، وحَمْلِها على الحقيقة؛ لا على المجاز، إلا أنهم لا يكيِّفون شيئًا من ذلك، ولا يَحُدُّون فيه صفةً محصورة..»

*«የሱና ባለቤቶች (አህሉ-ስ-ሱን-ናህ) በቁርአንና በሱን-ና የተወሱትን (የአላህ) ባህሪያት በሙሉ በማረጋገጥ፣ በነርሱም በማመን፣ እንዲሁም በዘይቤያዊ ትርጓሜ (መጃዝ) ሳይሆን* ***በቀጥተኛ መልዕክታቸው በመቀበል*** ***በአንድ አቋም ላይ ተሰባስበዋል፤*** *ሆኖም ስለየትኛውም (ባህሪይ) አኳኋን አይገምቱም፤ ይህንንም በተገደበ ገለፃ (ስለአኳኋኑ) አይመጥኑም..!»*[1]

---

**18**- ታዋቂው ዓሊም ***አቡ ሱለይማን አል-ኸጦ-ጣቢ***[2] እና ስመ-ጥሩ የሐዲሥ ጠቢብ ***አል-ኸጢብ አል-በግዳዲ***[1] እንዲህ ይላሉ፡-

(1) "አት-ተምሂድ" ሊ'ብኒ ዐብዲ'ል-በር (7/145)

(2) *ሐምድ ኢብኑ ሙሐመድ ኢብኒ'ል-ኸጦ-ጣብ፣* የሐዲሥና የፊቅህ እውቀቶችን ያጣመሩ ሊቅ፤ በ 388 ዓ.ሂ አርፈዋል። "አል-ጉንያህ ዐኒ'ል-ከላሚ ወአህሊሂ" ስለተሰኘው መፅሀፋቸው *አል-ኢማም ኢብኑ ረጀብ* አውስተው "ይህ ከአብዛኛው መፃህፍታቸው ላይ የሚወሰደውን ከዚህ የተለየና የ"አህሉ'ል-ከላም"ን መንገድ የሚገጥም ንግግራቸውን ትተው እንደተመለሱ ያመላክታል።" ብለዋል። ["ፈትሑ'ል-ባሪ" ሊብኒ ረጀብ (7/237)]

«أما الكلام في الصفات، فإنّ ما رُوي منها في السنن والصحاح؛ مذهبُ السلف –رضوان الله عليهم– إثباتُها، وإجراؤها على ظواهرها، ونفيُ الكيفية والتشبيه عنها. وقد نفاها قوم، فأبطلوا ما أثبته الله سبحانه، وحقّقها من المثبتين قوم، فخرجوا في ذلك إلى ضرب من التشبيه والتكييف. والقصد إنّما هو سلوك الطريقة المتوسطة بين الأمور، ودين الله بين الغالي فيه والمقصِّر عنه.»

***«(የአላህን) ባህሪያት በተመለከተ በ"ሱነን" እና በ"ሲሓሕ" ጥራዞች በተላለፉት እነዚህ ዘገባዎች ዙሪያ የሰለፎች አካሄድ፡- ባህሪያቱን ማፅደቅና ጉልህ መልዕክታቸውን (ተቀብሎ) ማስኬድ፣ እንዲሁም (ዝርዝር ይዘታቸውንና ሁኔታቸውን አስመልክቶ የሚነሳ) የ"እንዴት" ጥያቄንና ማመሳሰልን ውድቅ ማድረግ ነው። አንዳንዶች ጭራሽ መልዕክታቸውን አስተባብለው አላህ ለራሱ ያረጋገጠውን አፍርሰዋል፤ ሌሎች መልዕክታቸውን የተቀበሉ ደግሞ በዚህ ላይ ድንበር በማለፍ ወደ ማመሳሰልና ስለሁኔታቸው ወደ መዘላበድ ወጥተዋል! ሚዛናዊው አካሄድ መካከለኛው ጎዳና ላይ***

---

(1) *አሕመድ ኢብኑ ዐሊይ ኢብኒ ሣቢት፤ ታላቁ የሐዲሥ ጠቢብ፤ ኢብኑ'ስ-ሰምዓኒይ "ያለ ምንም እሰጥ-አገባ የጊዜያቸው ኢማምና ሓፊዝ ነበሩ!" ብለው አወድሰዋቸዋል። በ 463 ዓ.ሂ አረፉ።*

*መጓዝ ነው፤ የአላህ ዲን በፅንፈኛ እና በልግምተኛ መካከል ነው!»*[1]

---

**በጥቅሉ ስለጉዳዩ ሌሎች እልፍ አላፍ ትውፊቶችን ለማየት በርካታ የቀደምት ዑለማዎችን መዛግብት ማመሳከር የሚመከር ነው።**[2]

(1) “መስአላህ ፊ’ስ-ሲፋት” ሊ’ል-ኸጢብ አል-በግዳዲ ገፅ 8፤ “ተዝኪረቱ’ል-ሑፍ-ፋዝ” ሊዝ-ዘሀቢይ (3/1142)፤ “ሲየሩ አዕላሚ’ን-ኑበላእ” (18/283)፤ “አል-ዑሉው” ገፅ 172፣ 185

(2) ለአብነት ያህል፡- “ኸልቁ አፍዓሊ'ል-ዒባድ” ሊ'ል-ቡኻሪይ፣ “አስ-ሱን-ናህ” ሊዐብዲ'ላህ ኢብኒ አሕመድ፣ “አስ-ሱን-ናህ” ሊ’ል-ኸል-ላል፣ “አት-ተውሒድ” ሊ’ብኒ ኹዘይማህ፣ “አት-ተውሒድ” ሊ’ብኒ መንዳህ፣ “አሽ-ሸሪዓህ” ሊ’ል-ኣጁር-ሪይ፣ “አል-ኢባነህ” ሊ’ብኒ በጥ-ጠህ፣ “አስ-ሲፋት” ሊ’ድ-ዳረቁጥኒይ፣ “ሸርሑ ኡሱሊ’ዕቲቃዲ አህሊ’ስ-ሱን-ነህ” ሊ’ል-ላለካኢይ፣ “አል-አስማኡ ወ’ስ-ሲፋት” ሊ’ል-በይሀቂይ.. እና ሌሎችን መጥቀስ ይቻላል።

**ጥቆማ**

ያሳለፍናቸውን ጥቅሶች አስመልክቶ ሁለት ነገሮችን ማለት እወዳለሁ፦

1- እነዚህና ሌሎች የማይሰፈሩ ጥቅሶች የህዝበ-ሙስሊሙ ምርጥ ትውልዶች የአላህ ባህሪያትን ከምንም ነገር ጋር ሳያመሳስሉና ስለሁኔታቸውም ሳይዘባርቁ፡ እንዲሁም ትርጉም-አልባ ሳያደርጉና ቀጥተኛ መልዕክታቸውንም ሳያዛቡ በተገቢው መልኩ ተቀብለው ያፀድቁ እንደነበር በቀጥታ ያረጋግጣሉ![1]
ይህ እውነታ አንዳንድ ቡድኖች ሰለፎች የአላህ ባህሪያት የተወሱባቸው አንቀፆችን ቀጥተኛ መልዕክት የማይቀበሉ ወይም የማያውቁ እንደነበሩ የሚነዙት ባዶ ሙግት ግልፅ ቅጥፈት መሆኑን ያሳያል!

---

(1) ባሳለፍናቸው ዘገባዎች ላይ የተፈለገው የሰለፎች ጥቅል አካሄድ ምን ይመስል እንደነበር በጥቅል መርኋዊ ምሳሌዎች በአጭሩ ማመላከት እንጂ በተለያዩ የአላህ ዝርዝር ባህሪያት ላይ የተናገሩትን ማረጋገጫ ዘገባዎች መሰብሰብ አይደለም (ይህ አጭር ፅሑፍ ነውና!)፤ ዝርዝሩ በተለያዩ የቀድሞ የዐቂዳና የሐዲሥ መዛግብት ላይ በሰነድ የሰፈረና እጅግ የተሠራጨ ነው!
በነገራችን ላይ ሰሓቦች በዚህ ርእስ ላይ የተናገሩት አስተምህሮት ከነርሱ ትውልድ በኋላ ከመጡት ሊቃውንት ንግግሮች ጋር ሲነፃፀር በቁጥር አናሳ የሆነበት ምክንያት በዘመናቸው ይህን ጉዳይ የተመለከቱ ቢድዓዎች ባለመከሰታቸው እርማት ስላላስፈለገ ነው! ያኔማ ሁሉም በንፁህ ልቦና በቁርኣንና በሐዲሥ የተጠቀሱትን የጌታ መገለጫዎች ያለምንም አባዜና አጉል ፈሊጥ ያስተናግዱና ያስተላልፉ ነበር!

→ ይህንን ከሚያጎሉ የታሪክ እውነታዎች መካከል ለዘመናት እንደ ጀህሚይ-ያህ እና ሙዕተዚላህ ካሉ የ"ተዕጢል" ጎራዎች ጋር ያካሄዱት የተፋፋመ የትግል ምዕራፍ ነው፡- ባንድ በኩል እነዚህ ቡድኖችን "ሙዐጥ-ጢላህ" (የአላህን ስሞችና ባህሪያት ከትክክለኛ ትርጓሜያቸው የሚያራቁቱ) ብለው ሲጠሯቸው በሌላ በኩል ደግሞ እነዚያ የጥመት አንጃዎች ዛሬ ወራሾቻቸው እንደሚያደርጉት ሰለፎችን "ሙሸብ-ቢሃህ" (አላህን ከፍጡራን ጋር የሚያመሳስሉ) እያሉ ይወርፏቸው ነበር!

↳ ታዲያ ሰለፎች ባህሪያቱን እንዳሉ የማይቀበሉ ወይም መልዕክታቸውን በጥቅሉም ቢሆን ጭራሽ እንደማያውቁ የሚናገሩ ቢሆኑ ኖሮ ይህን ሁሉ የጦዘ ፍልሚያ ምን አመጣው?! **ለምንስ በተቃራኒው ጎራ "አመሳሳዮች" ተብለው ተዘለፉ?!** ልብ ይበሉ![1]

2- ይህንን የቀድሞዎቹ የሙስሊሙ አርዓያዎችን የአንድነት አቋም በጥቅሉም ይሁን በዝርዝር የሚያፋርስ አንድም ትክክለኛና ግልፅ ዘገባ ከጥንት ጀምሮ አልተገኘም፤ ወደፊትም አይገኝም! **ብዙ የጥመት ተጣሪዎች የሚያጣቅሷቸው ተቃራኒ ዘገባዎች = ወይ ትክክለኛ የሰነድ ቅብብሎሽ የሚጎድላቸው ደካማ ወሬዎች፤ ወይ ደግሞ ጭራሽ የሰነድ ልጓም የሌላቸው ልቅ ቅጥፈቶች ናቸው! ይህ**

(1) ለተጨማሪ ማብራሪያ ሶስተኛውን ጠንቅ አስመልክቶ ያሳለፍነውን ገለፃ ተመልሰው ይመልከቱ!

**ካልሆነ ዘገባዎቹ አስተውሎት ይሹ ይሆናል እንጂ ካመላከትነው መርሆ የወጡ አይደሉም!**

**ልብ ይበሉ! በመፃህፍት ላይ ተፅፎ የተገኘ ሁሉ የተረጋገጠ ዘገባ አይደለም!**

➢ **ታላቁ የኢስላም ሊቅ *ዐብዱ'ላህ ኢብኑ'ል-ሙባረክ*** (181 ዓ.ሂ) **እንዲህ ይላሉ፦**

«الْإِسْنَادُ مِنَ الدِّينِ، وَلَوْلَا الْإِسْنَادُ لَقَالَ مَنْ شَاءَ مَا شَاءَ»

➢ ***«"ኢስናድ" (ሐዲሥ ወይም ሌላ ዘገባ ከአንድ ሰው ወደሌላ የሚተላለፍበት የቅብብሎሽ ሠንሠለት) የዲን አካል ነው፤ "ኢስናድ" ባይኖር ኖሮ ማለት የፈለገ ሁሉ ያሻውን ባለ ነበር!»***

**በተጨማሪም እንዲህ ብለዋል፦**

«بَيْنَنَا وَبَيْنَ الْقَوْمِ الْقَوَائِمُ» – يَعْنِي: الْإِسْنَادَ–.

➢ ***«በኛና በሌሎቹ መካከል (የሚዳኝ) "ኢስናድ" አለ!»***[1]

**በመሆኑም ከላይ የተጠቀሱት ሁሉም ጥቅሶች በግርጌ እንደተመላከተው ወይ ከባለቤቶቹ ከራሳቸው መፃህፍት የተወሰዱ ናቸው፤ ወይ ደግሞ በ"ኢስናድ" ከተዘገቡባቸው ትክክለኛ ምንጮች!**

●●●

(1) ሁለቱም በሶሒሕ ሙስሊም መግቢያ ላይ (1/15) የሰፈሩ ትክክለኛ ዘገባዎች ናቸው!

## ክፍል ሁለት

### የሁለተኛው መርሆ ማብራሪያ

በቁርኣንና በሀዲሥ በቀጥታ ወይም በተዘዋዋሪ ውድቅ የተደረጉ ጉድለቶችን ሁሉ ውድቅ ማድረግ

ከእውነተኛ አምላክ መገለጫዎች አንዱ ከየትኛውም ዓይነት እንከንና ጉድለት የጠራ ፍፁም መሆኑ ነው። የአላህ ስሞችም መቼም ቢሆን ምሉዕነቱን የሚያንፀባርቁ ሲሆኑ ባህሪያቱም በተለያዩ መንገዶች የበላይነቱን ያረጋግጣሉ።

እንዲሁም መለኮታዊ ታላቅነቱን የሚፃረሩ የጉድለት መገለጫዎች ሁሉ ውድቅ መሆናቸውን አሳውቆናል። ፍጡራንን መምሰልን ጨምሮ ከተለያዩ የጉድለት ባህርያት ፍፁም የጠራና የላቀ መሆኑን በተለያዩ የቁርኣን አንቀፆች ነግሮናል።

✸ ታዲያ እዚህ ላይ ማስተዋል የሚሹ ሶስት ነጥቦች አሉ፡-

**አንደኛ፡-** በአብዛኛዎቹ የቁርኣን አንቀፆች የምናስተውለው እውነታ አላህ ለልቅናው የተገቡ ባህሪያቱን በዝርዝር ገለፃዎች ማፅደቁን ሲሆን ለርሱ የማይገቡ የጉድለት ባህሪያትን ግን በደፈናው ወድቅ ማድረጉን ነው።

ከዚህ በስተኋላ ያለው ጥበብ በአዎንታዊ ገለፃዎች መልካም ባህሪያትን መዘርዘር ፍፁምነትንና ምሉዕነትን በማጠናከር ውዳሴን የሚያነባብርና አዳማጩ ላያውቃቸው የሚችሉ የታላቅነት መገለጫዎችንም በተለያዩ መንገዶች የሚያስረዳ መሆኑ ነው።

በአንፃሩም ጭራሽ የሌሉ ዝርዝር እንከኖችን ያለ ምክንያት **በመደርደር** በየተራ ከማፋረስ ይልቅ በጥቅል ገለፃ መጠቀም ይበልጥ ክብርን ያጐላል። እስቲ የሚከተለውን **ምሳሌ** እናስተውል፡-

አንድ ዓለማዊ ንጉስን በአርኪ ገለፃ ለማሞካሸት የፈለገ ተናጋሪ የንጉሱን መልካም ባህሪያት **በመዘርዘር** *«ንጉሳችን አዋቂ፣ አስተዋይ፣ ጀግና፣ ሩህሩህ፣ ፍትሀዊ፣ ታጋሽ፣ ቸር፣ መልከ-መልካም ..ወዘተ ነው!»* ቢል ውዳሴው ያማረ ይሆናል።

እንዲሁም **በጥቅሉ** *«ከዘመናችን ነገስታት እንደርሱ ያለ አይገኝም፣ ስብዕናው ከጉድለት የፀዳ ነው..»* ቢባል ገለፃው የተዋበ ይሆናል።

በአንፃሩ የተለያዩ እንከኖችን በዝርዝር ገለፃ በመደርደር *«ንጉሳችን መሀይም አይደለም፣ እንደ እገሌም ቂል አይደለም፣ አረመኔም አይደለም፣ ሽፍታም አይደለም፣ ኪስ አያወልቅም፣ ሰካራምም አይደለም፣ ቆሻሻም አይደለም፣ መናጢም አይደለም፣ ዱርዬም አይደለም፣ ለልመናም ደጅ አይጠናም፣ በየቤቱም አይልከሰከስም፣ ከለምፅና ከቁምጥና ነፃ ነው፣ እንስሳም አይመስልም፣ ሰይጣንም አይመስልም..»* ቢባል ነገሩ እውነት ቢሆን እንኳ ከማላቅ ወደ ማሳቅ የሚያደላ የአሽሙር ሀተታ ይሆናል።[1]

(1) የኢስላም ስመ-ጥር ሊቃውንትንና ታላላቅ መሪዎችን ገድልና የእምነት ጥንካሬ የሚያወሱ መዛግብትን ስናገላብጥ አንድም ቦታ ላይ *«እገሌ አስካሪ መጠጥን አይጠጣም ነበር፣ አይሰርቅም ነበር፣ አያመነዝርም ነበር..!»* የሚል ሀተታ አናገኝም! ይህ ከግለሰቡ ታላቅነት አንፃር ቀድሞውኑ ሊወሳ =>

ስለሆነም አላህ በቁርኣን ውስጥ በአፍራሽ ገለፃዎች ውድቅ ካደረጋቸው ባህሪያት ይልቅ ለራሱ በአዎንታዊ ገለፃዎች ያረጋገጣቸው መልካም ባህሪያቱ በቁጥር እጅግ የበዙ ናቸው። ይህንን መርሆ ለማረጋገጥ ሁለት ቁርኣናዊ ምሳሌዎችን በመግቢያነት እንውሰድ፡-

**አንደኛው፡-**

قَالَ تَعَالَى: ﴿هُوَ ٱللَّهُ ٱلَّذِى لَآ إِلَـٰهَ إِلَّا هُوَ ۖ عَـٰلِمُ ٱلْغَيْبِ وَٱلشَّهَـٰدَةِ ۖ هُوَ ٱلرَّحْمَـٰنُ ٱلرَّحِيمُ ﴿٢٢﴾ هُوَ ٱللَّهُ ٱلَّذِى لَآ إِلَـٰهَ إِلَّا هُوَ ٱلْمَلِكُ ٱلْقُدُّوسُ ٱلسَّلَـٰمُ ٱلْمُؤْمِنُ ٱلْمُهَيْمِنُ ٱلْعَزِيزُ ٱلْجَبَّارُ ٱلْمُتَكَبِّرُ ۚ سُبْحَـٰنَ ٱللَّهِ عَمَّا يُشْرِكُونَ ﴿٢٣﴾ هُوَ ٱللَّهُ ٱلْخَـٰلِقُ ٱلْبَارِئُ ٱلْمُصَوِّرُ ۖ لَهُ ٱلْأَسْمَآءُ ٱلْحُسْنَىٰ ۚ يُسَبِّحُ لَهُۥ مَا فِى ٱلسَّمَـٰوَٰتِ وَٱلْأَرْضِ ۖ وَهُوَ ٱلْعَزِيزُ ٱلْحَكِيمُ ﴿٢٤﴾﴾ [الحشر: ٢٢ – ٢٤]

➡ «እርሱ አላህ ነው፤ ያ ከርሱ በቀር ሌላ አምላክ የሌለ ፣ ድብቁንና ግልፁን አዋቂ፣ እርሱ በጣም ሩህሩሁና አዛኙ ነው።

እርሱ አላህ ነው፤ ያ ከርሱ በቀር ሌላ አምላክ የሌለ ፤ ንጉሡ፣ ከጉድለት ሁሉ የጠራው፣ የሰላም ባለቤት፣ ደህንነትን ሰጪው፣

---

=> የማይገባ በመሆኑ ያለምክንያት መነገሩ ጭራሽ ጥርጣሬን የሚያጭር ሊሆን ይችላል። ሆኖም በደፈናው «የአላህን ክልከላዎች በፅኑ ይጠነቀቅ ነበር!» ከተባለ ከክብሩ ጋር የሚሄድ ሙገሳ ይሆናል።

(ባሮቹን) ጠባቂው፣ አሸናፊው፣ ኀያሉ፣ ኩሩው! አላህ ከሚያጋሩት (ሁሉ) ጥሩት የተገባው ነው፡፡

እርሱ አላህ ነው፤ ያ ፈጣሪው፣ (ካለምንም) አስገኚው፣ ቅርጽን አሳማሪው! ለእርሱ ከሁሉ የተሻሉ መልካም ስሞች አሉት፤ በሰማያትና በምድርም ያለው ሁሉ እርሱን ያወድሳል፡፡ እርሱም አሸናፊው ጥበበኛው ነው፡፡»[አል-ሐሽር 22-24]

↳ በነዚህ አናቅፅ አላህ ራሱን በተለያዩ የምልዐት ባህሪያትና መጠሪያዎች በዝርዝር የገለፀ ሲሆን ከማንኛውም እንከንና ግድፈት የጠራ መሆኑን የገለፀው ግን **በጥቅሉ** «ከሚያጋሩት ሁሉ ጥሩት የተገባው ነው!» በማለት ነው።

**ሁለተኛው፡-**

📖 قَالَ تَعَالَىٰ: ﴿لَيْسَ كَمِثْلِهِۦ شَىْءٌ ۖ وَهُوَ ٱلسَّمِيعُ ٱلْبَصِيرُ﴾ [الشورى: ١١]

➡ «እንደርሱ ያለ (አምሳያ) ምንም የለም፤ እርሱም ሰሚውና ተመልካቹ ነው፡፡» [አሽ-ሹራ 11]

↳ በዚህ አንቀፅ ላይ አላህ ፍጡራንን እንደማይመስል ሲነግረን *“ይህንን ወይም ያንን አይመስልም!”* የሚል ዝርዝር አላሰፈረም፤ ሆኖም **በጥቅል** ቃል አምሳያ እንደሌለው ተናግሯል። በአንፃሩ ደግሞ ለማንነቱ መገለጫ የሆኑ የምሉእነት ባህሪያቱን ያፀደቀው የልቅና ባህሪያትን ያዘሉ ሁለት **ዝርዝር** ስሞቹን በማውሳት ነው።

በቁርኣን ይህን መሰል **ጥቅል** አፍራሽ ገለፃዎችን በበርካታ ቦታዎች ላይ እናገኛለን፤ ለአብነት ያህልም፡-

📖 قَالَ تَعَالَىٰ:﴿سُبْحَٰنَ رَبِّكَ رَبِّ ٱلْعِزَّةِ عَمَّا يَصِفُونَ﴾[الصافات: ١٨٠]

➥ «ጌታህ - የልሽናፊነት ጌታ- ከሚገልፁት (ሁሉ) ጥራት የተገባው ነው!»[አስ-ሳፍ-ፋት 180]

📖 قَالَ تَعَالَىٰ: ﴿سُبْحَٰنَ ٱللَّهِ عَمَّا يَصِفُونَ ۝٩١ عَٰلِمِ ٱلْغَيْبِ وَٱلشَّهَٰدَةِ فَتَعَٰلَىٰ عَمَّا يُشْرِكُونَ ۝٩٢﴾[المؤمنون: ٩١ – ٩٢]

➥ «አላህ ከሚገልፁት (ሁሉ) ጥራት የተገባው ነው! የድብቁም የግልፁ ዐዋቂ፤ ከሚያጋሩት(ሁሉ) የላቀ ነው!»[አል-ሙእሚኑን 91-92]

📖 قَالَ تَعَالَىٰ:﴿هَلْ تَعْلَمُ لَهُۥ سَمِيًّا﴾[مريم: ٦٥]

➥ «ለርሱ በስሙ ወደር ታውቃለህን?»[መርየም 65]

📖 ﴿وَلَمْ يَكُن لَّهُۥ كُفُوًا أَحَدٌۢ﴾[الإخلاص: ٤]

➥ «ለእርሱም አንድም ብጤ የለውም፡፡»[አል-ኢኽላስ 4]

እነኚህ ሁሉ ቁርኣናዊ ገለፃዎች አላህ ፍጡራንን ከመምሰልና ከሌሎች ጉድለቶችና ግድፈቶች ሁሉ የጠራና የላቀ መሆኑን በጥቅሉ ይገልፃሉ።

ብዙ የጥመት ሰለባዎች ግን ስለአላህ የሚያሰፍሩት ገለፃ የሚያጠነጥንበት መዘውር ይህን ቁርኣናዊ ስልት የተቃረነ ነው፤ *«አላህ እንዲህ አይደለም፣ እንዲያም አይደለም፤ ይህንን*

*አይመስልም፤ ያንንም አይመስልም፤ ከዚህ የጠራ ነው፤ ከዚያም የጠራ ነው…»* የሚሉ የራሳቸውን አሉታዊ ሀተታዎች ያዘወትራሉ፤ ከዚህም ጋር ትክክለኛ ባህሪያቱን የሚያፋርሱባቸውን አሻሚ ገለፃዎችን አያይዘው ይዘረዝራሉ![1] በአንፃሩ የሚዘረዝሯቸው የምሉዕነት መገለጫዎች ካሉ ግን በጣም ጥቂት ናቸው!

በመሠረቱ አላህ ቀድሞውኑ ከፍጡራኑ ጋር በፍፁም የማይነፃፀር በመሆኑ ከግድፈት መገለጫዎች ለማጥራትና ለማላቅ ታስቦ ቢሆን እንኳ ይህ አይነቱን ገለፃ መደርደር ከልዕልናውና ከግርማው ጋር የሚስማማ ስርዓት አይደለም!

✸ ታዲያ *አንዳንድ* ዝርዝር የጉድለት መገለጫዎች ከላይ እንደተጠቆመው ለአላህ እንደማይገቡ በምሳሌነት የተጠቀሱባቸው አንቀፆች መኖራቸው ይህንን አመዛኝ ቁርአናዊ አካሄድ አያፋልስም፤ ምክንያቱም፡-

1- እነዚህ አፍራሽ ገለፃዎች የተውሱት ከላይ እንዳየነው ምሳሌ በአንድ ቦታ ላይ የተደረደሩ የጉድለት ባህሪያትን በየተራ በሚያስተናግድ ሀተታ አይደለም፤ በተለያዩ ቦታዎች ላይ በተለያዩ አገባቦች የሚገኙ ናቸው።

(1) ለምሳሌ፡- *አቡ'ል-ሐሰን አል-አሽዐሪይ «መቃላቱ'ል-ኢስላሚይ-ዪን»* በተባለው መፅሃፋቸው (1/235) ሙዕተዚላዎች ስለጌታቸው የሚሉትን አስመልክቶ ያስተላለፉትን የሚቀፍ ዘገባ ማየት ይችላሉ! በዚሁ መልኩ አንድ የ"አሕባሽ" አስተምህሮት ሰባኪ ፈጣሪን አስመልክቶ ሽታና ጣዕም.. የሌለው መሆኑን በአማርኛ ሲያትት በቪዲዮ ተመልክቻለሁ!

2- እነዚህ ዝርዝር ገለፃዎች የተጠቀሱት ለተገቢ ምክንያቶች ሲሆን በጥበባዊ ሂደትና አገባብ የታጀቡ ናቸው፤ ለአብነት ሁለት ምክንያቶችን እንጥቀስ፡-

2.1- አንዳንድ ከሀዲያን ስለ አላህ የተናገሩትን ቅጥፈት ለማረም፡-

**ለምሳሌ፡-** ልጅ እንደሌለው አጥብቆ ተናግሯል፤ ምክንያቱም የተለያዩ የኩፍር አራማጆች አላህ ልጅ እንዳለው ሞግተዋልና፡-

📖 قَالَ تَعَالَى: ﴿ وَقَالُوا۟ ٱتَّخَذَ ٱلرَّحْمَٰنُ وَلَدًا ﴿٨٨﴾ لَّقَدْ جِئْتُمْ شَيْـًٔا إِدًّا ﴿٨٩﴾
تَكَادُ ٱلسَّمَٰوَٰتُ يَتَفَطَّرْنَ مِنْهُ وَتَنشَقُّ ٱلْأَرْضُ وَتَخِرُّ ٱلْجِبَالُ هَدًّا ﴿٩٠﴾ أَن
دَعَوْا۟ لِلرَّحْمَٰنِ وَلَدًا ﴿٩١﴾ وَمَا يَنۢبَغِى لِلرَّحْمَٰنِ أَن يَتَّخِذَ وَلَدًا ﴿٩٢﴾ ﴾ [مريم: ٨٨ – ٩٢]

➡ «“አር-ረሕማን ልጅን ያዘ” አሉም፤ (ወደ) ከባድ አደጋ በርግጥ መጣችሁ፤ በዚህ የተነሳ ሰማያት ሲሰነጠቁ፣ ምድርም ልትቀደድ፣ ተራሮችም ተንደው ሲወድቁ ይደርሳሉ፤ - ለአር-ረሕማን ልጅን ስለሰየሙ! ለአር-ረሕማንም ልጅ መያዝ አይገባውም!»[መርየም 88-92]

2.2- በቁርኣን የተወሱ የአላህ ምሉዕ ባህሪያትንና ድርጊቶችን በተመለከተ በአንዳንድ ሰዎች ሊታሰብ የሚችልን እንከን ከአዕምሮ አስቀድሞ በማስወገድ ፍፁምነቱን ማፅናት፡-

**ለምሳሌ፡-** ግዙፎቹን ሰማያትና ምድርን መጠበቅ እንደማይከብደው ተናግሯል፡-

📖 قَالَ تَعَالَىٰ: ﴿وَسِعَ كُرْسِيُّهُ ٱلسَّمَٰوَٰتِ وَٱلْأَرْضَ وَلَا يَـُٔودُهُۥ حِفْظُهُمَا﴾ [البقرة: ٢٥٥]

➥ «ኩርሲዩ ከሰማያትና ከምድር የሰፋ ነው፤ ጥበቃቸውም አይከብደውም»[አል-በቀራህ 255]

ፍጡራን አንድን ድርጊት መፈፀም ከቻሉ የሚችሉት በልፋትና በችግር ሊሆን ይችላል፤ ፈጣሪ ግን ከዚህ ሁሉ እንከን የጠራና የላቀ ነው።

3- እነዚህ የግድፈት ባህሪያት ውድቅ ሲደረጉ በተዘዋዋሪ ተቃራኒ ይዘታቸው የሚፀድቅ ስለሚሆን ምሉዕነትን ያመላክታሉ። ይህን መልዕክት ይበልጥ የሚያብራራው ሁለተኛው ነጥብ ነው፡-

ooo

**ሁለተኛ፡-** አላህ ከተለያዩ የጉድለት መገለጫዎች የጠራ መሆኑን ሲነግረን ሁለት ቁም-ነገሮችን በቀጥታ እና በተዘዋዋሪ እንገነዘባለን፡-

**በቀጥታ፡-** ይህ ባህሪ ለአላህ ስለማይገባ ውድቅ መሆኑን፤

**በተዘዋዋሪ ደግሞ፡-** የዚህ ጉድለት ተቃራኒ የሆነው የልቅና ባህሪ ለአላህ እንደሚፀድቅ። ከእንዲህ አይነቱ ገለፃ በዋነኝነት የሚፈለገው መልዕክትም ይኸኛው ነው! "እንዴት?" ማለት ጥሩ!

⮎ የአፍራሽ ገለፃ አላማና ይዘት በቀጥተኛ መልዕክቱ ላይ ብቻ የተገደበ ከሆነ እንደ ውዳሴ አይቆጠርም። ምክንያቱም ንግግሩ

እንዲያመላክት የተፈለገው የባህሪውን አለመኖር ብቻ ከሆነ ኢምንትነትን (አለመኖርን) የሚጠቁም ይሆናል፤ ኢምንትነት ደግሞ ባዶነት እንጂ ምሉዕነት አይደለም!

- በዚህም የተነሳ አንዳንዴ እነኚህ የጉድለት ባህሪያትን **ጭራሽ ሊቀበሉ የማይችሉ** ግዑዝ አካላትም በዚህ መሰል አፍራሽ አረፍተ-ነገር ሊገለፁ ይችላሉ።[1]

**ለምሳሌ፡-** "ይህ ግድግዳ ሰውን አይበድልም!" ቢባል ቃሉ እውነት ከመሆኑ ጋር ገለፃው ውዳሴን አያመለክትም! ምክንያቱም ግድግዳው በመሠረቱ ይህንን ባህሪይ የማስተናገድ ተፈጥሮ ስለሌለው ነው እንጂ የበደል ተፃራሪ የሆነውን ፍትህ የተላበሰ ሆኖ አይደለምና! "ድንጋዩ አያንቀላፋም!" ቢባልም "ንቁ ነው!" ማለት ስላልሆነ እንደዚሁ ልቅናውን አይጠቁምም።

- በተመሳሳይ መልኩም አንድን ጥፋት ለመፈፀም **አቅም የሌለው** አካል "ክፉ አይሰራም!" ማለቱ ብቻ ውዳሴን አያስጨብጥም፤ ምክንያቱም የዚህን እኩይ ድርጊት ተቃራኒ (በጎነት) እንዲያስገነዝብ ታልሞ የተነገረ ስላልሆነ ነው።

(1) ይህንን መርሆ ካመላከቱት ሊቃውንት መካከል ታዋቂው የአል-ኢማም አሽ-ሻፊዒይ ቅርብ ተማሪ የነበሩት አል-ኢማም ዐብዱ'ል-ዐዚዝ ኢብኑ የሕያ አል-ኪናኒ (240 ዓ.ሂ) አንዱ ናቸው፤ "አል-ሐይዳህ ወሊ'ዕቲዛር" የተሰኘውን መፅሀፋቸውን ገፅ 46 ይመልከቱ።

ለምሳሌ፡- “ሌባው የቤተ-መንግስትን ንብረት አይሰርቅም!” ማለት ጨዋነቱን የሚያስረዳ ባለመሆኑ እንደ ውዳሴ አይቆጠርም!

ስለዚህ አላህ ከተለያዩ እንከኖችና የጉድለት መገለጫዎች የጠራ መሆኑን የሚያሳውቅበት ንግግሩ በተዘዋዋሪ የእነዚህ ተፃራሪ የሆኑትን የምሉዕነት ባህሪያቱን የሚያመላክት የውዳሴ ገለፃ ነው። በዚህም መሠረት የድክመት ባህሪን ውድቅ ሲያደርግ የብርታቱን ሃያልነት የሚያፀና ይሆናል፤ ከበደል የጠራ መሆኑን ሲናገርም ፍትሀዊነቱን ያረጋግጣል፤ እንቅልፍም ሆነ ማንገላጀት እንደማይዘው ሲነግረንም የህይወቱን ምሉዕነትና የቁጥጥሩን ብርቱነት ያስገነዝባል፤ እንደማይረሳ ሲነግረንም የእውቀቱን ፍፁምነት ያስታውሳል...!

ይህንን ለመረዳት እነኚህ እውነታዎች የተገለፁባቸውን ቁርአናዊ አንቀፆች አገባብና የአገላለፅ ሂደት ማስተዋል በቂ ነው።

ይህንን እውነታ ያልተረዱ ብዙ ስህተተኞች ግን ከላይ እንደተጠቀመው አላህ የዘረዘራቸውን አብዛኛዎቹን አዎንታዊ መገለጫዎች በመተው የራሳቸውን አፍራሽ ገለፃዎችን በባዶ ይዘት በመደርደራቸው አላህን ያወደሱ ይመስላቸዋል!

ooo

**ሶስተኛ፡-** አላህ ከጉድለት መገለጫዎች ሁሉ የጠራ ነው ሲባል በቁርአንና በመልዕክተኛው አስተምህሮት በዝርዝር ገለጻ ውድቅ የሆኑትን ብቻ ሳይሆን ከዚያ ውጭ ያሉትንም ለርሱ ልቅና የማይገቡ የትኞቹንም የእንከን ባህሪያት እንደሚያካትት ማስተዋል

ያሻል። ምክንያቱም በጥቅሉ ለአላህ የተረጋገጡትን የምልዓት ባህሪያት ማፅደቅ ተቃራኒ የጉድለት መገለጫዎችን ውድቅ ማድረግ ነውና!

ለምሳሌ፡- አለማወቅ ገደብ-የለሽ እውቀቱን እንደሚፃረር፣ ስህተት ፍፁምነቱን እንደሚሽር፣ የበታችነት የበላይነቱን እንደሚቃረን፣ ለቅሶ (የድክመት መገለጫ በመሆኑ) የጌትነት መገለጫውን እንደሚያፋርስ፣ ለመረዳት ብዙ አስተውሎት አይጠይቅም፤ ምክንያቱም ለአላህ የፀደቁትን የምልዐት ባህሪያት የሚፃረር እንከን ሁሉ ለልዕልናው እንደማይገባ ለማወቅ የግድ ዝርዝር መረጃዎች መጠቀስ አያስፈልጋቸውም፤ በዚህ ረገድ የተወረዱት አብዛኛዎቹ አንቀፆች ከላይ እንዳየነው ጥቅል ገለፃዎችን ያዘሉ የመሆናቸው አንደኛው ጥበብ ይህ ነው! ይህ ቁርአናዊ ስልት በቂ በመሆኑ አስፈላጊ ባልሆነበት ሂደት ላይ የጉድለት ባህሪያትን እየደረደሩ በየተራ ውድቅ ማድረጉ ተገቢ ስርዓት አለመሆኑን ከላይ ተረድተናል!

# ክፍል ሶስት

## የሶስተኛው መርሆ ማብራሪያ

በርዕሱ ካይ በቁርኣንና በሐዲሥ ያልተወሱ ቃላትንና ገለፃዎችን መልክታቸውን ሳያጣሩ አለመቀበል

በቁርኣንና በትክክለኛ ሐዲሥ የፀደቁ ቃላትንና ገለፃዎችን እንዳሉ መቀበል የግድ መሆኑ ከላይ ተብራርቷል። እነዚህ ቃላትና ገለፃዎች ምንጊዜም ከእንከን የጠሩ ናቸውና ትርጉማቸውን ወይም መልዕክታቸውን የማያውቅም ሰው ቢሆን አማኝ እስከሆነ ድረስ ያለ ቅድመ-ሁኔታ በመለኮታዊነታቸው ሊቀበላቸው ይገባል!

ይህ ርዕስ ከላይ እንደተወሳው ከፍተኛ ጥንቃቄ የሚሻ በመሆኑ የነብያት እውነተኛ ተከታዮች በተቻላቸው አቅም ስለ አላህ የሚናገሩትን ገለፃ ከቁርኣንና ከሐዲሥ በተወሰዱ ቃላት ላይ ብቻ ለመገደብ ይጥራሉ።

### የቃላት ምድብ

✷ ስለ አላህ የሚነገሩ ገለፃዎችን በተመለከተ በቁርኣንና በሐዲሥ ያልተወሱ ቃላትን በሶስት ደረጃዎች ከፍለን ማየት እንችላለን፦

### ሀ- የማያሻማ መልዕክት ያላቸው ትክክለኛ ቃላት፦

እነኚህ ቃላት በቁርኣንና በሐዲስ የተነገሩትን እውነታዎች የሚገጥሙ እንጂ የሚያፋርሱ ስላልሆኑ አስፈላጊ በሚሆንበት አጋጣሚ በጥቅም ላይ ማዋል ይፈቀዳል! ሆኖም ቃላቱን

**የምንጠቀመው ለማብራሪያነት እንጂ ከአላህ መልካም ስሞችና የላቁ መገለጫዎች በመቁጠር ሂደት አይደለም።**

**ለምሳሌ፡- የአበው ሊቃውንት (ሰለፎች) በዘመናቸው የነበሩት የመጀመሪያዎቹ ጀህሚይ-ያዎች *"አላህ ሁሉም ቦታ ነው!"* የሚል ፈሊጥ ሲያናፍሱ ፈጣሪ ከፍጥረተ-ዓለሙ ውጭ መሆኑን ለመጠቆም *"አላህ ከዐርሹ በላይ ነው፤ ከፍጡራኑም ጭራሽ የተነጠለ ነው!"* (بَائِنٌ مِنْ خَلْقِهِ) በማለት ማረሚያ ያስተላልፉ ነበር።**

**ለአብነት ያህል፡-**

➤ **ታላቁ ኢማም *ዐብዱላህ ኢብኑ'ል-ሙባረክ (181 ዓ.ሂ)* እንዲህ ይላሉ፡-**

«نَعْرِفُ رَبَّنَا – عَزَّ وَجَلَّ– [بِأَنَّهُ] فَوْقَ سَبْعِ سَمَوَاتٍ عَلَى الْعَرْشِ، بَائِنٌ مِنْ خَلْقِهِ بِحَدٍّ، وَلَا نَقُولُ كَمَا قَالَتِ الْجَهْمِيَّةُ: هَهُنَا» – وَأَشَارَ بِيَدِهِ إِلَى الْأَرْضِ–!

***«ጌታችን ከሰባት ሰማያት በላይ በዐርሹ ላይ ሆኖ ከፍጡራኑ በገደብ ጭራሽ የተነጠለ (የተለየ) በመሆኑ እናውቀዋለን፤ "ጀህሚይ-ያዎች" እንደሚሉት እዚህ [ነው] አንልም!»* (በእጃቸው ወደ መሬት እየጠቆሙ)[1]**

(1) "አስ-ሱን-ነህ" ሊዐብዲ'ላህ ኢብኒ'ል-ኢማም አሕመድ (1/111፣ 175፣ 307)፣ "አር-ረድ-ዱ ዐለ'ል-ጀህሚይ-ያህ" ሊ'ድ-ዳሪሚይ ገፅ 47 ፣

- እንዲሁም የቢድዐህ አራማጆች አላህ ከዐርሹ በላይ መሆኑን የሚያረጋግጡ ግልፅ ማስርጃዎችን ማጣመምና መልዕክታቸውን ማዛባት ሲጀምሩ አንዳንድ ታላላቅ ዑለማዎች “አላህ በዛቱ ከዐርሹ በላይ ነው!” በማለት እውነታውን መግለፅ ጀመሩ![1]

✸ ልብ ልንለው የሚገባው እነዚያ ታላላቅ የሰለፍ ሊቃውንት በነዚህ ቃላት የሚያስተላልፉት መልዕክት ግልፅና የታወቀ ከመሆኑ ባሻገር የቁርኣንን ፅኑ መልዕክት ከጥፋተኞች ጥምዘዛ የሚከላከል መሆኑን ነው። ቃላቱ የቀድሞውን ቁርኣናዊ እውነታ ለማፅናት የሚወሱ እንጂ አዲስ መልዕክትን የሚያፀድቁ ባለመሆናቸው በጊዜያቸው ያለአንድም ተቃውሞ ይነገሩ ነበር።

## ለ- ለአላህ የማይገባ መልዕክት የሚያስተላልፉ ቃላት፡-

ከዚህ በፊት እንደተገለፀው እነደነዚህ አይነት ስለፈጣሪ የግድፈት መልዕክትን በቀጥታም ይሁን በተዘዋዋሪ የሚያስተጋቡ ቃላትን በፍፁም መጠቀም እንደማይቻል ጥርጥር የለም።

---

“አል-አስማኡ ወ’ስ-ሲፋት” ሊ’ል-በይሀቂይ (2/169) እና በሌሎችም መዛግብት ላይ በትክክለኛ ሰነድ ተላልፏል።

(1) ለአንዳንድ ምሳሌዎች “አል-ዑሉው” ሊ’ዝ-ዘሀቢይ ገፅ (235-236) ይመልከቱ። “ዛት” (ذات) የሚለው ቃል በመሰል አገባቦቹ የሚወክለው መልዕክት የአንድ ነገር ህልውና በተጨባጭ የሚረጋገጥበት ገሀዳዊ መለያ ነው! ብዙዎች እንደሚያደርጉት “ዛት”ን በ“አካል” መተርጎም መልዕክቱን ማጥበብ ይሆናል!

**ሐ- እውነትም ስህተትም ሊተላለፍባቸው የሚችሉ አሻሚና መጤ ቃላት፡-**

የላይኛው መርሆ ማብራሪያ የሚያጠነጥነውም እነዚህን ቃላት አስመልክቶ ሙስሊሞች ሊኖራቸው በሚገባው ትክክለኛ አቋም ዙሪያ ነው።

አብዛኛዎቹ የ“ተዕጢል” ጐራዎች ብዙሃኑ ሙስሊሞች የአላህ ባህሪያትን በትክክል እንዳያረጋግጡ ለማገድ የሚነዟቸው አሻሚ ቃላት ያሉ ሲሆን ከነሱም መካከል፡- “ጂስም” (جِسْم)፣ “ጂሃ” (جِهَة) “ጀውሀር” (جَوْهَر)፣ “ዐረድ” (عَرَض).. እና ሌሎችም ይገኛሉ።[1]

እዚህ ላይ ሊያስተውሉት የሚገባው ለነኚህ ቃላት ከቋንቋዊ መልዕክቶቻቸው ባሻገር የሚሰጧቸው ፍልስፍናዊ ትርጓሜዎች መኖራቸውን ነው! በዚህም መሠረት እነርሱን ውድቅ በማድረግ ሊያፋርሱ የሚፈልጉት አንዳንድ የዋሆች እንደሚያስቡት ለአላህ የማይገቡ ጉድለቶችን ሳይሆን ራሱን የገለፀባቸውን ባህሪያቱን ነው።

ታዲያ ገለፃዎቹን አስመልክቶ ጥቅል ቁርአናዊና ሐዲሣዊ ማስረጃዎች የሚጠቁሙትና የህዝበ-ሙስሊሙ አርዓያ የሆኑት ቀደምት የኢስላም ትውልዶችና ምሁራን የተጓዙበት የሐቅ ጎዳና የሚከተለው ነው፡-

(1) ከነዚህ ስያሜዎች ጋር የተያያዘ ትንታኔ በምዕራፍ ሁለት ላይ ይመጣል!

1- ስለአላህ ይህን መሰል ቃላትን በአዎንታዊም ይሁን በአፍራሽ ገለፃ ከመጠቀም ፍፁም መቆጠብ

2- እነኚህን ቃላት በአዎንታዊ ወይም በአፍራሽ ገለፃ የሚያወሳ ተናጋሪ ሲያጋጥመን የተፈለገበትን መልዕክት ማጣራት፡-

- ትክክለኛና ተገቢ መልዕክትን አስቦ ከሆነ ትክክለኛውን **መልዕክት** ተቀብለን (በሌላ ሸሪዓዊ ገለፃ) ማፅደቅ፤

- የታሰበው መልዕክት ስህተት ከሆነ ደግሞ ውድቅ ማድረግ!

- ሀሳቡ ትክክለኛና ትክክለኛ ያልሆነ መልዕክትን የቀላቀለ ከሆነ ደግሞ ሁለቱን ለይቶ ትክክለኛውን **መልዕክት** (በሌላ ሸሪዓዊ ገለፃ) ማፅደቅና ትክክለኛ ያልሆነውን መልዕክት ውድቅ ማድረግ![1]

አዎን! በዚህ አደገኛ ርዕስ ላይ ይህን መሰል መጤ ቃላትን በደፈናው መቀበል ወይም መቃወም የማንም **ግዴታም መብትም** አይደለም!

---

(1) ታዲያ አንድ ሰው ይህንን ዝርዝር በአግባቡ የሚተገብርበት በቂ እውቀት የሌለው፣ ወይም ያለበት ጊዜና ሁኔታ የማይፈቅድለት፣ አሊያም ዝርዝር ውስጥ መግባቱ ከጥቅሙ ጉዳቱ የሚያመዝን ከሆነ ይህንን ቃል ለማፅደቅም ይሁን ለመቃወም መረጃ ባለመኖሩ እንደሚቆጠብ አሳውቆ የእሰጥ-አገባውን በር መዝጋት አለበት።

በአንፃሩ በእንዲህ አይነት ቃላትና ገለፃዎች እውነታን ለመመዘንና ሙስሊሞችንም ለመፈተን መሞከር ሁሌም ውዥንብርና ክርክር የሚያስከትል አዲስ የፈጠራ ስልት ነው፤ የሙስሊም ጥሪ ወደ ቁርኣናዊና ሀዲሣዊ መለኮታዊ እውነታዎች እንጂ ወደሚያምታቱ ፍልስፍናዊ ገለፃዎች መሆን የለበትም፤ በእምነት ጉዳይ ላይ የሚነሱ ውዝግቦች የሚቋጩት ሁሉም በሚያምንበት የበላይ ፍርድ ብቻ ነውና!

ሰለፎች እነኚህን መሰል ቃላት በዚህ ረገድ የሚጠቀሙ ሰዎችን ያወግዙና በዚህ ተግባራቸው ብቻ ከሱን-ናህ ጎራ የወጡ የቢድዓ ሰዎች እንደሆኑ ይፈርዱ ነበር።(1)

ነገር በምሳሌ

በዚህም መሠረት አላህን በተመለከተ “ጂስም”(2) «ነው!» ወይም «አይደለም!» ብሎ መናገሩ የተከለከለ ነው። ምክንያቱም

(1) “ደርኡ ተዓሩዲ’ል-ዐቅሊ ወን-ነቅል” (1/254)

(2) “ጂስም” (جِسْم) በተለመደው የዐረብኛ ልሳን “ሰውነት” ማለት ሲሆን ብዙ ቀደምት የቋንቋ ሊቆች በመዝገበ-ቃላት ላይ የሚያስተላልፉትም ይህንኑ መልዕክት ነው። ሆኖም “አላህ ጂስም አይደለም” የሚል ፈሊጥ የሚያናፍሱት የፍልስፍና ባለቤቶች ይህንን ቃል በዚህ መልኩ አይደለም የሚተረጉሙት! እንዲያውም ቃሉ የሚሰጠውን ፍልስፍናዊ ትርጓሜ በተመልከተ እርስ በርሳቸው ይወዛገባሉ! *አቡ’ል-ሐሰን አል-አሽዐሪይ* “መቃላቱ’ል-ኢስላሚይ-ዪን” በተሰኘው መፅሀፋቸው (2/4-8) አስራ ሁለት የተለያዩ አቋሞችን ጠቅሰዋል! አብዛኛዎቹ በዚህ ስያሜ ስር ተጨባጭ ቁስ አካላትን ብቻ ሳይሆን መገለጫ ባህሪያትን የሚያስተናግዱ እንደ =>

**በየትኛውም የቁርአን አንቀፅና የነብዩ አስተምህሮት ላይ እንዲሁም በመጀመሪያዎቹ ቀና ትውልዶች አንደበት ይህ ቃል በአዎንታዊም ሆነ በአፍራሽ ገለፃ ለአላህ መገለጫ ሆኖ ከቶም አልተወሳምና!**

ስለሆነም *«"ጂስም" ነው!»* የሚል ተናጋሪ ከቃሉ ኋላ ያሰበው መልዕክት፡-

**- እንደፍጡራን አይነት የአካል ግንባታ** ከሆነ ለአላህ የማይገባ በመሆኑ ውድቅ ይሆናል! በተለያዩ የቁርአንና የሐዲሥ አስረጆች የተረጋገጡትን የአላህን ባህሪያት ማፅደቅ ግን በፍፁም ይህንን መልዕክት አያስገነዝብም፤ ወደዚህም አያመራም፤ የአላህ ባህሪያትና መገለጫዎች ለርሱ ተገቢ የሆኑት ከፍጡራን ፍፁም በተለየና ለርሱ ልቅና በሚገባ ሁኔታ ብቻ ነውና!

- (ያሰበው) **የአላህ ህልውና የሚረጋገጥበትንና የሚለይበትን "ዛት"** ከሆነ ደግሞ (መልዕክቱ) ተቀባይነት ያገኛል! መቼም አላህ "ዛት" እንዳለው ሁሉም ይስማማል!

**ምንም ቢሆን ግን ገለፃው ስህተት ነው!**

---

=> ውሃ፣ አየር፤ ብርሃን እና እሳት ያሉ ሊታዩ የሚችሉም ይሁኑ የማይችሉ ገህዳዊ ግኝት ያላቸውን ነገሮችን ሁሉ ያካትታሉ! ስለሆነም "አላህ ጂስም አይደለም!" በሚለው መፈክር ሽፋን የሚያራምዱት አቋም የአላህን ገህዳዊ ህልውና መግፈፍ ነው! ተጨማሪ ማብራሪያ ወደ ፊት ይመጣል!

በዚሁ ዝርዝር መሠረት «"ጂስም" አይደለም!» የሚል ተናጋሪን እናስተናግዳለን! ገለፃው ግን አሁንም ስህተት ነው! በፍልስፍና የታነፁ ተናጋሪዎች የሚያራቡት የውዥንብር ቃል!

➢ *አል-ኢማም አሕመድ* በእስር ላይ እያሉ የተከራከሯቸውን "ጀህሚይ-ያዎች" አስመልክቶ እንዲህ ይላሉ፡-

«ولقد احتجُّوا بشيء ما يَقْوى قلبي ولا ينطق لساني أن أَحكيَه، وأنكروا الرواية والآثار، وما ظننتهم على هذا حتى سمعتُ مقالتهم، ولقد جَعل برغوث يقول لي: الجسم كذا وكذا، وكلاما هو الكفر بالله العظيم، فجعلت أقول: ما أدري ما هذا، إلا أني أعلم أنه أحدٌ صمد، لا شِبه له ولا عِدل، وهو كما وصف نفسه، فسكت عني!»

*«(ከአስከፊነቱ የተነሳ) ላስተላልፈው ልቤ በማያስችለውና ምላሴም በማይታዘዝልኝ (የፍልስፍና) መረጃ ሞገቱኝ! ሐዲሦችንና ዘገባዎችን አስተባበሉ፤ ንግግራቸውን እስክሰማ ድረስ በዚህ መልኩ አልገምታቸውም ነበር! 'ብርቹሥ' (የተባለው) "ጂስም፤ እንቶ ፈንቶ.." እያለኝ በታላቁ አላህ እንደመካድ የሚቆጠር ንግግር መናገር ጀመረ! እኔም "ይህ ምን እንደሆነ አላውቅልህም፤ ነገር ግን እርሱ (አላህ) አንድዬና "ሰመድ" (የሁሉ መጠጊያ)፤ አምሳያም ሆነ አቻ የሌለው መሆኑን አውቃለሁ፤ እርሱም ራሱን እንደገለፀው ነው.." ማለት ያዝኩኝ! ከዚያም ዝም አለኝ»*[1]

---

(1) "ዚክሩ ሚሕነቲ'ል-ኢማሚ አሕመድ" ሊሐንበል ኢብኒ ኢስሓቅ ገፅ 52፤ "አል-ኢባናህ" ሊ'ብኒ በጥ-ጠህ" (2/253)፤ "አል-ቢዳያህ ወ'ን-ኒሃያህ" ሊ'ብኒ ከሢር (14/201)

በጥቅሉ የሀቅ ባለቤቶች በቁርኣንና በሐዲሥ መረጃዎች የተረጋገጡ ባህሪያትን ያፀድቃሉ፤ በቁርኣንና በሐዲሥ በቀጥታም ይሁን በተዘዋዋሪ ውድቅ የተደረጉትን ውድቅ ያደርጋሉ፤ በዝምታ የታለፉትን ደግሞ በዝምታ ያልፋሉ፤ ሲያፀድቁም በእውቀት፣ ሲያስተባብሉም በእውቀት! የእውነተኛ አማኝነትና ተከታይነት ምልክት ይሄ አይደለምን?!

**ሸብር!**

**እዚህ ላይ ልብ ሊሉት የሚገባ ነጥብ አለ፡- በቁርኣንና በሀዲሥ የተረጋገጡትን የጌታ ባህሪያት በሚያጠራጥር ወይም በሚያሳቅቅ ቃል መግለፅ እውነታውን አይቀይረውም!**

➤ ***አል-ኢማም አሕመድ*** **እንዲህ ብለው ነበር፡-**

«..وَلَا نُزِيلُ عَنْهُ صِفَةً مِنْ صِفَاتِهِ لِشَنَاعَةٍ شُنِّعَتْ.. »

***“የሚፀየፍ ተፀይፎ ስላወገዘ (ብለን) ከባህሪያቱ አንዱንም አናስወግድም!”***[1]

**በ"ተዕጢል" አቀንቃኞች ንግግር ላይ *“አላህ ለራሱ ያፀደቃቸውን ባህሪያት አንቀበልም!”* የሚል ቀጥተኛ የማስተባበያ ገለፃ ላይገኝ ይችላል! ሆኖም አብዛኛውን ጊዜ ለዚህ ዓላማ መንገዱን**

(1) “አል-ኢባና” ሊ’ብኒ በጥ-ጠህ (3/326)፣ “ዘም-ሙ’ት-ተእዊል” ሊ’ብኒ ቁዳማህ፤ ገፅ 22

የሚደለድሉት ባህሪያቱን ያለ አደብ በተለያዩ ቅፅላዎች እየጠሩ እውነታውን በማድበስበስ ነው[1]:-

እንደመስማትና ማየት ያሉትን ባህሪያቱን «አዕራድ» (أَعْرَاض) ይሏቸዋል፣ እንደ ፊትና እጅ ያሉትን «አዕዷእ» (أَعْضَاء) ወይም «ጀዋሪሕ» (جَوَارِح) ብለው ይሰይሟቸዋል፣ እንደ ንግግር ያሉ ሲፈልግ የሚፈፅማቸውን አድራጎቶች ደግሞ «ሐዋዲሥ» (حَوَادِث) ሲሉ ይጠሯቸዋል፣ "አስቲዋእ"ን (በዐርሹ ላይ መሆኑን)ና ከፍጥረተ ዓለሙ በላይ መሆኑን «ተሐይ-ዩዝ» (تَحَيُّز) ይሉታል፣ ከውሳኔውና ድርጊቱ ኋላ ያሉትን ጥበቦችና ዓላማዎች «አግራድ» (أَغْرَاض) ናቸው ይላሉ...!

በዚህ ላይ ደግሞ እነዚህን ቃላትና መሰሎቻቸውን በተምታታ ፍልስፍናዊ ይዘታቸው እንጂ በመሠረታዊው ቋንቋዊ መልዕክታቸው አይተረጉሟቸውም፣ እንደዚያም ሆኖ የአላህ ባህሪያትን ከማመሳሰል በፀዳ ግንዛቤ በቁርኣንና በሐዲሥ እንደተገለፁት የሚቀበሉትን የሐቅ ባለቤቶችን *"አላህን በነዚህ አሸማቃቂ መገለጫዎች ይገልፃሉ!"* እያሉ በቅጥፈት ይወርፋሉ!

(1) «ሊበሏት ያሰቧትን አሞራ 'ጅግራ' ይሏታል»!

➢ ***አል-ኢማም ዑሥማን ኢብኑ ሰዒድ አድ-ዳሪሚይ***[1] **ይህንን ውዥንብር ያስፋፋ ለነበረ አንድ የጀህሚይ-ያህ አቀንቃኝ ምላሽ ሲሰጡ እንዲህ ይላሉ፡-**

«..وَأَمَّا دَعْوَاكَ أَنَّهُمْ يَقُولُونَ: جَارِحٌ مُرَكَّبٌ؛ فَهَذَا كُفْرٌ، لَا يَقُولُهُ أحدٌ من الْمُسلمين! وَلَكنَّا نُثْبِتُ لَهُ السَّمْعَ وَالْبَصَرَ وَالْعَيْنَ بِلَا تَكْيِيفٍ، كَمَا أَثْبَتَهُ لِنَفْسِهِ فِيمَا أَنْزَلَ مِنْ كِتَابِهِ، وَأَثْبَتَهُ لَهُ الرَّسُول، وَهَذَا الَّذِي تُكَرِّرُهُ مَرَّةً بَعْدَ مَرَّةٍ: "جَارِحٌ، وَعُضْوٌ.." وَمَا أَشْبَهَهُ؛ حَشْوٌ وَخُرَافَاتٌ، وَتَشْنِيعٌ لَا يَقُولُهُ أَحَدٌ مِنَ الْعَالَمِينَ! وَقَدْ رَوَيْنَا رِوَايَاتِ السَّمْعِ وَالْبَصَرِ وَالْعَيْنِ فِي صَدْرِ هَذَا الْكِتَابِ بِأَسَانِيدِهَا وَأَلْفَاظِهَا عَنْ رَسُولِ اللَّهِ - صَلَّى اللَّهُ عَلَيْهِ وَسَلَّمَ-، فَنَقُولُ كَمَا قَالَ، وَنَعْنِي بِهَا كَمَا عَنَى، وَالتَّكْيِيفُ عَنَّا مَرْفُوعٌ، وَذِكْرُ "الْجَوَارِحِ وَالْأَعْضَاءِ" تكلّف مِنْك، وتشنيع!»

***«..(አህሉ'ሱን-ናህ ስለአላህ ባህሪያት) "የተገጣጠመ አካል.." እንደሚሉ መሞገትህን በተመለከተ ደግሞ ይሄማ ከሙስሊሞች መካከል አንዱም የማይናገረው ኩፍር (ክህደት) ነው! ነገር ግን መስማትን፣ ማየትን፣ አይንን.. እርሱ ራሱ ባወረደው መፅሀፍ ለራሱ እንዳረጋገጠውና መልዕክተኛውም (ﷺ) እንዳፀደቁለት ስለ***

(1) *ዑሥማን እብኑ ሰዒድ አድ-ዳሪሚይ፤* ታላቁ የሱን-ናህ ኢማም፡ ከአል-ኢማም አህመድና ከሌሎች ታላላቅ ኢማሞች የሀዲስን ዘርፈ-እውቀት የቀሰሙ የዘመናቸው ተቀዳሚ ዓሊም ነበሩ። *አቡ'ል-ፈድል አል-ጃሩዲ* "በህይወትም እያለ ከሞተም በኋላ በአርዓያነቱ የሚከተሉት ተምሳሌት ነው!" ብለው አወድሰዋቸዋል! *ያረፉት* በ 280 ዓ.ሂ ነው።

*ሁኔታው ሳናነሳ እናፀድቅለታለን! ይህ በየጊዜው የምትደጋግመው “ጃሪሕ፣ ኡድው..” እና የመሳሰለው ገለፃ በዓለም ማንም የማይናገረው ፍሬ-ቢስ ሀተታ፣ የማይመስል ተረትና (ስም ለማጥፋት የምታጋንንበት) ማሸማቀቂያ ነው! በዚህ መፅሀፍ መጀመሪያ ላይ መስማት፣ ማየትና አይንን (ለአላህ) የሚያረጋግጡ ዘገባዎችን ከነሰነዳቸውና ከነቃላታቸው ከአላህ መልዕክተኛ አስተላልፈናል! እናም እርሳቸው እንዳሉት እንላለን፤ በገለፃዎቹ የፈለጉትንም መልዕክት እንፈልጋለን! ስለሁኔታው ማንሳት ከኛ የማይጠበቅ ነው! “ጀዋሪሕ” እና “አዕዷእ”ን ማውሳት ደግሞ ያንተ ፀጉር ስንጠቃና ማሸማቀቂያ ነው!»*(1)

አዎን! ጉዳዩን በጥልቅ የማይረዱ ሙስሊሞችን ለማደናገርና የአላህን ባህሪያት እንዳያፀድቁ ለማስበርገግ የሚጠቀሙባቸው የሽብር ስያሜዎች!

﴿ إِنْ هِيَ إِلَّآ أَسْمَآءٌ سَمَّيْتُمُوهَآ أَنتُمْ وَءَابَآؤُكُم مَّآ أَنزَلَ ٱللَّهُ بِهَا مِن سُلْطَٰنٍ ۚ إِن يَتَّبِعُونَ إِلَّا ٱلظَّنَّ وَمَا تَهْوَى ٱلْأَنفُسُ ۖ وَلَقَدْ جَآءَهُم مِّن رَّبِّهِمُ ٱلْهُدَىٰٓ ﴿٢٣﴾ أَمْ لِلْإِنسَٰنِ مَا تَمَنَّىٰ ﴾... [النجم: ٢٣ – ٢٤]

(1) “ነቅዱ ዑሥማን ኢብኒ ሰዒድ ዐላ ቢሽር አል-መሪሲ አል-ዐኒድ” ሊ’ድ-ዳሪሚይ (2/679)

➥ «እነኚህ እናንተና አባቶቻችሁ የሰየማችኋቸው ስያሜዎች እንጂ (ሌላ) አይደሉም፤ አላህ በነርሱ (ተጨባጭነት ላይ) ምንም ማስረጃ አላወረደም! ከጌታቸውም በርግጥ ምሪቻ መጥቶላቸው ሳለ ጥርጣሬንና ነፍሶች የሚዘነበሉለትን እንጂ ሌላ አይከተሉም፤ ወይስ ለሰው የተመኘው (ሁሉ) አለው?!..»[አን-ነጅም 23-23]

# ምዕራፍ ሁለት

- እውነቱን የሳቱት ቡድኖች
- ውዥንብሮችና እርማቶች
- የጥሠቱ እውነተኛ ሠነሻዎች
- ማስተካከያ መርሆዎችና ምሳሌዎች

## መግቢያ

## ጠርዘኞቹ!

ከላይ የተብራራው ፍንትው ያለ የሐቅ ጎዳና አንዱ መገለጫ ሚዛናዊነቱና መካከለኝነቱ መሆኑን አውቀናል። ከዚህ ነብያዊ ፋና ያፈነገጡ በርካታ አንጃዎች ያሉ ሲሆን በዋነኝነት ሁለት ዓይነት ጠርዘኛ ምድቦች ውስጥ ይካተታሉ፡-

**ምድብ አንድ**፡- አላህን ከፍጡራን ጋር የሚያመሳስሉ፤

**ምድብ ሁለት**፡- የአላህን ባህሪያት በከፊል ወይም በሙሉ የሚያፋርሱ።

የነዚህ ጠርዘኛ ምድቦች ዋነኛ መገለጫ በመጀመሪያው መርሆ ማብራሪያ ላይ እንደተዘረዘረው የሀቅ ባለቤቶች አበክረው የሚጠነቀቋቸውን አራት አፍራሽ ጠንቆች በተለያዩ መፈክሮች በመከለል ማራመዳቸው ነው! የመጀመሪያዎቹ ጥመት በጥቅሉ የሚዞረው በመጀመሪያዎቹ ሁለት ጠንቆች ("ተክዪፍ"ና "ተምሢል") ዛቢያ ላይ ሲሆን የሌሎቹ ደግሞ በተቀሩት ሁለቱ ("ተዕጢል"ና "ተሕሪፍ") ላይ ነው።

ሁለቱም ተቃራኒ ምድቦችን ለዚህ አስከፊ መዘዝ የዳረጓቸው መነሻዎችና ብዥታዎች አሉ፤ እያንዳንዱን ከመሠረቱ ፈንቅለው የሚጥሉ በርካታ አጥጋቢ ምላሾችም አሉ፤ ዋና ዋናዎቹን እንደሚከተለው እናያቸዋለን።

○○○

# ክፍል አንድ

## ምድብ አንድ

### አላህን ከፍጡራን ጋር የሚያመሳስሉ

ፈጣሪን በአንዳንድ ባህሪያት ከፍጡር ጋር የሚያመሳስሉ ጭፍራዎች በኢስላም ታሪክ ብቅ ብለው ነበር። የኢስላም ሊቃዉንት "ሙሸብ-ቢሀ" (مشبِّهة) ወይም "ሙመሥ-ሢላህ" (ممثِّلة) በሚል ስያሜ ስር ያጠቃልሏቸዋል።[1]

---

(1) ከነርሱም መካከል የሚከተሉት ይገኙበታል፦

*አል-ጀዋሪቢይ-ያሁ፦ የዳዉድ አል-ጀዋሪቢይ ተከታዮች ናቸው። "ጌታ በሰው ቅርፅ ያለ ነው! ከሁለት ነገሮች በስተቀር ሁሉም የሰው አካላት አሉት.."!!* እያለ በሚዘገንን መልኩ ይዘረዝር ነበር! አላህ የስራውን ይስጠው!

*አል-ከራሚይ-ያሁ፦ የሙሐመድ ኢብኑ ከር-ራም አስ-ሰጅስታኒ* ተከታዮች ሲሆኑ አስራ ሁለት የሚሆኑ የተለያዩ አንጃዎች ናቸው። "አላህ ከዐርሹ በላይ ያልለበት ሁኔታ እንዲህ ነው፣ እንዲያ ነው.." እያሉ በመዘላበድ ይታወቃሉ!

*አል-ሂሻሚያሁ፦ የሂሻም ኢብኑ'ል-ሐከም* ተከታዮች ናቸው። ስለ-አላህ የተለያዩ የኩፍር ንግግሮችን በመቀባዠር የታወቀ ነበር፤ *"ርዝመቱ፣ ጎኑና ጥልቀቱ እኩል ነው..!"* ይል ነበር!

ሌሎች ተመሳሳይ ቡድኖችም በታሪክ አልፈዋል። ንግግሮቻቸውም በተለያዩ የታሪክ ማህደራት ሰፍረዋል።

**የእነዚህ ጭፍራዎችና የመሰሎቻቸው ጥፋት በአብዛኛው ከሚከተሉት ሶስት ነጥቦች አይወጣም፡-**

**1- ባህሪያቱን ከፍጡራን ባህሪያት ጋር ማመሳሰል፡-**

**⤷ በዚህም አቋማቸው ከላይ ከተወገዙት አፍራሽ ጠንቆች ሁለተኛውን (ተምሢል) ይተገብራሉ!**

➢ ***አል-ኢማሙ አሕመድ*** **እንዲህ ብለዋል፡-**

«الْمُشَبِّهَةُ تَقُولُ: بَصَرٌ كَبَصَرِي، وَيَدٌ كَيَدِي، وَقَدَمٌ كَقَدَمِي، وَمَنْ قَالَ ذَلِكَ فَقَدْ شَبَّهَ اللَّهَ بِخَلْقِهِ»

***«ሙሸብ-ቢሃዎች "እንደኔ አይነት ማየት፣ እንደኔ አይነት እጅ፣ እንደኔ አይነት እግር.." ይላሉ! እንደዚያ ያለ ሰው አላህን ከፍጡራኑ ጋር አመሳስሏል!»***(1)

**2- የአላህን ባህሪያት ሲያፀድቁ ወሰን በመተላለፍ የባህሪያቱን ሁኔታና ዝርዝር ይዘት አስመልክቶ እንደመሰላቸው መዘላበድ፡-**

**⤷ በዚህ ተግባራቸው የመጀመሪያውን ጠንቅ (ተክዪፍ) በቀጥታ ይፈፅማሉ!**

**3- በቁርኣንና በሐዲስ ጭራሽ ያልተወሱ ባህሪያትንና መገለጫዎችን ለአላህ መስጠት፡-**

(1) "ኢብጣሉ'ት-ተእዊላት ሊአኽባሪ'ስ-ሲፋት" ሊ'ል-ቃዲ አቢ የዕላ (1/43)፣ "አል-ኢባናህ" ሊ'ብኒ በጥ-ጦህ (3/326)

⮎ በዚህም ሂደታቸው የሶስቱን መሰረታዊ መርሆዎች መልዕክት ይፃረራሉ!

እነዚህ አንጃዎች ግኝታቸው እየተመናመነ ከመሄዱም በላይ ጥመታቸው ግልፅ በመሆኑ አብዛኛው የሙስሊም ህብረተሰብ በአባዜያቸው የመለከፉ እድል አናሳ ነው። ማንኛውም የንፁህ አእምሮ ባለቤት በዓለማቱ ፈጣሪ ሀያሉ አምላክና በፍጡራኑ መካከል ምንም አይነት የባህሪይ አንድነት ሊኖር እንደማይችል ያለአስተማሪ ይረዳል! ስለዚህ ስህተታቸውን ለማስረዳት ብዙ ማብራሪያዎች መደርደሩ እምብዛም አስፈላጊ ላይሆን ይችላል። ሆኖም ለብዥታቸው መነሻዎች ከሆኑት ምክንያቶች ዋነኛውን ጠቅሰን ማረሚያውን እናስከትል።

**ብዥታ**

- *«የአላህ ቁርኣን ሰዎች በሚገነዘቡት ቋንቋ የወረደ በመሆኑ ስለራሱ የነገረንን ሁሉ በገሀዱ ዓለም በምናየው (በፍጡራን) ይዘት መተርጎም አለብን።»* አሉ!!

**መልሶች**

ይህ ሙግት በበርካታ መንገዶች አጥጋቢ ምላሽ ይሰጠዋል፤ ሆኖም ሶስት ምላሾችን ብቻ ባጭሩ እንመልከት፦

**አንደኛ፦** አላህ በቁርኣኑ ሰዎች በሚገነዘቡት ቋንቋ ራሱን እንደገለፀው ሁሉ በዚያው ቁርኣኑና በዚያው ግልፅ ቋንቋ ጭራሽ አምሳያ እንደሌለውም ነግሮናል!

📖﴿لَيۡسَ كَمِثۡلِهِۦ شَيۡءٞۖ وَهُوَ ٱلسَّمِيعُ ٱلۡبَصِيرُ﴾[الشورى: ١١]

➡ «እንደርሱ ያለ (አምሳያ) ምንም የለም፤ እርሱም ሰሚውና ተመልካቹ ነው፡፡»[አሽ-ሹራ 11]

📖﴿وَلَمۡ يَكُن لَّهُۥ كُفُوًا أَحَدُۢ﴾[الإخلاص: ٤]

➡ «ለእርሱም አንድም ብጤ የለውም፡፡»[አል-ኢኽላስ 4]

📖﴿هَلۡ تَعۡلَمُ لَهُۥ سَمِيّٗا﴾[مريم: ٦٥]

➡ «ለርሱ በስሙ ወደር ታውቃለህን?»[መርየም 65]

➢ ***ኢብኑ ዐብ-ባስ*** (رضي الله عنه) **ይህን አንቀፅ ሲያብራሩ እንዲህ ይላሉ:**

« هل تعلم للربّ مِثلًا أو شبيهًا ؟!»

***“ለጌታ አምሳያ ወይም ቢጤን ታውቃለህን?”***(1)

**ሁለተኛ፡-** **በገሀዱ ዓለም ከምናያቸው ተጨባጭ እውነታዎች አንዱ ፍጡራን ራሳቸው በብዙ ጥቅል መጠሪያዎች በስም ደረጃ ሊጋጠሙ ቢችሉም በይዘትና በአኳኋን መለያየታቸው ነው። ታዲያ የባህሪያት ጥቅል ስያሜ መገጣጠም በፍጡራን መካከል እንኳ የይዘትንና**

(1) “ተፍሲሩ’ጥ-ጦበሪ” (18/226)

የሁኔታን አንድነት ወይም መመሳሰል የሚያመላክት ካልሆነ እንዴት የፈጣሪና የፍጡር መመሳሰልን ያመላክታል?![1]

**ሶስተኛ፡-** ፈጣሪ በፈጣሪነቱ ከፍጡራን ጭራሽ የሚለይ ስለሆነ ባህሪያቱም ከፍጡራን ባህሪያት ጭራሽ ይለያሉ! የባህሪያቱ ምጥቀትም በሰዎች ግምት የሚለካ ስላልሆነ ዝርዝር ይዘታቸውን አስመልክቶ የሚነገር ወሬ ሁሉ ያለ እውቀት የሚሰነዘር መላምት ነው! ይህ ደግሞ በጣም የተወገዘ የሰይጣን ጎዳና ነው![2] ውስን አእምሯችን፡ እንኳን ስለፈጣሪ ስለ ፍጡር ባህሪያትና ሁኔታ እንኳ ሙሉ ግንዛቤ የለውምና!

በዚህ ጉዳይ አንድ ጊዜ ታላቁ ኢማም ***ዐብዱ’ር-ረሕማን ኢብኑ መህዲ*** (197 ዓ.ሂ) ከአንድ ወጣት ጋር ያደረጉትን **ውይይት** እነሆ፡-

---

(1) የዚህ ታላቅ መርሆ ማብራሪያ ከበርካታ ምሳሌዎች ጋር አለፍ ብሎ ይመጣል፤ ኢን-ሻአ'ላህ!

(2) አላህ የሰይጣንን ወጥመዶች ሲያመላክት እንዲህ ይላል፡-

﴿ إِنَّمَا يَأۡمُرُكُم بِٱلسُّوٓءِ وَٱلۡفَحۡشَآءِ وَأَن تَقُولُواْ عَلَى ٱللَّهِ مَا لَا تَعۡلَمُونَ ﴾ [البقرة: ١٦٩]

➥ «እርሱም የሚያዛችሁ በመጥፎና በአፀያፊ ወንጀል፤ እንዲሁም በአላህ ላይ የማታውቁትን እንድትናገሩ ነው»[አል-በቀራህ 169]

- [አል-ኢማም ኢብኑ መህዲ:-] *“ስለ ጌታ እንደምትናገር፣ (ሁኔታውን) እንደምትገልፅና እንደምታመሳስለው ወሬ ደርሶኛል!”*
- [ወጣቱም:-] *“አዎን..!”* በማለት ስለአላህ ባህሪያት ይዘት መናገር ጀመረ!
- [አል-ኢማም ኢብኑ መህዲ:-] *“ልጄ ሆይ! ቆይ ረጋ በል! እስቲ መጀመሪያ ስለ ፍጡር እናውራ፤ ስለ ፍጡር (ይዘት ማወቅ) ከተሳነን ስለ ፈጣሪ ደግሞ እጅግ በበለጠ መልኩ የሚሳነን መሆኑን እናረጋግጣለን! ጂብሪል ስድስት መቶ ክንፎች ያሉት ሆኖ ነብያችን (ﷺ) እንዳዩት ከዐብዱ'ላህ ኢብን መስዑድ (رضي الله عنه) ስለተላለፈልን ሐዲሥ ንገረኝ!”*[1]
- (ወጣቱም ሐዲሡን አወቀው።)
- [አል-ኢማም ኢብኑ መህዲ:-] *“ስድስት መቶ ክንፎች ስላሉት ፍጡር ይዘት ንገረኝ!”*
- (ወጣቱም የሚለው ጠፍቶት ይመለከታቸው ጀመር!)
- [አል-ኢማም ኢብኑ መህዲ:-] *“ልጄ ሆይ! (እንዲያውም) ጥያቄውን ላቅልልህ፤ አምስት መቶ ዘጠና ሰባት ክንፎችን እተውልሀለሁ! ስለ ባለ ሶስት ክንፎች ፍጡር ሁኔታ ንገረኝ! እስቲ ሶስተኛውን ክንፍ ሁለቱን አላህ ካኖረበት (የተለመደ) ቦታ የተለየ ቦታ ላይ ግጠመው!”*

---

(1) ሐዲሡ አል-ቡኻሪ (3232) እና ሙስሊም (174) ዘንድ የተዘገበ ሲሆን በውይይቱ ላይ የጠቀሱትን የዘገባ ሰነድ ለማሳጠር ስል ትቸዋለሁ!

- [ወጣቱም፡-] *“ስለ ፍጡር ባህሪይ ይዘት ማወቅ በርግጥ አቅቶናል፤ ስለ ፈጣሪ ደግሞ በበለጠ መልኩ እጅግ የሚያቅተን ነን! እናገር የነበረውን ትቼ መመለሴን አስመሰክሮታለሁ፤ አላህንም መሃርታ እጠይቃለሁ!”*(1)

ooo

(1) “ሸርሑ ኡሱሊ’ዕቲቃዲ አህሊ’ስ-ሱን-ናህ” ሊ’ል-ላለካኢይ (3/585)፣ “ሒልየቱ’ል-አውሊያእ” ሊአቢ ኑዐይም (9/8)

## ክፍል ሁለት

### ምድብ ሁለት

### የአላህን ባህሪያት በከፊል ወይም በሙሉ የሚያፋርሱ

እነዚህ ቡድኖች በኢስላም ሊቃውንት ዘንድ “ሙዐጥ-ጢላህ” (مُعَطِّلَة) በሚል ስያሜ የሚታወቁት ናቸው። አላህ በቁርአኑና በመልዕክተኛው (ﷺ) እንደበት ለራሱ ያፀደቃቸውን ባህሪያት በሙሉ ወይም በከፊል ይነፍጋሉ! ከአገባቡ ሂደት ጋር በማይስማማ መልኩ ቢሆን እንኳ ትርጓሜያቸውን ይቀለምማሉ! ይህን ጥመታቸውን ሲያራምዱ ፈጣሪን በማላቅ ግርዶሽ ስለሚከለሉ ከላይኞቹ በተለየ መልኩ ብዙ ሰዎች ላይ የበዛ ወይም ያነሰ ተፅእኖ ማሳደር ችለዋል!

ስለሆነም ለጥመታቸው መነሻ የሆኗቸውን ዋና ዋና ብዥታዎች በአላህ ፈቃድ ጠራርጎ የሚያፀዳ (በአንፃሩ) ሰፋ ያለ ማብራሪያ እናስከትላለን! **በቅድሚያ** ስለማንነታቸው አጭር ጥቆማ እናስተላልፍ!

እነኚህ ቡድኖችን (ሙዐጥ-ጢላህ) በዋነኝነት **ለአራት** ከፍለን ልናያቸው እንችላለን[1]፡-

(1) ለግንዛቤ እንዲያመች የጥመታቸው አስከፊነት እየጨመረ በሚሄድበት ቅደም-ተከተል አስቀምጫቸዋለሁ።

**1ኛ- የአላህን ስሞችና አንዳንድ መገለጫዎች በጥቅሉ እያፀደቁ ከፊል ባህሪያቱን የማይቀበሉ**

ይኸኛው ጎራ የአሽዐሪይ-ያህ የማቱሪዲይ-ያህ እና የመሳሰሉት ቡድኖችን ያካትታል።(1) በጥቅሉ ከሚቀበሏቸው ጥቂት ባህሪያት ውጪ ያሉትን እንዳሉ ማፅደቅ "አላህን ከፍጡራን ጋር ማመሳሰል

(1) የአሽዐሪይ-ያህ ቡድኖች የአቡ'ል-ሐሰን አል-አሽዐሪይ ተከታዮች እንደሆኑ ይናገራሉ፤ በመሠረቱ በእምነት አጀንዳዎች ላይ የአንድን ግለሰብ መንገድ በጭፍን መከተል በሸሪዓው የተወገዘ ነው፤ በዚህ ላይ አቡ'ል-ሐሰን በስተመጨረሻ ወደ አህሉ'ስ-ሱን-ናህ መንገድ በጥቅሉ ተመልሰዋል፤ ለዚህም እማኝ ከሚሆኑ ድርሳናቸው መካከል "አል-ኢባናህ ዐን ኡሱሊ'ድ-ዲያናህ"፣ "መቃላቱ'ል-ኢስላሚይ-ዪን ወ'ኽቲላፉ'ል-ሙሶል-ሊን"፤ "ሪሳላህ ኢላ አህሊ'ሥ-ሠኛር" እና ሌሎች መፅሀፎች ይገኛሉ። የአሽዐሪይ-ያዎችን የዘመናት የእምነት ጉዞ ያስተዋለ ቡድኑ ከጊዜ ወደ ጊዜ የመጀመሪያውን ፈር እየለቀቀና ይበልጥ በፍልስፍና ጥመት ውስጥ እየሰመጠ እንደሄደ ማስተዋል ይችላል! በመሆኑም የቀድሞዎቹ መሪዎቻቸው የሚያፀድቋቸውን በርካታ ባህሪያት የኋለኞቹ በማስተባበል ከሙዕተዚላዎች አቋም ጋር እጅግ የሚቀራረብ አካሄድ መስርተዋል! ከበርካታ ምእተ-አመታት በፊት ጀምሮ የአሽዐሪይ-ያህ ቡድን በቁርኣንና በሐዲሥ ከፀደቁት የአላህ ባህሪያት መካከል ሰባቱን ብቻ በመቀበል ላይ ተወስነዋል! እነሱንም በተገቢው መልኩ አያፀድቁም!! ከዚህም ባሻገር በኢማን፣ በቀደርና በሌሎች በርካታ የእምነት አጀንዳዎች ላይም በጀህሚይ-ያዎች ተፅዕኖ ስር በማደራቸው ከትክክለኛው ነብያዊ ፋና በጣም ርቀዋል! (የ"አሕባሽ" ቡድን በነዚህ ጉዳዮች ላይ የሚያስተጋባው አቋም ትክክለኛ ገፅታ ከዚህ የወጣ አይደለም! አብዛኞቹ ማቱሪዲያዎች ደግሞ ከበፊቱም ስምንት ባህሪያትን ብቻ በ"ማፅደቅ" ላይ ተገድበዋል!)

*ነው!”* በሚል አባዜ ቀጥተኛ መልዕክታቸውን በሌላ ይተረጉማሉ![1] የሚፀድቁና የማይፀድቁ ባህሪያትን ለመለየት የሚመረኮዙበት ሚዛን “አእምሯዊ” እንጂ የቁርኣንና የሐዲሥ “ቃላዊ” መረጃ እንዳልሆነ በርካታ መሪዎቻቸው ይናዘዛሉ!!

**2ኛ- ስሞቹን በመጠሪያነት ብቻ እያፀቀደቁ ሁሉንም ባህሪያቱን የማይቀበሉ**

ይኸኛው ጎራ ደግሞ በዋነኛነት የሙዕተዚላዎችን[2] ቡድን ያቀፈ ነው፤ *“በምንም አይነት ባህሪ አላህን መግለፅ እርሱን ከፍጡራን*

---

(1) *ታዲያ* የቁርኣንና የህዲስ *መረጃዎችን* ቀጥተኛ መልዕክት የሚያዛቡባቸው ስልቶችና የሚሰጧቸው ትርጓሜዎች ሰለፎች በአንድ ድምፅ ካወገዟቸው ከጥንቶቹ ጀህሚያዎች በቀጥታ የተኮረጁ እንደሆኑ ለማወቅ አንዳንድ (ከአሽዐሪይ-ያዎች መፈልፈል በፊት የነበሩ) ቀደምት ሊቃውንት ለጀህሚያዎች ውዥንብር ምላሽ ለመስጠት ያዘጋጁቸውን መፃህፍት ማየት ይቻላል! ለዚህ ጥሩ ምሳሌ የሚሆነው *አል-ኢማም ዑሥማን ኢብኑ ሰዒድ አድ-ዳሪሚይ* (በ 280 ዓ.ሂ *ያረፉ*) *ቢሽር አል-መሪሲ* (218 ዓ.ሂ) በተባለው አንድ የጀህሚይ-ያህ አቀንቃኝ ላይ የፃፉት ምላሽ ነው!

(2) *ሙዕተዚላዎች* የአእምሮን ድርሻ ከተገቢው በላይ በማግዘፍ የእምነት ጉዳዮች ዋነኛ *መሠረት* ስላደረጉት ከፍልስፍናቸው ጋር ያልገጠሙትን የቁርኣንና የሐዲሥ *መረጃዎች* ሁሉ ከቻሉ እያስተባበሉ ካልቻሉ አጣምመው እየተረጎሙ ኖረዋል! እምነታቸውን የሚመሰርቱባቸው አምስት መለያ ምሶሶዎች አሏቸው! በጥቅሉ እንደ አንጃ ያላቸው ግኝት ቢመናመንም አብዛኛዎቹ እምነቶቻቸው በሌሎች አማካይነት ተላልፈዋል! በአሁኑ ጊዜ ሺዓዎች (ዘይዲያዎችን ጨምሮ)፤ ኢባዲይ-ያዎችና ሌሎች ቡድኖች =>

*ጋር ማመሳሰል ነው!" በሚል አጉል ፈሊጥ የአላህን መልካም ስሞች ከመልካም ትርጓሜያቸው ነጥለው ያራቁታሉ! "ባህሪያትን የሚያስተናግድ ነገር ሁሉ 'ጂስም' ነው፤ ሁሉም ጂስሞች ደግሞ አንድ አይነት ናቸው!"*[1] ይላሉ!

**3ኛ- ስሞቹንና ባህሪያቱን ባጠቃላይ የማይቀበሉ**

የዚህ አባባል ባለቤቶች የመጀመሪያዎቹ ፅንፈኛ ጀህሚያዎችና መሰሎቻቸው ሲሆኑ ለአላህ ምንም አይነት ስሞችንም ሆነ ባህሪዎችን አያረጋግጡም፤ *"ያልለ ነው (مَوجُود)፤ ግን በምንም አይነት አዎንታዊ መገለጫዎች አይጠራም!"* ይላሉ! *"ይህን*

---

=> በአላህ ስሞችና ባህሪያት ዙሪያ የሚያስተጋቡት የሙዕተዚላዎችን አቋም ነው! አሽዐሪያዎችና ማቱሪዲያዎችም በዚህ ርዕስ ላይ ከነርሱ ብዙ የራቁ አይደሉም!

(1) ይህንን ትንግርታቸውን ሲያብራሩ *«ማንኛውም "ጂስም" የተገማጠመው ሊከፋፈሉ ከማይችሉ ትናንሽ ተመሳሳይ የ"ጀውሃር" ንጥረ-ነገሮች ስለሆነ አንዱ ከሌላው በቅርፅ ቢለያይም በመሠረቱ "ጂስሞች" ሁሉ ተመሳሳይ ናቸው..!»* ይላሉ! ይህንን ፍልስፍና እንኳን ሸሪዓህ ተራ አእምሮ እንኳ አንቅሮ እንደሚተፋው ግልፅ ነው! የሳይንስ ግኝቶችም የሚያረጋግጡት ጭራሽ ውድቅ መሆኑን ነው! ለማንኛውም ስለ እንዲህ ያሉ ቃላት ("ጂስም"፣ "ጀውሀር"..ወዘተ) ሊኖረን የሚገባንን አቋም በምዕራፍ አንድ በሶስተኛው መርሆ ማብራሪያ ላይ አሳልፈናል።

*ካደረግን (በዓለም ላይ) ካሉ ነገሮች ጋር ይመሳሰልብናል!"* በማለት በአፍራሽ ገለፃዎች ብቻ ይገልፁታል![1]

**4ኛ- ስለአላህ በምንም አይነት አዎንታዊም ይሁን አፍራሽ መልኩ "ነው" ወይም "አይደለም" ማለትን ውድቅ የሚያደርጉ**

አብዛኛዎቹ የዚህ ድንበር-ዘለል አቋም ባለቤቶች የአላህን ስሞችና ባህሪያት ብቻ ሳይሆን ከተለያዩ ሸሪዓዊ ህግጋትና ከእምነት ጉዳዮች ጋር የተያያዙ እውነታዎችን ሁሉ የሚያስተባብሉ ፈላስፋዎችና የባጢኒይ-ያህ አንጃዎች ናቸው![2]

---

(1) አንዳንድ የኢስላም ሊቃውንት *ጀህም ኢብኑ ሰፍዋን* አላህን ፈጣሪ (خالق) እና ቻይ (قادر) ከሚሉት መጠሪያዎች በስተቀር በምንም እንደማይገልፅ አስተላለፈዋል። ["ደርኡ ተዓሩዲ'ል-ዐቅሊ ወ'ን-ነቅል" (5/187)]

(2) እነርሱ ዘንድ ስለ አላህ ባህሪያት፣ ስለመጨረሻው ቀንና፣ ስለተለያዩ የአምልኮ (የዒባዳ) ዘርፎች የተነገሩ እውነታዎች በሙሉ የብዙሀኑን ልብ ለመግዛትና ህይወታቸውን ስርዓት ለማስያዝ ተብሎ የተነገሩ ማስመሰያዎች እንጂ ትክክለኛ ገፅታ የላቸውም!! ይህንን ሚስጥር የሚያውቁት ግን ጥቂቶች እንደሆኑ ይናገራሉ። ለምሳሌ:- ስለጀነት ፀጋዎችና ስለጀሀነም ስቃዮች የተነገረን *"የምስኪኑን ህዝብ ስብዕና ለመግራት እንጂ እውነት ሆኖ አይደለም"* ይላሉ! አንዳንዶቹ እንደሚሉት *የሰላት ትርጓሜ = ሚስጥሮቻቸውን ማወቅ፣ የፆም ትርጓሜ ደግሞ= ሚስጥሮቻቸውን መደበቅ፣ የሐጅ ደግሞ = ሸይኾቻቸውን መጎብኘት..* ወዘተ ነው። የዚህ አቋም ባለቤቶች ሙሉ በሙሉ ከኢስላም የወጡ ከህዲያን እንደሆኑ ሁሉም ሙስሊሞች ይስማማሉ።

*“አላህን በምንም ዓይነት አዎንታዊም ሆነ አፍራሽ ገለፃ አንገልፅም!”* በማለት አእምሮ ሊቀበለው በማይችል መልኩ ሁለት ተፃራሪ ባህሪዎችን ውድቅ ያደርጋሉ! *“ያልለ አይደለም ( لا موجود)፤ የሌለም አይደለም (ولا غير موجود)፤ ህያውም አይደለም፣ ሟችም አይደል፤ አዋቂም አይደል፣ አላዋቂም አይደል..ወዘተ”* እያሉ ይቀላምዳሉ! አንዳንዶቹ *“ነውም አንልም! አይደለምም አንልም!”* ይላሉ!!

ምክንያታቸውንም ሲናገሩ፡- *“በአዎንታዊ መልኩ ከገለፅነው (በዓለም ላይ) ከሚገኙ ነገሮች ጋር ይመሳሰልብናል፤ በተቃራኒው ከገለፅነው ደግሞ ከሌሉ ነገሮች ጋር ይመሳሰልብናል”* ይላሉ!!

ooo

**ምርመራ**[1]

የነዚህን አራት ጎራዎች ንግግሮች ያስተዋለ አንድ ቁም ነገር ይገነዘባል። ሁሉም የሚዘምሩት አላህን ከፍጡራን መገለጫዎች የማጥራትና የማላቅ አዝማች ቢሆንም እውነታው ግን በተቃራኒው አላህን ከፍጡራኑ ጋር የማመሳሰል አዘቅት ውስጥ መውደቃቸው ነው!

(1) የበሽታው መነሻ ትክክለኛ መንስኤ ወደ ፊት ይጠቀሳል፤ ምንነቱን ለመረዳት ምርመራ ይቀድማል!

✷ በዚህ ረገድ የኢስላም ሊቃውንት ዘንድ ከታወቁ መርሆዎች መካከል የሚከተለው አባባላቸው አንዱ ነው፡-

«كُلُّ مُعَطِّلٍ مُمَثِّلٌ»

«ሁሉም "ሙዐጥ-ጢል" (የአላህን ባህሪያት ከቀጥተኛ መልዕክታቸው የሚያራቁት) = "ሙመሥ-ሢል" (አላህን የሚያመሳስል) ነው!»

☞ "እንዴት?" ማለት ጥሩ!

ይህን መርሆ በሁለት መንገዶች ማብራራት ይቻላል፡-

**1ኛው-** ሙዐጥ-ጢላዎች በቁርዓንና በሱን-ናህ የተረጋገጡትን የጌታ ባህሪያት መልዕክት እንዲቀለምሙ ያደረጋቸው ቀድሞውኑ የመረጃዎቹን መልዕክት የተረዱት የፍጡራን ባህሪያትን በሚረዱበት ይዘት መሆኑ ነው!

ለምሳሌ፡- አላህ በዐርሹ ላይ መሆኑን የሚያረጋግጡ ማስረጃዎችን ሲሰሙ የሚገነዘቡት መልዕክት አንድ ፍጡር በሌላ ነገር ላይ መሆኑን በሚገነዘቡበት ይዘት ስለሆነ *"አላህ ከዐርሽ በላይ ከሆነ ለርሱ ዐርሽ ያስፈልገዋል ማለት ነው! ዐርሽ ይሸከመዋል ማለት ነው! ..ወዘተ"* በሚል ፈሊጥ የበላይነት ባህሪውን ወደማፋረስ አመሩ! ቀድሞውኑ ይህን የፍጡር መገለጫ ከማስረጃዎቹ የሚረዳው ህሊናው በማመሳሰል አባዜ የተበከለ ብቻ ነው!

✷ ይህም የነዚህና የተቃራኒዎቹ ቡድኖች (ሙሸብ-ቢሀህ) ብዥታ መነሻ ተመሳሳይ መሆኑን ያሳያል! እነዚያ በሽታቸውን ስላላወቁት

ፈውስ አልፈለጉም! እነዚህ ደግሞ ምናባቸው ውስጥ ከተፀነሰው የማመሳሰል በሽታ ለመፈወስ የማስረጃዎችን መልዕክት በማዛባት ወደ ሌላ በሽታ ሸሹ፤- ህፃናት ከሰው ለመደበቅ አይናቸውን እንደሚጨፍኑት!!

እይታቸው በዚህ ብዥታ ያልተጋረደው አብዛኛዎቹ ሙስሊሞች ግን ቀድሞውኑ ከማመሳሰል በፀዳ ሚዛናዊ ግንዛቤያቸው ባህሪያቱን ለርሱ ብቻ በሚገባ መልኩ ስለሚያፀድቁ መረጃዎችን ለመቆልመም መንደፋደፍ አላስፈለጋቸውም!

**2ኛው-** እነዚህ ቡድኖች "ከማመሳሰል ለማምለጥ" በሚያደርጉት ጉዞ ላይ ሁሉ የፈሩት አይቀርላቸውም!

ብዙዎች አላህን ህያው ከሆኑ ነገሮች ጋር ላለማመሳሰል በሚል ፈሊጥ የተለያዩ መገለጫዎቹን በማስተባበል ለሙታንና ለግዑዛን ብቻ በሚገቡ ባህሪያት ይገልፁታል!

ሌሎች ደግሞ ከዚህ ተነስተው በህይወት ካሉም ከሌሉም የዓለም ፍጡራን ጋር ከማመሳሰል ሰመመን ለመዳን ህልውናውን በሚገፍ መልኩ ጭራሽ የሌሉ ነገሮች በሚገለፁበት መገለጫዎች ያወሱታል!

ሌሎች የጠናባቸው ደግሞ፡ ካልሉም ከሌሉም ነገሮች ጋር ከማመሳሰል ለመገላገል ብለው ሁሉንም ወድቅ በማድረግ ፍፁም ሊኖሩ በማይችሉ ነገሮች አፍራሽ መገለጫዎች ይገልፁታል!

ከላይ ያሳለፍናቸው አራት ጎራዎች ይህን ምናባዊ ሽሽት እንደየግንዛቤያቸው እያከናወኑ በመገስገስ አሁን ያሉበት የተዕጢል

አዘቅት ውስጥ መነከራቸው ግልፅ ነው! የሚደንቀው ከሚሸሹት “ችግር” ይልቅ የሚገቡበት “መፍትሄ” የባሰ መሆኑ ነው! ከድጡ ወደ ማጡ!

**የበሽታው መዘዝ**

↳ ይህ የሚያሳየው ማንኛውም በተዕጢል የተበከለ ልቦና በዚህ ረገድ **አራት ዋና ዋና የጥፋት መዘዞችን** በአንድ ላይ እንደሚያስተናግድ ነው፤ ሁለት የ“ተሽቢህ” (ማመሳሰል) እና ሁለት የ“ተዕጢል” መራራ ፍሬዎች! በቅደም ተከተል እንደሚከተለው ይገለፃሉ፡-

1. ከላይ እንዳየነው የአላህ ባህሪያትን የተመለከቱ መረጃዎች ያዘሉት ግልፅ መልዕክት አላህን ከፍጡራን ጋር የሚያመሳስል መሆኑን ማሰባቸው፤ *(“ተሽቢህ”)*

2. በመቀጠል የእነዚህን መለኮታዊ መረጃዎች መልዕክት በማዛባት ትክክለኛ ትርጓሜያቸውን መግፈፍ፤ *(“ተዕጢል”)*

3. ከዚያም ለአላህ የተገቡትን ትክክለኛ ባህሪያት በመንፈግ መገለጫዎቹን ማራቆት፤ *(“ተዕጢል”)*

4. በመጨረሻም ከላይ እንደተብራራው ጉድለትን በሚያንፀባርቁ ባዶ ገለፃዎች በማውሳት ከግኡዛንና ግኝት ከሌላቸው ነገሮች ጋር በተዘዋዋሪ ማመሳሰል! *(“ተሽቢህ”)*

ከዚህ ሁሉ አስከፊ ጠንቆች ለመዳን **ቀላሉ መፍትሄ** የህዝበ-ሙስሊሙ ምርጥ ትውልዶች እንዳደረጉት የአላህን ባህሪያት

ከምንም ነገር ጋር ሳያመሳስሉና ስለሁኔታቸውም ሳይዘባርቁ፣ እንዲሁም ትርጉም-አልባ ሳያደርጉና ቀጥተኛ መልዕክታቸውንም ሳያዛቡ ለጌትነቱ በሚገባ መልኩ አረጋግጦ ማለፍ ነበር!

ሆኖም እነዚያ የተዕጢል አንጃዎች ይህንን ሚዛናዊና ንፁህ መንገድ እንደ "ማመሳሰል" በመቁጠር ከጥንት ጀምሮ የሐቅ ተከታዮችን "ሙሸብ-ቢሃህ" (አላህን ከፍጡራን ጋር የሚያመሳስሉ) እያሉ በሀሰት ሲያጥላሉና በከሃዲነት ሲፈርጁ ኖረዋል!! የላይኛው ማብራሪያ በእውነት አመሳሳዮቹ እነርሱ ራሳቸው እንደሆኑ በግልፅ ያስረዳል!

➢ ***አል-ኢማም አሕመድ*** እንዲህ ብለዋል፡-

«وَقَدْ رَأَيْتُ لأَهْلِ الأَهْوَاءِ وَالْبِدَعِ وَالْخِلافِ أَسْمَاءً شَنِيعَةً قَبِيحَةً يُسَمُّونَ بِهَا أَهْلَ السُّنَّةِ، يُرِيدُونَ بِذَلِكَ عَيْبَهُمْ وَالطَّعْنَ عَلَيْهِمْ، وَالْوَقِيعَةَ فِيهِمْ، وَالإِزْرَاءَ بِهِمْ عِنْدَ السُّفَهَاءِ وَالْجُهَّالِ، أَمَّا الْجَهْمِيَّةُ فَإِنَّهُمْ يُسَمُّونَ أَهْلَ السُّنَّةِ: "الْمُشَبِّهَةَ"، وَكَذَبَ الْجَهْمِيَّةُ أَعْدَاءُ اللَّهِ! **بَلْ هُمْ أَوْلَى بِالتَّشْبِيهِ**..»

*«የግላዊ ዝንባሌ፣ የቢድዓህ፣ እና የውዝግብ አራማጆች አህሉ'ስ-ሱን-ናህን የሚሰይሙባቸውን አፀያፊና አስጠሊታ ስሞችን አይቻለሁ! በዚህም የሚፈልጉት እነርሱን ማነወር፣ መተቸትና መዝለፍ እንዲሁም እነሱን ምኞችና መሀይማን ዘንድ ማጣጣል ነው! ጀህሚይ-ያዎችማ አህሉ'ስ-ሱን-ናህን "ሙሸብ-ቢሃህ" ብለው ይጠሯቸዋል፤ እነዚህ የአላህ ጠላት የሆኑት ጀህሚይ-ያዎች*

*ዋሽተዋል! እንዲያውም እነርሱ (ራሳቸው) ለ"ተሽቢህ" (ማመሳሰል) ይበልጥ የተገቡ ናቸው..!»* [1]

➢ እንደዚሁም ***አል-ኢማም አል-ቡኻሪይ*** (256 ዓ.ሂ) እንደሚከተለው ይላሉ፡

«وَقَالَ بَعْضُ أَهْلِ الْعِلْمِ: "إِنَّ الْجَهْمِيَّةَ هُمُ الْمُشَبِّهَةُ؛ لأنهم شبّهوا ربّهم بالصنم والأصم والأبكم الذي لا يسمع ولا يُبصر ولا يتكلم ولا يخلق!"»

*«አንዳንድ የእውቀት ባለቤቶች እንዲህ አሉ፡- "ጀህሚይ-ያዎች ናቸው አመሳሳዮቹ! ምክንያቱም ጌታቸውን ከማይሰማ፣ ከማያይ፣ ከማይናገርና ከማይፈጥር ጣኦት፣ ደንቆሮና ዲዳ ጋር አመሳስለውታልና!"»*[2]

ooo

---

(1) "ኢብጣሉ'ት-ተእዊላት ሊአኽባሪ'ስ-ሲፋት" ሊ'ል-ቃዲ አቢ የዕላ (1/46)
(2) "ኽልቁ አፍዓሊ'ል-ዒባድ" ሊ'ል-ቡኻሪይ (2/59)

## ክፍል ሶስት

### መድሃኒት

በዚህ ላይ ያሉትን የግንዛቤ ግድፈቶች የሚያስተካክሉና የስህተተኞችን የብዥታ መነሻ ጠራርገው የሚያስወግዱ **ሶስት ቁልፍ መሠረቶችን** እናስከትላለን፡-

| አንደኛው መሠረት |
| --- |
| የስያሜ አንድነት የይዘትን መመሳሰል አያመላክትም! |

ማብራሪያ

የሁለት ነገሮች ስያሜ በቃል ደረጃ መጋጠሙ የግድ አንድ አይነት ባህሪይ የሚያወርሳቸው እንዳልሆነ ግልፅ ነው!

አዎን! በነባራዊው ዓለም ከምናያቸው ተጨባጭ እውነታዎች አንዱ ፍጡራን ራሳቸው በብዙ ጥቅል መጠሪያዎች በስያሜ ደረጃ ሊጋጠሙ ቢችሉም በይዘትና በአኳኋን በሰፊው መለያየታቸው ነው።

ይህንን ይበልጥ የሚያስረዳን የሚከተለው ነጥብ ነው፡-

✷ የአንድን ባህሪ ስያሜ ለብቻው ስንሰማ በአእምሯችን የሚጫር **ጥቅል** መልዕክት አለ። ይህ ጥቅል መልዕክት ግን በዚህ **ጥቅልነቱ** የሚገኘው በህሊናችን እንጂ በገሃዱ ዓለም ላይ አይደለም፤ በገሀዱ ዓለም የሚገኙት ባህሪያት ሁሌም የተገደቡና ባህሪያቱን ከተላበሱት ነገሮች ማንነትና መገለጫ ጋር የተሳሰሩ ናቸውና!

<u>በመሆኑም የባህሪውን ባለቤት ማንነት በሚያስረዳ አገባብ ቃሉን ስንሰማው የመጀመሪያውን ልቅ መልዕክት የሚገድብ መለያ እንገነዘባለን።</u>

ለምሳሌ፦ **<u>“መኖር/ግኝነት”</u>** (existence /وجود ) የሚለውን ነጠላ ቃል ስንሰማ የሆነ **ጥቅል** መልዕክት በአእምሯችን ይፀነሳል፤ ለጊዜው የምናስበው ውስን የ“መኖር” ዓይነት ላይኖር ይችላል።

**ሆኖም፦** *“የትንኝ መኖር፣ የሰው መኖር፣ የመላኢካዎች መኖር፣ የአጋንንት መኖር፣ የአየር መኖር፣ የምድር መኖር፣ የሰማይ መኖር፣ የዐርሽ መኖር..”* እየተባለ ሲዘረዘር መልዕክቱ <u>ከባህሪው ባለቤቶች ማንነት ጋር በሚሄድ ይዘት ስለሚተረጎም የተለያዩ ግንዛቤዎችን እንጨብጣለን!</u> ሁሉም “መኖር” የተባለውን **ጥቅል** ገለፃ በጥቅሉ የሚጋሩ ቢሆንም በገሀዱ ዓለም ያላቸው የ“መኖር” ይዘት ግን እጅግ ይለያያል! እንዲያውም ባህይሪውን በተላበሱት ማንነት መካከል ያለው ልዩነት እየሰፋ በሄደ ቁጥር ባንዱ “መኖር”ና በሌላኛው “መኖር” መካከል ያለውም ልዩነት እንዲሁ ይጐላል።

ሌሎች ምሳሌዎች

- **<u>“ሀይል”</u>** የሚለውን ቃል በነጠላ ስንሰማ የምንገነዘበው ጥቅል መልዕክት አለ።

*“የሰው ሀይል፣ የጉንዳን ሀይል፣ የማሽን ሀይል፣ የኒውክሌር ሀይል፣ የመላኢካ ሀይል ..”* ሲባል ግን የመልዕክቱ ይዘት

በባለቤቱ ማንነት ላይ ይወሰናል! ሁሉም ሀይል አላቸው፣ ግን ሀይላቸው በአይነትም በብርታትም ይለያያል!

- **"ብርሃን"** ሲባልም እንደዚሁ!

*"የሻማ ብርሃን፣ የአምፖል ብርሃን፣ የፀሃይ ብርሃን፣ መላኢካዎች የተፈጠሩበት ብርሃን..."* ሁሉም ብርሃን ከመሆናቸው ጋር በመካከላቸው ያለው ልዩነት የትየለሌ ነው!

- **"ክንፍ"** የሚለውን ነጠላ ስያሜ ስንሰማ ከመብረር ጋር የተያያዘ ጥቅል መልዕክት እንገነዘባለን።

ታዲያ ወፎች ክንፍ አላቸው፣ ትንኝም እንዲሁ! አውሮፕላንም እንዲሁ! መላኢካዎችም እንደዚያው!

የክንፋቸው ይዘት ግን በጣም ይለያያል፤ "ክንፍ" በሚለው ባህሪ **ጥቅል** ስያሜ በመጋጠማቸው ተመሳሰሉ አይባልም!

መቼም የአላህ ክቡር ባለሟል የሆኑት መላኢካዎች ከትንኝ፣ ከአእዋፍና ከግዑዙ አውሮፕላን ጋር እንዳይመሳሰሉ ሰግተን አላህ ያጎናፀፋቸውን ክንፍ አንሰልባቸውም!

አላህ እንዲህ ይላል፦

﴿.. جَاعِلِ ٱلْمَلَـٰٓئِكَةِ رُسُلًا أُو۟لِىٓ أَجْنِحَةٍ مَّثْنَىٰ وَثُلَـٰثَ وَرُبَـٰعَ ۚ يَزِيدُ فِى ٱلْخَلْقِ مَا يَشَآءُ ۚ﴾ [فاطر: ١]

➥ «..መልዕክትን ባለ ሁለት፣ ባለ ሶስትና ባለ አራት ክንፎች መልዕክተኞች አድራጊ፤ ከፍጥረትም የፈለገውን ይጨምራል..»[ፋጢር 1]

↳ ስለዚህ መላኢካዎችን ባናያቸውም አላህ የነገረንን ተመርኩዘን ከነርሱ ማንነት ጋር የሚሄድ ልዩ ክንፍ እንዳላቸው እናምናለን እንጂ *"ክንፍ ማለት የእንቅስቃሴያቸውን ፍጥነት ለማሳየት የሚውል ዘይቤያዊ ቃል ነው..! ኪናዊ ገለፃ ነው..! ምንትሴ..!"* እያልን የማይመስል ሀተታ አንዘባርቅም! በተቃራኒውም *"ክንፋቸው የላባ ነው! እንዲህ ይመስላል፤ እንዲያ ይመስላል!.."* እያልን ያላየነውን ካየነው ጋር በማነፃፀር ያለ እውቀት አንፈላፈልም![1]

ያሳለፍናቸውን ሌሎች ምሳሌዎች በተመለከተም እንደዚሁ ተመሳሳይ መርሆ እንከተላለን!

## የጀነት ምሳሌ

አላህ ለመልካም ባሮቹ በዘልዓለማዊው የጀነት አገር ውስጥ ካዘጋጃቸው የተለያዩ ሽልማቶችና መስተንግዶዎች መካከል

(1) እንዲህ ዓይነት ሙግት በመላኢካዎች የማመን ግዴታን የሚያጓድል መሆኑ የታወቀ ከሆነ በተመሳሳይ ፈሊጥ የአላህን ትክክለኛ ባህሪያት ማስተባበል በአላህ የማመን ግዴታን ይበልጥ እንደሚያጓድል ጥርጥር የለም! ያስተውሉ!

የተወሰኑትን እንደዘረዘረልን የታወቀ ነው! እዚያ ስላሉ ልዩ ልዩ አርኪ መጠጦችና መብሎች፣ ፍራፍሬዎች፣ ወንዞች፣ ጌጣጌጦችና የሀር አልባሳት፣ ከፍ ያሉ አልጋዎች፣ የተሸቆጠቆጡ ህንፃዎችና ሰገነቶች፣ አገልጋዮች፣ ቆነጃጂት ሚስቶች እና ስለ ሌሎችም ፀጋዎች አሳውቆናል![1]

ታዲያ በአንድ በኩል የእነዚህን ቃላትና ገለፃዎች ጥቅል መልዕክት የምንገነዘብ ቢሆንም በሌላ በኩል የፀጋዎቹን ውስጣዊ ይዘት ግን እንደማናውቅ ግልፅ ነው! አላህም እነዚህንና መሰል ፀጋዎችን ከመዘርዘሩ ጋራ ባሮቹን ሰለሚጠብቋቸው ልዩ ሽልማቶች ማንም እንደማያውቅ መግለፁ ይህንን ያረጋግጣል፤ አላህ እንዲህ ብሏል፡-

﴿ فَلَا تَعۡلَمُ نَفۡسٞ مَّآ أُخۡفِيَ لَهُم مِّن قُرَّةِ أَعۡيُنٖ جَزَآءَۢ بِمَا كَانُواْ يَعۡمَلُونَ ﴾

[السجدة: ١٧]

➥ «(ሙእሚኖች) ይሰሩት በነበረው ምክንያት ከአይኖች መርጊያ (የፀጋ ዓይነቶች) ለምንዳነት የተደበቀላቸውንም (ማንኛይቱም) ነፍስ አታውቅም!»[አስ-ሰጅደህ 17]

እንደዚሁም ነብያችን (ﷺ) እንዲህ ብለዋል፡-

(1) ከጀነት ባለ ፀጎች ሁሉ ይበልጥ አናሳ የሆነውን ደረጃ የሚያገኘው ግለሰብ በጀሀነም ተቀጥተው ከሚወጡት ሰዎች የመጨረሻው ሲሆን ሽልማቱም የዱንያ አገር ሙሉ ፀጋ እና አስር እጥፍ ጭማሪ እንደሆነ በሐዲሥ ተረጋግጧል። [አል-ቡኻሪ (806)፣(6571)፣ ሙስሊም (182)፣(186)፣ (191) እና ሌሎችም ዘግበውታል።]

☜ «قَالَ اللهُ - عَزَّ وَجَلَّ-: أَعْدَدْتُ لِعِبَادِيَ الصَّالِحِينَ، مَا لَا عَيْنٌ رَأَتْ، وَلَا أُذُنٌ سَمِعَتْ، وَلَا خَطَرَ عَلَى قَلْبِ بَشَرٍ..»

➡ «አላህ እንዲህ ብሏል፦ "ለደጋግ ባሮቼ አይን አይቶት የማያውቀ፣ ጆሮም ሰምቶት የማያውቅና በሰው ልቦና ውስጥ ብሎ የማያውቅ (ፀጋን) አዘጋጅቻለሁ!"..»[1]

***ነገር ግን ባለንበት የዱንያ አገርም ከጀነት ፀጋዎች ጋር በመጠሪያ አንድ የሆኑ ፀጋዎችን እናያለን! እንዲያውም በደፈናው ስለ ወዲያኛው ዓለም የተነገሩንን ምሳሌዎች የምንረዳው በዚህኛው ዓለማችን ከምናውቃቸው ተመሳሳይ ስያሜዎች ጥቅል ቋንቋዊ ትርጓሜ በመነሳት ነው! ይህ የስም መመሳሰል ግን ሃሳብን ለመረዳት ከማገልገሉ ያለፈ ተፅእኖ ሊኖረው አይገባም።***

***ስለሆነም በጀነትና በዱንያ ፀጋዎች መካከል የስያሜ እንጂ የይዘትና የሁኔታ መመሳሰል እንደሌለ ሁላችንም እናውቃለን!***

➢ ታላቁ ሰሓቢይ ***ዐብዱ'ላህ ኢብኑ ዐብ-ባስ*** (رضي الله عنه) እንዲህ ይላሉ፦

«ليسَ في الدّنيا ممّا في الجنّةِ إلا الأسماءُ.»

***«በጀነት ውስጥ ካሉ ነገሮች ዱንያ ውስጥ ምንም የለም - ከስሞች በስተቀር!»***[1]

(1) አል-ቡኻሪይ (3244)፣ (4779)...፣ ሙስሊም (2824)

ስለሆነም የጀነትን ፀጋ በአይናችን ባናይም በቁርአንና በትክክለኛ ሐዲሦ አስተምህሮት ላይ ተመርኩዘን መልዕክቱን እናፀድቃልን እንጂ መቼም ዘልዓለማዊውን የጀነት ፀጋ ከጠፊው የዱንያ ፀጋ ለመለየት በሚል ፈሊጥ እነዚህን አምላካዊ ገለፃዎች ከትርጓሜ አናራቁትም፤ እንዲሁም ግልፅ መልዕክታቸውን በመቆልመም *"መጠጡ የነፍስ እርካታን፣ ፍራፍሬዎቹ የመልካም ስራን ውጤት፣ አልባሳቱ የኃጢያት መሸፈንን.. ይወክላሉ! ..ቅብርጥስዮ..!"* እያልን የጀነትን ህልውና ከመሰረቱ አናፋርስም![2]

---

(1) "ተፍሲሩ'ጥ-ጠበሪይ" (1/392)፣ "ተፍሲር ኢብኒ አቢ ሓቲም" (1/66)፣ "አል-በዕሦ ወ'ን-ኑሹር" ሊ'ል-በይሀቂይ ገፅ 542፣ እና ሌሎች መዛግብት ላይ በትክክለኛ ሰነድ ተላልፏል።

(2) ከሞት በኋላ መቀስቀስን የሚያስተባብሉት የባጢኒይ-ያህ ቡድኖች መረጃዎችን በዚህ መልኩ እንደሚያጣምሙ ጥቆማ አልፏል፤ ሌሎች የተዕጢል ጎራዎች ለነርሱ በዚህ ጉዳይ ላይ የሚሰጧቸውን ምላሾች በአላህ ባህሪያት ላይ ለራሳቸው ቢመከሩባቸው መልካም ነበር! ምክንያቱም *"ለምን እነዚህን ግልፅ እውነታዎች በሌላ በመተርጎም ታስተባብላላችሁ?"* ሲሏቸው መልሳቸው *"እናንተ የአላህን ባህሪያት የተመለከቱ እውነታዎችን በሌላ እንደምትተረጉሙት ነው እንጂ ማስተባበል አይደለም! እናንተው በከፈታችሁት በር ነው የገባነው!!"* የሚል ይሆናል!! አላህ ልብ ይስጠን!

መቋጫ

↳ **ስለዚህም** የባህሪያት ጥቅል ስያሜ መገጣጠም በፍጡራን መካከል እንኳ የይዘትንና የሁኔታን አንድነት ወይም መመሳሰል የሚያመላክት ሳይሆን እንዴት የፈጣሪና የፍጡር መመሳሰልን ያመላክታል?!

ፍጡራን ራሳቸው አንዳንድ ጥቅል ስያሜዎችን እየተጋሩ በመካከላቸው አላህ ብቻ የሚያውቀው ሰፊ ልዩነትና መበላለጥ መኖሩ የተረጋገጠ ከሆነ በታላቁ ፈጣሪና በደካማው ፍጡር መካከል ያለው ልዩነት እንዴት ይመጠናል?! በምንስ ይለካል?! የዚህ ልዩነት ሚስጥርስ በየትኛው አንደበት ይፈታል?!

**በመሆኑም** አላህን ራሱን በገለፀበት መልኩ በመግለፅ ሂደት ምንም አይነት የማመሳሰል ስጋት ሊፈጠር አይገባም፤ ለፈጣሪ የፀደቁት ባህሪያትን የምናረጋግጠው ለርሱ ብቻ በሚገባ ልዩ መልኩ እንጂ ከፍጡር ጋር በሚያመሳስለው ይዘት አለመሆኑን አውቀናልና!

➤ አል-ኢማም ***አቡ’ል-ሐሰን አል-አሽዓሪይ*** (324 ዓ.ሂ) እንዲህ ብለዋል፦

« ..لم يكن وصفُه بأنه حيّ وقادرٌ وعالم يوجب تشبيهَه لمن وصفناه بذلك منّا، وإنما يوجب اتفاقُهما في ذلك اتفاقًا في حقيقة الحي والقادر والعالِم، وليس اتفاقهما في حقيقة ذلك يوجب تشابهاً بينهما، ألا ترى أنّ وصْفَ الباري –عز وجل– بأنه موجود ووصْفَ الإنسانِ بذلك لا يوجب تشابهاً بينهما، وإن كانا قد

اتفقا في حقيقة الموجود، ولو وجب تشابهما بذلك لوجب تشابه السواد والبياض بكونهما موجودَين..»

*«እርሱን (አላህን) "ህያው፣ ቻይ፣ አዋቂ.." ብሎ መግለፅ ከእኛ (ፍጡራን) መሀል በእነዚህ ባህሪያት ከምንገልፃቸው ጋር የሚያመሳስለው አይደለም! ይልቁንም በነዚህ መገለጫዎች መጋጠማቸው የሚያስገነዝበው "ህያው፣ ቻይ፣ አዋቂ.." በሚሉት* ***ጥቅል*** *እውነታዎች መጋጠማቸውን እንጂ መመሳሰላቸውን አይደለም፤ ፈጣሪ "ያልለ" (الموجود) መሆኑንና ሰውም "ያልለ" (الموجود) መሆኑን መግለፅ ሁለቱም በጥቅሉ ያልሉ በመሆናቸው እውነታ ላይ ቢጋጠሙም መመሳሰላቸውን ግን የሚያስገነዝብ እንዳልሆነ አትመለከትም?! በዚህ ረገድ የግድ የሚመሳሰሉ ቢሆኑ ኖሮ ነጭና ጥቁር ሁለቱም ያልሉ /የሚገኙ/ በመሆናቸው (ብቻ) የሚመሳሰሉ በሆነ ነበር!..»*[1]

## ቁርአናዊ ማረጋገጫ

የላይኛውን መሠረት ከሚያረጋግጡ እውነታዎች መካከል አላህ ራሱን በሰየመባቸው ስሞች ፍጡራንን የጠራባቸው በርካታ

(1) "ሪሳላህ ኢላ አህሊ'ሥ-ሠግር" ሊአቢ'ል-ሐሰን አል-አሽዓሪይ ገፅ (120-121)

አንቀፆች መኖራቸው ነው! ባህሪያቱን በገለፀባቸው ቃላትም የአንዳንድ ፍጡራንን ባህሪያት ገልጿል!

የተወሰኑ ቁርኣናዊ ምሳሌዎችን አብረን እንቃኝ፡-

አላህ ራሱን በርካታ ቦታዎች ላይ "ህያው" (الحَيّ) ብሎ ሰይሟል፡-

﴿ ٱللَّهُ لَآ إِلَٰهَ إِلَّا هُوَ ٱلۡحَيُّ ٱلۡقَيُّومُ ﴾[البقرة : ٢٥٥، وآل عمران ٢]

➥ «(ለዘላለም) ህያውና ራሱን ቻይ (ተብቃቂ) ከሆነው አላህ በቀር (እውነተኛ) አምላክ የለም!»[አል-በቀራህ 255/ ኣሊ-ዒምራን 2]

﴿ وَتَوَكَّلۡ عَلَى ٱلۡحَيِّ ٱلَّذِي لَا يَمُوتُ ﴾[الفرقان: ٥٨]

➥ «በዚያም በማይሞተው ህያው (አምላክ) ላይ ተመካ..»[አል-ፉርቃን 58]

↳ እንዲሁም ከፍጡራኑ ከፊሉን በተመሳሳይ ስያሜ ጠርቷል፡-

﴿ يُخۡرِجُ ٱلۡحَيَّ مِنَ ٱلۡمَيِّتِ وَيُخۡرِجُ ٱلۡمَيِّتَ مِنَ ٱلۡحَيِّ ﴾[الروم: ١٩]

➥ «ከሙት ህያውን ያወጣል፤ ከህያውም ሙትን ያወጣል!»[አር-ሩም 19]

ታዲያ "ህያው" የሚለው ቃል በጥቅል መልዕክቱ የፈጣሪንና የፍጡርን ህያውነት ቢያካትትም ይዘታቸው ግን ጭራሽ ሊነፃፀር የሚችል አይደለም፤ የፈጣሪ ህያውነት በሰዎች እንደበት የሚብራራ ባይሆንም ቢያንስ ከፍጡራን በተለየ መልኩ መጀመሪያና መጨረሻ የሌለው፣ ከማንኛውም እንከን የጠራ ፍፁም.. መሆኑን እናውቃለን!

በመሆኑም ከማመሳሰል "ለማምለጥ" ብለን የቃሉን ግልፅ ትርጓሜ መቆልመም አያስፈልገንም! ይህ ማመሳሰል ከሆነ መቼም ህያው ካልሆኑ ነገሮች ጋር ከማመሳሰል አይብስም! ልብ ይበሉ!

☞ እንዲሁም ራሱን "ሰሚው"ና "ተመልካቹ" ብሎ ጠርቷል፡-

﴿لَيۡسَ كَمِثۡلِهِۦ شَيۡءٞۖ وَهُوَ ٱلسَّمِيعُ ٱلۡبَصِيرُ﴾ [الشورى: ١١]

➥ «እንደርሱ ያለ (አምሳያ) ምንም የለም፤ እርሱም ሰሚውና ተመልካቹ ነው።»[አሽ-ሹራ 11]

﴿إِنَّ ٱللَّهَ كَانَ سَمِيعَۢا بَصِيرٗا﴾ [النساء: ٥٨]

➥ «በርግጥ አላህ (ሁሌም) ሰሚ፣ ተመልካች ነበር!»[አን-ኒሳእ 58]

↳ ከፍጡራኑም ከፊሉን በዚያው ስያሜ ገልጿል፡-

﴿إِنَّا خَلَقۡنَا ٱلۡإِنسَٰنَ مِن نُّطۡفَةٍ أَمۡشَاجٖ نَّبۡتَلِيهِ فَجَعَلۡنَٰهُ سَمِيعَۢا بَصِيرًا﴾
[الإنسان: ٢]

➡«እኛ ሰውን ልንፈትነው ከተቀላቀለ የፍትወት ጠብታ ፈጠርነው፤ እናም ሰሚ፣ ተመልካች አደረግነው።»[አል-ኢንሳን 2]

አዎን! አላህ ሰሚና ተመልካች ነው፤ ሰውም እንዲሁ! ሆኖም የአላህ መስማትና ማየት ከሰው መስማትና ማየት ጋር ሊነፃፀር አይችልም። የልዩነቱን ሚስጥር በውስን ግንዛቤያችን መፍታት ባንችልም ቢያንስ የአላህ መስማት እንደ ደካማው ፍጡር በርቀት ወይም በሌላ ምክንያቶች እንደማይገደብ እናውቃለን! የድምፆች ዝግታ ወይም መደራረብ፣ አሊያም የቋንቋዎች መለያየት ምንም ሳያግደው ሁሉንም እኩል ይሰማል! ጨለማም ይሁን ሌላ ግርዶሽ ሳይወስነው ሁሉንም እኩል ያያል! ጥራትና ፍፁምነት የተገባው ጌታችን ስሙ የተቀደሰ ነው!

መቼም ከፍጡራን ጋር እንዳይመሳሰል ሰግተን ይህን መሰል የምልዐት መገለጫ በመንፈግ በማያዩና በማይሰሙ ነገሮች አንመስለውም!

እንዲሁም ራሱን "ሩህሩህ"ና "አዛኝ" (رَءُوفٌ رَّحِيمٌ) ብሎ ጠርቷል፦

﴿إِنَّ ٱللَّهَ بِٱلنَّاسِ لَرَءُوفٌ رَّحِيمٌ﴾[البقرة: ١٤٣]

➡«አላህ ለሰዎች በጣም ሩህሩህ አዛኝ ነው»[አል-በቀራህ 143]

↳ መልዕክተኛውንም በተመሳሳይ ቃል እንዲህ ሲል ገልጿል፦

📖 ﴿ لَقَدۡ جَآءَكُمۡ رَسُولٞ مِّنۡ أَنفُسِكُمۡ عَزِيزٌ عَلَيۡهِ مَا عَنِتُّمۡ حَرِيصٌ عَلَيۡكُم بِٱلۡمُؤۡمِنِينَ رَءُوفٞ رَّحِيمٞ ﴾ [التوبة: ١٢٨]

➥ «ከራሳችሁ የሆነ፣ ችግራችሁ ፅኑ የሚሆንበት፣ በእናንተ (መድህን) ላይ የሚጓጓ፣ ለአማኞችም በጣም ሩህሩህ አዛኝ የሆነ መልዕክተኛ በርግጥ መጥቶላችኋል!»[አት-ተውባህ 128]

የፈጣሪ ርህራሄና እዝነት ግን እንደ ፍጡር ርህራሄና እዝነት እንዳልሆነ የታወቀ ነው!

☞ እንዲሁም ራሱን "ንጉስ" ብሎ ሰይሟል:-

📖 ﴿ فَتَعَٰلَى ٱللَّهُ ٱلۡمَلِكُ ٱلۡحَقُّ ﴾ [طه: ١١٤، المؤمنون: ١١٦]

➥ «አላህ - እውነተኛው ንጉሱ - (ከሃዲያን ከሚሉት) ላቀ!»[ጧሃ 114፣ አል-ሙእሚኑን 116]

📖 ﴿ هُوَ ٱللَّهُ ٱلَّذِي لَآ إِلَٰهَ إِلَّا هُوَ ٱلۡمَلِكُ ٱلۡقُدُّوسُ ... ﴾ [الحشر: ٢٣]

➥ «እርሱ አላህ ነው ፤ ያ ከእርሱ በቀር ሌላ አምላክ የሌለ ፤ ንጉሱ ፣ ከጉድለት ሁሉ የጠራው..»[አል-ሐሽር 23]

⤷ ለአንዳንድ ፍጡራንም ይህንን መጠሪያ አፅድቋል:-

📖 ﴿ وَقَالَ ٱلۡمَلِكُ ٱئۡتُونِي بِهِۦ... ﴾ [يوسف: ٥٠، ٥٤]

➥ « ንጉሡም "አምጡልኝ" አለ..»[ዩሱፍ 50 ፥ 54]

ይኸኛው ንጉስ ግን እንደዚያኛው ንጉስ እንዳልሆነ ግልፅ ነው!

☞ ራሱን "አዋቂ"ና "ቻይ" (ታጋሽ) (عَلِيمٌ حَلِيمٌ) ብሎ ሰይሟል፡-

📖 ﴿وَٱللَّهُ عَلِيمٌ حَلِيمٌ﴾[النساء: ١٢]

➥ «አላህም አዋቂ ቻይ ነው!»[አን-ኒሳእ 12]

⤿ ከፍጡራንም እነኚህን መጠሪያዎች የሰጣቸው አሉ፡-

📖 ﴿وَبَشَّرُوهُ بِغُلَٰمٍ عَلِيمٍ﴾[الذاريات: ٢٨]

➥ «በአዋቂ ወንድ ልጅ (ኢስሓቅ) አበሰርነው፡፡»[አዝ-ዛሪያት 28]

📖 ﴿فَبَشَّرْنَٰهُ بِغُلَٰمٍ حَلِيمٍ﴾[الصافات: ١٠١]

➥ «በቻይ ወንድ ልጅ (ኢስማዒል) አበሰርነው፡፡»[አስ-ሷፋት 101]

ታዲያ የፈጣሪ አዋቂነትና ቻይነት ከፍጡር ጋር እንደማይመሳሰል የተረጋገጠ ነው።

⇨ በባህሪያትም ደረጃ ስለራሱ ባወሳባቸው ገለፃዎች ስለፍጡራን አውስቷል፡-

ለራሱ "እወቀት"ን አፅድቋል፦

📖﴿أَنزَلَهُۥ بِعِلْمِهِۦ﴾[النساء: ١٦٦]

➥ «(ቁርኣንን) በእውቀቱ አወረደው..»[አን-ኒሳእ 166]

📖﴿وَلَا يُحِيطُونَ بِشَيْءٍ مِّنْ عِلْمِهِۦٓ إِلَّا بِمَا شَآءَ﴾[البقرة: ٢٥٥]

➥ «ከእውቀቱም እርሱ በሻው ካልሆነ በቀር ምንም ያህል አያካልሉም።» [አል-በቀራህ 255]

↪ አንዳንድ ባሮቹንም በዚህ ባህሪ ገልጿል፦

📖﴿وَإِنَّهُۥ لَذُو عِلْمٍ لِّمَا عَلَّمْنَـٰهُ﴾[يوسف: ٦٨]

➥ «እርሱም (የዕቁብ) እኛ ስላሳወቅነው የእውቀት ባለቤት ነው»[ዩሱፍ 68]

📖﴿فَرِحُوا۟ بِمَا عِندَهُم مِّنَ ٱلْعِلْمِ﴾[غافر: ٨٣]

➥ «እነርሱ ዘንድ ባለው እውቀት ተደሰቱ!»[ጋፊር 83]

ይኸኛው እውቀትና ያኛው ግን ፍፁም አይመሳሰሉም!

ለራሱ "ሃይል" አፅድቋል፦

📖﴿إِنَّ ٱللَّهَ هُوَ ٱلرَّزَّاقُ ذُو ٱلْقُوَّةِ ٱلْمَتِينُ﴾[الذاريات: ٥٨]

➥ «አላህ በርግጥ እርሱ ነው ሲሳይ ሰጭ፣ የሃይል ባለቤት፣ ብርቱው!»[አዝ-ዛሪያት 58]

﴿أَوَلَمْ يَرَوْا۟ أَنَّ ٱللَّهَ ٱلَّذِى خَلَقَهُمْ هُوَ أَشَدُّ مِنْهُمْ قُوَّةً﴾[فصلت: ١٥]

➥ «ያ የፈጠራቸው አላህ እርሱ ከነሱ በሃይል የበረታ መሆኑን አላዩምን?!»[ፉስ-ሲለት 15]

⤷ ለአንዳንድ ፍጡራንም ሀይልን አፅድቋል፡-

﴿وَيَزِدْكُمْ قُوَّةً إِلَىٰ قُوَّتِكُمْ﴾[هود: ٥٢]

➥ «..በሃይላቸሁም ላይ ሃይል ይጨምርላችኋል..»[ሁድ 52]

ይኸኛው ሃይልና ያኛው ጭራሽ አይገናኙም!

☞ እንዲሁም ለራሱ "ፍላጎት"ን/"መሻት"ን እንዳረጋገጠው ለባሮቹም በዚያው አንቀፅ አረጋግጧል፡-

﴿تُرِيدُونَ عَرَضَ ٱلدُّنْيَا وَٱللَّهُ يُرِيدُ ٱلْـَٔاخِرَةَ﴾[الأنفال: ٦٧]

➥ «የቅርቢቱን ዓለም ጥቅም ትፈልጋላችሁ፤ አላህ የመጨረሻይቱን ዓለም ይፈልግላችኋል!»[አል-አንፋል 67]

የፈጣሪ ፍላጎት ግን ከፍጡር ፍላጎት ይለያል።

☞ ለራሱ "መውደድ"ን እንዳረጋገጠውም ለባሮቹ አረጋግጧል፡-

﴿فَسَوۡفَ يَأۡتِي ٱللَّهُ بِقَوۡمٖ يُحِبُّهُمۡ وَيُحِبُّونَهُۥٓ﴾[المائدة: ٥٤]

➥ «..አላህም የሚወዳቸውንና የሚወዱትን ህዝቦች ወደፊት ያመጣል..»[አል-ማኢዳህ 54]

ሁለቱ መውደዶች ግን ይለያያሉ።

ለራሱ (ከሃዲያንን) "መጥላት"ን እንዳፀደቀውም ለፍጡራን አፅድቋል፡-

﴿إِنَّ ٱلَّذِينَ كَفَرُواْ يُنَادَوۡنَ لَمَقۡتُ ٱللَّهِ أَكۡبَرُ مِن مَّقۡتِكُمۡ أَنفُسَكُمۡ إِذۡ تُدۡعَوۡنَ إِلَى ٱلۡإِيمَٰنِ فَتَكۡفُرُونَ﴾[غافر: ١٠]

➥ «እነዚያ የካዱት ሰዎች "ወደ እምነት በምትጠሩና በምትክዱ ጊዜ አላህ (እናንተን) መጥላቱ ነፍሶቻችሁን (ዛሬ) ከመጥላታችሁ የበለጠ ነው" ተብለው ይጥጠራሉ፡፡»[ጋፊር 10]

ሁለቱ መጥላቶች ግን የተለያዩ ናቸው።

(በሴረኛ ጠላቶቹ ላይ) "እንደሚያሴር" እንደገለፀው አንዳንድ ፍጡራንም እንደሚያሴሩ ገልጿል፡-

﴿وَيَمۡكُرُونَ وَيَمۡكُرُ ٱللَّهُۖ وَٱللَّهُ خَيۡرُ ٱلۡمَٰكِرِينَ﴾[الأنفال: ٣٠]

➥ «(እነሱም) ያሴራሉ፤ አላህም ያሴራል፤ አላህም ከሚያሴሩ ሁሉ የተሻለ ነው!»[አል-አንፋል 30]

📖 ﴿ إِنَّهُمْ يَكِيدُونَ كَيْدًا ﴿١٥﴾ وَأَكِيدُ كَيْدًا ﴿١٦﴾ فَمَهِّلِ ٱلْكَٰفِرِينَ أَمْهِلْهُمْ رُوَيْدًا ﴿١٧﴾ ﴾
[الطارق: ١٥-١٧]

➡ «እነርሱ ማሴርን ያሴራሉ፤ እኔም ማሴርን አሴራለሁ፤ ከሃዲዎችንም ቀን ስጣቸው፤ ጥቂትን ጊዜ አቆያቸው!»[አጥ-ጧሪቅ 15-17]

የፍጡራን ማሴር በጥቅል እይታ እንደ አላማውና አፈፃፀሙ አዎንታዊ ወይም አሉታዊ ገፅታ ሊኖረው ይችላል! ሆኖም የአላህ "ማሴር" የአመፀኞችን የጥፋት ሴራ እነርሱ በማይገምቱት ዘዴ በማምከንና አዘናግቶ በመቅጣት ስለሆነ ሁሌም አዎንታዊ ከመሆኑ ባሻገር የረቀቀ ጥበቡን፣ የመጠቀ ችሎታውንና አሸናፊነቱን ከሚያጎሉት እውነታዎች ይመደባል።

ታዲያ በሁሉም የቁርኣን አንቀፆች የሚስተዋለው አገባብ የሚያስገነዝበው መልዕክት በዚህ የምሉዕነት ይዘት የተገደበ በመሆኑ ልቅ በሆነ ሂደት "አላህ ያሴራል" ብሎ እንደ መገለጫው መቁጠር ተገቢ አይሆንም፤ ገለፃው ቁርኣናዊ አገባቡን በመልዕክት ደረጃ የተከተለ መሆን አለበትና።

☞ ለራሱ "ዒዝ-ዛህ" (عِزّة) (1) እንዳፀደቀው ለመልዕክተኛውና ለአማኞችም አፅድቋል፦

(1) "ዒዝ-ዛህ" (عِزّة) በዐረብኛ ሶስት መልዕክቶችን ሊያስጨብጥ ይችላል፦ አሸናፊነት፣ ሀያልነት/ብርቱነት እና ክቡርነት/የደረጃ የበላይነት። =>

📖﴿وَلِلَّهِ ٱلۡعِزَّةُ وَلِرَسُولِهِۦ وَلِلۡمُؤۡمِنِينَ﴾[المنافقون: ٨]

➥ «አሸናፊነትም ለአላህ፣ ለመልዕክተኛውና ለሙእሚኖች ነው!»[አል-ሙናፊቁን 8]

የአላህ አሸናፊነት እንደ ፍጡራኑ አይደለም፤ ሀያልነቱና ክቡርነቱም እንዲሁ!

☞ እንዲሁም ራሱን በ“ተናጋሪነትና በማናገር” ገልጿል፡-

📖﴿وَكَلَّمَ ٱللَّهُ مُوسَىٰ تَكۡلِيمًا﴾[النساء: ١٦٤]

➥ «አላህም ሙሳን ማነጋገርን አነጋገረው!»[አን-ኒሳእ 164]

📖﴿تِلۡكَ ٱلرُّسُلُ فَضَّلۡنَا بَعۡضَهُمۡ عَلَىٰ بَعۡضٍ مِّنۡهُم مَّن كَلَّمَ ٱللَّهُ﴾[البقرة: ٢٥٣]

➥ «እነዚያ መልዕክተኞቹ ናቸው፤ ከፊላቸውን ከከፊላቸው አስበለጥን፤ ከነሱም መካከል አላህ ያነጋገረው አለ..»[አል-በቀራህ 253]

↳ ለከፊል ፍጡራኑም ይህንኑ ባህሪ አፅድቋል፡-

---

=> [“ሸእኑ’ድ-ዱዓእ” ሊ’ል-ኸጥ-ጣቢ ገፅ 47-48፣ “አል-ካፊየቱ አሽ-ሻፊያህ” (“ኑኒይ-የቱ’ብኒ’ል-ቀይ-ዪም”) የስንኝ ቁጥር 3262-3265 ይመልከቱ።]

📖 ﴿وَقَالَ ٱلْمَلِكُ ٱئْتُونِي بِهِۦٓ أَسْتَخْلِصْهُ لِنَفْسِي ۖ فَلَمَّا كَلَّمَهُۥ قَالَ إِنَّكَ ٱلْيَوْمَ لَدَيْنَا مَكِينٌ أَمِينٌ﴾[يوسف: ٥٤]

➥ «ንጉሡም፡- "እርሱን አምጡልኝ፤ ለራሴ ግለኛ ሳደርገው" አለ፤ ባናገረውም ጊዜ "አንተ ዛሬ እኛ ዘንድ ታማኝ ባለሟል ነህ" አለ፡፡»[ዩሱፍ 54]

አዎን! ሁለቱ ማናገሮች እንደሚለያዩ አይታበልም! *"አላህ የሚናገር ከሆነ ሰዎች ለመናገር የሚያስፈልጋቸው ነገር ሁሉ የግድ ያስፈልጉታል!!"* በሚል አጉል ፈሊጥ ባህሪውን መንፈግ ቂልነት ነው! የጌታን ልዩ የመሆን ሚስጥርም መጋፋት ነው!

☞ እንዲሁም ራሱን ከበላይ በመሆን (ኢስቲዋእ) ገልጿል፡-

📖 ﴿ٱلرَّحْمَٰنُ عَلَى ٱلْعَرْشِ ٱسْتَوَىٰ﴾[طاه: ٥]

➥ «አር-ረሕማን በዐርሹ ላይ ሆነ»[ጧሃ 5]

(በሌሎች ስድስት አንቀፆችም ይህንኑ መልዕክት አፅንቷል!)

↳ ፍጡራኑንም በአንዳንድ ቦታዎች ላይ በተመሳሳይ ቃል ገልጿል፡-

📖 ﴿فَإِذَا ٱسْتَوَيْتَ أَنتَ وَمَن مَّعَكَ عَلَى ٱلْفُلْكِ ...﴾[المؤمنون: ٢٨]

➥ «አንተ አብረውህ ካሉት ጋር በመርከቧ ላይ (ወጥተህ) በተስተካከልክ ጊዜ..»[አል-ሙእሚኑን 28]

📖﴿وَٱسْتَوَتْ عَلَى ٱلْجُودِيِّ﴾[هود: ٤٤]

➥ «(መርከቧም) "ጁዲይ" (በተባለ ተራራ) ላይ ተስተካከላ ቆመች»[ሁድ 44]

📖﴿..وَجَعَلَ لَكُم مِّنَ ٱلْفُلْكِ وَٱلْأَنْعَٰمِ مَا تَرْكَبُونَ ۝١٢ لِتَسْتَوُۥا۟ عَلَىٰ ظُهُورِهِۦ ثُمَّ تَذْكُرُوا۟ نِعْمَةَ رَبِّكُمْ إِذَا ٱسْتَوَيْتُمْ عَلَيْهِ﴾[الزخرف: ١٢-١٣]

➥ «ከመርከቦችና ከቤት እንስሳዎች የምትሳፈሩባቸውን ያደረገላችሁም ነው፦ በጀርባዎቹ ላይ (ወጥታችሁ) እንድትስተካከሉ፣ ከዚያም በርሱ ላይ በተስተካከላችሁ ጊዜ የጌታችሁን ፀጋ እንድታስታውሱ..»[አዝ-ዙኽሩፍ 12-13]

***የፈጣሪ ከበላይ መሆንና የፍጡር ፍፁም እንደሚለያይ ማንም የማይስተው እውነታ ነው! "አላህ ከዐርሽ በላይ ከሆነ ለርሱ ዐርሽ ያስፈልገዋል ማለት ነው! ዐርሽ ይሸከመዋል ማለት ነው! ምንትሴ.."*** እያሉ የተለመዱ ደረቅ ማስፈራሪያዎቻቸውን በማራገብ የበላይነቱን የሚያስተባብሉ ሰዎች ከዚህ በፊት እንደተጠቆመው መጀመሪያውኑ የአላህን ከዐርሽ በላይ የመሆን ይዘት የሚገነዘቡት ልክ ፍጡራን ከፍ ባለ ነገር ላይ በሚሆኑበት ይዘት ስለሆነ ከማመሳሰል በሽታቸው ለመዳን የተለመደውን የትርጉም ማጣመም ይፈፅማሉ! «ማንኛውም "ሙዐጥ-ጢል" "ሙሸብ-ቢህ" ነው!» ብለን አልነበር?!

ቀድሞውኑ የአላህን ከዐርሽ በላይ መሆን በዚህ መልኩ የሚረዳ ለአላህ ተገቢውን ክብር የሚሰጥ አይደለም! አላህ ከእንደዚህ አይነት ጉድለት የጠራ ነው! ከማንኛውም ፍጡር ምንም አይነት እርዳታ የማይፈልግ ተብቃቂ ጌታ ነው! ዐርሽን፣ ሰማያትንና ምድርን እንዲሁም መላ ፍጡራንን በወሰን-የለሽ ችሎታው የሚቆጣጠረውና የሚያስተናብረው ማን ሆነና?! ያለ እርሱ እርዳታ የትኛውም ፍጡር ሊኖርም ሆነ ሊቆም መች ይችልና?! ሃያሉ አምላካችን ልቅናና ጥራት የተገባው ነው!

﴿إِنَّ ٱللَّهَ يُمۡسِكُ ٱلسَّمَٰوَٰتِ وَٱلۡأَرۡضَ أَن تَزُولَاۚ وَلَئِن زَالَتَآ إِنۡ أَمۡسَكَهُمَا مِنۡ أَحَدٖ مِّنۢ بَعۡدِهِۦٓۚ إِنَّهُۥ كَانَ حَلِيمًا غَفُورٗا﴾[فاطر: ٤١]

➥ «አላህ ሰማያትንና ምድርን እንዳይወገዱ ይይዛቸዋል፤ ቢወገዱ ከእርሱ ሌላ አንድም የሚይዛቸው የለም! እነሆ እሱ ታጋሽ መሀሪ ነው።»[ፋጢር 41]

እንዲሁም ለራሱ “እጅ” አፅድቋል፡-

﴿قَالَ يَٰٓإِبۡلِيسُ مَا مَنَعَكَ أَن تَسۡجُدَ لِمَا خَلَقۡتُ بِيَدَيَّۖ﴾[ص: ٧٥]

➥ «“ኢብሊስ ሆይ! በሁለት እጆቼ ለፈጠርኩት ከመስገድ ምን ከለከለህ?!” አለ።»[ሷድ 75]

↳ ለፍጡራኑም እጆችን አፅድቋል፡-

📖 ﴿يُخۡرِبُونَ بُيُوتَهُم بِأَيۡدِيهِمۡ وَأَيۡدِي ٱلۡمُؤۡمِنِينَ﴾ [الحشر: ٢]

➥ «ቤቶቻቸውን በእጆቻቸውና በሙእሚኖች እጆች ያፈርሳሉ!»[አል-ሐሽር 2]

የፈጣሪ እጆች ግን ከፍጡር እጆች ሙሉ በሙሉ የተለዩ ናቸው! ስለ አላህ እጆች ሲሰሙ በህሊናቸው ከሚወጥኑት የፍጡር እጆች ምስል ለመሸሽ በ'ተእዊል' ስም ባህሪውን ከመሠረቱ መናድ የታወቀው የ"ተዕጢል" አራማጆች ተውኔት ነው!

---

✸ በነዚህና በሌሎች ብዙ አንቀፆች ላይ አላህ ለራሱ ባፀደቃቸው በርካታ መጠሪያዎችና ባህሪዎች ፍጡራኑን መጥራቱና መግለፁ ይታወቃል።(1) እነዚህን ባህሪያት በተገቢው መልኩ ማፅደቅ ማመሳሰል ከተባለ ውንጀላው በተዘዋዋሪ የሚቀሰረው በቁርኣን ባለቤት ላይ ይሆናል!!

➢ *አል-ኢማም አድ-ዳሪሚይ* (280 ዓ.ሂ) እንዲህ ብለዋል፡-

(1) ለተጨማሪ ምሳሌዎች "አት-ተውሒድ.." የተሰኘውን የ*አል-ኢማም ኢብኑ ኹዘይማህ* (311 ዓ.ሂ) መፅሀፍ (1/51-69)፣ እንዲሁም "አት-ተድሙሪይ-ያህ" የተሰኘውን የ*ሸይኹ'ል-ኢስላም ኢብኑ ተይሚይ-ያህ* መፅሀፍ ከገፅ 21 እስከ 30 ይመልከቱ።

«فَإِنْ كُنَّا مُشَبِّهَةً عِنْدَكَ أَنْ وَحَّدْنَا اللهَ إِلَهًا وَاحِدًا بِصِفَاتٍ أَخَذْنَاهَا عَنْهُ وَعَنْ كِتَابِهِ فَوَصَفْنَاهُ بِمَا وَصَفَ بِهِ نَفْسَهُ فِي كِتَابِهِ، فَاللَّهُ فِي دَعْوَاكُمْ أَوَّلُ الْمُشَبِّهِينَ بِنَفسِهِ! ثُمَّ رَسُولُ اللهِ ﷺ الَّذِي أَنْبَأَنَا ذَلِكَ عَنْهُ!!»

*«አላህን ከርሱና ከመፅሃፉ በያዝናቸው ባህሪያት መሠረት በመፅሃፉ ራሱን በገለፀበት በመግለፅ አንድ አምላክ አድርገን ነጥለን በመገዛታችን አንተ ዘንድ አመሳሳዮች ከሆንን በሙግታችሁ መሠረት የመጀመሪያው ራሱን አመሳሳይ አላህ ነው ማለት ነው! ቀጥሎም ይህንን ስለርሱ ያሳወቁን የአላህ መልዕክተኛ ﷺ !»* [1]

**መቼም ይህንን ለማለት የሚደፍር ሙስሊም የለም!**

➢ **እንዲሁም *አል-ኢማም ኢብኑ ዐብዲ'ል-በር (463 ዓ.ሂ)* እንዲህ ይላሉ፡-**

«وَمُحَالٌ أَنْ يَكُونَ مَنْ قَالَ عَنِ اللهِ مَا هُوَ فِي كِتَابِهِ مَنْصُوصٌ مُشَبِّهًا إِذَا لَمْ يُكَيِّفْ شَيْئًا وَأَقَرَّ أَنَّهُ لَيْسَ كَمِثْلِهِ شَيْءٌ»

(1) "ነቅዱ ዑሥማን ኢብኒ ሰዒድ ዐላ ቢሽር አል-መሪሲ አል-ዐኒድ" ሊ'ድ-ዳሪሚይ (1/303)

*«ስለአላህ በመፅሃፉ በግልፅ የሰፈረውን የተናገረ ስለሁኔታው ካልገለፀና እንደርሱ ያልለ (አምሳያ) እንደሌለ ካረጋገጠ በፍፁም አመሳሳይ ሊሆን አይችልም!»*[1]

**ቀላሉ መፍትሄ**

**የአላህ ስሞችና ባህሪያት የተወሱት የርሱ ሆነው፣ ወደ እርሱም ተጠግተው ስለሆነ ከርሱ ውጭ ለማንም ተገቢ አይሆኑም! የፍጡራን መገለጫዎችና ባህሪያትም የተወሱት የነሱ ሆነው፣ ወደ ባለቤቶቹ ተጠግተው ስለሆነ ለፈጣሪ ተገቢ አይሆኑም! የፈጣሪን መገለጫ ለርሱ ብቻ በሚገባ መልኩ እናፀድቃለን፤ የፍጡራንን ደግሞ ለነርሱ ብቻ በሚገባ መልኩ! አለቀ! ደቀቀ!**

(1) “አሊ’ስቲዝካር” ሊብኒ ዐብዲ’ል-በር (2/528)

ሁለተኛው መሠረት

## ስለከፊል የአላህ መገለጫዎች መናገር ስለሌሎቹም እንደመናገር ነው!

ማብራሪያ

ስለከፊል የአላህ ባህሪያት በአረጋጋጭም ይሁን በአፍራሽ ትንታኔ መናገር ስለሌሎችም እንደመናገር ነው። ይህ ማለት የአላህን ባህሪያት አንዱን ከሌላው ሳይለዩ ሁሉንም በቁርአንና በትክክለኛ ሐዲሥ በተጠቀሱበት ሂደት እኩል ማስተናገድ የግድ ነው፤ ከፊሉን ተቀብሎ ሌላውን ማስተባበል ግን እርስ በርሱ የሚጋጭ የተምታታ አካሄድ ነው።

የተወሰኑ ባህሪያትን እየተቀበሉ ከሌሎቹ የሚደነብሩት አንዳንድ ጐራዎች እነዚያኞቹን ከማፅደቅ ያገዳቸው የማመሳሰል ስጋት እነዚህኞቹም ላይ እንደማይቀርላቸው ሊያስተውሉ ይገባል! መፍትሄው እነዚህን ለርሱ ብቻ በሚገባ ይዘት እንደተቀበሉት ሁሉ በሌሎቹም ላይ የሚወጥኑትን ተጨባጭ ያልሆነ ስጋት ወደ ኋላ በመተው ሁሉንም ለርሱ ብቻ በሚገባ ሂደት መቀበል ነው! እነዚህን ማፅደቅ ማመሳሰል ካልሆነ ሌሎቹንም ማፅደቅ ማመሳሰል አይሆንም! ሌሎቹን ማፅደቅ ማመሳሰል ከሆነ ግን እነዚህንም ማፅደቅ ማመሳሰል ነው!

ምሳሌ

አንድ ሰው እንደ አሽዐሪይ-ያዎች ለአላህ እውቀትን (عِلم)፣ ችሎታን (قُدرة)፣ መስማትን (سَمْع)፣ ማየትን (بصر)፣

መፈለግ/መሻትን (مشيئة/إرادة) እና መሰል ባህሪያትን በጥቅሉ እንደሚያፀድቅ እየተናገረ እንደ መውደድ (مَحبّة)፣ መጥላት (كراهية)፣ እዝነት (رحمة) ያሉ ሌሎችን ደግሞ የማይቀበልና ቀጥተኛ ትርጓሜያቸውን የሚቆለምም ከሆነ "ባፀደቅካቸውና በተቃወምካቸው ባህሪያት መካከል ምንም ለውጥ የለም፤ ምክንያቱም ስለ አንዱ ባህሪ በምትተነትንበት መልኩ ስለሌላውም መተንተን ይቻላልና!" እንለዋለን!

"ባህሪያቱን ያፀደቅከው በእነዚህ ስያሜዎች ከሚገለፁ የፍጡራን ባህሪያት ጋር ሳታመሳስል ከሆነ ያስተባበልካቸውንም ባህሪያት በዚሁ መልኩ ከፍጡራን ባህሪያት ጋር ሳታመሳስል ማፅደቅ ትችላለህ!"

- እርሱም፡- *"ግን እኮ **መቆጣት** ለፈጣሪ አይገባም! ምክንያቱም ቁጣ የንዴት ስሜት ነው፤ የደም መፍላት ነው!..»* የሚል ምላሽ ከሰነዘረ እንዲህ እንለዋለን፡-

- *"**ፍላጎት**ስ ጥቅምን ለማግኘት ወይም ጉዳትን ለማስቀረት በልብ የሚያድር ስሜታዊ ዝንባሌ አይደለምን?!"*

- እርሱም፡- *"አይ! ይህማ የፍጡር **ፍላጎት** መገለጫ ነው! እኔ ለጌታ የማፀድቀው **ፍላጎት** ለርሱ ማንነት የሚገባውን ነው!"* ማለቱ አይቀርም!

- እኛም፡- *"ያኛውም የፍጡር ቁጣ መገለጫ ነው! እኛ እንድታፀድቅ የጠየቅንህም መቆጣት ለጌታ ማንነት የሚገባውን ነው!"* እንለዋለን![1]

ስለሌሎች ባህሪያትም በተመሳሳይ ሂደት ምላሽ ይሰጠዋል!

✸ *"እነዚህን ባህሪያት ከሌሎች ነጥዬ በቀጥታ ያረጋገጥኩት አእምሯዊ መረጃዎችን በመመርኮዝ ነው! ለምሳሌ፡- ፍጡራኑን በተለያዩ ነገሮች መለያየቱና ማበላለጡ ፍላጎት/መሻት እንዳለው ያሳያል..ወዘተ"* ብሎ ከተከራከረ[2] በሶስት **መንገዶች** መልስ መስጠት እንችላለን፡-

1- በእንዲህ ያለ የእምነት ጉዳይ ላይ በ"አእምሮ" ላይ ብቻ ተመርኩዞ መለኮታዊ እውነታዎችን ማፅደቅና መሻር ከባድ አደጋ ያዘለ የስህተት አካሄድ ነው![3] እስቲ ንገረን ጉበዝ! **በማን አእምሮ ነው የቁርኣንና የሐዲሥ እውነታዎች የሚለኩት?!** ደግሞም በመሰል ርዕሰ-ጉዳዮች ላይ የሚነሱ ውዝግቦችን ሊቋጭ የሚችለው

---

(1) የባህሪን ጥቅል መልዕክትና ባህሪው በፍጡር ላይ የሚያስከትለውን ተፅዕኖ አለመለየት ለመሰል ስህተቶች መነሻ ነው። ለምሳሌ፡- "የደም መፍላት" ቁጣ በሰው ላይ የሚያሳድረው አንድ ተፅዕኖ እንጂ ቁጣ ራሱ አይደለም! "የጥርስ መገለጥና የጉንጭ መሰብሰብ" እኛ የምናውቀው የሳቅ ውጤት እንጂ ሳቅ ራሱ አይደለም!..

(2) ብዙ የአሽዐሪይ-ያህ አቀንቃኞች እንደሚሉት!

(3) ማብራሪያውን አለፍ ብሎ ይደርሱበታል፤ ኢን-ሻአ'ላህ!

ብቸኛው ፍርድ ከበላይ የሚመጣ አምላካዊ ብይን ነው! ሁሉም የራሱን ዳኛ ከሰየመ ግን መስማማት ላይ አይደረስም!

2- እነዚያን ባህሪያት ባፀደቅክባቸው አእምሯዊ መንገዶች ወይም በተሻለ መልኩ በቁርኣንና በሐዲሥ የተወሱትን ሌሎች ባህሪያት ማረጋገጥ ይቻላል!

**ለምሳሌ፡-** ለባሮቹ በጐ መዋሉና ጥፋታቸውን ይቅር ማለቱ “እዝነቱ”ን ያመላክታል፤ ታዛዦችን በመልካም መመንዳቱ “መውደዱ”ን ያመላክታል፤ ከሃዲያንን ለዘላለም መቅጣቱ እነርሱን “መጥላቱ”ን ያሳያል..!

3- በምትለው ብንስማማ እንኳ ከአንድ በላይ ማስረጃዎች ሊቀርቡለት በሚችል ነጥብ ላይ አንድ ማስረጃ መጓደሉ (ሌላ ማስረጃ እስካለ ድረስ) ነጥቡን ውድቅ አያደርገውም! ወደ አንድ ከተማ ከሚያመሩ ሁለት መንገዶች አንዱ ቢዘጋ ወደ ከተማው ጭራሽ መድረስ አይቻልም ማለት ነው እንዴ?!

**ስለሆነም** “አእምሯዊ” መረጃዎች የሚያመላክቱት ሰባቱን ወይም ስምንቱን ባህሪያት ብቻ ቢሆን ኖሮ እንኳ ሌሎቹ በቁርኣንና በሐዲሥ እስከተረጋገጡ ድረስ ያለማመንታት ልንቀበላቸው ይገባል![1]

(1) ይህ ምላሽ የስህተተኞችን የአቋም ግጭትንና መምታታት ለማሳየት የሚነገር እንጂ ቁርኣንና ሐዲሥ በውስጣቸው አእምሯዊ ማስረጃዎችን አላቀፉም ማለት እንዳልሆነ ግልፅ ነው!

✷ እዚህ ላይ ትኩረት የሚሻው ነጥብ ከፊል ባህሪያትን ብቻ የሚያፀድቁ ሰዎች እነሱንም ጭራሽ ለሚያስተባብሉ ሌሎች ጐራዎች ምላሽ ለመስጠት በጥቅሉ የሚጠቀሙበት ስልት ራሱ ለነሱ ለራሳቸው መልስ ለመስጠት የሚያገለግል መሆኑ ነው!

ለምሳሌ፡- የአሽዐሪይ-ያህ ቡድኖች የሚቀበሏቸውን ጥቂት ባህሪያት ከነአካቴው ለሚያስተባብሉት ሙዕተዚላዎችና ጀህሚይ-ያዎች እነዚህን ባህሪያት ማፅደቅ አላህን ከፍጡራን ጋር ማመሳሰል እንዳልሆነ በማብራራት ምላሽ ይሰጧቸዋል! ይህ ስልታቸው ራሱ እነርሱ ራሳቸው የሚያስተባብሏቸውን ባህሪያት አስመልክቶ የሚሰጣቸው የማረሚያ ስልት ይሆናል! ለሌሎች ይህን ምላሽ እየሰጡ ለራሳቸው 'አሻፈረን' ካሉ ግን ቀመራቸው (ፎርሙላቸው) የተመሰቃቀለ በመሆኑ ውጤቱም እንደዚያው ነው የሚሆነው![1]

---

(1) በመሠረቱ ከቁርአን መለኮታዊ አስተምህሮት በማፈንገጥ ሌላ አመለካከትን ያስተናገደ ሁሉ እንዲህ የተምታታ ሂደት መከተሉ አይቀርም፤ አላህ እንዲህ ይላል፡-

📖 ﴿ أَفَلَا يَتَدَبَّرُونَ ٱلْقُرْءَانَۚ وَلَوْ كَانَ مِنْ عِندِ غَيْرِ ٱللَّهِ لَوَجَدُواْ فِيهِ ٱخْتِلَٰفًا كَثِيرًا ﴾ [النساء: ٨٢]

➥ «ቁርኣንን አያስተነትኑምን?! ከአላህ ሌላ ዘንድ (የወረደ) ቢሆን ኖሮ በውስጡ ብዙ ግጭቶችን ባገኙ ነበር!»[አን-ኒሳእ 82]

ለዚህ ነው አላህ ከሃዲያንን በሚከተለው መልኩ የገለፃቸው፡- =>

**✸ ይህን መሠረት በማብራራት የአላህ ባህሪያትን በሙሉ በመንፈግ ባዶ ስሞችን የሚቀበሉት ሙዕተዚላዎችን በተመሳሳይ ስልት ማረም ይቻላል! እንዲህ እንላቸዋለን፡-**

**«ስሞቹንና ባህሪያቱን መለያየት የተምታታ አካሄድ ነው! *"በገሀዱ አለም በባህሪያት እንደሚገለፅ የምናውቀው "ጂስም" ብቻ ነው.. እንቶ ፈንቶ!"* በማለት ባህሪያቱን የምታስተባብሉ ከሆነ በስያሜም ደረጃ በገሀዱ አለም 'ህያው'፣ 'አዋቂ'፣ 'ቻይ'፣..ወዘተ ተብሎ እንደሚጠራ የምታወቁት "ጂስም" ስለሆነ ስሞቹንም ልታስተባብሉ ነውን?!»**

**✸ እንደዚሁም *"ስለ አላህ በጥቅሉ መኖሩን እንጂ ምንም አይነት ስሞችንም ይሁን ባህሪያት አናፀድቅም!"* ለሚሉት ፅንፈኛ ጀህሚይ-ያዎችና መሰሎቻቸውም እንዲህ እንላቸዋለን፡-**

**«የአላህን "መኖር" ያረጋገጣችሁት ከፍጡራን "መኖር" ጋር ሳታመሳስሉ ከሆነ የስሞቹንና የባህሪያቱንም ይዘት ከፍጡራን ስሞችና ባህሪያት ጋር ሳታመሳስሉ ማፅደቅ ይገባችኋል፤ ስሞቹንና ባህሪያቱን ማፅደቅ ማመሳሰል ከሆነ ደግሞ "መኖሩን"ም ማፅደቅ**

---

=> 📖 ﴿ بَلۡ كَذَّبُواْ بِٱلۡحَقِّ لَمَّا جَآءَهُمۡ فَهُمۡ فِيٓ أَمۡرٖ مَّرِيجٍ ﴾[ق: ٥]

➥ «ይልቁንም እውነቱ በመጣላቸው ጊዜ አስተባበሉ፤ እነርሱ በተምታታ ነገር ውስጥ ነው ያሉት!»[ቃፍ 5]

ማመሳሰል ስለሚሆን ጭራሽ “መኖሩ”ን በግልፅ አንደበት ልትክዱ ነው!»

በእንዲህ አይነት አካሄድ ይህ “መሠረት” ሁሉም የጥመት ሰለባዎች ራሳቸውን እንዲያርሙ በር የሚከፍት ነው፤ ታዲያ ማን ይሆን ወደ ምራቻ አፀድ የሚገባው?!

ooo

ሶስተኛው መሠረት

## ስለ አላህ ባህሪያት መናገር ስለ "ዛቱ" እንደመናገር ነው !

ማብራሪያ

ፍጡር በገሀዱ አለም ህልውናው የሚለይበት "ዛት" (ذات) [1] እንዳለው ሁሉ ፈጣሪም ልዩ "ዛት" እንዳለው ይታወቃል። አብዛኛዎቹ አንጃዎች ይህንን በግልፅ አንደበት ለማስተባበል አይደፍሩም! ታዲያ ሁሉም በጥቅሉ እንደሚስማማው የአላህ "ዛት" ከሌሎች "ዛቶች" ጋር በፍፁም የማይመሳሰል ነው።

ይህን ካረጋገጥን የርሱ "ዛት" መገለጫ ባህሪያትም ከሌሎች "ዛቶች" መገለጫ ባህሪያት ይለያሉ ማለት ነው! ስለዚህ የአላህን ባህሪያት ከፍጡራን ባህሪያት ጋር ላለማመሳሰል በመስጋት ትርጓሜያቸውን የሚጠመዝዙት ቡድኖች ለአላህ ሌሎች "ዛቶች"ን የማይመስል "ዛት" እንዳረጋገጡት ሁሉ ለዚህ ልዩ "ዛቱ" የሌሎች "ዛቶች"ን ባህሪያት የማይመስሉ ልዩ ባህሪያትን ማረጋገጥ የግድ ይላቸዋል!

---

(1) "ዛት" (ذات) የሚለው ቃል በመሰል አገባቦቹ የሚወክለው መልዕክት የአንድ ነገር ህልውና በተጨባጭ የሚረጋገጥበት ገሀዳዊ መለያ እንደሆነ አሳልፈናል። ብዙዎች እንደሚያደርጉት "ዛት"ን በ"አካል" መተርጎም መልዕክቱን ማጥበብ ይሆናል!

➤ ስመ-ጥሩ የሐዲሥ ጠቢብ ***አል-ኸጢብ አል-በግዳዲ*** (463 ዓ.ሂ) እንዲህ ይላሉ:-

«والأصلُ في هذا أنّ الكلامَ في الصفات فرعٌ عن الكلام في الذات، ويحتذي في ذلك حذْوَه ومثالَه، فإذا كان معلوماً أن إثبات ربِّ العالمين -عزّ وجلّ- هو إثباتُ وجودٍ، لا إثباتُ كيفيةٍ، فكذلك إثباتُ صفاته، إنما هو إثبات وجودٍ، لا إثبات تحديدٍ وتكييفٍ..» .

*«የዚህ ጉዳይ መሠረት:- ስለ ባህሪያቱ መናገር ስለ "ዛቱ" የመናገር ቅርንጫፍ መሆኑ ነው! የርሱንም ዱካና ምሳሌ ይከተላል! የዓለማቱ ጌታን ህልውና ማፅደቅ መኖሩን እንጂ ሁኔታውን (ገድቦ) ማፅደቅ እንዳልሆነ ታዋቂ ከሆነ እንደዚያው ባህሪያቱንም ማፅደቅ መኖራቸውን ማፅደቅ እንጂ ይዘታቸውንና ሁኔታቸውን ገድቦ ማፅደቅ አይደለም!»*[1]

አዎን! ስለ አላህ "ዛት" ይዘትና ሁኔታ እንደማናውቀው ሁሉ ስለ ባህሪያቱ ይዘትና ሁኔታ አናውቅም፤ ሆኖም ያንን በጥቅሉ እንደምናፀድቀው ሁሉ ይህንንም እናፀድቃለን!

(1) "መስአላህ ፊ'ስ-ሲፋት" ሊ'ል-ኸጢብ አል-በግዳዲ ገፅ 8፤ "ተዝኪረቱ'ል-ሁፍ-ፋዝ" ሊዝ-ዘሀቢይ (3/1142)፤ "ሲየሩ አዕላሚ'ን-ኑበላእ" (18/283)፤ "አል-ዑሉው" ገፅ 172
*ታዋቂው ዓሊም አቡ ሱለይማን አል-ኸጥ-ጣቢ* (388 ዓ.ሂ) እንዲሁ ተመሳሳይ ንግግር አላቸው፤ "አል-ዑሉው" ገፅ 185 ይመልከቱ።

“ዛት”ና ባህሪይ አይነጣጠሉም!

በመሠረቱ አንድን “ዛት” ከሌላው የሚለዩት መገለጫዎቹ ስለሆኑ ምንም አይነት ባህሪ የሌለው “ዛት” ጭራሽ ሊኖር አይችልም - በህሊና ሰመመን ካልሆነ በስተቀር! ባህሪያትም በገሀዱ ዓለም ለብቻቸው ከባህሪያቱ ባለቤት ተነጥለው ሊኖሩ እንደማይችሉ ጥቆማ አልፏል! ስለሆነም የአላህን ባህሪያት በሙሉ ወይም በከፊል ማስተባበል የመኖር ህልውናውን በሙሉ ወይም በከፊል እንደ ማስተባበል ነው!

ሰለፎች ይህንን እውነታ አስቀድመው ስለተረዱ የ“ተዕጢል” ጎራዎች የሚያመልኩት የሌለ ባዶ ኢምንትን (عدم) እንደሆነ ይናገሩ ነበር! ለአብነትም ያህል፡-

➢ ታላቁ ኢማም ***ሐም-ማድ ኢብኑ ዘይድ*** (179 ዓ.ሂ) እንዲህ ይላሉ፡-

«مَثَلُ الْجَهْمِيَّةِ مَثَلُ رَجُلٍ قِيلَ لَهُ: أَفِي دَارِكَ نَخْلَةٌ؟ قَالَ: نَعَمْ. قِيلَ: فَلَهَا خُوصٌ؟ قَالَ: لَا. قِيلَ: فَلَهَا سَعَفٌ. قَالَ: لَا. قِيلَ: فَلَهَا كَرَبٌ؟ قَالَ: لَا. قِيلَ: فَلَهَا جِذْعٌ؟ قَالَ: لَا. قِيلَ: فَلَهَا أَصْلٌ؟ قَالَ: لَا. قِيلَ: فَلَا نَخْلَةَ فِي دَارِكَ!»

«የጀህሚይ-ያዎች ምሳሌ ልክ *“በግቢህ ውስጥ ዘንባባ አለ?”* ተብሎ እንደተጠየቀ ሰው ነው፤

- እሱም *“አዎን!”* አለ።

- *“(ዛፉ) ቅጠል አለው?”* ተባለ።

- *“አይ!”* አለ!

- *“ዘርፍ አለው?”* ተባለ።

- *“አይ!”* አለ!

- *“ቅርንጫፍስ አለው?”* ተባለ።

- *“አይ!”* አለ!

- *“ግንድስ አለው?”* ተባለ።

- *“አይ!”* አለ!

- *“ስር አለው?”* ተባለ።

- *“አይ!”* አለ!

- *“እንግዲያውስ በግቢህ ውስጥ ዘንባባ የለም!”* ተባለ!»[1]

➢ ***አል-ኢማም ዐብዱላህ ኢብኑ’ል-ሙባረክ*** (181 ዓ.ሂ) እንዲህ ብለዋል፡-

(1) “ሸርሑ መዛሂቢ አህሊ’ስ-ሱን-ናህ” ሊብኒ ሻሂን ገፅ 23፣ “ኢብጣሉ’ት-ተእዊላት ሊአኽባሪ’ስ-ሲፋት” ሊ’ል-ቃዲ አቢ የዕላ (1/55)፣ “አል-ሑጅ-ጃህ ፊ በያኒ’ል-መሐጅ-ጃህ” ሊአቢ’ል-ቃሲም አት-ተይሚይ (1/441)

«لَيْسَ تَعْبُدُ الْجَهْمِيَّةُ شَيْئًا!»

*«ጀህሚይ-ያዎች ምንም ነገር አያመልኩም!»*[1]

- በሌላም ጊዜ እንዲህ ብለዋል፡-

«..فَإِنَّهُمْ يَجْعَلُونَ رَبَّكَ الَّذِي تَعْبُدُ لَا شَيْءَ!»

*«..እነርሱ የምትገዛው ጌታህን የሌለ ነገር ያደርጉታልና!»*[2]

➢ ***አል-ኢማም የዚድ ኢብኑ ሃሩን*** (206 ዓ.ሂ) እንዲሁ ተመሳሳይ ንግግር አላቸው።[3]

➢ ***አል-ኢማም ሙሐመድ ኢብኑ'ል-ሐሰን አሽ-ሸይባኒ*** (189 ዓ.ሂ) እንዲህ ብለዋል፡-

(1) "አስ-ሱን-ናህ" ሊዐብዲ'ላህ ኢብኒ'ል-ኢማሚ አሕመድ (1/109)

(2) "አስ-ሱን-ናህ" ሊዐብዲ'ላህ ኢብኒ'ል-ኢማሚ አሕመድ (1/110)

(3) "አስ-ሱን-ናህ" ሊ'ል-ኸል-ላል (5/91)፣ "አል-ኢባናህ" ሊብኒ በጥ-ጣህ (2/100)

«..فَمَنْ قَالَ بِقَوْلِ جَهْمٍ فَقَدْ فَارَقَ الْجَمَاعَةَ؛ لِأَنَّهُ قَدْ وَصَفَهُ بِصِفَةِ لَا شَيْءَ!»

*«..የጀህምን ንግግር የተናገረ ከሙስሊሞች ስብስብ አፈንግጧል! ምክንያቱም ጭራሽ በሌለ ነገር መገለጫ ገልፆታልና!»*[1]

➢ **የኢማሞች ኢማም በመባል የሚታወቁት *ኢብኑ ኹዘይማህ*** (311 ዓ.ሂ) **እንዲህ ብለዋል፡-**

«..وَجَلَّ رَبُّنَا عَنْ مَقَالَةِ الْمُعَطِّلِينَ، وَعَزَّ أَنْ يَكُونَ عَدَمًا كَمَا قَالَهُ الْمُبْطِلُونَ، لِأَنَّ مَا لَا صِفَةَ لَهُ عَدَمٌ! »

*«ጌታችን ከሙዐጥ-ጢላህ ንግግር የላቀ ሆነ! ሀሰተኞች እንደሚሉትም የሌለ ኢምንት ከመሆን የጠራ አሸናፊ ሆነ! - ምክንያቱም (ምንም) ባህሪ የሌለው ነገር = የማይገኝ ኢምንት ነውና!»*[2]

➢ **ታዋቂው የኢስላም ሊቅ *አል-ኢማም ኢብኑ ዐብዲ'ል-በር*** (463 ዓ.ሂ) **እንዲህ ይላሉ፡-**

«..وَيَزْعُمُونَ أَنَّ مَنْ أَقَرَّ بِهَا مُشَبِّهٌ، وَهُمْ عِنْدَ مَنْ أَثْبَتَهَا نَافُونَ لِلْمَعْبُودِ!»

---

(1) "ሸርሑ ኡሱሊ'ዕቲቃዲ አህሊ'ስ-ሱን-ነቲ ወል-ጀማዐህ" ሊ'ል-ላለካኢይ (2/432)

(2) "አት-ተውሂድ" ሊ'ብኒ ኹዘይማህ (1/26)

*«..በነርሱ (በአላህ ባህሪያት) ያመነ አመሳሳይ እንደሆነ (ሙዐጥ-ጢላህ) ይሞግታሉ! እነርሱ (የአላህን ባህሪያት) ያፀደቁት ዘንድ የአምላክን (መኖር) የሚያፋርሱ ናቸው!»*[1]

✷ እነዚያ የሰለፍ ሊቃውንት ከላይ የሰፈረው ድምዳሜ ላይ የደረሱት ነገሩን በተዘዋዋሪ የሚያስገነዝቡ የቀደምት ጀህሚይ-ያዎችን ንግግሮች በማስተዋል ብቻ እንደሆነ ከታወቀ የኋለኞቹ ስለ አላህ በድፍረት የሚናገሩትን የሚከተለውን ቁልጭ ያለ አፍራሽ ሀተታ ቢሰሙ ኖሮ ምን ይሉ ነበር፡-

*«ليس داخلَ العالَمِ ولا خارجَهُ، ولا محايثا له ولا مباينا، ولا متّصلا به ولا منفصلا عنه، ولا فوق ولا تحت..!!»*

ትርጉሙም፡- *«በፍጥረተ-ዓለሙ ውስጥ አይደለም፤ (ከፍጥረተ-ዓለሙ) ውጭም አይደለም! በርሱ (ድንበር) ወስጥ የገባም አይደለም፤ የወጣም አይደለም! ከርሱ ጋር የተያያዘም አይደለም፤ የተነጠለም አይደለም፤ ከላይም አይደለም፤ ከታችም አይደለም!..»*!![2]

---

(1) “አት-ተምሂድ” ሊ'ብኒ ዐብዲ'ል-በር (7/145)

(2) እንደ አሽዐሪ-ያህ ያሉ ጎራዎች የሚያስተጋቡትን ይህንን መሰል ቃል በሰለፎች ዘመን የነበሩት የተዕጢል አቀንቃኞች በግልፅ ለመናገር አብዛኛውን ጊዜ አይደፍሩም ነበር! ከዚህ ይልቅ *“አላህ በቦታ ስለማይገደብ ሁሉም ቦታ ነው ያለው!”* ማለትን ነበር የሚመርጡት። ያኔ አላህ ከዐርሽ =>

*የቀድሞው የአሽዐሪይ-ያህ መንገድ እውነተኛ ጠንሳሽ የሆነው ኢብኑ ኩል-ላብ* (243 ዓ.ሂ) እንኳ እንዲህ ይላል፡-

---

=> በላይ አለመሆኑን መናገር እጅግ የሚያሳቅቅ አስገራሚ ትንግርት በመሆኑ የተነሳ ከጥቂት አጋጣሚዎች በስተቀር በግልፅ ባይናዘዙም ይህንን የተረዱ ዑለማዎች ግን በመገረም ያጋልጧቸው ነበር! ይህንን ከሚያሳዩ ጥቅሶች መካከል፡-

ታላቁ ኢማም ***ሐም-ማድ ኢብኑ ዘይድ*** (179 ዓ.ሂ) ስለ ጀህሚይ-ያዎች እንዲህ አሉ፡- *«እነርሱ የሚጥሩት (የሚዘይዱት) 'በሰማይ ምንም* (አምላክ) *የለም' ለማለት ነው!»* ["አስ-ሱን-ናህ" ሊዐብዲ'ላህ ኢብኒ አሕመድ (1/117-118)፣ "ኽልቁ አፍዓሊ'ል-ዒባድ" ሊ'ል-ቡኻሪይ ገፅ 31፣ "አስ-ሱን-ናህ" ሊ'ል-ኸል-ላል (5/127)]

በተመሳሳይ መልኩ ***ዐብ-ባድ ኢብኑ'ል-ዐው-ዋም*** (185 ዓ.ሂ)፡- *«ቢሽር አል-መሪሲን እና ጓዶቹን አናግሬያቸዋለሁ! የንግግራቸው መጨረሻ የሚመለሰው "በሰማይ ምንም የለም!" ወደሚለው (ነጥብ) እንደሆነ አይቻለሁ!»* ["አስ-ሱን-ናህ" ሊአብዲ'ላህ ኢብኒ አሕመድ (1/126-127)፣ "አስ-ሱን-ናህ" ሊ'ል-ኸል-ላል (5/113)]

ይህን መሰል የመገረም ንግግር ከተናገሩት ኢማሞች መካከል፡- ***አይ-ዩብ አስ-ሰኽቲያኒ*** (131 ዓ.ሂ)፣ ***ጀሪር ኢብኑ ዐብዲ'ል-ሐሚድ*** (187 ዓ.ሂ)፣ ***አቡ በክር ኢብኑ'ል-ዐይ-ያሽ*** (194 ዓ.ሂ)፣ ***ዐብዱ'ር-ረሕማን ኢብኑ መህዲ*** (198 ዓ.ሂ) እና ሌሎች ይገኛሉ።

ሆኖም ዘመን ሲገፋ፣ እውቀት ሲጠፋ፣ ጥመት ሲስፋፋ የጥንቶቹ ሙዐጥ-ጢላህ የሚያለባብሱትን የኋለኞቹ አይን አውጥተው ገለጡት! አልፈውም አላህ ከዐርሹ በላይ መሆኑን የሚያረጋግጡ ሙስሊሞችን በሙሉ በከሃዲነት ፈረጁ! ወይ ፈተና!

«وأَخْرَجُ من النظر والخبر قولُ من قال: لا هو في العالم ولا خارجٌ منه! فنفاه نفيًا مستويًا؛ لأنه لو قيل له: صفه بالعدم، ما قدر أن يقولَ فيه أكثرَ منه..!»

*«ከአእምሯዊ ምልከታም ከነጋሪት ማስረጃዎችም (ቁርአንና ሐዲሥ) ይበልጥ ያፈነገጠው ደግሞ "በፍጥረተ-ዓለሙ ውስጥም አይደለም፤ ውጭም አይደለም!" በማለት (ሁለቱንም) እኩል የሚያፈርሰው ተናጋሪ ንግግር ነው! ምክንያቱም "(አላህን) ጭራሽ በሌለ ኢምንትነት መገለጫ ግለፀው!" ቢባል ከዚህ የበለጠ ንግግር ሊናገር አይችልምና!»*[1]

---

**ያሳለፍናቸው የሶስቱ መሠረቶች ማብራሪያዎች የሁለቱንም ጠርዘኛ ምድቦች "የማመሳሰል" በሽታ ከመሠረቱ የሚፈነቅሉ ፍቱን መድሃኒቶች መሆናቸውን አይተናል። ብዙሃኑ የሙስሊም ህብረተሰብ እነዚህን መሠረቶች ባሳለፍነው መልኩ መተንተንና ማስረዳት ባይችል እንኳ እውነታውን በፍልስፍና ባልተበከለ ልቦና ስለሚያገናዝብ በአላህ ስሞችና ባህሪያት ዙሪያ ያለው እምነት እነዚያ ቡድኖች ከገቡበት ውጥንቅጥ የጠራ ነው።**

●●●

(1) "በያኑ ተልቢሲ'ል-ጀህሚይ-ያህ" ሊሸይኺ'ል-ኢስላም (1/44)፣ "ደርኡ ተዓሩዲ'ል-ዐቅሊ ወን-ነቅል" (6/119) (ኢብኑ ቴሚያህ ... )

# ክፍል አራት

## ሸሪዓዊ ልባስ!

ሙዐጥ-ጢላዎች አላህ ራሱን የገለፀባቸውን ባህሪያት እንዳሉ ተቀብሎ ማፅደቅ እርሱን ከፍጡራን ጋር ማመሳሰል እንደሆነ በመሞገት መልዕክታቸውን ለመቀየር ደፋ ቀና የሚሉት ከቁርኣን ወይም ከትክክለኛ ሐዲሥ መረጃ አግኝተው እንዳልሆነ ግልፅ ነው! ነገሩ ሌላ ነው![1] ሆኖም አብዛኛዎቹ በሸሪዓ ልባስ ብዥሃኑን ለመሸንገል በየአጋጣሚው የሚያነሷቸው አንዳንድ ጥቅል ጥቅሶች እንዳሉ ይታወቃል! አንድ የቁርኣን አንቀፅ በምሳሌነት እንውሰድ፡-

﴿لَيْسَ كَمِثْلِهِۦ شَيْءٌ ۖ وَهُوَ ٱلسَّمِيعُ ٱلْبَصِيرُ﴾ [الشورى: ١١]

➥ «እንደርሱ ያለ (አምሳያ) ምንም የለም፤ እርሱም ሰሚውና ተመልካቹ ነው፡፡»[አሽ-ሹራ 11]

እስካሁን ባሳለፍናቸው ማብራሪያዎች ይህን መሰል ጥቅል የቁርኣን አንቀፆች ለአላህ የፀደቁትን ዝርዝር ባህሪያት የሚያፋርስ መልእክት እንደሌላቸው በተለያዩ መንገዶች ያረጋገጥን ቢሆንም ጥቂት **ተያያዥ ጥቆማዎችን** በአጭሩ እናክል፡-

1- ይህንና መሰል የቁርኣን አንቀፆችን ያወረደው ሌሎች ባህሪያቱ የተረጋገጡባቸውን አንቀፆችንም ያወረደው ጌታ ራሱ ስለሆነ

(1) የነገሩን እውነተኛ ገፅታ አለፍ ብለው ይደርሱበታል!

የሚጋጩ መልዕክቶች ሊኖሯቸው አይችልም! ስለዚህ በሁሉም ማመን ግዴታ ነው። ይህ የሚቻለው ደግሞ ሁሉንም ባህሪያቱን ከምንም ጋር ሳያመሳስሉ በማፅደቅ ብቻ እንደሆነ ተብራርቷል።

2- ስለባህሪያቱ ሁኔታ ሳያነሱ መልዕክታቸውን ለርሱ ብቻ በሚገባ መልኩ ማፅደቅ አላህ ወድቅ ያደረገው ማመሳሰል ውስጥ እንደማይካተት የታወቀ ነው፤ ምክንያቱም የስያሜ መገጣጠም የይዘትን መመሳሰል አያመላክትምና! የዚህ ማብራሪያም ከምሳሌዎች ጋር አልፏል።

3- የላይኛው አንቀፅ ሁለት ዋና ዋና መልእክቶችን አዝሏል፡-
«ሇንደርሱ ያለ (ለምሳያ) ምንም የለም» የሚለው የአንቀፁ የመጀመሪያ ክፍል ፈጣሪን ከፍጡር ጋር በምንም መልኩ ማመሳሰል ውድቅ መሆኑን የሚያስገነዝብ ሲሆን፤ «እርሱም ሰሚውና ተመልካቹ ነው» የሚለው መቋጫ ደግሞ መስማትና ማየትን ጨምሮ ለአላህ በመረጃ የተረጋገጡትን ስሞችና ባህሪያት ተቀብሎ ማፅደቅ የግድ መሆኑን ይጠቁማል። ስለሆነም መረጃነቱ ለኛ እንጂ ለነሱ አይደለም! የዚህን አንቀፅ መልእክት ራሱ በትክክል ተግባራዊ አድርገው ቢሆን ወደ እውነተኛው ጎዳና በተመሩ ነበር! ይህን የሚያፀናው ደግሞ የሚቀጥለው ነጥብ ነው፡-

4- አንድ ነገር የሚወደሰው በመገለጫዎቹ ምጥቀት እንጂ በባህሪ-አልባነቱ እንዳልሆነ ግልፅ ነው! «ሇንደርሱ ያለ (ለምሳያ) ምንም የለም» ማለቱ ውዳሴ በመሆኑ **የመለያ ባህሪያቱን መብዛት** እንጂ ተቃራኒውን ሊያመላክት አይችልም! ምክንያቱም ቃሉ የሚያሳየው ባህሪያት እንደሌሉት ቢሆን ኖሮ ባዶነትን የሚጠቁም ይሆን ነበር፤

ባዶነት ደግሞ እንደስያሜው ባዶነትን እንጂ ምሉዕነትን እንደማያስጨብጥ ከዚህ በፊት አይተናል።

5- እንደነሱ አባባል አላህ እጅግ ብዙ ቦታዎች ላይ በተለያዩ ስልቶች ራሱን የገለፀባቸውን ጉልህ መልዕክቶች መቀበል እንደሌለብን የሚያመላክተን እንዲህ በደፈናው አምሳያ እንደሌለው በመንገር ብቻ ከሆነ ንግግሩ በብዙኃኑ ሙስሊሞች የማይፈታ የቅኔ ቋጠሮ ነው ማለት ነው!! ቃሉ ከእንዲህ ያለ መድበስበስ ፍፁም ለጠራውና ለላቀው ጌታችን ምስጋናና ውዳሴ የተገባ ነው!

እንዴ! የላይኛውን ጥቅል አንቀፅ እንደ መረጃ አጣቅሶ አላህ ራሱን በተደጋጋሚ የገለፀበትን እዝነት፣ ቁጣ፣ መውደድ፣ መጥላት፣ መናገር፣ በዐርሹ ላይ መሆን፣ ፊት፣ እጅ ..እና ሌሎች በጣም ብዙ መገለጫዎችን በአንድ ስንዝር መደምሰስ እኮ አላህ በምድር ላይ ያለውን ነገር ሁሉ ለኛ እንደፈጠረልን የተናገረበትን ጥቅል አንቀፅ(1) ተመርኩዞ እንደ ስርቆት፣ ዘረፋ፣ ዝሙት፣ አስካሪ መጠጥ፣ የአሳማ ስጋን መብላት.. ያሉ ግልፅ ሸሪዓዊ ክልከላዎችን ከማስተባበል የከፋ ነው። ምክንያቱም አላህ ስለራሱ የገለፀባቸው አንቀፆች ስለ ሐላልና ሐራም ህግጋት ከገለፀባቸው ይበልጥ የጐሉና የበዙ ናቸውና!

●●●

(1) ﴿هُوَ ٱلَّذِى خَلَقَ لَكُم مَّا فِى ٱلْأَرْضِ جَمِيعًا﴾ [البقرة: ٢٩]
➥ «እርሱ ያ በምድር ያለውን በሙሉ ለናንተ የፈጠረ ነው::»[አል-በቀራህ 29]

## ክፍል አምስት

### የበሽታው እውነተኛ መነሻ!

“ታዲያ ግን እነዚያ የጥመት አራጋቢዎች እንዲያው ምን ነክቷቸው ነው ጥርት ያለውን የነብያት ጐዳና የሚፃረሩት ጃል?!” ብለው ብዙዎች ሲጠይቁ በህሊናዬ ይታየኛል! **መልሱም፡-**

**መሪዎቻቸው በዋነኝነት ሀይማኖታዊ ምራቻን የሚያፈላልጉት በቁርኣን ወይም በነብያት አስተምህሮት ውስጥ ስላልሆነ ነው!**[1]

“እንዴት?” ማለት ጥሩ!

ከላይ እንዳየነው ቀጥተኛውን መንገድ በመልቀቅ የጥመት ጉዞ የጀመሩት ቡድኖች የብዥታቸው ዋነኛ መነሻ ምን እንደሆነ አውቀናል፤ የማመሳሰል ብዥታ! ብዙዎች የማይረዱት ከባድ እውነታ ግን ለዚህ መነሻ ሌላ መነሻ መኖሩ ነው። በርዕሱ ላይ

(1) ይህ በዚህ ጉዳይ ላይ የተሳሳተን ሁሉ የሚመለከት ፍርድ ባይሆንም ዋነኞቹን ያለ ምንም ማጋነን ይመለከታል፤ እንዲያው ለመሆኑ የቁርኣንና የሐዲሥ መመሪያዎችን *“ቃላዊ ማስረጃዎች እንጂ አእምሯዊ ስላልሆኑ እርግጠኝነትን አያወርሱም!”* እያሉ ከሚያጣጥሉ አንደበቶች ምን ይጠበቃል?!
*“የቁርኣንና የሐዲሥ ማስረጃዎች እርግጠኝነትን አያስገኙም!”* የሚለው አቋም የሙዕተዚላዎችና የአብዛኛዎቹ አሽዐሪይ-ዮች እምነት መሆኑን በግልፅ ከተናዘዙት የአሽዐሪይ-ያህ አቀንቃኞች መካከል *አል-ጁርጃኒይ* አንዱ ነው። [“ሸርሑ’ል-መዋቂፍ” (“አል-ቃኢድ ኢላ ተስሒሒ’ል-ዐቃኢድ” ሊ’ል-ሙዐል-ሊሚይ ገፅ 44 ላይ እንደተመለከተው)]

ካሏቸው ሁሉም ዝርዝር ብዥታዎች በስተ-ጀርባ ያለ አንድ ጉዳይ አለ! “ዒልሙ’ል-ከላም”!

### “ዒልሙ’ል-ከላም”

ይህ ዘርፍ ስለፈጣሪ መኖርና መሰል እምነታዊ ጉዳዮች ሀይማኖታዊ **ባልሆነ** መንገድ የሚያጠና የተምታታ **ፍልስፍናዊ አካሄድ** ሲሆን አብዛሃኛዎቹ መርሆዎቹ ከጥንቶቹ የግሪክ ፈላስፋዎች አስተምህሮት የተቀዱ ናቸው!!

የተለያዩ የጥመት ጭፍራዎች በአላህ ስሞችና ባህሪያት ዙሪያ በተሳሳተ የእምነት ጎዳና ላይ እንዲያዘግሙ እውነተኛ መነሻ የሆናቸው ይኸው ፍልስፍና ነው! ይዘቱ ቀጥተኛ አእምሯዊ ስልቶች ላይ የተገነባ ቢመስላቸውም እውነታው ግን በውስጡ ከትክክለኛ ግንዛቤ የራቁ መንደርደሪያ ሀሳቦችና ድምዳሜዎች የተሰገሰጉበት ረጅም የሙግት ጎዳና መሆኑ ነው!

በዚሁ አካሄድ ላይ ዕድሜያቸውን የፈጁ ሙግተኞች ከቀናው ቁርአናዊ መንገድ ከማፈንገጣቸው ባሻገር መጨረሻቸው ግራ መጋባት፣ መጠራጠርና መቆጨት መሆኑን የአብዛኞዎቹ ታሪክ ይመሰክራል![1] ቀድሞውኑ በእምነት ጉዳይ ላይ የፈጣሪን ግልፅ መመሪያ ወደኋላ ገሸሽ አድርጎ ወደ ከሀዲያን የሀሳብ ቅርጫት የማምራት ውጤት ይህ እንጂ ምን ሊሆን ይችላል?! እንዴትስ

(1) የተወሰኑ ምሳሌዎችን ለማግኘት “ደርኡ ተዓሩዲ’ል-ዐቅሊ ወን-ነቅል” (1/159-163)፣ “አስ-ሰዋዒቁ’ል-ሙርሰላህ” (2/664-669) ይመልከቱ።

የዚህ ታላቅ መለኮታዊ ሀይማኖት ባለቤቶች በእምነታቸው መሠረቶች ላይ የሌሎች ጥገኛ ሊሆኑ ይችላሉ?! ስለፈጣሪ ባላወቁ ከሀዲያን ፈሊጥ ላይ ተመርኩዞ ስለፈጣሪ ለማወቅ መኳተን ተኩላን ለእረኝነት ከመምረጥ አይብስም?!

በመሆኑም የቀደምት ትውልድ ዑለማዎች በአንድ አቋም ይህንን መንገድና ባለቤቶቹን አጥብቀው ያወግዙ ነበር![1] አንድ ምሳሌ ብቻ እንይ:-

➢ *አል-ኢማም* ***አሽ-ሻፊዒይ*** እንዲህ ብለዋል:-

«لأَنْ يُبْتَلَى الْعَبْدُ بِكُلِّ مَا نَهَى اللَّهُ عَنْهُ سِوَى الشِّرْكِ، خَيْرٌ لَهُ مِنَ "الْكَلامِ"، وَلَقَدِ اطَّلَعْتُ مِنْ أَصْحَابِ الْكَلامِ عَلَى شَيْءٍ، مَا ظَنَنْتُ أَنَّ مُسْلِمًا يَقُولُ ذَلِكَ!»

*«አንድ ሰው ከ“[ዒልመ’ል]-ከላም” ይልቅ ከሽርክ በስተቀር ባሉት አላህ በከለከላቸው* ***ሁሉም*** *(ሀጢያቶች) ቢፈተን ይሻለዋል! በርግጥ ከ“ከላም” ባለቤቶች ሙስሊም ይናገረዋል ብዬ ያልጠረጠርኩትን ነገር ሰምቻለሁ!»*[2]

---

(1) በዚህ ረገድ የተናገሩትንም በ“ሰነድ” ያሰፈሩ በርካታ መዛግብት ይገኛሉ። ለምሳሌ ያህል:- “ዘም-ሙ’ል-ከላሚ ወአህሊሂ” የተባለውን የ*አቡ ኢስማዒል አል-ሀረዊ* (481 ዓ.ሂ) ባለ **አምስት ጥራዝ** ጥንቅር ይመልከቱ።

(2) “አዳቡ’ሽ-ሻፊዒይ ወመናቂቡሁ” ሊብኒ አቢ ሓትም ገፅ 137፣ “ዘም-ሙ’ል-ከላሚ ወአህሊሂ” ሊአቢ ኢስማዒል አል-ሀረዊ (4/306-307) ቁጥር 1164፣ “ሒልየቱ’ል-አውሊያእ” ሊአቢ ኑዐይም (9/111-112)፣ “መናቂቡ’ሽ-ሻፊዒይ” ሊ’ል-በይሀቂይ (1/453-454)..እና ሌሎች መዛግብት ላይ በትክክለኛ ሰነድ ሰፍሯል።

ታዲያ ሰለፎች ይህንን መጤ አካሄድ እንዲህ የኮነኑት አንዳንዶች እንደሚገምቱት በአዳዲስ ፍልስፍናዊ ቃላት የተሞላ ስለሆነ ብቻ አይደለም፤ ከመሠረታዊ የዲን መርሆዎች ጋር ከመጣረስ አልፎ ወደ ክህደትና ጥርጣሬ አዘቅቶች አንሸራቶ ስለሚያስገባም ጭምር እንጂ!

**ለምሳሌ፡- *አል-ኢማም አቡ ዩሱፍ*** (182 ዓ.ሂ) እንዲህ ብለዋል፡-

«مَنْ طَلَبَ الدِّينَ بِالْكَلَامِ تَزَنْدَقَ..!»

*«ዲንን በ"ከላም" የፈለገ ሰው ዚንዲቅ (ከእምነት የወጣ ከሃዲ) ይሆናል..!»*(1)

✸ ታዲያ እንዴት ይህ ሰርጎ-ገብ ፍልስፍና የአላህን ባህሪያት እንዲያፋርሱ ምክንያት ሆናቸው?

ጉዱ እንዲህ ነው፡-

↻ የነሱ ዋነኛ ልፋትና ትልቁ ጥረት የፈጣሪን መኖር "አእምሯዊ" ብለው በሚጠሩት ፍልስፍናዊ መንገድ ማረጋገጥ ነው! ይህንንም የሁሉም ሰው **ተቀዳሚ** ግዴታ አድርገውታል!(1)

---

(1) "ሸርሑ ኡሱሊ'ዕቲቃዲ አህሊ'ስ-ሲን-ናህ" ሊ'ል-ላለካኢይ (1/166)፤ "አል-ኢባናህ" ሊ'ብኒ በጥ-ጣህ (አል-ኪታቡ'ል-አው-ወል) (2/537-538)፤ "ዘም-ሙ'ል-ከላሚ ወአህሊህ" (4/210)። *አል-ኢማም **ማሊክም** ይህንኑ ማለታቸው ተዘግቧል።*

ታዲያ ይህንን ለማረጋገጥ ሁሉም የሚከተሉትን ፍልስፍናዊ ቀመር "ደሊ'ሉ'ል-አዕራድ" (دليل الأعراض) ወይም "ደሊሉ ሑዱሚ'ል-ዓለም" (دليل حدوث العالم) ብለው ይጠሩታል። ይህ መንገድ ሀተታው የበዛ፣ ሀሳቡ የተንዛዛ፣ ቃናው የጠነዛ ከመሆኑ ጋር ለብዙ ንትርኮች በር የሚከፍት ደካማ ስልት ነው! እንዲያም ሆኖ ግን በአንድ ጎን በዚህኛው ስልት የፈጣሪ መኖርን ማረጋገጥና በሌላ ጎን በቁርኣንና በነብዩ (ﷺ) አስተምህሮት የተወሱትን አብዛኛዎቹን የፈጣሪ ባህሪያት ማፅደቅ የማይቻል እንደሆነ ያምናሉ! - አንዱ ሌላውን ያፋርሳልና! ስለሆነም "ብቸኛ" አድርገው የሚያምኑትን ይህን "አእምሯዊ ስልት" ከመተው የአላህ ባህሪያት የፀደቁባቸውን ቁርኣናዊና ሐዲሣዊ ማስረጃዎችን መጋፈጥ መረጡ፤ - የቻሉትን ትርጉሙን በመቆልመም፣ ያልቻሉትን ደግሞ...!!

የዚህን "ሚስጥር" ለመረዳት የስልቱን ይዘት በጣም በማሳጠር እንደሚከተለው እንገልፀዋለን!

(1) አልፎ ተርፎም ይህንን ሀተታ ጭራሽ ሳያውቁ ንፁህ የእምነት ኑሮ የሚገፉትን ብዙሃኑ ህዝበ-ሙስሊም አስመልክቶ ተወዛግበዋል፦ እምነታቸው ትክክል ነው ወይስ ውድቅ? ወይስ ትክክል ከመሆኑ ጋራ በህይወቱ አንዴም ቢሆን የፈጣሪን መኖር በዚህኛው ስልት ያላረጋገጠ ሁሉ ወንጀለኛ ይሆናል?! ይህ ፍርዳቸው ወደዱም ጠሉም ሰሓቦችንና ቀደምት ትውልዶችን የሚመለከት ይሆናል! ምክንያቱም እነርሱ ይህንን ፍልስፍናዊ መንገድ የሚያውቁና የሚያራምዱ እንዳልነበሩ ግልፅ ስለሆነ!!

*“ማንኛውም ነገር ከሁለት ክፍሎች አይወጣም!” አሉ! “ወይ ‘ጀውሀር’ (جوهر) ነው! ወይ ደግሞ ‘ዐረድ’ (عَرَض)!” “‘ጀውሀር’ የሚባለው ገሀዳዊ ግኝት ያለው ቁስ አካል ሲሆን፤ ሲገጣጠም ‘ጂስም’ ይሆናል! ‘ዐረድ’ ደግሞ የ‘ጂስም’ መገለጫ (ባህሪ) ነው!”* አሉ።

*“ማንኛውም ‘ጂስም’ እንደ መንቀሳቀስ ወይም አለመንቀሳቀስ ካሉ የ‘ዐረድ ክስተቶች’ ስለማይነጠል (ጀውሀርና ዐረድ) አንዱ ሌላውን ቀድሞ አይገኝም! ሌላን ነገር ቀድሞ ያልተገኘ ሁሉ ከጊዜ በኋላ የተገኘ መጤ ነው፤ ማንኛውም መጤ ነገር ደግሞ ለመገኘት የግድ አስገኚ ያስፈልገዋል።”*

*“በዚህ ‘ማስረጃ’ መሠረት በዓለማችን ላይ ያሉት ነገሮች ሁሉ እያንዳንዳቸው የ‘ጀውሀር’ና የ‘ዐረድ’ ቅንብር በመሆናቸው ከጊዜ በኋላ የተገኙ መጤ ናቸው፤ ማንኛውም መጤ ነገር ደግሞ የግድ አስገኚ ስለሚያስፈልገው ይህ አለም አስገኚ (ፈጣሪ) አለው ማለት ነው!”* ይላሉ!

***“በዚህ መሠረት ጌታ “ዐረድ” (ባህሪያት)ን የሚያስተናግድ ከሆነ “ጂስም” ይሆናል! “ጂስም” ደግሞ ፍጡር እንጂ ፈጣሪ አይሆንም!”*** የሚለው ድምዳሜ ላይ ደረሱ![1]

(1) ሁሉም ሙዓጥ-ጢላዎች ስለ አላህ ባህሪያት ያላቸው አፍራሽ አቋም የተገነባበት ዋነኛ መሠረት ይህ ነው፤ ሆኖም “መረጃውን” በመተንተን ሂደት ላይ በጥቂቱ የሚለያዩ አቀራረቦችንና ቅደም-ተከተሎችን =>

↳ እንግዲህ ሙስሊሞች ሆይ! የነገሩ ሁሉ እውነተኛ መነሻ ይህ ነው! የአላህን ባህሪያት የሚያፋርሱበት እውነተኛው “መረጃቸው”ም ይኸው ነው!- ፍልስፍናውን የሸሪዓ ልባስ ለማልበስ ያለ ቦታው የሚመዟቸው አንቀፆች ቢኖሩም!!

**ጥቆማ**

↳ ይህን ፍርክርክ ስልት ተጠቅሞ አላህ በግልፅ ቋንቋ ለራሱ ያፀደቃቸውን መገለጫዎች ማፋረስ ከመሠረቱ ውድቅ የሆነ አካሄድ መሆኑን በብዙ መንገዶች የሚያረጋግጡ አስተማማኝ ሸሪዓዊና ቀጥተኛ አእምሯዊ መልሶች እንዳሉ የታወቀ ነው። ሆኖም በዋነኝነት የተፈለገው የችግሩን እውነተኛ መንስኤ ማመላከት ስለሆነ በሚከተሉት ጥቂት ጥቆማዎች እንብቃቃለን!፡-

**1-** በቅድሚያ የፈጣሪን መኖር ማወቅ አእምሯዊ ብቻ ሳይሆን እጅግ ጉልህ ህዋሳዊና ተፈጥሯዊ እውነታ (فطرة) በመሆኑ አብዛኛዎቹ ከሀዲያን እንኳ ያልተጠራጠሩበት መስክ ነው! ታዲያ እነዚያ የ“ከላም” አንጃዎች እድሜያቸውን የሚፈጁት እነ *አቡ ጀህል* እና *አቡ ለሀብ* እንኳ ቀድሞውኑ ያልተጠራጠሩበትን ጉዳይ ለማረጋገጥ መሆኑ አያሳዝንም?!

---

=> ሊጠቀሙ ይችሉ ይሆናል! ሙዕተዚላዎችና የቀድሞዎቹ አሽዐሪይ-ዮች በአንዳንድ ባህሪያት ዙሪያ የተለያዩ አቋሞችን ያንፀባረቁት በዚሁ ሂደት የ“ዐረድ”ን ትርጓሜ አስመልክቶ በነበራቸው ቀጭን ልዩነት የተነሳ ነው። ፅሁፉን እንዳላወሳሰበው ባልሰጋ ኖሮ ዝርዝሩን ከነምላሹ ባሰፈርኩ ነበር!

📖﴿قَالَتْ رُسُلُهُمْ أَفِي ٱللَّهِ شَكٌّ فَاطِرِ ٱلسَّمَٰوَٰتِ وَٱلْأَرْضِ﴾[إبراهيم:١٠]

➥ «መልዕክተኞቻቸውም “በአላህ ደግሞ ጥርጥር አለ እንዴ?- የሰማያትና የምድር ፈጣሪ በሆነው?!” አሉ፡፡»[ኢብራሂም 10]

**2-** ይህን ስልት የዲን አካል አድርጎ መቁጠር ውግዝ የፈጠራ ተግባር ከመሆኑ ባሻገር እንዲያውም በነብያት ጭራሽ የማያምኑ ፈላስፋዎች[1] የተጓዙበት መንገድ ነው! ይህንን የራሳቸውን ስልት የቀረቀሩትም የነብያትን መልዕክት ከመሠረቱ የማይቀበሉ በመሆናቸው ነው![2] ነብያት ወለል ባሉ በርካታ ስልቶች አላህን ብቻ ወደ ማምለክ ከመጣራታቸው ጋራ ሰዎች የፈጣሪን መኖር በዚህኛው መንገድ ማመን እንዳለባቸው አንድም ጊዜ እንዳላስተማሩ ሁሉም ያውቃል! የዚህ ህዝበ-ሙስሊም ቀደምት ትውልዶችም በፍፁም ይህንን መንገድ አልተጠቀሙም፤ በተቃራኒው ስለዚህ ግርድፍ ፍልስፍና የሰሙት ሁሉ ሲቃወሙትና ሲያጣጥሉት ነበር።

➢ *አል-ኢማም* **አቡ ሐኒፋ** እንዲህ ተብለው እንደተጠየቁ ተዘግቧል፡-

«مَا تَقُولُ فِيمَا أَحْدَثَ النَّاسُ مِنَ الْكَلَامِ فِي الْأَعْرَاضِ وَالْأَجْسَامِ؟»

---

(1) እንደ *አሪስቶትል/አሪስ ጣጣሊስ ያሉ!*

(2) “*አል-ችንያህ ዐቂ’ል-ከላሚ ወአህሊሂ” የተሰኘውን የአል-ኢማም አል-ኸጥ-ጣቢይ* (388 ዓ.ሂ) አጭር መፅሀፍ ይመልከቱ።

*«ሰዎች ስለ “አዕራድ” (የ“ዐረድ” ብዙ ቁጥር) እና «አጅሳም» (የ“ጂስም” ብዙ ቁጥር) ስለፈጠሩት ወሬ ምን ይላሉ?»*

መልሳቸው እንደሚከተለው ነበር፦

فَقَالَ:«مقَالَاتُ الْفَلَاسِفَةِ! عَلَيْكَ بِالْأَثَرِ وَطَرِيقَةِ السَّلَفِ، وَإِيَّاكَ وَكُلَّ مُحْدَثَةٍ؛ فَإِنَّهَا بِدْعَةٌ!»

- *«የፈላስፋዎች ንግግር (ነው)! አደራህን “አሠር” (የረሱልና የሰሀባዎችን ፋና) እና የቀድሞዎቹን ትውልዶች (ሰለፎች) መንገድ (ተከተል!)፤ (አደራህን) ሁሉንም አዳዲስ (መንገዶች) ተጠንቀቅ፤ እነሱ ቢድዓህ ናቸውና!»*[1]

**3-** ስልቱ ከብዙ ልፋት በኋላ የፈጣሪን መኖር የሚያመላክት ቢሆን ኖሮ እንኳ ፍንትው ያለውን የእውነታዎች ሁሉ እውነታ እንደ ድብቅ ጉዳይ በእንዲህ ያለ ጥምዝምዝና ውስብስብ መንገድ ለማረጋገጥ መሞከር ትልቅ ስህተት ነው። ምክንያቱም ትክክለኛ አእምሮ የሚፈርደው የመረጃ አቀራረብ ስልት ድብቅ ነገርን አድማጩ በሚያምንበት ግልፅ መረጃ ማመላከት እንደሚገባ እንጂ በተቃራኒው ግልፁን እውነታ በድብቅ መንገድ ለማረጋገጥ መኳተን አይደለም።

(1) “ዘም-ሙ’ል-ከላሚ ወአህሊሂ” ሊ’አቢ ኢስማዒል አል-ሀረዊ (4/213-214) ቁጥር= 1015 ፤ “አሓዲሥ ፊ ዘም-ሚ’ል-ከላሚ ወአህሊሀ” ሊአቢ’ል-ፊድል አል-ሙቅሪእ ገፅ 86

➢ ***አቡ'ል-ሐሰን አል-አሽዐሪይ እንዲህ ይላሉ፡-***

«..كان ما يُستدَل به من أخباره – عليه السلام– على ذلك أوضح دلالةً من دلالة الأعراض التي اعتمد على الاستدلال بها الفلاسفة ومن اتبعها من القدرية، وأهلِ البدع المنحرفين عن الرسل – عليهم السلام –؛ من قِبل أن الأعراض لا يصح الاستدلال بها إلا بعد رتب كثيرة يطول الخلاف فيها، ويدِّق الكلام عليها..»

***«..በርሳቸው (በረሱልﷺ) ንግግሮች ላይ በመመርኮዝ መረጃን ለዚህ ጉዳይ ማቅረብ ፈላስፋዎችና እነሱን የተከተሏቸው እንደ 'ቀደሪይ-ያህ' (ሙዕተዚላህ) ያሉ ከመልዕክተኞች (መንገድ) ያፈነገጡ የቢድዓህ ባለቤቶች ከሚመረኮዙበት የ'አዕራድ' መረጃ ስልት ይበልጥ ግልፅ ነው! ምክንያቱም የ'አዕራድ' መረጃ ግቡን የሚመታው የረዘመ ውዝግብና የተወሳሰበ ንግግርን ካቀፉ ብዙ ደረጃዎች በኋላ ነው..!»***[1]

**4-** የዚህ ስልት አንዳንድ መንደርደሪያዎች በስህተት ላይ የተገነቡ በመሆናቸው በትክክለኛ አእምሯዊ ሂደት የሚፈለገውን ግብ በመምታት ፈንታ በተቃራኒው ብዙ አስከፊ መዘዞችን ያስከትላሉ! ብዙዎች ይህንን መጤ ስልት በመመርኮዛቸው የተነሳ ከላይ እንዳሳለፍነው የአላህን ህልውና በሚያፋርስ መልኩ መገለጫዎቹን

---

(1) "ሪሳላህ ኢላ አህሊ'ሥ-ሠግር" ሊአቢ'ል-ሐሰን አል-አሽዓሪይ ገፅ (105-106)

ሲንዱ ላስተዋለ ለማረጋገጥ የሚለፉት የፈጣሪ መኖርን ሳይሆን አለመኖርን ይመስላል!

እንዲያው ሌላው ቀርቶ በማያወላዳ ሁኔታ የፀደቁትን የአላህ መገለጫዎች ለማስተባበል ዋነኛ መነሻ ከመሆን ሌላ ምንም መዘዝ ባይኖረው ኖሮ እንኳ ውድቅ ለመሆኑ ይህ ብቻ በቂ ማስረጃ ይሆን ነበር! ታዲያ ከመቶ ያለፉ ሌሎች ክፉ መዘዞችን የሚያስከትል መሆኑ ከታወቀስ ምን ይባላል ጎበዝ?![1]

**5-** ይህ ስልት የተመሠረተባቸው አንዳንድ መንደርደሪያዎችና ፅንሰ ሃሳቦች አሻሚ ይዘት ያላቸው ከመሆናቸው ባሻገር እውነታን በሚጥስ መልኩ ለሚታለመው ውጤት እንዲውሉ የሚቆለመሙ ቃላትን ያማከለ ነው።

ለምሳሌ፡- "ዐረድ" የሚለው የባህሪ ስያሜ ውስጥ 'ድርጊቶችን' ሁሉ ያካትታሉ፤ *"ማንኛውንም 'ክስተት' (حوادث) መፈፀምና ማስተናገድም* ***መቀየር (ለውጥ)*** *በመሆኑ የፍጡር እንጂ የፈጣሪ መገለጫ አይደለም!.."* በማለት አሻሚ ቃል ይሰነዝራሉ! ይህን የሚሉት አላህ በሚሻ ጊዜ የሚፈፅማቸውን አድራጎታዊ መገለጫዎች ሁሉ በ'ክስተት' ስም ውድቅ ለማድረግ ነው! ይህንን ሲያራምዱም ለባህሪዎቹ የተለመዱ ቅጥያዎችን እየለጠፉ ነው። ለምሳሌ፡- በፈለገው ጊዜ መናገሩን *"'ክስተት' ነው!"* በማለት

(1) "ሙኽተሰር አስ-ሰዋዒቅ አል-ሙርሰላህ" (2/481) ይመልከቱ!

ያጣጥሉታል[1]፤ በቁርኣኑ እንዳፀደቀው በእለተ-ቂያማህ ለፍርድ መምጣቱን *"እንቅስቃሴ ነው..!"* በማለት ያስተባብሉታል። ምክንያቱም በነሱ ቤት መንቀሳቀስም ሆነ አለመንቀሳቀስ ሁለቱም ክስተት ናቸው! *"ክስተት ደግሞ መቀየር ነው! ፈጣሪ ደግሞ አይቀየርም!.."* ይላሉ።

→ በመሠረቱ መናገርም ይሁን መንቀሳቀስ ወይም አለመንቀሳቀስ "መቅቀየር" መሆናቸው የነሱ ፍልስፍናዊ አጠራር እንጂ ከነሱ ውጭ ያሉ ባለ አእምሮዎች የሚስማሙበት እንዳልሆነ ግልፅ ነው!

→ "የመንቀሳቀስ"ና "ያለመንቀሳቀስ" ማስፈራሪያን በተመለከተ በቅድሚያ ከዚህ በፊት እንደተብራራው ይህን መሰል በቁርኣንና በሐዲሥ የሌሉ ገለፃዎችን በአዎንታዊም ይሁን በአፍራሽ መልኩ አንጠቀምም! በቃ! በርዕሱ ላይ የቁርኣንና የሐዲሥን ገለፃ አንተላለፍም!

ሆኖም ይህንንና መሰል የሽብር ቃል የሚነዙ ሰዎች ከዚህ በስተጀርባ የሚያገኙት ተጨባጭ ውጤት እንደሌለ ሊያውቁ ይገባል! ምክንያቱም፡- የአላህ መምጣት እንደ ፍጡር የግድ መንቀሳቀስን የሚያስገነዝብ ከሆነ ቁርኣንና ትክክለኛ ሐዲሥ

---

(1) አሽ-ዐሪይ-ዮችና ማቱሪዲይ-ያዎች ከዚህ ለመሸሽ ብለው ነው *"ቁርኣንን የአላህ ቃል ብለን የምንጠራው በዘይቤያዊ ገለፃ ሲሆን ይህም ጥቅል መልዕክቱ ከአላህ ዘንድ የወረደ ከመሆኑ አንፃር ብቻ እንጂ ቃላቱና የፊደላቱ ክሽን ግን ፍጡር ነው"* በማለት በሙዕተዚላዎችና በሰለፎች መሃል ለመስፈር የሞከሩት!

በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ የሚያስገነዝበው ነገር ሁሉ ሐቅ ነው! ይህንን የግድ የሚያስገነዝብ ካልሆነ ደግሞ የሙዓጥ-ጢላዎች ተቃውሞ ከመሠረቱ ተንኮታኮተ ማለት ነው። - ሁለቱም አያዋጣቸውም! ስለዚህ በመሰል ስልቶች ቁርአናዊ እውነታን መጋፋት መረጃዎችን ከማጣመም በቀር የሚፈይደው ትርፍ የለም!

**ደግሞም** በጥቅሉ አላህ የሻውን ሁሉ ማድረግ የሚችል መሆኑ የምሉእነቱ መገለጫ እንጂ ጉድለት አይደለም! ይህንን ፅኑ እውነታ በአሻሚ ቃላት መናድ አይቻልም!

➢ ታዋቂው የኢስላም ሊቅ ***አል-ፉደይል ኢብኑ ዒያድ*** (187 ዓ.ሂ) እንዲህ ይላሉ፡-

«إِذَا قَالَ لَكَ جَهْمِيٌّ: أَنَا أَكْفُرُ بِرَبٍّ يَزُولُ عَنْ مَكَانِهِ، فَقُلْ: أَنَا أُؤْمِنُ بِرَبٍّ يَفْعَلُ مَا يَشَاءُ»!

*«አንድ ጀህሚይ "እኔ ከቦታው በሚወገድ ጌታ እክዳለሁ!" ካለህ "እኔ ደግሞ የሻውን በሚሰራ ጌታ አምናለሁ!" በል!»*[1]

(1) "ኸልቁ አፍዓሊ'ል-ዒባድ" ሊ'ል-ቡኻሪ ገፅ 33፣ "አል-ኢባናህ" ሊ'ብኒ በጥ-ጠህ (3/203)፣ "ሸርሑ ኡሱሊ'ዕቲቃዲ አህሊ'ስ-ሱን-ናህ" ሊ'ል-ላለካኢይ (3/452)

➢ ***አል-ኢማም ኢስሓቅ ኢብኑ ራሀወይህ (238 ዓ.ሂ) እና አል-ኢማም የሕያ ኢብኑ መዒን (233 ዓ.ሂ) ተመሳሳይ ንግግር አስፍረዋል።***[1]

**→ በጣም የሚደንቀው ደግሞ አላህ ዘንድ እውነተኛ አምላክ ያለመሆን አንድ ምልክት አለመናገር ሲሆን እነርሱ ዘንድ ግን መናገር ነው!! አላህ እንዲህ ብሎ ተናገሯል፡-**

﴿ وَٱتَّخَذَ قَوۡمُ مُوسَىٰ مِنۢ بَعۡدِهِۦ مِنۡ حُلِيِّهِمۡ عِجۡلًا جَسَدًا لَّهُۥ خُوَارٌۚ أَلَمۡ يَرَوۡاْ أَنَّهُۥ لَا يُكَلِّمُهُمۡ وَلَا يَهۡدِيهِمۡ سَبِيلًاۘ ﴾[الأعراف: ١٤٨]

➥ «የሙሳ ህዝቦችም ከርሱ (መሄድ) በኋላ ጩኸት ያለው በድን ጥጃ ከጌጦቻቸው (በመስራት) (አምላክ አድርገው) ያዙ፤ እርሱ እንደማያናግራቸውና መንገድ እንደማይመራቸው አላዩምን?!..»[አል-አዕራፍ 148]

●●●

(1) "አል-ኢባናህ" ሊ'ብኒ በጥ-ጠህ (3/206)፣ "ሸርሑ ኡሱሊ'ዕቲቃዲ አህሊ'ስ-ሱን-ናህ" ሊ'ል-ላለካኢይ (3/456)፣ "አል-አስማኡ ወ'ስ-ሲፋት" ሊ'ል-በይሀቂይ (2/375-376)፣ "ሲየሩ አዕላሚ'ን-ኑበላእ" ሊ'ዝ-ዘሀቢይ (11/376)

## ተውሒድን በንፅፅራዊ አመክንዮ?

**በመሠረቱ የእምነት ጉዳዮችን በንፅፅራዊ አመክንዮ ላይ መገንባት እንደማይፈቀድ ቀደምት የኢስላም ሊቃውንት ተስማምተዋል።**

➢ **ታላቁ የፊቅህ ምሁርና የአቡ ሐኒፋ ቅርብ ተማሪ አል-ኢማም *አቡ ዩሱፍ* (182 ዓ.ሂ) እንዲህ ብለዋል፡-**

«وَلَيْسَ التَّوْحِيدُ بِالْقِيَاسِ لأَنَّ الْقِياسَ يَكُونُ فِي شَيْءٍ لَهُ شَبَهٌ وَمَثَلٌ، وَاللَّهُ لَا شبه لَهُ وَلا مثل»

***«ተውሒድ በንፅፅራዊ አመክንዮ አይሆንም፤ ምክንያቱም ንፅፅር ቢጤና አምሳያ ላለው ነገር ብቻ የሚሆን ነው። አላህ ደግሞ ቢጤም አምሳያም የለውም!»***(1)

➢ **እንዲሁም ታላቁ ሊቅ *ኢብኑ ዐብዲ'ል-በር* (463 ዓ.ሂ) እንዲህ ይላሉ፡-**

«لَا خِلَافَ بَيْنَ فُقَهَاءِ الْأَمْصَارِ وَسَائِرِ أَهْلِ السُّنَّةِ، وَهُمْ أَهْلُ الْفِقْهِ وَالْحَدِيثِ فِي نَفْيِ الْقِيَاسِ فِي التَّوْحِيدِ»

---

(1) ኢብኑ መንዳህ - "አት-ተውሒድ" ጥራዝ 3፣ ገፅ 306፤ ቁጥር 890፤ አቡ'ል-ቃሲም አት-ተይሚይ - "አል-ሑጅ-ጃህ ፊ በያኒ'ል-መሓጅ-ጃህ" ጥራዝ 2 ገፅ 122

*«በተውሒድ ጉዳይ ላይ ንፅፅራዊ ልኬት ውድቅ ስለመሆኑ የየከተሞች ሊቃውንት እንዲሁም የፊቅህና የሐዲሥ እውቀት ባለቤት የሆኑት ሌሎች አህሉ’ስ-ሱን-ናዎች መካከል ምንም ውዝግብ የለም!»*(1)

እዚህ ላይ ልብ ሊሉት የሚገባው እምነትን በሚያወርሱ ትክክለኛ አእምሯዊ መረጃዎች መሠረት እውነታዎችን ማመዛዘንና ማገናዘብ ይኸኛው ምልከታ ውስጥ እንደማይካተት ነው። ሆኖም በሸሪዓ የፀደቁ እውነታዎችን ለማፍረስ በ“አእምሯዊ” ንፅፅሮች ላይ መመርኮዝ አደገኛ ነው። በአዋቂዎች አንደበት የተወገዘውም ይኸው ነው።

- ስመ-ጥሩ የሐዲሥ ጠቢብ ***አል-ኸጢብ አል-በግዳዲ*** (463 ዓ.ሂ) ይህንን ሲጠቅሱ እንዲህ ብለዋል፦

«..وَالضَّرْبُ الثَّانِي مِنَ الْقِيَاسِ فِي التَّوْحِيدِ: هُوَ الْقِيَاسُ الْمَذْمُومُ الَّذِي يُؤَدِّي إِلَى الْبِدَعِ وَالْإِلْحَادِ؛ نَحْوُ تَشْبِيهِ الْخَالِقِ بِالْخَلْقِ، وَتَشْبِيهِ صِفَاتِهِ بِصِفَاتِ الْمَخْلُوقِينَ، وَدَفْعِ قَايِسِهِ مَا أَثْبَتَ اللَّهُ تَعَالَى لِنَفْسِهِ، وَوَصَفَتْهُ بِهِ رُسُلُهُ مِمَّا يَنْفِيهِ القايس بِفِعْلِهِ.»

(1) ኢብኑ ዐብዲ’ል-በር - “ጃሚዑ በያኒ’ል-ዒልሚ ወፈድሊሂ” ጥራዝ 2 ገፅ 887

*«በተውሒድ ላይ ሁለተኛው የ“ቂያስ” (ንፅፅራዊ አመክንዮ) አይነት ወደ ቢድዓ እና ከሀይማኖት ወደ ማፈንገጥ የሚያመራው የተወገዘው ቂያስ ነው፤ (ለምሳሌ) ፈጣሪን ከፍጡር ጋር ወደ ማመሳሰል፣ ባህሪያቱንም ከፍጡራን ባህሪያት ጋር ወደ ማመሳሰል፣ እንዲሁም ቂያስ አድራጊው አላህ ለራሱ ያፀደቀውንና መልዕክተኞቹም እርሱን የገለፁበትን (መገለጫ) በቂያሱ ከሚያስተባብላቸው ሌሎች እውነታዎች ጋር ገሸሽ እንዲያደርግ የሚያበቃ ነው።»*[1]

**ወሳኝ ማብራሪያ**

**የብዙ ስህተቶች መነሻ ከህዋሳችን ስለተሰወሩ መለኮታዊ ጉዳዮች ይዘት ለመገንዘብ በአለማችን የምናያቸውን ነገሮች እንደ መመዘኛ በመውሰድ መላምት መሰንዘር ነው።**

ስለ መለኮት ስናስብ ስለ ተፈጥሯዊ ህግጋት ያለን ቅድመ ግንዛቤና ስለፍጡራን የምናውቃቸው እውነታዎች ሳናውቀው ተፅእኖ እንዳያሳድሩብን መጠንቀቅ ያሻል። ይህ በመለኮታዊ አጀንዳዎች ላይ ይቅርና በአለማዊ ነገሮች ላይ እንኳ ትክክለኛ ድምዳሜ ላይ ለመድረስ የሚያስችል አካሄድ አይደለም። ይህንን ቁልጭ አድርጎ የሚያሳይ **አንድ ትልቅ ምሳሌ** አብረን እናጢን፡-

(1) “አል-ፈቂሁ ወል-ሙተፈቅ-ቂህ” ሊ’ል-ኸጢብ አል-በግዳዲ ገፅ 397

## የ“ሩሕ” ምሳሌ

ሩሓችን (ነፍሳችን) የህያውነታችን ሚስጥርና የእኛነታችን ዋና ክፍል ከመሆኗ ጋር ትክክለኛ ምንነቷን ግን በውል አናውቅም! ይህ ከመሆኑ ጋር ሰዎች ስለ ሩሕ ምንነት የሚሰነዝሯቸው መላምቶች እጅግ ብዙ ናቸው![1]

አንዳንዶች *“ልዩ ‘ጂስም’ ነች!”* ሲሉ ሌሎች ደግሞ *“‘ዐረድ’ ነች!”* ይላሉ! ሌሎች *“እንዷሁ ‘ህይወት’ ከመሆኗ ውጭ የተለየ ህልውና የላትም!”* ሲሉ አንዳንዶች የሰውነት አንድ አካል መሆኗን ይገልፃሉ። ከዚህ ውጭ የሚደንቁ ዝርዝሮችንም የሚያትቱ አሉ!

ይበልጥ ትኩረት የሚስበው ግን አንዳንድ ፈላስፋዎች ሩሕን የሚገልፁት ፈጣሪን በሚገልፁበት ስልት መሆኑ ነው!! *“በሰውነት ውስጥም አይደለችም፤ ከሰውነት ውጭም አይደለችም! ከሰውነት ጋር የተያያዘችም አይደለችም፤ የተነጠለችም አይደለችም፤ የምትንቀሳቀስም አይደለችም፤ የማትንቀሳቀስም አይደለችም..!”* ይላሉ! የጠናባቸው ደግሞ *“በዓለም ውስጥም አይደለችም፤ ውጭም አይደለችም!”* ይላሉ!![2]

(1) ለብዙ ምሳሌዎች “አር-ሩሕ” ሊብኒ’ል-ቀይ-ዪም ከ(2/573) ጀምሮ ይመልከቱ።

(2) “አት-ተድሙርይ-ያህ” ሊሸይኺ’ል-ኢስላም ገፅ 51

መቼም ይህ ምን አይነት ቋንቋ እንደሆነ የሚያውቀው አላህ ብቻ ነው!! “ጭራሽ ስላልተፈጠረች ሩሕ መገለጫ ንገሩን!” ቢባል ምን የተለየ ነገር እንደሚያክሉ አሁንም አላህ ነው የሚያውቀው!

**የውዝግቡ ዋና መነሻ ሰዎች በነባራዊው ዓለም የሚያውቁት የሩሕ አምሳያ ሳይኖር ህልውናዋ ስለሚረጋገጥበት መገለጫ በተዛነፈ ንፅፅር መገመታቸው ነው።**[1]

**ለምሳሌ፡-** አንዳንዶች ይዘቷን ከ‘ጂስም’ ለመለየት ህልውናዋን ከመሠረቱ በሚያፋርስ መልኩ ይተረጉሟታል! ሌሎች ደግሞ አንዳንድ መገለጫዎቿን በማየት ብቻ *“እንደማንኛውም ‘ጂስም’ ነች!”* ይላሉ! እነዚህ ወገኖች በዚህ ገለፃ የፈለጉት ‘ሰውነት’ ማለትን ከሆነ ይህ ግልፅ ስህተት ነው! ምክንያቱም ሩሕ ከሰውነት ጋር ተለያይታ የምትወሳና ከርሱም ተነጥላ በራሷ ህልውና ልትገኝ የምትችል በመሆኗ ነው! ያሏት አንዳንድ ባህሪያትም ከሰውነት ወይም ከሌሎች ‘ጂስሞች’ ባህሪያት ጋር በቃል ደረጃ ቢገጥሙም በሁኔታ ግን ይለያያሉ።[2]

(1) ከዚህ በፊት እንደተጠቆመው የአንድን ነገር ሁኔታ ማወቅ የሚቻልባቸው አማራጮች ሶስት ብቻ ናቸው፡- እርሱን ማየት፣ አምሳያውን ማየት፣ ምንነቱን በተመለከተ እውነተኛ የሆነ ገለፃ ማግኘት።

(2) ለምሳሌ፡- ከተኛ ሰው ሰውነት በሙሉ ሳትነጠል ወደ ላይ መውጣቷ፤ እንዲሁም እንቅስቃሴዋ እንደ ሌሎች ‘ጂስሞች’ ሳይሆን እንደ መላኢካዎች ረጅም ርቀትን በቅፅበት የሚያዳርስ መሆኑ..ወዘተ ይጠቀሳሉ። [“ሸርሑ ሐዲሢ’ን-ኑዙል” ሊሸይኺ’ል-ኢስላም ገፅ (262-301)፣(396-400) ይመልከቱ።]

"'ጂስም' ናት!" ሲሉ ያሰቡት የራሷ ህልውና ያላት፣ "እዚህ" ወይም "እዚያ" በማለት ሊያመላክቷት የሚቻል ለማለት ከሆነ ግን የቃሉ አጠቃቀም አሻሚ ቢሆንም ሀሳቡ ልክ ነው።

ያም ሆነ ይህ ትክክለኛው አካሄድ በማስረጃ የተደገፉትን መገለጫዎቿን ማፅደቅና በርግጠኝነት የማያውቁትን ጉዳይ ደግሞ በዝምታ ማለፍ ነበር፤ የሚከተለው አምላካዊ ፍርድ የሁሉንም መላምት በር የሚዘጋ ነውና!

﴿وَيَسۡـَٔلُونَكَ عَنِ ٱلرُّوحِۖ قُلِ ٱلرُّوحُ مِنۡ أَمۡرِ رَبِّي وَمَآ أُوتِيتُم مِّنَ ٱلۡعِلۡمِ إِلَّا قَلِيلٗا﴾ [الإسراء:٨٥]

➥ «ስለ ሩሕም ይጠይቁሃል፤ "ሩሕ ከጌታዬ (ሚስጥራዊ) ጉዳይ ነው፤ ከእውቀትም ጥቂትን እንጂ አልተሰጣችሁም!" በላቸው።» [አል-ኢስራእ 85]

ታዲያ ከዚህ ጋር ሩሕ በተለያዩ ቁርአናዊና ሐዲሣዊ ማስረጃዎች በተለያዩ ጥቅል መገለጫዎች መወሳቷን መርሳት አይገባም! እንደምትሰማ፣ እንደምታይ፣ እንደምታውቅ፣ እንደምትደሰት፣ እንደምትከፋ፣ በእንቅልፍ ወቅት ከሰውነት (ሳትላቀቅ) እንደምትወጣ፣ በሞት ጊዜ ጭራሽ ከአካል እንደምትነጠል፣ የሟቹ አይንም እንደሚከተላት፣ መላኢካዎች እንደሚይዟትና በልዩ ከፈን

እንደሚያኖሯት፣ ከዚያም ወደ ሰማይ እንደምታርግና ተመልሳ ከሰውነት ጋር እንደምትዋሃድ እና ሌሎች ባህሪዎቿ ተገልፀዋል።[1]

*መቋጫ*

☞ ***ታዲያ*** የሩሕን ትክክለኛ ይዘት አለማወቃችን በመረጃ የፀደቁትን ጥቅል መገለጫዎቿን በተለያዩ ፈሊጦች የምናፋርስበት ምክንያት እንደማይሆነን ግልፅ ነው። እናም እነዚህን ባህሪያት ማስተባበል ህልውናዋን መንፈግ ከሆነ **የታላቁን ጌታ ባህሪያት ሁኔታና ውስጣዊ ይዘት ባለማወቃችን ጥቅል መልዕክታቸውን ማስተባበል ደግሞ ከዚህ እጅግ የከፋ መሆኑንን ማስተዋል አይከብድም!**

**ሩሕ** ፍጡር ከመሆኗ ጋር በገሃዱ ዓለም የሚታወቅ አምሳያ ስለሌላት መገለጫዎቿ በልዩ መልኩ ያለ "እንዴት" የሚረጋገጡላት ከሆነ የሩሕ ፈጣሪ ደግሞ ከዚህ እጅግ በላቀ መልኩ ፍፁም አምሳያ የሌለው ስለሆነ የመጠቁት ባህሪያቱ ያለ "እንዴት" በልዩ መልኩ መረጋገጣቸው ይበልጥ የተገባ ነው ማለት ነው! ያስተውሉ!

የእኛ ድርሻ የተነገረንን ተቀብለን ቃሉንም ጥቅል መልዕክቱንም ማፅደቅ እንጂ በውስን አእምሯችን ያልተረዳነውን ጉዳይ ሁሉ በራሳችን አተረጓጎም በመጠምዘዝ እውነታውን ማፋረስ አይደለም!! እናም አላህ ስለራሱ የነገረንን ነገር ይዘት ተረዳንም አልተረዳን

(1) ለተጨማሪ መገለጭዎቿና ማስረጃዎቻቸው "አር-ሩሕ" ሊብኒ'ል-ቀይ-ዩም ከ(2/580) ጀምሮ ይመልከቱ።

እንዳለ መቀበል የግድ ነው፤ ሁኔታው ባይገለፅልንም የተባልነውን ሳንቀይር ማመን አማራጭ የሌለው መንገድ ነው።

አእምሯችን አንዳንዴ አለማዊ ነገሮችን እንኳ በአግባቡ ላይረዳ እንደሚችል ግልፅ ነው፤ ከሁለት ክፍለ ዘመናት በፊት የነበሩ ነዋሪዎች ዛሬ በእጃችን ስላሉት ቀላል የቴክኖሎጂ መሳሪያዎች ትንቢት ሰምተው ቢሆን ኖሮ ብዙዎቹ ጭራሽ ሊሆን የማይችልና አእምሮም የማይቀበለው እንደሆነ በፈረዱ ነበር![1]

(1) **ሌላ አጭር ምሳሌ፡-** እንዲህ ብለን እናስብ፡- ከአለማዊ ስልጣኔ ሙሉ በሙሉ የራቀ ማህበረሰብ ውስጥ የሚኖሩ ሰዎች ከመካከላቸው አንድ ታማኝ ግለሰብ ወደ ከተማ የመውጣት እድል አግኝቶ እዚያ ስላየው ጉድ ለዘመዶቹ ሲያጫውት *"የሰውን ንግግር ድምፁን ሳይቀይር እንዳለ የሚደግም ቁራጭ ብረት አየሁ!"* ይላቸዋል፤ - የሞባይል ቀፎ ወይም ሌላ የድምፅ መቅረጫ መሳሪያ ማለቱ ነው! ከዚህ በላይ ሊያስረዳቸው አልቻለም፤ ቢችልም ኖሮ እነሱ አይገነዘቡትም! ችግሩ ግን እነሱ ከርሱ ተለይተው ያለ በቂ እውቀት የራሳቸውን መላምት መሰንዘር ያዙ! *"ያ እገሌ የነገረን ብረት የሰውን ንግግር የሚደግም ከሆነ የሚሰማበት ጆሮና የሚናገርበት ምላስ አለው ማለት ነው! ምላስ ካለው ደግሞ የግድ አፍ ይኖረዋል! ..ስለዚህ ህይወት ያለው ፍጡር ነው! እንደዛ ከሆነ ደግሞ በአፉ መመገቡ አይቀርም! የሚመገብ ከሆነ ደግሞ..!! አይ! እንደዚያማ አይሆንም! የብረት እንስሳ አይተን አናውቅም! ስለዚህ እገሌ ማለት የፈለገው 'ሰው ሲናገር ብረቱ የሚናገር ይመስላል!' ለማለት እንጂ..! ወይ ደግሞ ተሳስቶ ይሆን?.."*...ምሳሌውን እናንተው ጨርሱት!

በመሰል አካሄድ ዝርዝሩን ያላወቅነውን የመለኮት ርዕስ ከነአካቴው ማስተባበል ደግሞ ከዚህ የከፋ ነው፤ የኛ የሙስሊሞች መገለጫም አይደለም። አላህ ከሃዲያንን ሲወቅስ እንዲህ ብሏል፡-

📖﴿بَلۡ كَذَّبُواْ بِمَا لَمۡ يُحِيطُواْ بِعِلۡمِهِۦ وَلَمَّا يَأۡتِهِمۡ تَأۡوِيلُهُۥۚ﴾[يونس: ٣٩]

➡ «ይልቁንም እውቀቱን ባላካበቱት ነገር አስተባበሉ፤ ገሃዳዊው ፍቺ ገና ሳይመጣላቸው በፊት!»[ዩኑስ 39]

**በመሆኑም *"አላህ እንዲህ አይነት ባህሪ ካለው እንዲህ ነው ማለት ነው..!"*** እያሉ ራሱን የገለፀባቸውን ባህሪያት ይዞት ያለ እውቀት መተንተን ለአደገኛ መዘዞች ይዳርጋል! የ"ተዕጢል" ጭፍራዎች ጥመት ዋነኛ መነሻ ይሄ እንጂ ሌላ ምን ሆነና?!

➢ ***አል-ኢማም ዐብዱል-ዐዚዝ ኢብኑ'ል-ማጀሹን*** (164 ዓ.ሂ) እንደሚከተለው ብለዋል፡-

«..فأَمَّا الَّذِي جحَدَ مَا وَصفَ الرَّبُّ مِنْ نَفْسِهِ تَعَمُّقًا وَتَكَلُّفًا فقَدِ اسْتَهْوَتْهُ الشَّيَاطِينُ فِي الْأَرْضِ حَيْرَانَ، فَصَارَ يَسْتَدِلُّ بزَعَمِهِ عَلَى جَحْدِ مَا وَصفَ الرَّبُّ وَسَمَّى مِنْ نَفْسِهِ بِأَنْ قَالَ: لَا بُدَّ إِنْ كَانَ لَهُ كَذَا مِنْ أَنْ يَكُونَ لَهُ كَذَا! فَعَمِيَ عَنِ الْبَيِّنِ بِالْخَفِيِّ، وجَحَدَ مَا سَمَّى الرَّبُّ مِنْ نَفْسِهِ، بصَمْتِ الرَّبُّ عَمَّا لَمْ يُسَمِّ مِنْهَا..»

*«..ጌታ ከራሱ ባህሪያት የገለፀውን ጠልቆ በመፈላፈልና በመፍጨርጨር ያስተባበለውማ ግራ የተጋባ ሆኖ ሰይጣኖች (አታልለው) በምድር ላይ መንገድ አስተውታል፤ በመሆኑም "እንዲህ ያለ ነገር ያለው ከሆነማ የግድ እንዲህ ያለ ነገርም*

*ይኖረዋል..!" በማለት ጌታ ከራሱ ባህሪያት የገለፀውንና የሰየመውን ለማስተባበል በርሱ ቤት መረጃ ማቅረብ ያዘ! በድብቁ የተነሳ ከግልፁ ታወረ! ጌታ ስለ ራሱ ሳያወሳ በዝምታ ባለፋቸው (ዝርዝሮች) ምክንያትም ስለ ራሱ (በግልፅ) ያወሳውን ካደ!»* [1]

አዎን! ያላወቅነውን አለማወቃችን ያወቅነውን እንድናስተባብል ምክንያት ሊሆነን አይገባም! ያስተውሉ!

---

✸ ልብ ሊሉት የሚገባው ነጥብ በነብያት አስተምህሮት ውስጥ ከትክክለኛ አእምሯዊ እውነታዎች ጋር የሚጋጭ አንድም ነገር የለም፤ ሊኖርም አይችልም! ከሰዎች አእምሮ ጣራ በላይ የሆኑ ነገሮች ግን አሉ! ታዲያ ጥመት የጠማቸው ጥራዝ ነጠቆች ይዘታቸውን ፍለጋ ያለ አቅማቸው ይፈላፈላሉ! ፀጉርም ይሰነጥቃሉ! አዋቂዎች ግን ከአላህ ዘንድ የወረደውን ሁሉ በቅን ልቦና ይቀበላሉ!

📖 ﴿ هُوَ ٱلَّذِىٓ أَنزَلَ عَلَيْكَ ٱلْكِتَٰبَ مِنْهُ ءَايَٰتٌ مُّحْكَمَٰتٌ هُنَّ أُمُّ ٱلْكِتَٰبِ وَأُخَرُ مُتَشَٰبِهَٰتٌ ۖ فَأَمَّا ٱلَّذِينَ فِى قُلُوبِهِمْ زَيْغٌ فَيَتَّبِعُونَ مَا تَشَٰبَهَ مِنْهُ ٱبْتِغَآءَ ٱلْفِتْنَةِ وَٱبْتِغَآءَ

(1) "አል-ኢባነህ" ሊ'ብኒ በጥ-ጠህ (3/63)፣ "አል-ዑሉው" ሊ'ዝ-ዘሀቢይ ገፅ 141

﴿تَأۡوِيلِهِۦۗ وَمَا يَعۡلَمُ تَأۡوِيلَهُۥٓ إِلَّا ٱللَّهُۗ وَٱلرَّٰسِخُونَ فِي ٱلۡعِلۡمِ يَقُولُونَ ءَامَنَّا بِهِۦ كُلّٞ مِّنۡ عِندِ رَبِّنَاۗ﴾ [آل عمران: ٧]

➥ «እርሱ ባንተ ላይ መፅሐፉን ያወረደው ነው፤ ከርሱ ፍፁም የሆኑ (ግልፅ) አንቀፆች አሉ፤ እነሱም የመፅሐፉ 'እናት' (መሠረትና ዋነኛ መገለጫ) ናቸው፤ ሌሎች (ደግሞ) "ሙተሻቢህ" (በአንፃሩ አሻሚ ገፅታ ያላቸው) ናቸው፤ እነዚያ በልባቸው ጥመት ያለባቸው ፈተናን በመፈለግና "ተእዊሉን"[1] በመፈለግ የተመሳሰለውን (አሻሚውን) ይከታተላሉ፤ "ተእዊሉን" ከአላህ በቀር ማንም አያውቅም፤ በእውቀት ውስጥ የሰረፁትም "በርሱ አምነናል፤ ሁሉም ከጌታችን ዘንድ ነው" ይላሉ..»[አሊ ዒምራን 7]

ተወዳጁ መልእክተኛ (ﷺ) ይህንን አንቀፅ አንብበው እንዲህ ብለዋል:-

☜ «إِذَا رَأَيْتُمُ الَّذِينَ يَتَّبِعُونَ مَا تَشَابَهَ مِنْهُ، فَأُولَائِكَ الَّذِينَ سَمَّى اللهُ؛ فَاحْذَرُوهُمْ»

(1) "ተእዊል" በቁርአናዊ አገባቡ መሠረት የሚያስተላልፈው:- "የአንድ ንግግር ገሃዳዊ ይዘት ወይም ውጫዊ ፍፃሜ" የሚለውን መልዕክት መሆኑንና ይህንን ገሀዳዊ ይዘት ወይም ፍፃሜ በቃል ደረጃ መግለፅም እንዲሁ "ተእዊል" እንደሚባል እንዳይዘነጉ!

➥ «እነዚያ ከርሱ (ከቁርኣን) የተመሳሰለውን (አሻሚ ሆኖ ያገኙትን) የሚከታተሉትን ካያችሁ አላህ (በአንቀፁ) የጠቀሰው እነሱኑ ነውና ተጠንቀቋቸው!»[1]

ooo

(1) አል-ቡኻሪይ (4547)፣ ሙስሊም (2665) ላይ ከእናታችን ዓኢሻህ እንደተላለፈው።

## ክፍል ስድስት

### “ተእዊል”

ከዚህ በፊት እንደተጠቆመው የአላህን መገለጫዎች መቀበል የማይፈልጉ ሁሉ የመረጃዎቹን ትክክለኛ መልዕክት በማፋረስ በሌላ የሚተኩበትን ሂደት “ተእዊል” ብለው ይጠሩታል! እነሱ ዘንድ የ“ተእዊል” ፍቺ፡- የአንድን ንግግር ጉልህ (ظاهر) መልዕክት በመተው በሌላ ዘይቤ መተርጎም ነው![1]

በዚህ ፍቺ መሠረት “ተእዊል”ን ሊያስተናግዱ የሚችሉ ንግግሮች የግድ ከአንድ በላይ መልዕክቶችን የተሸከሙ ሲሆኑ አንደኛው መልዕክት ከሌላው ይበልጥ የጎላ በመሆኑ ቀድሞ ወደ አእምሮ ይዘልቃል፤ ሆኖም ይኸኛው መልዕክት በቦታው ተፈላጊ እንዳልሆነ የሚያስገነዝብ አሳማኝ መረጃ ሲኖር ወደ ድብቁ መመለስ አማራጭ የሌለው ግዴታ ይሆናል ማለት ነው!

(1) ይህ ከጊዜ በኋላ የመጣ ቴክኒካዊ ፍቺ ሲሆን ቃሉ በቁርአናዊ አገባቡ መሠረት የሚያስተላልፈው፡- “የአንድ ንግግር ገሃዳዊ ይዘት ወይም ውጫዊ ፍፃሜ”፤ ወይም ይህንን ገሀዳዊ ይዘትና ፍፃሜ በቃል ደረጃ መግለፅ የሚለውን መልዕክት እንደሆነ አሳልፈናል። (ከገፅ 74-76 ይመልከቱ።) ስርወ-ቃሉ በሰለፎች ዘንድ በግስም ይሁን በስም መልኩ የሚያስጨብጠው መልዕክት በዚህ ዙሪያ ያለ ነው። ስለሆነም አንዳንድ ጊዜ ከቁርአን ውጭ ሰፋ ባለ አገባቡ በጥቅሉ “ተፍሲር” (መግለፅ፣ ማብራራት) የሚል መልዕክት ይኖረዋል። ሆኖም በቀጥተኛም ይሁን በ“ዘይቤያዊ”፣ በ“ግልፅ”ም ይሁን በ“ድብቅ” ትርጓሜ አይገደብም!

ይህንን ቀመር በአላህ ባህሪያት ላይ ተግባራዊ የሚያደርጉት እንደሚከተለው ነው፡- *“የአላህ ባህሪያት የተወሱባቸው አብዛኛዎቹ መረጃዎችን ጉልህ መልዕክት መቀበል አላህን ማመሳሰልና ለርሱ ጉድለትን ማፅደቅ ስለሆነ የግድ ሌላ ዘይቤያዊ ትርጉም ልንፈልግ ይገባል!”* ይላሉ።

በመሠረቱ ለዚህ መደምደሚያ ያበቃቸው እውነተኛ “መረጃቸው” ከዚህ በፊት ያየነው ፍልስፍናዊ መነሻ እንደሆነ ግልፅ ነው! ስለሆነም ስለ ተእዊል የሚያሰፍሩትን ትንታኔና የባህሪያቱን ትርጓሜ ለመቆልመም የሚከተሉትን ስልት ያስተዋለ አላማቸው አላህ የፈለገውን መልዕክት መረዳትና ማፅደቅ ሳይሆን ማስረጃዎቹ ከሚያንፀባርቁት ጉልህ መልዕክት በተገኘው ቀዳዳ ሁሉ መሸሽ እንደሆነ በቀላሉ ይረዳል![1]

እውነታው ይህ ስለሆነ እነርሱ ዘንድ በዋነኝነት ግዴታ የሚሆነው ጉልህ መልዕክታቸውን አለመቀበል መሆኑንና የተእዊል ትርጓሜ

---

(1) እንደ አዝማች ከሚደጋግሚቸው መርሆዎቻቸው መካከል የሚከተለው ስንኝ አንዱ ነው፡-

"وكُلُّ نَصٍّ أَوْهَمَ التَّشْبِيهَا أَوِّلْهُ أَوْ فَوِّضْ وَرُمْ تَنْزِيهَا"!

*«ማመሳሰልን የሚያስገነዝብ **ማንኛውም** መረጃን **በሌላ ትርጉም!** ወይም **ትርጓሜውን** (ወደ አላህ) **አስጠጋ!** አላህንም (ቀጥተኛው ትርጉም ከሚያስጨብጠው መልዕክት) **ለማጥራት ፈልግ!!»***
[“ጀውሀረተ’ተውሒድ” (“ቱሕፈቱ’ል-ሙሪድ” ከተባለው ማብራሪያ ጋር የታተመው) ገፅ 156]

ማፈላለግ ትርፍ ነገር መሆኑን ብዙዎቹ ይናዘዛሉ![1] አብዛኞቹ የአሽዐሪይ-ያህ መንገድ አቀንቃኞች በዚህ ላይ ተመስርተው የመረጃዎቹን ጉልህ መልዕክት ሳይቀበሉ ባዶ ቃላትን ብቻ ማስተናገድን ("ተፍዊድ"ን) "የሰለፎች መንገድ" ይሉታል![2] የ'ተእዊል' ትርጓሜ መስጠቱን ደግሞ የኸለፎች (ተተኪ ትውልዶች) መንገድ! አያይዘውም:- *"የሰለፎች አካሄድ ይበልጥ ከአደጋ የራቀ ነው፤ የኸለፎች ደግሞ ይበልጥ በእውቀትና በጥበብ የተሞላ ነው!"* ሲሉ ያለ እፍረት ይናገራሉ! እንግዲህ 'ኸለፎች' የሚሏቸው በ'ዒልመ'ል-ከላም' ፍልስፍና የተጠመቁትን መሰሎቻቸውን ነው!

ሱብሓነ'ላህ! እነዚያ የከሃዲያን ፍልስፍና አራማጆች፣ እነዚያ የእምነት ኋላ ቀሮች፣ እነዚያ የጥርጣሬ ተከታዮች.. አላህ ካወደሳቸውና ለሰው ዘር ተምሳሌት ካደረጋቸው ሰሓባዎችና ተከታዮቻቸው ጋር በምን ዓይነት ድፍረት ነው ቀድሞውኑ የሚነፃፀሩት?! እንዴትስ ሆኖ ነው ስለ አላህ ባህሪያት በእውቀትና በጥበብ ከነሱ የሚሻሉት!..

---

(1) ለአብነት ያህል "ሙሽኪል አል-ሐዲሥ" ሊብኒ ፉረክ (267)፣ "አሽ-ሻሚል" ሊ'ል-ጁወይኒ (561)፣ እንዲሁም "አሳሱ አት-ተቅዲስ" ሊ'ል-ፈኽር አር-ራዚ (173) ሊጠቀሱ ይችላሉ።

(2) ይህ በሰለፎች ላይ ቅጥፈት መሆኑን የሚያረጋግጡ ጥቅሶችን አሳልፈናል! እንዲሁም በምዕራፍ አንድ ባሳልፍነው የሶስተኛው መርሆ ማብራሪያ ላይ ይህንን ውድቅ የሚያደርጉ አንዳንድ ማስረጃዎችን አይተናል!

“ጉልህ (ظاهر) መልዕክት”!

የ‘ተእዊል’ ፅንሰ-ሀሳብ የተገነባው እነዚያ የቁርኣንና የሐዲሥ ማስረጃዎች የሚያስገነዝቡት ጉልህ መልዕክት “አላህን ከፍጡራኑ ጋር የሚያመሳስል ነው!” በሚለው መንደርደሪያ ላይ መሆኑ ከላይ ተጠቁሟል። አዎን! የችግሩ ምንጭ ይኸው መሆኑን ከበቂ ማብራሪያና ምላሽ ጋር አይተናል።

ሆኖም እዚህ ላይ ትኩረት ሊቸረው የሚገባ አንድ ነጥብ አለ! እይታቸው በማመሳሰል ብዥታ የተጋረደ ሰዎች አላህ ራሱን ከገለፀባቸው ንግግሮች በግርድፍ ግንዛቤያቸው የሚረዱትን የፍጡራን መገለጫ “ጉልህ (ظاهر) መልዕክት” ብለው መጥራታቸው የዋሆችን የሚያጠምዱበት የተለመደ ማሳሳቻ ነው! ይህ የጉድለት “መልዕክት” ለነሱና ለመሰሎቻቸው ብቻ ነው “ጎልቶ” የታየው! በጥቅሉ ማስረጃዎች የሚያንፀባርቁት “ጉልህ” መልዕክትን በተመለከተ ያላቸው እይታ በተዛባ ግንዛቤ ላይ የተመሠረተ ስለሆነ ለብዙ አስከፊ መዘዞች ይጋለጣሉ! አንዱና ዋነኛው አላህ ራሱን የገለፀባቸው ንግግሮች የሚያንፀባርቁት መልእክት ተገቢ እንዳልሆነ በማሰብ እንደምንም ብሎ በሌላ “የተእዊል” ትርጓሜ ለመተካት መኳተን ነው!

☞ ሱብሓነ’ላህ! ቀድሞውኑ አላህ ለሰዎች ምሪቻ ባወረደው ተአምራዊና ጥበባዊ መፅሀፍ ራሱን የገለፀበት ንግግሩ በጉልህ መልእክቱ የሚያስገነዝበው እንዲህ ያለ ክህደትን እንደሆነ ማሰብ ምን ያለ ድፍረት ነው?!

✷ አንድ ቁም ነገር እንተዋወስ! "ንግግር" ማለት የቋንቋን ስርዓት በጠበቀ ሂደት **የተዋቀሩ** ቃላት የሚያስገኙት ውጤት እንጂ ለየብቻ የሚመዘዙ ቁንፅል ቃላት ስብስብ እንዳልሆነ ይታወቃል! ስለሆነም የአንድ ቃል ጉልህ መልዕክት የሚንፀባረቀው **ከአገባቡ አኳያ** እንደሆነ ማንኛውም አስተዋይ ይረዳል! ይህም ማለት ቃሉ በአንድ አረፍተ-ነገር ወይም ሀረግ ተሰክቶ የሚያስገነዝበው መልዕክት በሌላ አገባብ ከሚያስገነዝበው ሊለይ ይችላል!

በዚሁ መልኩ ለጌታ መገለጫ ሆኖ የተወሳ ቃል በዚያ አሰካኩ የሚያንፀባርቀው **ጉልህ** መልዕክት በሌላ ቦታ የፍጡር መገለጫ ሆኖ ሲጠቀስ ከሚያንፀባርቀው ጋር በይዘት ፍፁም ይለያያል! -አላህ ለራሱ ያፀደቃቸው ባህሪያት በሙሉ የተከሸኑበት ቋንቋዊ አገባብ የሚያንፀባርቀው እውነተኛ **ጉልህ** መልዕክት ከፍጡራን ጋር መመሳሰሉን የሚጠቁምበት ምንም መንገድ የለምና። **ስለሆነም** ብዙሃኑ ሙስሊሞች እነዚያን ማስረጃዎች ሲሰሙ ወደ አእምሯቸው የሚሰርፀው ለፈጣሪ ሃያልነትና ልቅና የሚገባው መልዕክት በመሆኑ ሌላ ትርጓሜ ፍለጋ አልኳተኑም!

**በዚህ መሠረት** የአላህ ባህሪያት የተወሱባቸው ማስረጃዎች ጉልህ (ظاهر) ወይም ቀጥተኛ መልዕክት ተፈላጊ ነው ወይስ አይደለም? የሚለው ጥያቄ የሚፈታው ተናጋሪው ጉልህነትንና ቀጥተኛነትን ከሚለካበት ሚዛን አኳያ ይሆናል ማለት ነው፦ "ቀጥተኛው/ጉልህ መልዕክት" በሚለው ቃል ያሰበው የፍጡራንን መገለጫ ከሆነ ይህ ተፈላጊ እንዳልሆነ ግልፅ ነው፤ ለአላህ ልቅና የሚገባውን ከሆነ ደግሞ ይህ በርግጥ ተፈላጊ ነው። ሰለፎችም የመረጃዎቹን **ጉልህ** መልዕክት ማፅደቅ የግድ እንደሆነ ሲናገሩ የሚፈልጉት ይኸኛወን

ንፁህ ይዘት እንጂ በማመሳሰል አባዜ የተበከሉ ህሊናዎች የሚወጥኑትን እንዳልሆነ ግልፅ ነው!

ooo

## የ‘ተእዊል’ መስፈርቶች

ንግግሮች ከሚያስተላልፉት መልዕክት ግልፅነት አኳያ በሶስት ሊከፈሉ ይችላሉ[1]:-

**የመጀመሪያው ክፍል፡-** አንድ መልዕክትን ብቻ ቁልጭ አድርጎ የሚያስተላልፍ ነው! (نصّ)

**ሁለተኛው ደግሞ፡-** ከአንድ በላይ መልዕክቶችን ሊያስተላልፍ የሚችል ሲሆን አንደኛው መልዕክት ግን ከሌሎቹ ይበልጥ ጎልቶ ይንፀባረቃል! (ظاهر)

ሆኖም ከአገባቡ አንፃር ጉልህ መልዕክቱ ተፈላጊ እንደሆነ የሚያፀኑ አመላካቾች ሲኖሩ ወይም በተናጋሪው አንደበት በዚህኛው ይዘት ሲደጋገም መልዕክቱ በአንዱ ላይ ብቻ ስለሚወሰን ከመጀመሪያው ክፍል ጋር የሚቀላቀል ይሆናል ማለት ነው!

**ሶስተኛው ደግሞ፡-** ከአንድ በላይ መልዕክቶችን በእኩል ጉልህነት ሊያስገነዝብ የሚችል ሲሆን ተፈላጊውን መልዕክት ለመረዳት የግድ ማብራሪያ የሚሻ ነው! (مُجمل)

☞ አብዛኛዎቹ የቁርኣንና የሐዲሥ ገለፃዎች የመጀመሪያዎቹ ሁለቱ ክፍሎች ውስጥ እንደሚካተቱ ግልጽ ነው!

(1) ይህ በአብዛኛዎቹ የኡሱሉ’ል-ፊቅህ መፃህፍት ላይ የሚጠቀስ እውነታ ነው።

ታዲያ ‘ተእዊል’ ከላይ ባየነው ቴክኒካዊ ፍቺው መሠረት የአንድን ንግግር **ጉልህ** (ظاهر) መልዕክት በመተው በሌላ ዘይቤ መተርጎም በመሆኑ ተፈፃሚ የመሆን እድል ያለው በሁለተኛው ክፍል ላይ ብቻ እንደሆነ ልብ ይበሉ!

አብዛኛዎቹ የአላህ ባህሪያት የተጠቀሱባቸው ማስረጃዎች ደግሞ ከአገባባቸው አንፃር ከአንድ በላይ መልዕክትን የሚያስተላልፉ ስላልሆኑ የመጀመሪያው ክፍል ውስጥ የሚገቡ ናቸው! አንዳንድ ባህሪያት ላይ የሚጠቀሱ ዝርዝር መረጃዎች በመሠረታዊ እይታ በሁለተኛው ክፍል ውስጥ ሊገቡ ቢችሉም ባህሪያቱ በሌሎች ግልፅ ሂደቶች በመፅደቃቸውና በተመሳሳይ ይዘት በመደጋገማቸው ወደ መጀመሪያው ክፍል ይጠቃለላሉ! ስለሆነም ማስረጃዎቹ ለ‘ተእዊል’ የሚያስተርፉት ትንሽም አግድም የለም ማለት ነው!

ሆኖም እንዲያው ይሁን ተብሎ ሁሉም መረጃዎች በሁለተኛው ክፍል ውስጥ ቢካተቱ ኖሮ እንኳ የሚቀየር ነገር የለም! ምክንያቱም የአንድ ንግግርን ‘ጉልህ’ መልዕክት በመተው በሌላ “ዘይቤያዊ” ይዘት ለመተርጎም የግድ **አምስት** መስፈርቶች ሊሟሉ ይገባል! ይህ ማለት ተእዊሉ ግቡን የሚመታው **አምስቱንም ማጣሪያ ፈተናዎች** በየተራ ማለፍ ሲችል ብቻ ነው! ያ ደግሞ “ላም አለኝ በሰማይ..!” ነው! **ማጣሪያዎቹን እነሆ!**[1]

(1) ዑለማዎች የተእዊል መስፈርቶችን በተለያዩ ገለፃዎች አብራርተዋል፤ አምስቱን በራሴ ገለፃ አስፍሬያቸዋለው። ለምሳሌ ያህል፦ “መጅሙዑ’ል-ፈታዋ” (3/360)፣ “ሙኽተሰር አስ-ሰዋዒቅ” (1/94)፣ (3/946)፣ =>

ማጣሪያ ቁጥር 1

**ቃሉ የሚያንፀባርቀውን ጉልህ ወይም ቀጥተኛ መልዕክት በመተው ወደ ሌላ ዘይቤያዊ ትርጓሜ ማምራት ከተለመደው የቋንቋ ሂደት መውጣት በመሆኑ ለዚህ ምክንያት የሚሆን አሳማኝ መረጃ ማቅረብ፤**

➢ ***አል-ኢማም አሽ-ሻፊዒይ*** (204 ዓ.ሂ) እንዲህ ብለዋል፡-

«..وَالْحَدِيثُ عَلَى ظَاهِرِهِ، وَإِذَا احْتَمَلَ الْمَعَانِيَ فَمَا أَشْبَهَ مِنْهَا ظَاهِرَ الأَحَادِيثِ أَوْلاهَا بِهِ»

*«ሐዲሥ በጉልህ መልዕክቱ ላይ ነው ያለው፤ (ከአንድ በላይ) ትርጓሜዎችን የሚያስተናግድ ከሆነ የሐዲሡ ጉልህ መልዕክት የሚመስለው (መልዕክት) ይበልጥ ተገቢ ይሆናል።»*[1]

=> "አል-በሕሩ'ል-ሙሒጥ" ሊ'ዝ-ዘርከሺ (5/44) ፤ "አል-ሙዋፈቃት" ሊ'ሽ-ሻጢቢይ (3/330) ይመልከቱ።

(1) "አዳቡ'ሽ-ሻፊዒይ ወመናቂቡሁ" ሊ'ብኒ አቢ ሓቲም ገፅ 178፣ "ሒልየቱ'ል-አውሊያእ" ሊአቢ ኑዐይም (9/105)

ማጣሪያ ቁጥር 2

ቃሉ የሚተረጎምበት ዘይቤ በጥቅሉ በቋንቋ የሚታወቅ መሆኑ፤

ካልሆነ ግን ቋንቋ ላይ የሚፈፀም ቅጥፈት ይሆናል ማለት ነው!

ማጣሪያ ቁጥር 3

ይህ ዘይቤያዊ ትርጓሜ ከዚህኛው አገባብና የንግግር ሂደት አንፃር የሚታወቅ መሆኑ፤

ምክንያቱም አንድ ቃል በተወሰነ አገባብ የሚያስተላልፈውን ዘይቤያዊ መልዕክት በሌላ አገባብ ላያስተላልፍ ይችላልና!

ይህ ትኩረት የሚሻ ጉዳይ በመሆኑ በአማርኛ ምሳሌ እናብራራው! "መርገጥ" የሚለውን ስርወ ቃል በተለያዩ አገባቦች ሰክተን እንየው:-

1- "መብት መርገጥ"፣

2- "ጮቤ መርገጥ"፣

3- "ስብሰባ ረግጦ መውጣት"

ሁሉም ዘይቤዎች ከመርገጥ ጋር የተቆራኙ ቢሆንም መልዕክታቸው ግን እንደየአገባባቸው ስለሚለያይ አንዱን በሌላው መተርጎም አይቻልም!

ለምሳሌ፡- አንድ ሰው “እግሌ ረገጠኝ!” ሲል ንግግሩን በመብት ረገጣ ወይም በሌላ ዘይቤ መተርጎም ከመሠረታዊው ቋንቋዊ ሂደት መውጣት በመሆኑ የግድ አሳማኝ ምክንያት ያስፈልገዋል! ጭራሹኑ ቀጥተኛ መልእክቱን በሚያፀና እና ዘይቤያዊ ትርጓሜን በሚፃረር አገባብ ከታጀበማ ከአንድ በላይ መልዕክት አይኖረውም! ለምሳሌ፡- “እግሌ በቆዳ ጫማው ረገጠኝ!”፤ “...በተኛሁበት ሆዴ ላይ ረገጠኝ!” ወዘተ ሲባል የተእዊል በር ጥርቅም ብሎ ይዘጋል ማለት ነው! ያስተውሉ![1]

---

(1) *ይህንን መርሆ በመረዳት አንዳንድ ሙግተኞች አላህ በዐርሹ ላይ መሆኑን በሚያረጋግጡ አንዳንድ መረጃዎች ዙሪያ ቋንቋዊ ውዥንብር ለማንሳት «‘ኢስቲዋእ’ አስራ ምናምን ትርጉም አለው፤ ዐርሽ ይህን ያህል ትርጉም አለው..ምንትሴ!» የሚሉት ዋጋ የሌለው ተቃውሞ መሆኑን በቀላሉ ማወቅ ይቻላል፤ ምክንያቱም እነርሱ እንደሚሉት ቃሉ በተለያዩ አገባቦች ብዙ ትርጉሞችን የሚያንፀባርቅ ቢሆን እንኳ አላህ በቁርኣኑ ላይ ለራሱ ያፀደቀው ‘ኢስቲዋእ’ እና ‘ዐርሽ’ ግን በምንም መልኩ* **ከሚታወቀው** *አንድ መልዕክት ውጪ ትርጓሜ ሊኖረው አይችልም! -ንግግሩ ይህንን በሚያፀኑ አገባቦችና በርካታ መረጃዎች የታጀበ ነውና! በመሠረቱ በዓረብኛ ቋንቋ “ኢስተዋእ” የሚለው ቃል “ዐላ” (عَلَىٰ) ከሚለው መስተዋድድ ጋር ሲቆራኝ የሚጠቁመው “ከላይ መሆንን” ብቻ ነው። በአንፃሩ እነርሱ እንደሚያደርጉት ይህንን ቁርኣናዊ ሀረግ “ኢስተውላ” (ተቆጣጠረ!) ብሎ መቆልመም በ42 መንገዶች ወድቅ መሆኑን ለማረጋገጥ ከፈለጉ “ሙኽተሰር አስ-ሰዋዒቅ አል-ሙርሰላህ” (3/888-946) ይመልከቱ!*

ማጣሪያ ቁጥር 4

የንግግሩ ጉልህ መልዕክት አንዴ ከተለቀቀ በኋላ የተለያዩ ዘይቤያዊ ትርጓሜዎችን ሊያስተናግድ ስለሚችል አንዱን ለይቶ ለመምረጥ በቂ ምክንያት ማቅረብ!

ማጣሪያ ቁጥር 5

ጉልህ መልዕክቱን ለሚያጠናክሩና ይህን ዘይቤያዊ ትርጓሜ ለሚያፋርሱ ሌሎች መረጃዎችና አመላካቾች በሙሉ አጥጋቢ መልስ መስጠት!

---

ታዲያ የተዕጢል አራማጆች የሚያራግቧቸውን የ'ተእዊል' (የ"ተሕሪፍ") ትርጓሜዎችን በነዚህ ማጣሪያዎች ስንፈትናቸው ሁሉም ከጅምሩ ተንኮታኩተው እንደሚወድቁ ግልፅ ነው! መጣሪያ ቁጥር አንድን ለማለፍ የሚያቀርቡት ምክንያት *"ባህሪያቱን በቀጥታ ማፅደቅ ማመሳሰል ነው፤ የፍጡራንን መገለጫ መስጠት ነው.."* የሚለውን የተለመደ አባዜ ነውና! ይህ መነሻ ደግሞ ከመሠረቱ ውድቅ እንደሆነ በተለያዩ መገዶች አውቀናል። ስለዚህ ፋይሉ ከወዲሁ ይዘጋል ማለት ነው። በዚህ ላይ ይህንን ማጣሪያ ዘለው ቢያልፉ እንኳ አብዛኛዎቹ ትርጓሜዎች ሁለተኛውን ማጣሪያ አያልፉም! ከዚያ በኋላ ያሉትን የሚያልፍማ ለይስሙላ ያህል እንኳ አይገኝም!

ይህንን ይበልጥ ለመረዳት <u>እነርሱ "ጠንካራ" ብለው የሚደገፉትን</u> አንድ የ'ተእዊል' ትርጓሜ በምሳሌነት እንውሰድ፦

**ምሳሌ**[1]

**አላህ እንዲህ ብሏል፡-**

﴿قَالَ يَٰٓإِبۡلِيسُ مَا مَنَعَكَ أَن تَسۡجُدَ لِمَا خَلَقۡتُ بِيَدَيَّۖ﴾ [ص: ٧٥]

➥ «(አላህ) አለ፦ 'ኢብሊስ ሆይ! በሁለቱ እጆቼ ለፈጠርኩት (ለኣደም) እንዳትሰግድ ምን ከለከለህ?'»[ሷድ 75]

**አብዛኞዎቹ የተዕጢል ጎራዎች አላህ በዚህም ይሁን በሌሎች ቦታዎች ላይ ለራሱ ያረጋገጠውን እጅ የሚተረጉሙት በፀጋ/ውለታ (نِعمة) ወይም በችሎታ (قُدرة) ነው!**[2]

**እስቲ ይህንን ትርጓሜ በአምስቱ ማጣሪያዎች እንፈትነው፡-**

---

(1) በዚህ ምሳሌ ላይ የጥመት ሰለባዎች እንዴት ግልፅ ማስረጃዎችን በመተው በአሻሚ ነገሮች ላይ እንደሚንጠላጠሉ አብረን እንቃኛለን!

﴿فَأَمَّا ٱلَّذِينَ فِي قُلُوبِهِمۡ زَيۡغٞ فَيَتَّبِعُونَ مَا تَشَٰبَهَ مِنۡهُ ..﴾ [آل عمران: ٧]

➥ «እነዚያ በልባቸው ጥመት ያለ የተመሳሰለውን (አሻሚውን) ይከታተላሉ..»[ኣሊ ዒምራን 7]

(2) ለዚህ ተእዊል ሰፋ ያለ ምላሽ ከሰጡት ዑለማዎች መካከል *አቡ'ል-ሐሰን አል-አሽዐሪይ* አንዱ ናቸው። "አል-ኢባናህ" የተሰኘውን መፅሀፋቸውን ከገፅ 443 እስከ 469 (በአዲሱ እትም) ይመልከቱ።

✸ ***የመጀመሪያውን ማጣሪያ*** በተመለከተ መልዕክቱን ከጉልህ ይዘቱ ለማስወገድ የሚያቀርቡት ***‘መረጃ’*** ያው ***“እጅ ካለው ከፍጡራን ጋር ይመሳሰላል፤..‘ጂስም’ ይሆናል!..”*** የሚለው የተሰለቸ ሙግት ነው!

ይህ ደግሞ ከዚህ በፊት እንዳረጋገጥነው ጭራሽ መሠረት የሌለው ባዶ ስጋት ነው! የተለያዩ የአላህ ባህሪያትን ከፍጡራን ባህሪያት ጋር ሳናመሳስል እንደምናፀድቀው ሁሉ እጆቹም ከፍጡራን እጆች ፍፁም የተለዩ መሆናቸውን ከማፅናት ጋር ስለሁኔታቸው ሳንዘባርቅ ባህሪውን እንዳለ ከማፅደቅ የምንቆጠብበት ምንም ምክንያት የለም!

➢ *ታዋቂው የሐዲሥ ሊቅ አል-ኢማም **አት-ቲርሚዚይ** (279 ዓ.ሂ)* እንዲህ ብለዋል፡-

«..قَدْ ذَكَرَ اللَّهُ عَزَّ وَجَلَّ فِي غَيْرِ مَوْضِعٍ مِنْ كِتَابِهِ اليَدَ وَالسَّمْعَ وَالبَصَرَ، فَتَأَوَّلَتِ الجَهْمِيَّةُ هَذِهِ الآيَاتِ؛ فَفَسَّرُوهَا عَلَى غَيْرِ مَا فَسَّرَ أَهْلُ العِلْمِ، وَقَالُوا: إِنَّ اللَّهَ لَمْ يَخْلُقْ آدَمَ بِيَدِهِ! وَقَالُوا: إِنَّ مَعْنَى اليَدِ هَاهُنَا القُوَّةُ! **وقَالَ إِسْحَاقُ بْنُ إِبْرَاهِيمَ:** إِنَّمَا يَكُونُ التَّشْبِيهُ إِذَا قَالَ: يَدٌ كَيَدٍ، أَوْ مِثْلُ يَدٍ، أَوْ سَمْعٌ كَسَمْعٍ، أَوْ مِثْلُ سَمْعٍ... وَأَمَّا إِذَا قَالَ كَمَا قَالَ اللَّهُ تَعَالَى: يَدٌ، وَسَمْعٌ، وَبَصَرٌ، وَلاَ يَقُولُ: كَيْفَ، وَلاَ يَقُولُ: مِثْلُ سَمْعٍ، وَلاَ كَسَمْعٍ، فَهَذَا لاَ يَكُونُ تَشْبِيهًا، وَهُوَ كَمَا قَالَ اللَّهُ تَعَالَى فِي كِتَابِهِ:

﴿لَيْسَ كَمِثْلِهِۦ شَىْءٌۖ وَهُوَ ٱلسَّمِيعُ ٱلْبَصِيرُ﴾ [الشورى: ١١]»

*«አላህ ከአንድ በላይ ቦታዎች ላይ እጅን፣ መስማትንና ማየትን በርግጥ አውስቷል፤ **ጀህሚይ-ያዎች** ግን እነዚህን አንቀፆች*

*በ'ተእዊል' ተርጉመው የእውቀት ባለቤቶች ከገለፁት በተለየ መልኩ አብራሯቸው! እናም "አላህ አደምን በእጁ አልፈጠረም" አሉ! እንዲሁም "እዚህ ቦታ ላይ የ'እጅ' ትርጓሜ 'ሀይል' ነው!" አሉ!* ***ኢስሓቅ ኢብኑ ኢብራሂም*** [ኢብኑ ራሀወይህ] *እንዲህ አሉ፡- "ማመሳሰል የሚሆነው "እንዲህ ያለ ወይም ይሄ አይነት እጅ"፣ 'እንዲህ ያለ ወይም ይሄ አይነት መስማት' ሲባል ነው፤...ነገር ግን አላህ እንደተናገረው 'እጅ፣ መስማት፣ ማየት' ብሎ 'እንዴት' ካላለ፣ 'እንዲህ አይነት፣ እንዲያ ያለ መስማት..' ካላለ ማመሳሰል አይሆንም። አላህ ራሱ በመፅሃፉ እንዳለው 'እንደርሱ ያለ (አምሳያ) ምንም የለም፤ እርሱም ሰሚውና ተመልካቹ ነው'* [አሹ-ሹራ 11]*"*(1)

ስለዚህ ሊገነቡት ያሰቡት እዚሁ ላይ ተፍረክርኮ ይናዳል! የ'ተእዊሉ' በርም ከወዲሁ ይዘጋል! ሆኖም ምሳሌውን ይበልጥ ለማብራራት በይሁንታ እንቀጥል፡-

✸ ወደ **ሁለተኛው ማጣሪያ** ስናልፍ፡- በርግጥ "እጅ" (يد) የሚለው ቃል በአንዳንድ የዐረብኛ አገባቦች ውለታን ወይም ችሎታን ሊያመላክት ይችላል! ለዚህም በርካታ ምሳሌዎች አሉ። ሆኖም ይህ ዘይቤ በየትኛውም የቁርኣን አንቀፅ ላይ ተጠቅሶ አያውቅም፤ እጆችም ይሁኑ ውለታና ችሎታ በሁሉም ቦታዎች የተወሱት በተለመዱት ቃላት ነው! ስለዚህ ይህ ትርጓሜ በጥቅሉ ለቁርኣናዊ ገለፃ እንግዳ ነው ማለት ነው!

(1) "ሱነኑ'ት-ቲርሚዚይ" ኪታቡ'ዝ-ዘካህ፣ ከሀዲስ ቁጥር (662) በኋላ

ያም ሆነ ይህ አንድ ቃል በአንድ አገባብ የሚያስገነዝበውን መልዕክት በሌላ ላያስገነዝብ ስለሚችል የግድ በሚቀጥለው ማጣሪያ መፈተን ይኖርበታል፡-

✸ በሶስተኛው ማጣሪያ ላይ ደግሞ ምንም አይነት የ'ተእዊል' እድል አናገኝም! ምክንያቱም፡-

**1ኛ-** ዐረቦች እጅ (يد) በሚለው ቃል ውለታን ወይም ችሎታን የሚያመላክቱበት ዘይቤያዊ አሰካክ በአንቀፁ ላይ ከምናየው በግልፅ የሚለይ በመሆኑ ነው! ለምሳሌ፡-

«لَوْلاَ يَدٌ كَانَتْ لَكَ عِنْدِي لَمْ أَجْزِكَ بِهَا لَأَجَبْتُكَ»

ማለትም፡- *"እኔ ዘንድ ያለህ ያልመለስኩልህ "እጅ" (=ውለታ) ባይኖር ምላሽ እሰጥህ ነበር..!"*[1]

እንዲሁም *"እገሌ ይህንን የሚጋፈጥበት እጅ (=ችሎታ) የለውም!"* ይላሉ።

በአንቀፁ ላይ ያለው የቃሉ አገባብ ግን በዚህ መልኩ ሊተረጎም አይችልም! ምክንያቱም ዐረቦችም ይሁኑ ሌሎች *"በእጆቼ ሰራሁ፤ በእጄ ፃፍኩኝ፣ በእጄ ያዝኩኝ.."* የሚሉት በትክክል በእጅ መፈፀምን ለማመላከት ብቻ ነው! ለዚህም ነው አንድ ተናጋሪ *"ለእገሌ ብር ሰጠሁት፤..ደብዳቤ ፃፍኩኝ.."* ሲል የግድ በእጁ መስጠቱን ወይም መፃፉን አያስገነዝብም፤ ሌላ ሰው የርሱን ብር

(1) አል-ቡኻሪይ (2731) (*ዑርወህ ኢብኑ መስዑድ ለአቡ በክር የተናገረው*)

እንዲሰጠው ወይም በስሙ እንዲፅፍ ትዕዛዝ አስተላልፎ ሊሆን ይችላልና! *“በእጄ ሰጠሁት፤ ..በእጄ ፃፍኩኝ”* ካለ ግን በትክክል በራሱ እጅ መስጠቱንና መፃፉን ብቻ ነው የሚያሳየው!

ሆኖም አንዳንዶች ይህንን እውነታ ለማፋረስ ከዚህ ጋር የማይገናኝ አንቀፅ ይጠቅሳሉ፡-

📖 ﴿وَٱلسَّمَآءَ بَنَيۡنَٰهَا بِأَيۡيْدٍ﴾ [الذاريات: ٤٧]

➥ «ሰማይንም በሀይል (በጠናከረን) ገነባናት»[አዝ-ዛሪያት 47]

በአንቀፁ ላይ *“አይድ”* (أيد) የሚለው የ*“የድ”* (يد = እጅ) ብዙ ቁጥር መስሏቸው ነው! ይህ ግልፅ የቋንቋ ድህነት ነው! ምክንያቱም፡- ይህ ቃል *“ኣደ”* (آد = ጠነከረ/በረታ)፣ *“የኢዱ”* (يئيد = ይጠነክራል/ይበረታል) የሚለው ግስ **አርዕስት** (مصدر) እንጂ እነርሱ እንዳሰቡት አይደለም። ቃሉ በተለያየ ቅርፅ ሲነገርም የሚያስገነዝበው ይህንኑ (ብርታት/ጥንካሬ) ነው! ከቁርኣን ሁለት ምሳሌዎችን እንይ፡-

📖 ﴿وَٱذۡكُرۡ عَبۡدَنَا دَاوُۥدَ ذَا ٱلۡأَيۡدِ﴾ [ص: ١٧]

➥ «ባለ ሀይል (ብርታት) የሆነውን ባሪያችንን ዳዉድ አውሳ..»[ሷድ 17]

📖 ﴿وَأَيَّدَهُۥ بِجُنُودٍ لَّمۡ تَرَوۡهَا﴾ [التوبة: ٤٠]

➥ «ባላያችኋቸው ሰራዊቶችም አበረታው..»[አት-ተውባህ 40]

**እናም ይህ የታወቀ ቀጥተኛ ቋንቋዊ መልዕክቱ እንጂ ዘይቤያዊ ትርጓሜ ወይም ‘ተእዊል’ አይደለም! ከሰለፎችም ይሁን ከቋንቋ ሊቆች ቃሉን በመሰል አገባቦች ‘እጆች’ ብሎ የተረዳም ማንም የለም! ይህንን በአይኑ ለማየት የሚሻ የተለያዩ የ‘ተፍሲር’ና የቋንቋ መዛግብትን ማገላበጥ ብቻ ነው የሚጠበቅበት!**

➢ ***አል-ኢማም ኢብኑ ኹዘይማህ*** **እንዲህ ይላሉ፡-**

«فَمَنْ لَا يُفَرِّقُ بَيْنَ الْيَدِ وَالْأَيْدِ فَهُوَ إِلَى التَّعْلِيمِ وَالتَّسْلِيمِ إِلَى الْكَتَاتِيبِ أَحْوَجُ مِنْهُ إِلَى التَّرَؤُّسِ وَالْمُنَاظَرَةِ!»

***«በ“የድ” (እጅ) እና በ“አይድ” (ብርታት) መካከል ያለውን ልዩነት የማያውቅ ሰው ለመሪነትና ለክርክር ከሚያስቀድሙት ይልቅ ሊያስተምሩትና ለመሠረተ-ትምህርት ሊያስረክቡት የሚያስፈልገው ነው!»***[1]

**ስለሆነም ይህ ጭራሽ ከርዕሱ ውጭ የሆነ ሙግት ነው፤ ቃላቱ በፊደል ይዘታቸው ሊመሳሰሉ የሚችሉበት አገባብ ቢኖርም በመልዕክት ግን ጭራሽ የሚለያዩ ናቸውና!**[2]

(1) “አት-ተውሒድ” ሊኘብኒ ኹዘይማህ (1/191)

(2) ወደ መልካም ስራ ገፋፊ ምክንያትና የበግ ቆዳ ገፋፊ በስርወ ቃል ከመሠረቱ እንደሚለያዩት ማለት ነው!

በዚህ ላይ ደግሞ አላህ በአንቀፁ ላይ ያለው በጥቅሉ “ቢአይድ” (بِأَيْدٍ) እንጂ ወደ ራሱ በማስጠጋት “ቢአይዲና” (بأيدينا) አይደለም!

**2ኛ-** አላህ አባታችን ኣደምን በሁለት እጆቹ እንደፈጠራቸው በተናገረበት አንቀፅ ላይ ‘እጆች’ በሚለው ፈንታ ‘ፀጋዎች’ ወይም ‘ችሎታዎች’ የሚለውን አስገብተን ስንሞክር የዐረፍተ-ነገሩን ይዘት እጅግ ባይተዋር ያደርገዋል፦ *«በሁለቱ ፀጋዎቼ ለፈጠርኩት!»፤ «በሁለቱ ችሎታዎቼ ለፈጠርኩት!»*!! ለመሆኑ የአላህ ፀጋዎች ሁለት ብቻ ናቸው እንዴ?! ችሎታውስ ለሁለት ይከፈላልን?!

በዐረብኛ ቋንቋ አንድ ነገር በሁለትዮሽ (ጥንድ) (مُثَنَّى) ይዘት ከተገለፀ ብዛቱ የግድ (በቁጥር) ሁለት ብቻ እንደሆነ ያሳያል! የአላህ እጆች ደግሞ በዚህ ብቻ ሳይሆን በተለያዩ ማስረጃዎች ላይ ሁለት መሆናቸው ተረጋግጧል። በሌላ ቦታ ከአገባቡ ጋር በሚሄድ ቃና በነጠላ ወይም በብዜት አጠራር መጠቀሳቸው ግን በዐረብኛው ህግ መሠረት የተገደበ ቁጥርን ስለማያስገነዝብ ከዚያ ጋር የሚጋጭ አይደለም!

**3ኛ-** በአንቀፁ ላይ «በሁለቱ እጆቼ ለፈጠርኩት» የሚለው በፀጋ ወይም በችሎታ የሚተረጎም ከሆነ አባታችን ኣደም ከሌሎች ፍጡራን በምን ተለዩ?! በዚህ ትርጓሜ መሠረት *“አላህ ሁሉንም ነገር በእጁ ነው የፈጠረው!”* ብሎ መናገር ይቻላል ማለት ነው!

ሰዎች በትንሳኤ ቀን አማላጅ ፍለጋ ወደ ታላላቅ ነብያት እየሄዱ በልዩ ትሩፋቶቻቸው ሲያወድሷቸው አባታችን ኣደምን ደግሞ

*«አንተ የሰው ዘር አባት ነህ፤ አላህ በእጁ ፈጥሮሃል፤ መላኢካዎች እንዲሰግዱልህም አድርጓል..»*[1] የሚሏቸው ይህ አንድ መለያቸው ስለሆነ አይደል እንዴ?!

ይህ ግልፅ ነው፤ አል-ሐምዱ ሊ'ላህ! ሆኖም አንዳንዶች አሁንም ይህንን እውነታ ለማፋረስ ቋንቋዊ አገባቡ የሚለይ አንድ የቁርኣን አንቀፅ ይጠቅሳሉ፡-

﴿أَوَلَمْ يَرَوْا۟ أَنَّا خَلَقْنَا لَهُم مِّمَّا عَمِلَتْ أَيْدِينَآ أَنْعَـٰمًا﴾ [يس: ٧١]

➥ «እጆቻችን ከሰሩት እኛ እንስሶችን እንደፈጠርንላቸው ደግሞ አላዩምን?»[ያሲን 71]

ይህንን ከመጀመሪያው አንቀፅ ጋር በማነፃፀር *"ይህ አንቀፅ አላህ እንስሶችን በእጆቹ መፍጠሩን እንደማያመለክተው ሁሉ የመጀመሪያውም አደምን በእጆቹ እንደፈጠራቸው አያመለክትም!"* ይላሉ!

↳ ሆኖም የዐረብኛን ቋንቋ ጠልቆ የተረዳ ሰው የሁለቱን ልዩነት በቀላሉ ማስተዋል ይችላል። ልብ ይበሉ፤ በመጀመሪያው አንቀፅ ሰዋስዋዊ ሂደት ላይ የድርጊቱ ቀጥተኛ ባለቤት ሆኖ የተወሳው አላህ ራሱ ነው፤ እጆቹ ደግሞ የድርጊቱ መፈፀሚያ መሆናቸውን ለማሳየት ከመስተዋድድ ጋር ተቆራኝተዋል፡- «..በሁለቱ እጆቼ

(1) አል-ቡኻሪይ (3340)፣ (7516)፣ ሙስሊም (194)

ስፈጠርኩት..»! ይህ ዓይነት ገለፃ ከላይ እንዳየነው በትክክል በእጅ መፈፀምን የሚያስገነዝብ ነው!

በሌላኛው አንቀፅ ላይ ግን ድርጊቱን በቀጥታ ወደ እጆቹ በማስጠጋት «..እጆቻችን ከሰሩት..» ብሏል። ይህ የዐረብኛ አሰካክ የሚያመላክተው ድርጊትን በጥቅሉ መፈፀምን እንጂ የግድ በእጅ መስራትን አይደለም! አገባቡ የሚያፀናው ዋነኛ መልዕክት የተያያዘው ከእጆቹ ባለቤት ጋር እንጂ ከእጆቹ ራሳቸው ጋር አይደለምና! ያ ቢሆን ኖሮ "እንስሶችን በእጆቻችን እንደፈጠርንላቸው.." ባለ ነበር! ደግሞም በአንቀፁ ላይ ከእጆቹ ጋር ያቆራኘው ቃል «እንደፈጠርንላቸው» የሚለውን ሳይሆን «ከሰሩት» የሚለውን መሆኑ ይህንን እውነታ ያፀናል።

ይህ የተለመደ ገለፃ ሌሎች ቁርአናዊ ምሳሌዎችም አሉት፡-

﴿ وَمَآ أَصَٰبَكُم مِّن مُّصِيبَةٖ فَبِمَا كَسَبَتۡ أَيۡدِيكُمۡ وَيَعۡفُواْ عَن كَثِيرٖ ﴾[الشورى: ٣٠]

➥ «ከመከራም የሚያገኛችሁ ሁሉ እጆቻችሁ በሰሩት ነው፤ ከብዙም ይቅር ይላል»[አሽ-ሹራ 30]

﴿ ذَٰلِكَ بِمَا قَدَّمَتۡ أَيۡدِيكُمۡ وَأَنَّ ٱللَّهَ لَيۡسَ بِظَلَّٰمٖ لِّلۡعَبِيدِ ﴾[آل عمران: ١٨٢، الأنفال: ٥١]

➥ «ያ (ቅጣት) እጆቻችሁ ባስቀደሙት (ስራ) ነው፤ አላህም ለባሮቹ በዳይ ባለመሆኑ ነው!»[አሊ ዒምራን 182 / አል-አንፋል 51]

ልብ ያድርጉ! ሰዎች ኃጢያትን የሚፈፅሙት የግድ በእጆቻቸው ብቻ ስላልሆነ "በእጆቻችሁ በሰራችሁት.." ወይም "በእጆቻችሁ ባስቀደማችሁት.." ሳይሆን እጆቻችሁ በሰሩት፣ እጆቻችሁ ባስቀደሙት ነው ያለው። ስራ በብዛት የሚከናወነው በእጅ ከመሆኑ አንፃር ይህ ዓይነቱ ገለፃ በእጅ የማይፈፀም ስራን ጨምሮ ማንኛውንም ድርጊት በጥቅሉ ለማመላከት ይውላል! በአማርኛችን "እገሌ የእጁን አገኘ!" የሚለው ገለፃ ከዚህ ጋር ይቀራረባል፤ "የስራውን አገኘ!" ማለት እንደሆነ ግልፅ ነው።

ስለዚህ እነሱ ለሚያጣቅሱት አንቀፅ በአተርጓጎም አቻ የሚሆኑት እነዚህና መሰል አንቀፆች እንጂ የመጀመሪያው አይደለም!

በዚህ ላይ ይኸኛው ላይ ራሱ እጆቹን በፀጋ ወይም በችሎታ መተርጎም የሚያስኬድ አይደለም፤ አስፈላጊነትም የለውም፤ ቀድሞውኑ እንስሳዎችን በእጁ እንደፈጠረ የሚያስገነዝብ አይደለምና!

ደግሞም ፀጋ/ውለታ የሚፈለግበት "የድ" (يَد) ብዙ ቁጥሩ "አይዲ" (أَيْدِي) ሳይሆን "አያዲ" (أَيَادِي) ነው።[1]

(1) "አል-ኢባናህ" ሊ'አቢ'ል-ሐሰን አል-ሽዐሪይ ገፅ 452-453 ይመልከቱ።

ሆኖም ይኸኛውም ይሁን የመጀመሪያው አንቀፅ እነሱ በሚሉት ዘይቤ ቢተርጎም ኖሮ እንኳ ይህ ሁሉ ክርክር የአባታችንን አደም አንድ ትሩፋት ለመካድ ካልሆነ በስተቀር የአላህን ሁለት እጆች ለማስተባበል አይረዳቸውም ነበር! ምክንያቱም፡-

**4ኛ-** በቋንቋ ልማዳዊ ህግ መሠረት 'እጅ'፣ 'ፊት' እና የመሳሰሉት ቃላት በዘይቤያዊ ገለፃ የአንድ ህያው ነገር መገለጫ ሆነው የሚወሱት ቀድሞውኑ ከባህሪያቱ ባለቤቶች አንዱ ከሆነ ብቻ ነው!

**ለምሳሌ፡-** "ስልጣኑ በእገሌ እጅ ነው ያለው!" ሲባል ነገሩ በቁጥጥሩ ስር እንዳለ ወይም በፈቃዱ የሚወሰን እንደሆነ እንጂ 'ስልጣን' የሚባል ግዑዝ ነገር በመዳፉ ጭብጥ ውስጥ መኖሩን እንደማያሳይ ግልፅ ነው! እንዲሁም "እገሌ ለድሆች እጁን ይዘረጋል" ሲባል ለጋስነቱን፣ "እጁ አይፈታም" ሲባል ደግሞ ተቃራኒውን ያስገነዝባል! ሆኖም በሁለቱም ገለፃዎች ላይ የግድ የእጁ አካል ላይዘረጋም ላይታጠፍም ይችላል። ግን መስጠት አብዛኛውን ጊዜ የሚፈፀመው እጅን በመዘርጋት ከመሆኑ አኳያ ገለፃው ይህን መሰል መልዕክት ያስተላልፋል!

ታዲያ የቋንቋ ባለቤቶች በዚህ መሳይ ዘይቤ ሕያው ነገርን የሚገልፁት ቀድሞውኑ በትክክል እጅ ያለው ወይም የነበረው ከሆነ ብቻ ስለሆነ ከዘይቤያዊው መልዕክቱ ጎን ለጎን ከእጅ ባለቤቶች

አንዱ መሆኑን ያሳያል።[1] ጭራሽ ህይወት የሌለውን ነገር በተመለከተ ደግሞ “ፊት ለፊት” (بين يديه) እንደሚለው ካሉ እጅግ ጥቂት አገባቦች በስተቀር መሰል ዘይቤያዊ ገለፃዎችን በፍፁም አይጠቀሙም! ለምሳሌ፡- *“ዝናቡ በደመናው እጅ ነው!”* ወይም *“ደመናው ለእርሻው እጁን ይዘረጋል!”..* አይባልም!! ዘይቤው የሚሰራው ለእውነተኛ እጅ ባለቤቶች ብቻ ነውና![2]

በዚህ መሠረት አላህ በዘይቤያዊም ይሁን በሌላ ይዘት ስለ እጁ ያወሳበት ማንኛውም መረጃ በቀጥታም ይሁን በተዘዋዋሪ ባህሪውን በትክክል የሚያፀድቅ ነው! ሰለፎችም የአላህን እጅ በቀጥተኛ ንግግር ከሚያረጋግጡ ማስረጃዎች ባሻገር ይህን መሰል አንቀፆችንም በአስረጅነት ያጣቅሱ የነበረው ከዚህ አንፃር ነው። ለምሳሌ፡-

﴿وَقَالَتِ ٱلۡيَهُودُ يَدُ ٱللَّهِ مَغۡلُولَةٌۚ غُلَّتۡ أَيۡدِيهِمۡ وَلُعِنُواْ بِمَا قَالُواْۘ بَلۡ يَدَاهُ مَبۡسُوطَتَانِ يُنفِقُ كَيۡفَ يَشَآءُ﴾ [المائدة: ٦٤]

---

(1) ግለሰቡ እጆቹ የተቆረጡ ቢሆን እንኳ ቅድሚያ የእጅ ባለቤት የነበረ ከመሆኑ አኳያ በዚህ ገለፃ ውስጥ ይካተታል! ምክንያቱም ሰዎች በመሠረታዊ እይታ ባለ እጆች ናቸውና!

(2) “ነቅዱ ዑሥማን ኢብኒ ሰዒድ ዐላ ቢሽር አል-መሪሲ አል-ዐኒድ” ሊ’ድ-ዳሪሚይ (1/235-238)፤ “መጅሙዑ’ል-ፈታዋ” ሊሸይኺ’ል-ኢስላም (6/370)፤ እንዲሁም “ሙኽተሰር አስ-ሰዋዒቅ አል-ሙርሰላህ” (3/958-968) ይመልከቱ!

➥ «አይሁዶችም "የአላህ እጅ የታሰረች ናት!" አሉ! እጆቻቸው ይታሰሩ! ባሉትም ሳቢያ ይረገሙ! ይልቁንስ ሁለቱ እጆቹ የተዘረጉ ናቸው፤ እንደፈለገው ይለግሳል..»[አል-ማኢዳህ 64]

ይህ አንቀፅ የአላህን ቸርነት ያስገነዝባል፤ ከዚሁ ጋር ደግሞ በትክክል የእጆች ባለቤት መሆኑን አያይዞ ያሳያል፤ ሁለቱ መልዕክቶች የሚነጣጠሉ አይደሉምና!

በዚህ ላይ ደግሞ እነዚያ ከሃዲያን *"እጁ የታሰረች ናት!"* ባሉ ጊዜ የሰጣቸው መልስ ሙዐጥ-ጢላዎች እንደሚሉት *"እርሱ ጭራሽ እጅ የለውም!"* የሚል አይደለም! እንዲያውም «ሁለቱ እጆቹ የተዘረጉ ናቸው!» ብሎ በቁጥር ገድቦ ማስፈሩ እውነታውን ይበልጥ ያፀናል፤ አላህ ልብ ይስጠን!

እንደዚሁም፡-

📖 ﴿تَبَٰرَكَ ٱلَّذِى بِيَدِهِ ٱلْمُلْكُ﴾ [الملك: ١]

➥ «ያ ንግስና በእጁ የሆነው ጌታ ትሩፋቱ በዛ..»[አል-ሙልክ 1]

📖 ﴿فَسُبْحَٰنَ ٱلَّذِى بِيَدِهِۦ مَلَكُوتُ كُلِّ شَىْءٍ﴾ [يس: ٨٣]

➥ «ያ የሁሉም ነገር ስልጣን በእጁ የሆነው (ጌታ) ጥራት የተገባው ነው!»[ያሲን 83]

📖 ﴿بِيَدِكَ ٱلْخَيْرُ﴾ [آل عمران: ٢٦]

➥ «..መልካሙ (ሁሉ) በእጅህ ነው.፡፡»[አሊ ዒምራን 26]

እነዚህና መሰል አንቀፆች አላህ የንግስና፣ የስልጣንና የመልካም ነገር ሁሉ ባለቤት መሆኑን ሲያስገነዝቡ እጅ እንዳለውም በዚያው ያመላክታሉ፤ በመሠረቱ የእጅ ባለቤት ባይሆን ኖሮ እነዚህን መሰል ገለፃዎች አያሰፍርም ነበርና!

በዚህ መሠረት አንዳንድ ጊዜ ቀደምት የኢስላም ሊቃውንት እነኚህን መሰል አንቀፆች ሲያብራሩ የሐረጉን ጥቅል መልዕክት ብቻ አስፍረው ማለፋቸው እንደ 'ተእዊል' የሚቆጠር አይደለም፤ የእጅ ባለቤት መሆኑ የታወቀ በመሆኑ በየቦታው መጠቀሱ የግድ አይደለምና!

↳ በጥቅሉ የ'ተእዊል' አራማጆች ላለመስጠም ባገኘው እንጨት ላይ እንደሚንጠላጠል ሰው ብዙ ቢፍጨረጨሩም ይህንን ማጣሪያ ለማለፍ የሚያስችል መረጃ የላቸውም!

✷ አሁን ደግሞ ወደ **አራተኛው ማጣሪያ** እንለፍ፡- የአንቀፁን ጉልህ መልዕክት ከለቀቁ ወዲህ ከ'ዘይቤያዊ' ትርጓሜዎቹ አንደኛውን ለይቶ ለመምረጥ የሚያስችል በቂ ምክንያት አያቀርቡም! እንዲያውም አብዛኛዎቹ በዚህም ይሁን በሌሎች ቦታዎች ላይ 'ተእዊላቸውን' የሚያራምዱት በጥርጣሬ መንፈስ *"የተፈለገው እንዲህ ሊሆን ይችላል፤ እንዲያም ሊሆን ይችላል..!"* እያሉ የ'ምናልባት' ሀተታዎችን በመደርደር ነው።

➢ *አል-ኢማም **አድ-ዳሪሚይ*** (280 ዓ.ሂ) ለአንድ የጀህሚይ-ያህ አቀንቃኝ ይህንን ብለዋል፡-

«أوَلم تَذْكُرْ فِي كِتَابِكَ أَنَّهُ لَا يُحْتَمَل فِي التوحيد إِلَّا الصَّوَابُ فَقَطْ؟ فَكَيْفَ تَخُوضُ فِيهِ بِمَا لَا تَدْرِي: أَمُصِيبٌ أَنْتَ أَمْ مُخْطِئٌ؟! لِأَنَّ أَكْثَرَ مَا نراك تفسر التوحيد بِالظَّنِّ، وَالظَّنُّ يُخْطِئُ وَيُصِيبُ، وَهُوَ قَوْلُكَ: يَحْتَمِلُ فِي تَفْسِيرِهِ كَذَا، وَيَحْتَمِلُ كَذَا تَفْسِيرًا، وَيَحْتَمِلُ فِي صِفَاتِهِ كَذَا، وَيَحْتَمِلُ خِلَافَ ذَلِكَ، وَيَحْتَمِلُ فِي كَلَامِهِ كَذَا وَكَذَا. وَالِاحْتِمَالُ ظَنٌّ عِنْدَ النَّاسِ غَيْرُ يَقِينٍ، وَرَأْيٌ غَيْرُ مُبِينٍ، حَتَّى تَدَّعِيَ لِلَّهِ فِي صِفَةٍ مِنْ صِفَاتِهِ أَلْوَانًا كَثِيرَةً وَوُجُوهًا كَثِيرَةً أَنَّهُ يَحْتَمِلُهَا لَا تَقِفُ عَلَى الصَّوَابِ مِنْ ذَلِكَ فَتَخْتَارَهُ، فَكَيْفَ تَنْدُبُ النَّاسَ إِلَى صَوَابِ التَّوْحِيدِ، وَأَنت دائب تَجْهَل صِفَاته وَأَنْتَ تَقِيسُهَا بِمَا لَيْسَ عِنْدَكَ بِيَقِينٍ؟ »

*«ተውሒድ ላይ ከትክክለኛው አንድ እምነት በቀር ተቀባይነትን ሊያገኝ የሚችል እንደሌለ በመፅሀፍህ ጠቅሰህ የለ?! ታዲያ እንዴት ትክክል መሆንህን ወይም መሳሳትህን በማታውቅበት ንግግር ስለርሱ ትዘላብዳለህ?! ምክንያቱም ስለ ተውሒድ አብዛኛውን ጊዜ በግምት ስትተነትን ነው የምናይህ! ግምት ደግሞ ሊሳሳት ወይም እውነትን ሊገጥም ይችላል፤ ይህም "ተፍሲሩ እንዲህ ሊሆን ይችላል፤ ይህን ያህል ተፍሲሮችን ያስተናግዳል፤ በባህሪያቱም የተፈለገው እንዲህ ሊሆን ይችላል፤ ከዚህ የተለየ መልዕክትም ያስተናግዳል፤ ንግግሩም እንዲህ ያለ ትርጓሜ ሊኖረው ይችላል.." የምትለው ንግግርህ ነው! "ሊሆን ይችላል" የሚለው ግምት ሰዎች ሁሉ ዘንድ ጥርጣሬ እንጂ እርግጠኝነት አይደለም! ግልፅ ያልሆነ የግል አስተያየት ነው! ከባህሪያቱ በአንዱ ላይ ብቻ የተለያዩና ብዙ አይነት መላምቶችን "ሊሆን ይችላል" በማለት የምትሰነዝር እንጂ ትክክለኛውን ለይተህ የምትመርጥ እንኳ*

*አይደለህም! ታዲያ አንተ ራስህ ባህሪያቱን ሳታውቃቸው እየባዘንክና ራስህ እርግጠኛ ባልሆንክበት መመዘኛ እያነፃፀርካቸው እንዴት ሰዎችን ወደ ትክክለኛው ተውሒድ ልትጠራ ትችላለህ?!»*[1]

በመሠረቱ በዋነኝነት የሚያሳስባቸው ከጉልህ መልዕክቱ ማምለጥ እንጂ የተፈለገውን አምላካዊ መልዕክት መረዳት እንዳልሆነ ከላይ አይተናል!

**✷ አምስተኛው ማጣሪያ ላይ ደግሞ ጭራሽ መፈናፈኛ የለም! አላህ ለርሱ ልቅና የተገቡ እጆች እንዳሉት በማያወላዳ ቃል የሚያረጋግጡትን ሌሎች ማስረጃዎች በምን አቅም ነው ሊጋፈጡ የሚችሉት! እስቲ ለአብነት ያህል በጣም ጥቂቱን እንተዋወስ!**

**አላህ እንዲህ ብሏል፡-**

﴿ وَمَا قَدَرُوا۟ ٱللَّهَ حَقَّ قَدْرِهِۦ وَٱلْأَرْضُ جَمِيعًا قَبْضَتُهُۥ يَوْمَ ٱلْقِيَـٰمَةِ وَٱلسَّمَـٰوَٰتُ مَطْوِيَّـٰتٌۢ بِيَمِينِهِۦ ﴾ [الزمر: ٦٧]

(1) "ነቅዱ ዑሥማን ኢብኒ ሰዒድ ዐላ ቢሽር አል-መሪሲ አል-ዐኒድ" ሊ'ድ-ዳሪሚይ (2/798-799)

➥ «አላህንም በሚገባው ልክ አላከበሩትም! - ምድር በሙሉ በትንሳኤ ቀን ጭብጡ ሆና ሳለ፤ ሰማያትም በቀኙ የሚጠቀለሉ ሆነው..!»[አዝ-ዙመር 67]

የአላህ መልዕክተኛም (ﷺ) የአንቀጹን መልዕክት በአፅኖት ሲያረጋግጡ ጣቶቻቸውን እየጨበጡና እየዘረጉ በማሳየት እንዲህ አሉ:-

☜«يَأْخُذُ اللهُ -عَزَّ وَجَلَّ- سَمَاوَاتِهِ وَأَرَضِيهِ بِيَدَيْهِ، فَيَقُولُ: أَنَا اللهُ، أَنَا الْمَلِكُ..»

➥ «አላህ ሰማያቱንና ምድሮቹን በሁለት እጆቹ ይይዝና "እኔ አላህ ነኝ! እኔ ንጉሱ ነኝ!" ይላል።»(1)

እንዲሁም እንዲህ ብለዋል:-

☜«تَكُونُ الْأَرْضُ يَوْمَ الْقِيَامَةِ خُبْزَةً وَاحِدَةً، يَكْفَؤُهَا الْجَبَّارُ بِيَدِهِ، كَمَا يَكْفَأُ أَحَدُكُمْ خُبْزَتَهُ فِي السَّفَرِ؛ نُزُلًا لِأَهْلِ الْجَنَّةِ»

➥ «ምድር የትንሳኤ እለት አንድ ሙልሙል (ዳቦ) ትሆናለች፤ አንዳችሁ ዳቦውን እያገላበጠ ለጉዞ እንደሚያሰናዳው ሃያሉ (ጌታ) በእጁ አገላብጦ ለጀነት ባለቤቶች መስተንግዶነት ያሰናዳታል!»(1)

(1) (የሙስሊም ዘገባ) አል-ቡኻሪ (7412)፣ ሙስሊም (2788)፣ ከኢብኑ ዑመር እንዳስተላለፉት። እንዲሁም አል-ቡኻሪይ (7283) እና ሙስሊም (2787) ከአቡ ሁረይራህ የዘገቡትን ተመሳሳይ ሐዲሥ ይመልከቱ!

☜«إِنَّ الْمُقْسِطِينَ عِنْدَ اللهِ عَلَى مَنَابِرَ مِنْ نُورٍ، عَنْ يَمِينِ الرَّحْمَنِ -عَزَّ وَجَلَّ-، وَكِلْتَا يَدَيْهِ يَمِينٌ..»

➥ «ፍትኸኞች አላህ ዘንድ በብርኃን መንበሮች ላይ ከአር-ረሕማን በስተቀኝ በኩል ይሆናሉ፤ ሁለቱም እጆቹ ቀኝ ናቸው..»(2)

↳ የአላህ እጆች በነዚህና በሌሎች የቁርኣንና የሐዲሥ ማስረጃዎች እንዲሁም በሰሓቦችና በታቢዒዮች አንደበት 'ተእዊል'ን ሊያስተናግዱ በማይችሉ የተለያዩ አገባቦች ከመቶ ጊዜ በላይ(3) ተደጋግመው ተጠቅሰዋል! ከመያዝ፣ ከመጠቅለል፣ ከመጨበጥ፣ ከመዘርጋት፣ ከጣቶች፣ ከቀኝነት እና ከሌሎች መገለጫዎች ጋር ተወስተዋል! እነዚህ መረጃዎች የማያሳምኑት አላህ ልቦና እንዲሰጠው ይማፀን!

●●●

---

(1) አል-ቡኻሪ (6520)፣ ሙስሊም (2792)፣ *አቡ ሰዒድ አል-ኹድሪይ* ያስተላለፉት።

(2) ሙስሊም (1827)፣ *ዐብዱ'ላህ ኢብኑ ዐምር* ያስተላለፉት። እጆቹ ፍጡራን ዘንድ እንደተለመደው የሚበላለጡ ሳይሆኑ ሁለቱም በትሩፋት ቀኝ ናቸው፤ ይህ የታወቀ የዐረብኛ ስልት ነው። ከዚህ አንፃር ሌላኛው እጁን በ'ግራ' መሰየም ምንም እንኳ አንዳንድ አወዛጋቢ መረጃዎች ላይ ቢፀድቅም አላህን ከማላቅ አንፃር ቃሉን አለመጠቀሙ ተገቢ ስርዓት መሆኑን ያሳያል።

(3) "ሙኽተሰር አስ-ሰዋዒቅ አል-ሙርሰላህ" (3/984)

## “እናንተም እንደኛው..!”

ሙዐጥ-ጢላዎች የሚያራምዱት የ‘ተእዊል’ ቀመር ከመሠረቱ የተፉለሰ እንደሆነ አይተናል!

በዚህም የተነሳ የነብያት ተከታዮች ከቋንቋዊ አገባብ አንፃር ጎልቶ የሚንፀባረቀውን መልዕክት የሚያፀድቁባቸውን አንዳንድ ቀጥተኛ ትርጓሜዎች እንደ “ተእዊል” ቆጥረው *“የኛም ‘ተእዊል’ እንደዚህ ነው!”* በማለት የራሳቸውን ጥመት ለማቃናት ይሞክራሉ!

⮎ የዚህ ውዥንብር ዋነኛ መነሻ ከላይ እንደተጠቆመው የአንድን ንግግር መልዕክት ጉልህነት የሚያዩት ከተሳሳተ አቅጣጫ መሆኑ ነው!

ምሳሌ

ከዚህ በመነሳት የ“ተዕጢል” አራማጆች የሐቅ ባለቤቶችን ከሚሞግቱባቸው ምሳሌዎች አንዱን እንመልከት:-

- አላህ እንዲህ ብሏል:-

📖 ﴿وَهُوَ مَعَكُمۡ أَيۡنَ مَا كُنتُمۡ﴾ [الحديد: ٤]

➥ «እርሱም የትም ብትሆኑ ከናንተ ጋር ነው!»[አል-ሐዲድ 4]

**ብዥታ**

ይህንና መሰል አንቀፆችን በማጣቀስ የሐቅ ተከታዮችን እንዲህ ሲሉ ይሞግታሉ፡- *«የነዚህ አንቀፆች 'ጉልህ' መልዕክት የሚያስገነዝበው አላህ በምድር ላይ ከሰዎች ጋር ተቀላቅሎ እንዳለ ነው! ሆኖም በእውቀቱ፣ በመስማቱ፣ በማየቱ፣ በቁጥጥሩ ..ወዘተ እንጂ እርሱ ራሱ በ'ዛቱ' ከኛ ጋር እንዳልሆነ ማመናችሁ ወደ "ተእዊል" እንዳመራችሁ የሚያሳይ ነው! ስለዚህ እናንተ ጉልህ መልዕክቱን እንዳለ መቀበል ስለማይቻል ይህን "ተእዊል" እንደፈፀማችሁት እኛም ጉልህ መልዕቶችን መቀበል በማይቻልበት ቦታ ላይ ተእዊልን እንፈፅማለን!»*

**መልስ**

ይህ ውዥንብር ውድቅ እንደሆነ ከሚያረጋግጡ በርካታ ምላሾች መካከል ጥቂቱን እነሆ፡-

**አንደኛ፡-** ቀድሞውኑ የነዚህ አንቀፆች ጉልህ መልዕክት እናንተ እንዳላችሁት አላህ በ'ዛቱ' ምድር ላይ ከባሮቹ ጋር ተቅላቅሎ እንዳለ የሚያስገነዝብ ሊሆን አይችልም፤ አብዛኛዎቹ ሙስሊሞችም አንቀፆቹን ሲሰሙ ይህ አፀያፊ እሳቤ በአእምሯቸው ጭራሽ ውል የማይል ሆኖ ሳለ እንዴት 'ጉልህ' ይባላል?! በኢስላም ታሪክም አንድም ዓሊም መሰል አንቀፆችን እናንተ በምትወጥኑት መልኩ አልተረዳም! ይልቁንም አብሮነቱ በእውቀቱ፣ በመስማቱ፣ በማየቱ፣ በመቆጣጠሩና በመሳሰሉት ይዘቶች እደሆነና እርሱ ራሱ ግን ከዐርሹ በላይ እንደሆነ ያለ ምንም ውዝግብ ተስማምተዋል! ይህንን ስምምነታቸውን ከዘገቡት በርካታ ሊቃውንት መካከል አንዱ

የሆኑት *አል-ኢማም አቡ ዑመር አጥ-ጠለመንኪ* (429 ዓ.ሂ) እንዲህ ይላሉ፦

«أجمع المسلمون من أهل السنة على أن معنى ﴿وَهُوَ مَعَكُمْ أَيْنَ مَا كُنتُمْ﴾ ونحو ذلك من القرآن؛ أن ذلك علمُه، وأن الله فوق السموات بذاته مستوٍ على عرشه كيف شاء»

*«የሱን-ናህ ተከታይ ሙስሊሞች ﴿እርሱም የትም ብትሆኑ ከናንተ ጋር ነው!﴾ የሚለውና መሰል የቁርኣን መልእክት 'እውቀቱ' እንደተፈለገበትና አላህ ራሱ ደግሞ ከሰማያት በላይ በዐርሹ ላይ በሻው ሁኔታ ከፍ ብሎ እንዳለ ተስማምተዋል!»*[1]

ሌሎች ሊቃውንትም ይህንን የሰለፎች ስምምነት አፅድቀዋል።[2] ይህ እውነታ አንቀፆቹ የሚያንፀባርቁት ጉልህ መልዕክት እናንተ የምትሉት አይነት ሊሆን እንደማይችል ያረጋግጣል!

ሁለተኛ፦ "ከናንተ ጋር" (معكم) የሚለው አገላለፅ በዐረብኛም ይሁን በሌሎች ቋንቋዎች የሚያስተላልፈው መሠረታዊ መልዕክት ሰፊ በመሆኑ ጥቅል አብሮነትን እንጂ የግድ የቦታ መጋራትን

---

(1) "አል-ዉሱል ኢላ መዕሪፈቲ'ል-ኡሱል" በሚለው መፅሀፋቸው ያሰፈሩት። ["በያን ተልቢሲ'ል-ጀህሚይ-ያህ" (1/186)፤ "አል-ዑሉው" ገፅ 246 ይመልከቱ።]

(2) ከሰሓቦች ዘመን ጀምሮ የነበሩ ቀደምት ምሁራን የአላህ አብሮነት በእውቀቱና በመሳሰሉት ይዘቶች እንጂ በ'ዛቱ' እንዳልሆነ የተናገሯቸውን አንዳንድ ጥቅሶች ከአንቀፆቹ ማብራሪያዎች ጋር ለማየት *"አል-አሣሩ'ል-መርዊይ-ያህ ፊ ሲፈቲ'ል-መዒይ-ያህ"* የተሰኘውን መፅሀፍ ይመልከቱ!

የሚያስገነዝብ አይደለም! ይህንን ጥቅል መሠረታዊ መልዕክት በተወሰነ ይዘት ላይ የሚገድበው ቃሉ የተነገረበት አገባብና አኳያ ነው። 'ጉልህ' መልዕክት የሚባለውም ከዚህ አንፃር ሰዎች በቀላሉ የሚገነዘቡት መልዕክት ነው።

**ለምሳሌ፡-** በጎም ይሁን መጥፎ ተግባርን ከሌሎች ጋር መጋራት በአብሮነት (معيّة) ሊወሳ ይችላል፤ አላህ እንዲህ ብሏል፡-

📖 ﴿ يَٰٓأَيُّهَا ٱلَّذِينَ ءَامَنُوا۟ ٱتَّقُوا۟ ٱللَّهَ وَكُونُوا۟ مَعَ ٱلصَّٰدِقِينَ ﴾ [التوبة: ١١٩]

➥ «እናንተ ያመናችሁ ሆይ! አላህን (በመፍራት) ተጠንቀቁት፤ ከእውነተኞችም ጋር ሁኑ!»[አት-ተውባህ 119]

እንዲሁም መላኢካዎች ለመርየም እንዲህ እንዳሏት ነግሮናል፡-

📖 ﴿ ...وَٱرْكَعِى مَعَ ٱلرَّٰكِعِينَ ﴾ [آل عمران: ٤٣]

➥ «..ከአጎንባሾች ጋርም አጎንብሺ (ስገጂ)!»[አሊ ዒምራን 43]

ይህ መቼም እርሷ ከወንዶች ጋር ተቀላቅላ እንደምትሰግድ አያመላክትም!

- እንዲሁም አንድ ሰው በአንድ ሀይማኖታዊ ወይም ሌላ ርዕስ ላይ ስላለው አቋም ሲጠየቅ "ከ'እገሌ' ጋር ነኝ!" ብሎ ሊመልስ ይችላል፤ ምናልባት ግን በእሱና በ'እገሌ' መካከል ሰፊ የቦታ ርቀት ይኖራል፤ እንዲያውም 'እገሌ' ከብዙ ክፍለ-ዘመናት በፊት የኖረ

ግለሰብም ሊሆን ይችላል! ስለዚህ ከዚህ አገባብ የምንረዳው ጉልህ መልዕክት በአቋም ከርሱ **ጋር** መሆኑን እንጂ አንድ ቦታ ላይ መሰባሰባቸውን አይደለም!

- እንደዚሁ ሁሉ "**በንግድ ስራ** ከእገሌ ጋር መሆን፣ **በጋብቻ** ከእገሌ ጋር መሆን፣ **በሀሳብ** ከእገሌ ጋር መሆን፣ **በቦታ** ከእገሌ ጋር መሆን.." የሚሉት አባባሎች በአገባባቸው ልዩነት የተነሳ የተለያዩ የአብሮነት መልዕክቶችን ያስጨብጣሉ!

- እንዲሁም ዐረቦች "ለሊቱን ሙሉ ስንጓዝ ጨረቃ **ከኛ ጋር** ነበረች!" ሲሉ ከገለፃው ከጨረቃ ጋር በአንድ ቦታ መሰባሰባቸውን የሚገነዘብ የለም! ምናልባትም አንድ ሰው *"ይህ ጉልህ መልዕክቱ ነው!"* ብሎ ቢናገር ሊሳቅበት ይችላል!

- እንዲሁም በሌላ አገር ያሉ ሰዎችን በስልክ እያናገረ ወይም በቀጥታ የምስል ቀረፃ ድርጊታቸውን እየተከታተለ ያለ ግለሰብ "ከነእገሌ ጋር ነኝ.." ብሎ መናገሩ የተለመደ ነው።

- እንደዚሁም አንድ ንጉስ ወይም ባለ ፀጋ ወይም ሌላ ሰው በሌላ አገር ያሉ ወገኖቹን የተለያዩ እርዳታዎችን እንደሚለግሳቸው ለመግለፅ "አይዟችሁ! እኔ ከናንተ ጋር ነኝ!" ይላቸዋል!

➢ *አል-ኢማም አቡ ሐኒፋ* አላህ በሰማይ (ከፍጡራኑ በላይ) እንጂ በምድር አለመሆኑን በፅሁፍ ባሰፈሩ ጊዜ አንድ ሰው ﴿وَهُوَ مَعَكُمْ﴾ *(እርሱም ከናንተ ጋር ነው!)* ስለሚለው አንቀፅ ሲጠይቃቸው

*«ወደ አንድ ሰው ከርሱ የራቅክ ሆነህ ሳለ "እኔ ካንተ ጋር ነኝ!" ብለህ እንደምትፅፈው ነው!»* ብለው መመለሳቸው ተዘግቧል። (1)

**ስለዚህ** በነዚህና በመሰል አኳያዎች ፍጡራን ሩቅ ካሉት ጋር (አብረው) መሆናቸው የሚቻል ከሆነ አላህ ከፍጥረተ-ዓለሙ በላይ ከፍ ያለ ሆኖ ከባሮቹ ጋር መሆኑ እንዴት ይታበላል?! የፍጡራን አብሮነት የግድ በቦታ መሰባሰብን የሚያመላክት ካልሆነ የታላቁ ፈጣሪ አብሮነት እንዴት ይህንን ያመላክታል?!

✸ አላህ ከባሮቹ ጋር መሆኑን የገለፃባቸው አንቀፆች በቋንቋዊ አከሻሸናቸው ሁለት አይነት የአብሮነት መልዕክትን ሊያስገነዝቡ ይችላሉ፡-

1- ከሙስሊሙም ይሁን ከሌላው ጋር መሆኑን በሚያሳዩ **አገባቦች** ላይ በእውቀቱ፣ በመስማቱ፣ በማየቱ፣ በቁጥጥሩ.. ወዘተ ከሁሉም ጋር መሆኑን፤

2- አብሮነቱን በአማኞች ላይ በሚገድብ **አገባብ** ደግሞ ከላይኛው መልዕክት ባሻገር በእርዳታው፣ በእንክብካቤው፣ በጥበቃውና በመሳሰሉት አኳያዎች ከነርሱ ጋር መሆኑን።

እናም ከአንቀፆቹ **በቀጥታ** የምንረዳው **ጉልህ** መልዕክት ይህ በመሆኑ የ'ተእዊል' ጥምዘዛ አያስፈልገውም!

---

(1) "አል-አስማኡ ወስ-ሲፋት" ሊ'ል-በይሀቂይ (2/337) ይመልከቱ።

ሶስተኛ፡- አንቀፆቹ እርሱ በ‘ዛቱ’ ከእኛ ጋር ተቀላቅሎ መገኘቱን ጭራሽ እንደማያስገነዝቡ ከሚያስረዱት እውነታዎች መካከል አብዛኛዎቹ የእውቀቱን ፍፁምነትና መሰል መልዕክቶችን በሚያረጋግጡ አገባቦች የታጀቡ መሆናቸው ነው።

**ለምሳሌ የላይኛውን አንቀፅ በሙሉ አገባቡ እናጢነው፡-**

📖 ﴿ هُوَ ٱلَّذِى خَلَقَ ٱلسَّمَٰوَٰتِ وَٱلْأَرْضَ فِى سِتَّةِ أَيَّامٍ ثُمَّ ٱسْتَوَىٰ عَلَى ٱلْعَرْشِ ۚ يَعْلَمُ مَا يَلِجُ فِى ٱلْأَرْضِ وَمَا يَخْرُجُ مِنْهَا وَمَا يَنزِلُ مِنَ ٱلسَّمَآءِ وَمَا يَعْرُجُ فِيهَا ۖ **وَهُوَ مَعَكُمْ أَيْنَ مَا كُنتُمْ** ۚ وَٱللَّهُ بِمَا تَعْمَلُونَ بَصِيرٌ ﴾[الحديد: ٤]

➥ «እርሱ ያ ሰማያትንና ምድርን በስድስት ቀናት የፈጠረ፤ ከዚያም በዐርሹ ላይ ከፍ ያለ ነው፤ በምድር ወስጥ የሚገባውን፣ ከርሷም የሚወጣውን፣ ከሰማይ የሚወርደውን በእርሷ ውስጥ የሚያርገውንም ያውቃል፤ **እርሱም የትም ብትሆኑ ከናንተ ጋር ነው፤** ለሳህም የምትሰሩትን ተመልካች ነው!»[አል-ሐዲድ 4]

**ልብ ይበሉ! በዐርሹ ላይ መሆኑን ከገለፀ በኋላ የእውቀቱን ፍፁምነት በምሳሌዎች አስገነዘበን፤ ከዚያም ከኛ ጋር መሆኑን ጠቅሶ የምንሰራውን ሁሉ እንደሚመለከት በመንገር አንቀፁን ቋጨ። ከፊትና ከኋላ ያሉት አረፍተ-ነገሮች የአብሮነት መልዕክቱ በእውቀቱ፣ በማየቱና በመቆጣጠሩ የሚገለፅ መሆኑን ቁልጭ አድርገው ስለሚያብራሩ የአንቀፁ ጉልህ መልዕክት ምን እንደሆነ መረዳት አያዳግትም!**

በዚህ ላይ ደግሞ ከዐርሹ በላይ መሆኑን በመክፈቻው ላይ አስቀድሞ ማፅናቱ “ከናንተ ጋር ነው” ከሚለው ቃል እርሱ ራሱ በምድር ከባሮቹ ጋር መሆኑን ለመገንዘብ ምንም ያህል መፈናፈኛ አላስቀረም! አዎን! አላህ ከዐርሹ በላይ ከፍጥረተ-ዓለሙ ውጭ ከመሆኑ ጋር ከዕውቀቱ የሚሰወር፣ ከእይታው የሚሸሸግ፣ ከቁጥጥሩ የሚወጣ.. ቅንጣት ነገር ባለመኖሩ **በትክክል ከባሮቹ ጋር ነው!** ስለሆነም በርካታ የሰለፍ ሊቃውንት ሁለቱን መልዕክቶች በአንድ ላይ አያይዘው ይናገሩ ነበር። ለአብነት ያህል፦

➢ ታላቁ ሰሓቢይ ***ዐብዱ’ላህ ኢብኑ መስዑድ*** (رضي الله عنه) እንዲህ ይላሉ፦

«.. والله فوق العرش، ولا يخفى عليه شيءٌ مِن أعمالكم»

*«..አላህም ከዐርሹ በላይ ነው፣ ከምትሰሩትም ምንም ነገር አይሸሸግበትም!»*[1]

ሌላ ምሳሌ፦

(1) “አል-ሙዕጀሙ’ል-ከቢር” ሊ’ጥ-ጠበራኒ (9/228)፣ “አር-ረድ-ዱ ዐለ’ል-ጀህሚይ-ያህ” ሊ’ድ-ዳሪሚይ ገፅ 55፣ “አት-ተውሒድ” ሊብኒ ኹዘይማህ (1/243-244)፣ “አል-ዐዞማህ” ሊአቢ’ሽ-ሸይኽ (2/565)፣ “ሸርሑኡሱሊ’ዕቲቃዲ አህሊ’ስ-ሱን-ናህ” ሊ’ል-ላለካኢይ (3/395-396)፣ “አል-አስማኡ ወስ-ሲፋት” ሊ’ል-በይሀቂይ (2/291) ..እና በሌሎች መዛግብት የተላለፈ ሲሆን *አል-ኢማም አዝ-ዘሀቢይ* [“አል-ዑሉው” ገፅ 79] እና ሌሎች የዘገባውን ትክክለኛነት መስክረዋል።

📖 ﴿أَلَمْ تَرَ أَنَّ ٱللَّهَ يَعْلَمُ مَا فِي ٱلسَّمَٰوَٰتِ وَمَا فِي ٱلْأَرْضِ ۖ مَا يَكُونُ مِن نَّجْوَىٰ ثَلَٰثَةٍ إِلَّا هُوَ رَابِعُهُمْ وَلَا خَمْسَةٍ إِلَّا هُوَ سَادِسُهُمْ وَلَآ أَدْنَىٰ مِن ذَٰلِكَ وَلَآ أَكْثَرَ **إِلَّا هُوَ مَعَهُمْ أَيْنَ مَا كَانُوا۟** ۖ ثُمَّ يُنَبِّئُهُم بِمَا عَمِلُوا۟ يَوْمَ ٱلْقِيَٰمَةِ ۚ إِنَّ ٱللَّهَ بِكُلِّ شَىْءٍ عَلِيمٌ﴾ [المجادلة: ٧]

➥ «አላህ በሰማያት ውስጥ ያለውን በምድርም ውስጥ ያለውን ሁሉ የሚያውቅ መሆኑን አታይምን? ከሦስት ሰዎች መንሾካሾክ አይኖርም - እርሱ አራተኛቸው ቢሆን እንጂ፤ ከአምስትም (አይኖርም) - እርሱ ስድስተኛቸው ቢሆን እንጂ፤ ከዚያ ያነሰም የበዛም (አይኖርም) - **እርሱ የትም ቢሆኑ ከነርሱ ጋር ቢሆን እንጂ!** ከዚያም በትንሣኤ ቀን የሠሩትን ሁሉ ይነግራቸዋል፤ አላህ ነገሩን ሁሉ ዐዋቂ ነው።»[አል-ሙጃደላህ 7]

የአንቀፁ መክፈቻ ስለ እውቀቱ፣ መዝጊያውም ስለ እውቀቱ እንደሚያወሳ ያስተውሉ! አዎን! ቀደምት አበው መሰል አንቀፆችን ተገን በማድረግ "አላህ ሁሉ ቦታ ነው" ሲሉ ለሚከራርከሩ ወገኖች ማምታቻ ይህን መሰል ማብራሪያ እንደ እርማት ይሰጡ ነበር። [1]

አሁንም ሌላ ምሳሌ፡-

📖 ﴿قَالَ لَا تَخَافَآ ۖ إِنَّنِى مَعَكُمَآ أَسْمَعُ وَأَرَىٰ﴾ [طه: ٤٦]

(1) ለተወሰኑ ጥቅሶች *"አል-አሣሩ'ል-መርዊይ-ያህ ፊ ሲፈቲ'ል-መዒይ-ያህ"* የተሰኘውን መፅሀፍ ከገፅ 18 ጀምሮ ይመልከቱ!

➥ «(ሶላህም) "አትፍሩ! እኔ ከናንተ ጋር ነኝና - እሰማለሁ አያለሁም!" አለ።»[ጣሃ 46]

አራተኛ፡- አላህ ከፍጡራኑ በላይ መሆኑ ስፍር ቁጥር በሌላቸው መረጃዎች የተረጋገጠ በመሆኑ አብሮነቱ ከባሮቹ ጋር በቦታ መቀላቀሉን ሊያመላክት አይችልም![(1)]

---

↳ **በጥቅሉ** ይህ የሰለፎች ግንዛቤ ከሁል ጊዜው መርሃቸው ያፈነገጠ "ተእዊል" እንዳልሆነ ግልፅ ሆኗል፤ ምክንያቱም አላህ ከፍጡራኑ ጋር መሆኑን የገለፀባቸው ማስረጃዎች ቀድሞውኑ የቦታን መጋራት የሚያስገነዝቡ ስላልሆኑ መልዕክታቸውን ከላይ በተገለፀው መልኩ ማፅደቁ ጉልህ ቋንቋዊ ይዘታቸውን መከተል እንጂ የ"ተእዊል" ትርጓሜን ማራመድ አይደለምና! ይህንን የግድ "ተእዊል" ብለን መጥራት እንዳለብን የሙጥኝ ብሎ የሚሞግት ካለለ ደግሞ፡- ይህ ተፍሲር የተዕጢል አራማጆች እንደሚያደርጉት የማያወላዱ ማስረጃዎችን በሚፃረር ፀጉር ስንጠቃ ቃላትን መጠምዘዝና ትርጉም ማዛባት ሳይሆን ቁልጭ ያሉ ማስረጃዎችን ተመርኩዞ እውነታውን

(1) የአላህን ከፍጥረተ-ዓለሙ በላይ መሆን በቀጥታም ይሁን በተዘዋዋሪ የሚያረጋግጡ ዝርዝር መረጃዎች ከሺህ እንደሚበልጡ አንዳንድ ቀደምት ምሁራን ተናግረዋል! ለምሳሌ ከአንጋፋዎቹ የሻፊዒያህ መዝሀብ ሊቃውንት አንዱ እንዲህ ይላሉ፡- *«በቁርኣን ውስጥ አላህ ከፍጥረታቱ በላይ እንዳለ የሚያመለክቱ አንድ ሺህ ወይም ከዚያ በላይ የሆኑ መረጃዎች አሉ!»* ("መጅሙዑ'ል-ፈታዋ" ጥራዝ 5 ገፅ 121 ይመልከቱ።) በርካታ የኢስላም ሊቃውንትም የተወሰኑት መረጃዎችን ያሰባሰቡ ጥራዞችን ደርሰዋል!

ማብራራት ነው! ስለዚህ በምንም መልኩ የሐቅ ባለቤቶች መንገድ ከጥመት ሰለባዎች መንገድ ጋር ሊነፃፀር አይችልም። አል-ሐምዱ ሊጎላህ!

ከላይ በተብራራው መልኩ አላህ **ቅርብ** መሆኑን የጠቀሰባቸውና መሰል ገለፃዎች ላይ የሚነሱ ተመሳሳይ ውዥንብሮችም መልስ ሊያገኙ ይችላሉ!

ooo

# ክፍል ሰባት

## የማንቂያ ደወል!

በቁርኣንና በትክክለኛ ሐዲሦች በግልፅ ሂደት የፀደቁትን የአላህ ስሞችና ባህሪያት ለርሱ ልቅና በሚገባ መልኩ እንዳሉ ማረጋገጥ አማራጭ የሌለው ግዴታ መሆኑ በተለያዩ ማስረጃዎች ተብራርቷል!

ይሁንና አብዛኞዎቹን የአላህ መገለጫዎች ለፈጣሪ የማይገባ **ጉድለትን እንደሚያንፀባርቁ** በማመን ሳይታክቱ አንድ በአንድ የሚያፋርሱና ትርጓሜያቸውንም የሚጠመዝዙ ጎራዎች እንዳሉ አውቀናል። ይህ አካሄዳቸው በተዘዋዋሪ የሚያንፀባርቀው መልዕክት እጅግ አደገኛ ነው! ሆኖም አብዛኞዎቹ አይረዱትም!

↳ ከዚህ በፊት እንደተገለፀው የአንድ ተናጋሪ ንግግር በተወሰኑ ርዕሶች ላይ ሁል ጊዜ አሻሚና የተድበሰበሰ የሚሆነው፡-

- ወይ ስለ ጉዳዩ ካለው እውቀት ማነስ ነው፤

- ወይ ደግሞ ከአገላለፅ ችሎታው ማነስ ነው፤

- አሊያም እውነታውን የመግለፅ ፍላጎት (ቅንነት) ካለመኖር ነው!

ከእነኚህ ሶስት እንከኖች አንዱም በአላህና በመልዕክተኛው ንግግር ወስጥ ፍፁም ሊኖር እንደማይችል ደግሞ የማይታበል እውነታ ነው።[1]

በዚህ መሠረት እነዚያ የ‘ተዕጢል’ አራማጆች ካሉበት ሰመመን ይነቁ ዘንድ የሚከተሉትን ጥያቄዎች እናቀርብላቸዋለን፡-

1- የቁርኣን አንቀፆችና የመልዕክተኛው አስተምህሮቶች እነዚያን የተለያዩ የአላህ ባህሪያት ደግመው ደጋግመው በሚያፀኑ የተለያዩ አገባቦች የሚያወሱት ለምንደነው?

1.1- አላህና መልዕክተኛው ለጌታ የሚገባውን መገለጫ ‘እንደናንተ’ የማያውቁ ሆነው ነው?!

1.2- ወይስ እናንተ በምታዘወትሯቸው ቃላት እውነታውን መግለፅ ተስኗቸው?!

1.3- ወይስ ሆን ብለው ጉዳዩን በማድበስበስ ሙስሊሞችን ለማሳሳት ነው?!

መልሳችሁ *“እረ በፍፁም..!”* የሚል እንደሆነ እንጠብቃለን! ታዲያ ምነው ለነዚያ ግልፅ መለኮታዊ መመሪያዎች እጅ መስጠት ተሳናችሁ?!

(1) በምዕራፍ አንድ ላይ የመጀመሪያውን መርሆ ማብራሪያ ደግመው ቢያዩት ይበልጥ ይጠቀማሉ!

**2- አላህ ስለ ቁርኣን ወደ እውነት የሚመራ ብርሃን፣ የተብራሩ አንቀፆችን ያዘለ፤ ለግንዛቤ የቀለለ፤ በግልጽ ዐረብኛ ቋንቋ የወረደ እና የመሳሰሉት መገለጫዎችን የተላበሰ እንደሆነ የሚነግረን ሁሉ እውነት አይደለም ማለት ነው?!**

***መቼም "እውነት ነው እንጂ!.." ማለታችሁ አይቀርም! ታዲያ፡-***

**2.1- የጌታን ህልውና በሚመለከተው በዚህ ታላቅ መሠረት ላይ ቁርኣን የሚያንፀባርቀው ጉልህ መልዕክት ክህደትን የሚያስገነዝብ ሊሆን ይችላል?!**[1]

**2.2- ወይስ አላህ በተዟዟረ ዘይቤ ራሱን ለማወደስ በቀጥታ ጉድለትን የሚያስተላልፉ ገለፃዎችን ደጋግሞ ያሰፍራል?**

**2.3- እንዴትስ የቁርኣን አንቀፆች እርስ በርስ የሚቃረኑ ግልፅና ድብቅ መልዕክቶችን አጣምረው ያስተላልፋሉ? እንዲያ ከሆነ ቁርኣን ሰምና ወርቁ ከሚያደናግር የቅኔ ፈተና የባሰ እንቆቅልሽ ነው ማለት አይደል?!**

---

(1) ከአሽዐሪይ-ያህ ታላላቅ አቀንቃኞች አንዱ የሆነው *አስ-ሰኑሲ* (895 ዓ.ሂ) ***"የክህደት /የኩፍር/ መሠረቶች*** *ስድስት ናቸው.."* ብሎ አምስቱን ዘርዝሮ ስድስተኛውን እንዲህ ሲል ገለፀ፡- *"በእምነት መሠረቶች ላይ የቁርኣንና የሐዲሥ ጉልህ መልዕክቶችን በአእምሯዊ ማስረጃዎችና በቁርጠኛ ሸሪዓዊ እውነታዎች ሳይመዝኑ እንዳሉ መያዝ.."*!! ["ሸርሑ ኡም-ሚ'ል-በራሂን" ገፅ 81] እንደዚሁም *አስ-ሷዊ* እንዲህ ይላል፡- *"..የቁርኣንና የሐዲሥ ጉልህ መልዕክቶችን መያዝ ከኩፍር መሠረቶች ነውና!"!!*["ሓሺየቱ'ስ-ሷዊ ዓላ ተፍሲሪ'ል-ጀላለይን" (3/9)]

**3- በዚህ ጉዳይ ላይ ሰዎች ምራቻን የሚያገኙት እናንተ በምትዳክሩበት "አእምሯዊ" መንገድ ከሆነ ቁርኣን የመውረዱ ፋይዳ ምንድነው?**

**3.1- እንዲያውም እንደናንተ አባባል ቁርኣን ብዙ ቦታዎች ላይ ስለ አላህ መገለጫዎች የሚያንፀባርቀው ጉድለትን ስለሆነ አማኞች እነዚህን ገለፃዎች ተከትለው በገፍ "ከሚጠሙ" ጭራሹኑ ባይወርድ አይሻልም ነበር?!**

**3.2- ወይስ ዓላማው በውስጡ ያሉትን የአላህ መገለጫዎች በግሪክ ፈላስፋዎች መርሆ መሠረት እንደምንም ማፍረስና መልዕክታቸውን በተገኘው መሳሪያ መቆልመም የሚችለው "ጮሌ" ማን እንደሆነ እድሜ በማይፈታው የእንቆቅልሽ ፈተና መለየት ነው?!**

**3.3- ውዝግባችንን ሁሉ ወደ አላህና መልዕክተኛው አስተምህሮት እንድንመልስ በቁርኣን ውስጥ በአፅኖት የታዘዝነውስ "እንቆቅልሹን" ይባስ ለማወሳሰብ ነው?!**

**አንዳንዶች ከነዚህ ፅኑ ጥያቄዎች ለመገላገል የሚመዙት አንድ ደካማ መልስ አለ፡- *«እነዚህን አንቀፆች ያወረደው ሊፈትነን ነው!»* ይላሉ!**

**ይህ በዚህ ቦታ በፍፁም የማይገጥም መልስ ነው፤ ምክንያቱም፡-**

**ሀ- አላህ ሰዎችን የሚፈትነው እውነቱን ከጥመቱ በግልፅ የሚለዩ መመሪያዎችን ካወረደ በኋላ ብቻ ነውና! አላህ እንዲህ ብሏል፡-**

📖 ﴿ وَمَا كَانَ ٱللَّهُ لِيُضِلَّ قَوۡمَۢا بَعۡدَ إِذۡ هَدَىٰهُمۡ حَتَّىٰ يُبَيِّنَ لَهُم مَّا يَتَّقُونَۚ ﴾[التوبة: ١١٥]

➥ «አላህ ህዝቦችን ከመሩቸው በኋላ የሚጠነቀቁትን ግልፅ እስኪያደርግላቸው ድረስ የሚያጠማቸው አይደለም!» [አት-ተውባህ 115]

በነዚህ ሰዎች ግንዛቤ መሰረት ግን እርሱ አምሳያ እንደሌለው በደፈናው ከሚጠቁሙ ጥቂት አንቀፆች በቀር ባህሪያቱ በዝርዝር የተወሱባቸው አንቀፆችን ጉልህ መልዕክት መቀበል እንደማይገባ በቁርኣንም ይሁን በመልዕክተኛው አንደበት አንድም ግልፅ መረጃ ሳያስተላልፍልን የራሱን ቃል ተከትለን መንገድ ከሳትን በኋላ ለቅጣት ሊዳርገን ነው ማለት ነው!

**ለ-** ይህ ከጥቅሙ ይልቅ ጉዳቱ እጅግ ያመዘነና አብዛኛውን አማኝ ለጥመት የሚዳርግ ፈተና ይሆን ነበር፡- ለመሆኑ እነኚህን ግልፅ መልዕክት ያዘሉ አንቀፆችና ነብያዊ አስተምህሮቶች በ"ዒልመ'ል-ከላም" መርሆዎች ገልብጠው መረዳት የሚችሉት "ሙስሊሞች" ስንት ናቸው?!

**ሐ-** ይህ ከላይ እንደተብራራው የቁርኣንና የሐዲሥ አስተምህሮት ግልፅነትን የሚቃረን አባባል ነው!

**መ-** ይህ በቁርኣንና በሐዲሥ የተወደሱት ቀደምት ትውልዶች የማያውቁት አዲስ ፍልስፍና ነው፤ እውነት ቢሆን ከሌሎች በፊት አውቀውት ለተከታዩ ትውልድ በገለፁት ነበር።
ሌሎች ምክንያቶችንም መጥቀስ ይቻላል..

4- የአላህ መልዕተኛ (ﷺ) ዘንድ ኢስላምን ለመማር አዋቂውም አላዋቂውም፣ ከተሜውም አገሬውም፣ ትልቁም ትንሹም ሁሉም ከተለያየ የግንዛቤ ደረጃቸው ጋር ሲመጡ እርሳቸው አንዱን ከሌላው ሳይለዩ የአላህን ባህሪያት ያዘሉትን ቁርአናዊ አንቀፆችና ነብያዊ አስተምህሮቶች ያለ “ማስጠንቀቂያ” በገሀድ ያስተላልፉ ነበር። ታዲያ፡-

4.1- ግልፅ መልዕክቶቻቸው የተፈለጉ ባይሆን ኖሮ የ“ተእዊል” ማብራሪያዎችን በማከል ተከታዮቻቸውን ከውዥንብር እንዳያድኑ ምን ከለከላቸው?!

4.2- እንዴትስ ሙዐጥ-ጢላዎች ዘውትር እንደሚያደርጉት ባህሪያቱን በግልፅ ባያፋርሱ እንኳ ቢያንስ አንድ ቀን እንኳ ቀጭን ጥቆማ ሳያስተላልፉ አለፉ?

5- በአላህና በመልዕክተኛው አንደበት የተወደሱት ሰሓቦችና ተከታይ ትውልዶች የሙስሊሙ ህብረተሰብ ቀዳሚ ተምሳሌትና አርዓያ መሆናቸው ይታወቃል። ታዲያ፡-

5.1- ይህን መሠረታዊ “እውነታ” እነኚህ ምርጥ ትውልዶች ሳይረዱት ቀርተው ከጊዜ በኋላ የመጡት የከሃዲያን ፍልስፍና አቀንቃኞችና የእምነት ኋላ ቀሮች ደረሱበት ማለት ነው?!

5.2- ወይስ ሰለፎች እናንተ እንደምታደርጉት አጋጣሚ ሲመቻችም ሳይመቻች የእነዚህን መረጃዎች መልዕክት

ለማፋረስና ለመቆልመም ያልታደሉት ለዲን 'እንደ እናንተ' የሚቆረቆሩ ስላልነበሩ ነው?!

**5.3-** ይልቁንም በቁርኣንና በሐዲሥ የፀደቁትን የጌታ ባህሪያት በቀጥታና በተዘዋዋሪ የሚያረጋግጡ ግልፅ ንግግሮችን ይሰነዝሩ የነበረውስ ሆን ብለው ጉዳዩን ለማድበስበስ ነበር?!

---

**በመጨረሻም** አላህ ራሱን የገለፀባቸውን ባህሪያት ማፋረስን እንደ መሠረታዊ እምነት በመቁጠር በተለያዩ ውዥንብሮች የሙስሊሙን ህብረተሰብ ሰላም ለሚያደፈርሱት ወገኖች የሚከተለውን ስጦታ አበረክታለሁ፡-

## ታሪካዊ ውይይት

*"ቁርኣን ፍጡር ነው!"* የሚለውን የአላህን የመናገር ባህሪ የሚያፋርስ የክህደት አቋም ባለመቀበላቸው ታስረው የነበሩ አንድ በእድሜ ጠና ያሉ ዓሊም ከ*አሕመድ ኢብን አቢ ዱኣድ*[1] ጋር ኸሊፋው *አል-ዋሢቅ* (232 ዓ.ሂ) ባለበት ያደረጉትን ምልልስ በአጭሩ እንደሚከተለው አቀርበዋለሁ፡-

(1) ይህ የጀህሚይ-ያህ አቀንቃኝ *አል-ኢማም አሕመድ*ን ለማስገደል ሲጥር የነበረ የሱን-ናህ ቀንደኛ ጠላት ነው!

- [ኸሊፋው ለዓሊሙ፡-] *“ከአሕመድ ኢብን አቢ ዱኣድ ጋር ተወያዩ!”...*
- [ዓሊሙ፡-] *“አሚሩ’ል-ሙእሚኒን ሆይ! የምንመላለሳቸውን ቃላት በደንብ ብታስተውልልን..?”*
- [ኸሊፋው፡-] *“እሺ!”*
- [ዓሊሙ ለኢብኑ አቢ ዱኣድ፡-] *“ይህ ሰዎችን ወደ እርሱ የምትጣራው (የቢድዓህ) ንግግርህ የዲን እምነት ወስጥ የሚካተት ግዴታና ያለ እርሱ ዲን የማይሞላ ነውን?”*
- [ኢብኑ አቢ ዱኣድ፡-] *“አዎን!”*
- [ዓሊሙ፡-] *“አላህ መልዕክተኛውን (ﷺ) ወደ ባሮቹ ሲልክ እርሳቸው እንዲያስተላልፉ ከታዘዙት የዲን ጉዳይ የሸሸጉት ነገር አለ?”*
- [ኢብኑ አቢ ዱኣድ፡-] *“የለም”!*
- [ዓሊሙ፡-] *“ታዲያ መልዕክተኛው (ﷺ) ወደዚህ ንግግርህ ተጣርተዋል?!”*
- [ኢብኑ አቢ ዱኣድ፡-] (ፀጥ!)[1]
- [ዓሊሙ፡-] *“ተናገር እንጂ!”*
- [ኢብኑ አቢ ዱኣድ፡-] (አሁንም ፀጥ!)
- [ዓሊሙ ለኸሊፋው] *“አሚሩ’ል-ሙእሚኒን ሆይ! አንድ (ብለህ ቁጠርልኝ)!”*
- [ኸሊፋው፡-] *“አንድ!”*

---

(1) “አዎን!” ካለ በምንም መረጃ ሊደግፈው የማይችል አይን ያፈጠጠ ቅጥፈት ስለሚሆን ነው ዝም ያለው! መልዕክተኛው (ﷺ) ወደ ተዕጢል ተጣርተዋል ብሎ የሚሞግት ካለ የምላሱን ቅጥፈት ልቦናው ያውቀዋል!

- [ዓሊሙ ለኢብኑ አቢ ዱኣድ፡-] "ማነው እውነተኛው? ሀይማኖታችንን እንዳሚላልን የነገረን[አል-ማኢዳህ 3] አላህ? ወይስ ይህንን መጤ ንግግርህን እስክናምን ድረስ ጎዶሎ እንደሆነ የነገርከን አንተ?!"
- [ኢብኑ አቢ ዱኣድ፡-] (ፀጥ!)
- [ዓሊሙ፡-] "መልስልኝ!"
- [ኢብኑ አቢ ዱኣድ፡-] (አሁንም ፀጥ!)
- [ዓሊሙ ለኸሊፋው] "አሚሩ'ል-ሙእሚኒን ሆይ! ሁለት በልልኝ!"
- [ኸሊፋው፡-] "ሁለት!"
- [ዓሊሙ ለኢብኑ አቢ ዱኣድ፡-] "እስቲ ንገረኝ! ይህንን ንግግርህን መልዕክተኛው አውቀውት ነበር ወይስ አላወቁትም?"
- [ኢብኑ አቢ ዱኣድ፡-] "አውቀውታል!"
- [ዓሊሙ፡-] "ሰዎችን ወደዚያ ጠርተዋል?"
- [ኢብኑ አቢ ዱኣድ፡-] (አሁንም ፀጥ!)
- [ዓሊሙ ለኸሊፋው] "አሚሩ'ል-ሙእሚኒን ሆይ! ሶስት በልልኝ!"
- [ኸሊፋው፡-] "ሶስት!"
- [ዓሊሙ ለኢብኑ አቢ ዱኣድ፡-] "እንደምትለው የአላህ መልዕክተኛ (ﷺ) ይህንን እያወቁት ተከታዮቻቸውን ወደዚህ ባለመጣራታቸው ተብቃቅተዋል?"
- [ኢብኑ አቢ ዱኣድ፡-] "አዎን!"
- [ዓሊሙ፡-] "አቡ በክር፥ ዑመር፥ ዑሥማንና ዐሊይም እንደዚሁ በዝምታ ተብቃቅተው ነበር?"
- [ኢብኑ አቢ ዱኣድ፡-] "አዎን!"

- [ዓሊሙ ወደ ኸሊፋው በመዞር፡-] *“ረሱልን (ﷺ) አቡ በክርን፥ ዑመርን፥ ዑሥማንንና ዐሊይን ያብቃቃቸው ዝምታ የማያብቃቃህ ከሆነ፡- ለነሱ የተመቻቸው የማይመቸው ሁሉ አላህ ምቾትን ይንሳው!”*
- [ኸሊፋው፡-] *“አዎን! ረሱልን አቡ በክርን፥ ዑመርን፥ ዑሥማንንና ዐሊይን ያብቃቃቸው ዝምታ የማያብቃቃን ከሆነ፡- ለነሱ የተመቻቸው የማይመቸው አላህ ምቾትን ይንሳው!!”*

ከዚህ ጊዜ ጀምሮ ኸሊፋው የግል አቋሙን እንዳስተካከለ ይነገራል![1]

---

(1) “አሽ-ሸሪዓህ” ሊ’ል-አጁር-ሪይ ገፅ 91፤ “ታሪኹ በግዳድ” ሊ’ል-ኸጢብ (11/271)፤ “አል-ኢባናህ” ሊ’ብኒ በጥ-ጣህ (2/269)፤ እና ሌሎች መዛግብት ላይ ሰፍሯል።

## ክፍል ስምንት

## እውነታውን ለተፃረሩት ያለን ምልከታ

ትክክለኛውን የእምነት ጎዳና የሚስቱ ሁሉ አንድ ወጥ ብይን የሚመለከታቸው አይደሉም።

ሸይኹ'ል-ኢስላም ***ኢብኑ ተይሚይ-ያህ*** እንዲህ ይላሉ:-

«وَمِمَّا يَنْبَغِي أَيْضًا أَنْ يُعْرَفَ أَنَّ الطَّوَائِفَ الْمُنْتَسِبَةَ إِلَى مَتْبُوعِينَ فِي أُصُولِ الدِّينِ وَالْكَلَامِ **عَلَى دَرَجَاتٍ**: مِنْهُمْ مَنْ يَكُونُ قَدْ خَالَفَ السُّنَّةَ فِي أُصُولٍ عَظِيمَةٍ، وَمِنْهُمْ مَنْ يَكُونُ إِنَّمَا خَالَفَ السُّنَّةَ فِي أُمُورٍ دَقِيقَةٍ..»

*«..እንዲሁም ሊታወቅ የሚገባው ነገር በሀይማኖት መሠረቶችና በ"ከላም" ወደተለያዩ መሪዎች ራሳቸውን የሚያስጠጉ ጭፍራዎች በተለያዩ ደረጃዎች ላይ መሆናቸው ነው:- ከነርሱ መካከል **በታላላቅ መሠረቶች ላይ** ትክክለኛውን ፈለግ የተፃረረ አለ፤ ከነርሱ መካከል ደግሞ ትክክለኛውን ፈለግ የጣሰው **በውስብስብ ጉዳዮች** ላይ የሆነ ይኖራል...»*[1]

የአላህን መገለጫዎች በተመለከተው ታላቅ ርዕሰ-ጉዳይ ላይ ግልፅ ጥመትን ያራቡ የነበሩት የመጀመሪያዎቹ የጀህሚይ-ያህ አቀንቃኞች ሰለፎች ዘንድ በጥቅል እይታ እንደ ከሃዲያን ይታዩ ነበር።[2]

(1) *"መጅሙዑ'ል-ፈታዋ"* (3/348)

(2) ይህን እውነታ ያስተላለፉ በርካታ መዛግብት አሉ። ለምሳሌ:- ***አል-ኢማም አል-ላለካኢይ*** (418 ዓ.ሂ) የቁርአንን የአላህ ንግግር መሆን =>

ምክንያቱም ግልፅ ማስረጃዎችን በማስተባበል ሁሉንም የፈጣሪን ስሞችና ባህሪያት ከመሠረቱ በማፋረሳቸው ነው። ሆኖም በነሱ ተፅእኖ ስር ያደሩት ሁሉ የግድ በዚህ እይታ የሚገመገሙ አይደሉም! ሸይኹ'ል-ኢስላም ***ኢብኑ ተይሚይ-ያህ*** ስለ ፅንፈኛዎቹ ጀህሚይ-ያዎች እንዲህ ይላሉ:-

«وَتغلظ مَقَالَاتُهُمْ مِنْ ثَلَاثَةِ أَوْجُهٍ؛ **أَحَدُهَا**: أَنَّ النُّصُوصَ الْمُخَالِفَةَ لِقَوْلِهِمْ فِي الْكِتَابِ وَالسُّنَّةِ وَالْإِجْمَاعِ كَثِيرَةٌ جِدًّا مَشْهُورَةٌ وَإِنَّمَا يَرُدُّونَهَا بِالتَّحْرِيفِ. **الثَّانِي**: أَنَّ حَقِيقَةَ قَوْلِهِمْ

---

=> ለማስተባበል "ፍጡር ነው!" የሚሉትን ጀህሚይ-ያዎች በጥቅሉ በከሃዲነት የፈረጁ በርካታ የሰለፍ ሊቃውንትን ከዘረዘሩ በኋላ እንዲህ ይላሉ:-

«فَهَؤُلَاءِ خَمْسُ مِائَةٍ وَخَمْسُونَ نَفْسًا أَوْ أَكْثَرُ مِنَ التَّابِعِينَ وَأَتْبَاعِ التَّابِعِينَ وَالْأَئِمَّةِ الْمَرْضِيِّينَ سِوَى الصَّحَابَةِ الْخَيِّرِينَ عَلَى اخْتِلَافِ الْأَعْصَارِ وَمُضِيِّ السِّنِينَ وَالْأَعْوَامِ. وَفِيهِمْ نَحْوٌ مِنْ مِائَةٍ إِمَامٍ مِمَّنْ أَخَذَ النَّاسُ بِقَوْلِهِمْ وَتَدَيَّنُوا بِمَذَاهِبِهِمْ ، وَلَوِ اشْتَغَلْتُ بِنَقْلِ قَوْلِ الْمُحْدَثِينَ لَبَلَغَتْ أَسْمَاؤُهُمْ أُلُوفًا كَثِيرَةً»

***«እነኚህ ከደጋጎቹ ሰሓቦች ውጪ ያሉ ዘመናቸው ከመለያየቱና አመታት ከመተካካታቸው ጋር ከታቢዒዮች፣ ከነርሱ ተከታይ ትውልዶችና ከ(ሌሎች) ተወዳጅ ኢማሞች (የተውጣጡ) አምስት መቶ ሃምሳ ወይም ከዚያ በላይ የሚሆኑ ነፍሶች ናቸው! በውስጣቸውም ሰዎች ንግግራቸውን ይዘው መዝሃቦቻቸውን የሚከተሉ የሆኑ መቶ ያህል ኢማሞች ይገኛሉ! የቅርብ ጊዜዎቹን (ዓሊሞች) ንግግሮች በማጣቀስ ብጠመድ ኖሮ ስሞቻቸው ብዙ ሺዎች በደረሱ ነበር!»*** ["ሸርሑ ኡሱሊ'ዕቲቃዲ አህሊ'ስ-ሱን-ናህ" ሊ'ል-ላለካኢይ (2/344)]

تَعْطِيلُ الصَّانِعِ وَإِنْ كَانَ مِنْهُمْ مَنْ لَا يَعْلَمُ أَنَّ قَوْلَهُمْ مُسْتَلْزِمٌ تَعْطِيلَ الصَّانِعِ، فَكَمَا أَنَّ أَصْلَ الْإِيمَانِ الْإِقْرَارُ بِاَللَّهِ فَأَصْلُ الْكُفْرِ الْإِنْكَارُ لِلَّهِ. **الثَّالِثُ**: أَنَّهُمْ يُخَالِفُونَ مَا اتَّفَقَتْ عَلَيْهِ الْمِلَلُ كُلُّهَا وَأَهْلُ الْفِطَرِ السَّلِيمَةِ كُلِّهَا؛ **لَكِنْ** مَعَ هَذَا قَدْ يَخْفَى كَثِيرٌ مِنْ مَقَالَاتِهِمْ عَلَى كَثِيرٍ مِنْ أَهْلِ الْإِيمَانِ حَتَّى يَظُنَّ أَنَّ الْحَقَّ مَعَهُمْ لِمَا يُورِدُونَهُ مِنْ الشُّبُهَاتِ. وَيَكُونُ أُولَئِكَ الْمُؤْمِنُونَ مُؤْمِنِينَ بِاَللَّهِ وَرَسُولِهِ بَاطِنًا وَظَاهِرًا؛ وَإِنَّمَا الْتَبَسَ عَلَيْهِمْ وَاشْتَبَهَ هَذَا كَمَا الْتَبَسَ عَلَى غَيْرِهِمْ مِنْ أَصْنَافِ الْمُبْتَدِعَةِ، فَهَؤُلَاءِ لَيْسُوا كُفَّارًا قَطْعًا! بَلْ قَدْ يَكُونُ مِنْهُمْ الْفَاسِقُ وَالْعَاصِي، وَقَدْ يَكُونُ مِنْهُمْ الْمُخْطِئُ الْمَغْفُورُ لَهُ، وَقَدْ يَكُونُ مَعَهُ مِنْ الْإِيمَانِ وَالتَّقْوَى مَا يَكُونُ مَعَهُ بِهِ مِنْ وَلَايَةِ اللَّهِ بِقَدْرِ إيمَانِهِ وَتَقْوَاهُ.»

***«ንግግራቸው በሶስት ጎኖች አስከፊነቱ ይገለፃል፡- አንደኛ፡- ንግግራቸውን የሚቃረኑ የቁርአን፣ የሐዲሥና የኢጅማዕ ማስረጃዎች እጅግ ብዙና የታወቁ ናቸው። ሆኖም እነዚህን የሚመልሷቸው በማጣመም ነው! ሁለተኛው፡- የንግግራቸው እውነተኛ ገፅታ የፈጣሪን ህልውና ማስተባበል ነው - ምንም እንኳ ከነርሱ መካከል የንግግራቸው ውጤት የፈጣሪን ህልውና ማስተባበል መሆኑን የማያውቅ ቢኖርም! እምነት በመሠረታዊ እይታ በአላህ ማመን እንደሆነው ሁሉ ክህደትም በመሠረታዊ እይታ አላህን መካድ ነው። ሶስተኛው፡- እነርሱ ሁሉም የእምነት መንገዶችና የንፁህ ተፈጥሮ ባለቤቶች የሚስማሙባቸውን እውነታዎች ይፃረራሉ! ሆኖም ይህ ከመሆኑ ጋር የብዙ ንግግሮቻቸው እውነተኛ ገፅታ ከብዙ የኢማን ባለቤቶች ሊሰወር ይችላል - በሚያቀርቡት ውዥንብር የተነሳ እውነቱ ያለው እነርሱ ዘንድ እስኪመስለው ድረስ! ከመሆኑም ጋር እነዚያ አማኞች በግልፅም በድብቅም***

*በአላህና በመልዕክተኛው የሚያምኑ ይሆናሉ። ይህ የተምታታባቸውና የተመሳሰለባቸው ልክ ሌሎች የተለያዩ የቢድዓህ ሰለባዎች (እውነታው) እንደተምታታባቸው ነው! **በርግጠኝነት እነዚህ ከሃዲያን (ካፊሮች) አይደሉም!** ይልቁንም ከነርሱ መካከል አመፀኛና ወንጀለኛ የሚሆን ይኖራል፤ እንዲሁም የተሳሳተና ጥፋቱ የሚማርለት ይኖራል፤ ምናልባትም ኢማንና ተቅዋ (የአላህ ፍራቻ) ያለውና በዚያው ልክም የአላህን ወዳጅነት የሚጎናፀፍ ይኖራል!»*[1]

**ማስጠንቀቂያ**

**በተለያዩ ሊቃውንት አንደበት የአላህን ባህሪያት ማፉረስ ክህደትን (ኩፍርን) መፈፀም እንደሆነ የሚያስገነዝቡ ጥቅል ፍርዶችን መስፈርቶች ሳይሟሉ በቀጥታ በግለሰቦች ላይ ተፈፃሚ ማድረግ አይፈቀድም! ምክንያቱም በጥቅል ገለፃ *"ይህንን የሰራ ካፊር ይሆናል!"* ሲባል በዋነኝነት የሚፈለገው ተግባሩ የክህደት ተግባር (ኩፍር) እንደሆነ ማመላከት እንጂ ይህንን በየትኛውም ምክንያት የተገበረ ሁሉ ያለ ቅድመ-ሁኔታ ከኢስላም ይሰናበታል ማለት አይደለምና!**

**አሁንም ሸይኹ'ል-ኢስላም *ኢብኑ ተይሚይ-ያህ* እንዲህ ይላሉ:-**

«..فَتَكْفِيرُ الْمُعَيَّنِ مِنْ هَؤُلَاءِ الْجُهَّالِ وَأَمْثَالِهِمْ – بِحَيْثُ يُحْكَمُ عَلَيْهِ بِأَنَّهُ مِنْ الْكُفَّارِ – لَا يَجُوزُ الْإِقْدَامُ عَلَيْهِ إلَّا بَعْدَ أَنْ تَقُومَ عَلَى أَحَدِهِمْ الْحُجَّةُ الرسالية الَّتِي يَتَبَيَّنُ بِهَا أَنَّهُمْ

(1) "መጅሙዑ'ል-ፈታዋ" (3/354-355)

مُخَالِفُونَ لِلرُّسُلِ- وَإِنْ كَانَتْ هَذِهِ الْمَقَالَةُ لَا رَيْبَ أَنَّهَا كُفْرٌ-. وَهَكَذَا الْكَلَامُ فِي تَكْفِيرِ جَمِيعِ الْمُعَيَّنِينَ مَعَ أَنَّ بَعْضَ هَذِهِ الْبِدْعَةِ أَشَدُّ مِنْ بَعْضٍ، وَبَعْضُ الْمُبْتَدِعَةِ يَكُونُ فِيهِ مِنْ الْإِيمَانِ مَا لَيْسَ فِي بَعْضٍ؛ فَلَيْسَ لِأَحَدِ أَنْ يُكَفِّرَ أَحَدًا مِنْ الْمُسْلِمِينَ وَإِنْ أَخْطَأَ وَغَلِطَ حَتَّى تُقَامَ عَلَيْهِ الْحُجَّةُ وَتُبَيَّنَ لَهُ الْمَحَجَّةُ. وَمَنْ ثَبَتَ إيمَانُهُ بِيَقِينٍ لَمْ يَزُلْ ذَلِكَ عَنْهُ بِالشَّكِّ؛ بَلْ لَا يَزُولُ إلَّا بَعْدَ إقَامَةِ الْحُجَّةِ وَإِزَالَةِ الشُّبْهَةِ!»

*«...እንደነዚያ መሃይማንና መሰሎቻቸው ያሉ ግለሰቦችን በተመለከተ አንዳቸው ነብያትን የተፃረረ መሆኑ የሚገለፅበት መለኮታዊ ማስረጃ ከፀናበት በኋላ ካልሆነ በቀር ከከሃዲያን እንደሚመደብ በመፍረድ በ"ኩፍር" ወደ መፈረጅ ማምራት አይፈቀድም! - ንግግሩ ያለምንም ጥርጥር የክህደት ንግግር ቢሆን እንኳ! ከፊል ቢድዓዎች ከከፊሉ የባሱ ከመሆናቸውና ከፊል የቢድዓህ አራማጆች ከፊሎቹ ዘንድ የሌለ (የተሻለ) እምነት ያላቸው ከመሆናቸው ጋር ይህ ገለፃ ማንኛውንም ግለሰብ በከሃዲነት መፈረጅን የተመለከተ ነው!*

*እናም ማንም ሰው ከሙስሊሞች አንዱ ቢሳሳት እንኳ ማስረጃው ፀንቶ እስኪደርሰውና እውነተኛው መንገድ እስኪገለጥለት ድረስ በከሃዲነት የመፈረጅ መብት የለውም! <u>አማኝነቱ በርግጠኝነት የፀደቀ ሰው ይህ (አማኝነቱ) በጥርጣሬ አይወገድም፤ ይልቁንም ማስረጃው ከፀናበትና ውዥንብሩ ከፀዳለት በኋላ እንጂ አይወገድም!</u>»*[1]

(1) "መጅሙዑ'ል-ፈታዋ" (12/500-501)

ይህንን ሚዛናዊ የአህሉ’ስ-ሱን-ናህ አካሄድ የሚፃረር ፅንፈኛ አቋም የሚያንፀባርቁት ግለሰቦችና ቡድኖች ዋነኛ ስህተት ሁለት እርከኖች አሉት፡-

**አንደኛው፡-** ጥፋት ያልሆኑ ነገሮችን እንደጥፋት በመቁጠር፣ ወይም ጥፋት ቢሆኑ እንኳ ለክህደት ጭራሽ የማያበቁ ጉዳዮችን በማጋነን በክህደት መፈረጅ ሲሆን፤

**ሁለተኛው፡-** የኩፍር ወይም የሽርክ መገለጫዎችን የፈፀሙ ግለሰቦችን ወይም ቡድኖችን መስፈርቶች መሟላታቸውንና የብይኑን ተፈፃሚነት የሚያግዱ ምክንያቶች አለመኖራቸውን ሳያረጋግጡ በቀጥታ በከሃዲነት መፈረጅ ነው።

አንድ የኩፍር አቋም ያንፀባረቀ ግለሰብ በከሃዲነት እንዳይፈረጅ ሊያግዱ ከሚችሉ ምክንያቶች መካከል አለማወቅ፣ መሳሳት፣ መገደድና የመሳሰሉት ይገኛሉ።

ብዙ የቢድዓህ ጎጠኞች ሁለቱንም የስህተት እርከኖች በመፈፀም ህዝበ-ሙስሊሙን ሲያውኩና ሲከፋፍሉ እንደኖሩ የሚያረጋግጡ እማኞች በታሪክ ማህደር የሰፈሩ ሲሆን በነባራዊው ሂደት አንዳንዶቹ ዘንድ በተጨባጭ የምናየው የ“ተክፊር” ግንፍልተኝነትም በቂ መስካሪ ነው![1] የሚደንቀው ግን ከላይ

(1) “አሕባሾች” ለዚህ ጥሩ ምሳሌ ይሆናሉ! በርካታ ዑለማዎችን ጨምሮ ብዙዎችን ያለ አግባብ በከሃዲነት (በካፊርነት) እንዲፈረጁ ምክንያት የሆኗቸውን ግድፈቶች ከነእርማቶቻቸው በአጭሩ ለመቃኘት “ፊርቀቱ’ል-አሕባሽ” የተሰኘውን ጥናታዊ ፅሁፍ ከ(2/645) ጀምሮ ይመልከቱ።

ያሳለፍነው የአህሉ’ስ-ሱን-ናህ ሚዛናዊ ብይን በተለያዩ ፅሁፎቻቸው ከመብራራቱ ጋር እነርሱን በተቃራኒው የተክፊር ጥማት ያለባቸው አድርጎ ለመሳል የሚደረገው ያላሰለሰ መፍጨርጨር ነው፤ የማንን ለማን? !

ooo

# መዝጊያ

**እንግዲህ አንባቢ ሆይ!**

**1- እውነታው ግልፅ ነው! አላህ ለራሱ በቁርአኑ ወይም በመልዕክተኛው አንደበት ያፀደቀውን ሁሉ ያለ ማመሳሰልና ያለ ትርጉም ማጣመም እንቀበላለን፤ ለርሱ ልቅና በሚገባ መልኩ የባህሪያቱን ጥቅል መልዕክት እናረጋግጣለን። ይህ ነው የነብያትና የተከታዮቻቸው ጎዳና! ይህ ነው ውዝግብን የሚፈታው ቀላሉ የመፍትሄ አካሄድ!**

**2- ሁል ጊዜም ቢሆን የነብያት ተከታዮች የሚጓዙበት መንገድ በህሊና ሰላምና በልቦና ስክነት የታጀበ ነው! ተፃራሪው ደግሞ በንትርክና በጥርጣሬ የተወሳሰበ ነው።**

**3- በአንዳንድ ሁኔታዎች የጥመት አቀንቃኞች በርዕሱ ላይ የሚያንፀባርቁት ትክክለኛ አቋም ካለለ ቀድሞውኑ በቁርአንና በሐዲሥ በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ የሰፈረና የእውነት ተከታዮች ዘንድ የታወቀ እንጂ ሌላ ሊሆን አይችልም፤ ስለዚህ ከነርሱ የሚከጀል አዲስ እውነታ የለም። እውነትን ከገጠሙባቸው ውጭ ያሉ ንግግሮቻቸው ደግሞ የቁርአንም ይሁን ሌሎች አእምሯዊ መረጃዎች ላይ የተመረኮዙ አይደሉም፤ ሆኖም የሐቅ ተከታዮችን የሚጋፈጡባቸው ስልቶች በአብዛኛው ከሚከተሉት አራት ምድቦች አይወጡም፦**

**ሀ- አዳዲስ የቢድዓህ ፈሊጦችን መፈልሰፍና እነርሱን እንደ መመዘኛ ማቅረብ፤**

ለ- ፅኑ እውነታዎች ላይ ማጠራጠሪያ ጥናቶችን ማቅረብ፤

ሐ- እነ “እገሌ”ን በጭፍን መከተል፤[1]

መ- እውነተኞችን በሀሰት ለማጥላላት መቅጠፍ![2]

ይህንን አስተዋዮች አያጡትም![3]

---

(1) አላህ እንዲህ ይላል፡-

📖 ﴿ ٱتَّبِعُواْ مَآ أُنزِلَ إِلَيۡكُم مِّن رَّبِّكُمۡ وَلَا تَتَّبِعُواْ مِن دُونِهِۦٓ أَوۡلِيَآءَ ﴾ [الأعراف: ٣]

➥ «ከጌታችሁ ዘንድ ወደናንተ የወረደውን ተከተሉ፤ ከእርሱ ውጭ ሌሎች ረዳቶችን አትከተሉ!»[አል-አዕራፍ 3]

(2) የእውነት ተከታዮች ላይ ከሚቀጥፏቸው የተለመዱ ውሸቶች መካከል፡- *«አላህን በሰው ይመስላሉ፣ “እንደ ሰው አካል አለው!” ይላሉ..»*..ወዘተ የሚሉት ይገኙበታል!

(3) ታዋቂው ምሁር ኢብኑ’ል-ቀይ-ዪም የላይኛውን ቁምነገር ሲጠቁሙ እንዲህ ይላሉ፡-

واسمع نصيحةَ مَن له خُبْر بما    عند الورى من كثْرةِ الجَوَلانِ

ما عندهم واللهِ خيرٌ غيرَ ما    أخذوه عمّن جاءَ بالقُرآنِ

والكلُّ بعدُ: فبِدعةٌ أو فِرْيةٌ    أو بحثُ تشكيكٍ ورأيُ فُلانِ !

## ሶስት ምክሮች

### 1ኛ- ትክክለኛውን ጎዳና ለሳቱ

አላህ እንዲህ ይላል፡-

﴿قُلۡ إِنَّمَآ أَعِظُكُم بِوَٰحِدَةٍۖ أَن تَقُومُواْ لِلَّهِ مَثۡنَىٰ وَفُرَٰدَىٰ ثُمَّ تَتَفَكَّرُواْ﴾ [سبأ: ٤٦]

➥ «"እኔ የምገስጻችሁ በአንዲት ነገር ብቻ ነው!" በላቸው! ፡- ለአላህ ብላችሁ ሁለት ሁለት ሆናችሁና ለየብቻ ተነስታችሁ ከዚያ እንድታስተውሉ!..»[ሰበእ 46]

ያስተውሉ! ተጨባጩ ዓለም እንደሚመሰክረው ብዙ ሰዎች በተሰበሰቡበት አጋጣሚ እውነታን አጣርቶ የሚያሳይ ውይይት መፈፀም እጅግ አስቸጋሪ ነው - በተለይ በእምነት ጉዳይ ላይ! ምክንያቱም በአብዛኛው ንፁህ እሳቤን የሚያደፈርሱና ጭፍን ወገንተኝነትን የሚቀሰቅሱ ሁኔታዎች መንፀባረቃቸው አይቀርምና! በአንቀፁ ላይ እንደተመለከተው ሁለት ሆነው አንዱ የደረሰበትን እውነታ ለሌላው በማቅረብ በቅንነት መወያየት ለአስተውሎት አመቺ ሁኔታን ይፈጥራል! ለብቻው የሆነም ሰው ባልተረበሸ ልቦና መረጃዎችን የማገናዘብ እድል ይኖረዋል።(1)

ከዚህ ጋር አላህ ቀጥተኛውን መንገድ እንዲመራን መማፀን ሊዘነጋ የሚችል ጉዳይ አይደለም!

---

(1) "አል-በሕሩ'ል-ሙሒጥ" (ተፍሲር አቢ ሐይ-ያን) (7/290-291) ይመልከቱ።

**2ኛ- ጥርጣሬን ለሚያስተናግዱ**

መሠረቱ የተጠናከረ ርዕሰ-ጉዳይ ላይ ለሚነሱ አላፊ ውዥንብሮች ትክክለኛ ምላሽን አለማወቅህ/ሽ በጉዳዩ ላይ ጥርጣሬን አያጭርም! ምክንያቱም መሠረታዊ እርግጠኝነት በቅርንጫፋዊ ጥያቄ ሊናወጥ አይገባምና! በዚህ ላይ ደግሞ አንተ ልትፈታው ያልቻልከውን የጥርጣሬ ቋጠሮ ሌላ አዋቂ በአላህ ፈቃድ ይፈታዋል!

*«ልቦናህን ለአላፊ ሃሳቦችና ውዥንብሮች እንደ እስፖንጅ አታድርገው! - እነሱን መጥጦ ከነሱ ሌላ የሚተፋው አይኖረውምና! ነገር ግን እንደ ጠንካራ መስታወት አድርገው፡- ውዥንብሩ ከላይ በኩል ያልፋል፤ ወደ ውስጥ ግን አይዘልቅም! በጥራቱ አሳልፎ ያያቸዋል፤ በጥንካሬውም ይቋቋማቸዋል! የሚያጋጥምህን ውዥንብር ሁሉ ለልብህ የምታግተው ከሆነ ግን የውዥንብር መጠራቀሚያ ይሆናል!»*[1]

**3ኛ- እውነቱን ለተረዱ**

እውነትን ለማወቅ አላህ የረዳው ሰው እርሱን ሊያመሰግንና በዚያ ላይ እንዲያፀናው ሊማፀነው ይገባል። ሌሎችን በንቀት አይን ከማየትም ራሱን ሊጠብቅ የግድ ይላል።

(1) ከሸይኹ'ል-ኢስላም ኢብኑ ተይሚይ-ያህ ወርቃማ ምክሮች አንዱ ነው። "ሚፍታሑ ዳሪ'ስ-ሰዓዳህ" ሊ'ብኒ'ል-ቀይ-ዪም (1/140) ይመልከቱ።

በተረፈ እውነታውን ለማመላከት የምናደርገው ጥሪ ሁልጊዜ በጥበብና በእውቀት ላይ የተገነባ ይሁን! የተረዳ ሁሉ ሌላን ሊያስረዳ እንደማይችልም አይዘንጉ! ከፍሬ-ቢስ ክርክር መራቅም አንድ ብልሃት ነው! ከሁሉ በላይ ውድ ንብረታችን እምነታችን ነውና እንዳይበከል እንጠብቀው፤ እንንከባከበው!

አላህ ሁላችንንም ወደ ቀጥተኛው ጎዳና ይምራን!

ጨርሻለሁ!

- **معتقد أهل السنة والجماعة في أسماء الله وصفاته** - للدكتور محمد بن خليفة التميمي – الناشر: مكتبة أضواء السلف – الرياض – الطبعة الأولى

- **نقض الإمام أبي سعيد عثمان بن سعيد على المريسي الجهمي العنيد فيما افترى على الله عز وجل من التوحيد –** لعثمان بن سعيد الدارمي - تحقيق: رشيد بن حسن الألمعي- الناشر: مكتبة الرشد – الرياض – الطبعة الأولى

## مِن أَهَمّ مَراجِعِ المَادَّةِ العِلْمِيَّة :

- **الإبانة عن أصول الديانة** – لأبي الحسن علي بن إسماعيل الأشعري – تحقيق د. صالح بن مقبل العصيمي – الناشر: دار الفضيلة – الرياض – الطبعة الأولى

- **التدمرية (تحقيق الإثبات للأسماء والصفات وحقيقة الجمع بين القدر والشرع)** - لأبي العَباس أحمد بن عبد الحليم بن تيمية الحراني – تحقيق: د. محمد بن عودة السعوي - الناشر: مكتبة العبيكان – الرياض- الطبعة الثامنة.

- **تقريب التدمرية** - لمحمد بن صالح العثيمين - الناشر: مدار الوطن – الرياض.

- **الرد على الجهمية** - لعثمان بن سعيد الدارمي – تحقيق: أبي عاصم الشوامي – الناشر: المكتبة الإسلامية – القاهرة.

- **رسالة إلى أهل الثغر بباب الأبواب**– لأبي الحسن علي بن إسماعيل الأشعري – تحقيق: عبد الله شاكر الجنيدي - الناشر: عمادة البحث العلمي بالجامعة الإسلامية - المدينة المنورة -

- **فتح رب البرية بتلخيص الحموية** - لمحمد بن صالح العثيمين - الناشر: دار ابن الجوزي – الدمام.

- **الفتوى الحموية الكبرى** - لأبي العَباس أحمد بن عبد الحليم بن تيمية الحراني – تحقيق: د. حمد بن عبد المحسن التويجري - الناشر: مكتبة دار المنهاج – الرياض.

- **كتاب التوحيد وإثبات صفات الرب** – لمحمد بن إسحاق بن خزيمة – تحقيق: عبد العزيز بن إبراهيم الشهوان - الناشر: مكتبة الرشد – الرياض - الطبعة الخامسة

- **مختصر الصواعق المرسلة على الجهمية والمعطلة لابن قيم الجوزية** – اختصار محمد بن الموصلي – تحقيق: د. الحسن بن عبد القادر العلوي – الناشر: مكتبة أضواء السلف – الرياض.

- **مقالة التعطيل والجعد بن درهم** – للدكتور محمد بن خليفة التميمي – الناشر: مكتبة أضواء السلف – الرياض – الطبعة الأولى

والله المسؤول أن يوفّقني والمسلمين لسداد القول والعمل، ويُجنّبَنا الفوْتَ والزلل، والحمد لله رب العالمين.

أبو حُنيف إلياس بن أحمد

**الحمد لله** وكفى، والصلاة والسلام على عبده المصطفى، أما بعد:

فهذه رسالةٌ موجزة وضعتها باللّغة الأمهرية -الإثيوبية- في تقرير الدلائل على إثبات صفات الله الواردةِ في الكتاب وصحيح السنّة؛ لتكون -بإذن الله- وقايةً من سهام التعطيل وجُنّة، ولم يكن من مقصودي تحريرُ المسائل في أفراد الصفات، وإنما أشرت إلى قواعدَ راسخةٍ تَحُلّ العُقَد، وتُنير الدّرْبَ لمن رام تحقيقَ هذا الأصلِ من المُعْتَقَد، وحَلّيتها بأمثلةٍ تُقرّب الأقصى، وتُذَلِّلُ ما لعلّه عسُر على الفهم واسْتَعْصَى..

هذا، وقد استَقيتُ أغلب موادّ الرسالة من كتب بعض الأعلام، منها: "الفتوى الحموية الكبرى"، و"التدمرية" كلاهما لشيخ الإسلام ابن تيميّة، و"مختصر الصواعق المرسلة" للإمام ابن القيم - اختصار الموصلي-، و"الرد على المريسي" للإمام الدارمي، و"التوحيد" للإمام ابن خزيمة، وغير ذلك من مصنفات الأئمة الكثيرة التي أشرت إلى بعضها في الحواشي، مع زيادات تبين المقصود، وتفي بالموعود.

ومقاصد هذا التأليف مبسوطة في بابين؛ أما **الأول**: فيحتوي على شرح بعض الأصول في تقرير الحق الذي يجب على المسلمين اعتقاده، وبيان مذهب السلف في ذلك، وأما **الثاني**: ففي ذكر بعض القواعد التي تَدكّ حصونَ المخالفين، وتَقلع جذور مقالتهم.

وسمّيتها: **جُنة المؤمنين في إثبات صفات رب العالمين.**

# جُنَّة المؤمنين

## في إثبات

## صفات رب العالمين

(بِاللُّغَةِ الأَمْهَرِيَّةِ)

إعداد

أبو حُنيف إلياس بن أحمد

الطبعة الثانية

١٤٣٧ هـ